# ማውጫ

ገጽ

- የአወዛጋቢው እሾ
  አጭር የህይወት ታሪክ ---------- 7
- መግቢያ ---------- 16

1. መጀመሪያ ጥበብን የተመለከተ ሰው፣
   የመጀመሪያው አዋቂ (ጥበበኛ) እና ቅዱስ ነው
- ልዩ ተሰጥዖ ያለው ሰው ተራ እንደሆነ
  የሚሰማውና ተራ የሚሆነው እንዴት ነው?---------- 18
- የሁሉንም ጥያቄዎች የተሟላ መልስ ማግኘት
  ይቻል ይሆን?
  ሰይጣን መጀመሪያ ወደ ወንድ ያልሄደው
  ለምንድነው? ---------- 24
- ራስን አሳልፎ መስጠት የሚቻለው እንዴት ነው? ---------- 32
- ዕብደት ያለበት ነጥብ ጋ ስንደርስ ንቃታችን
  በከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ ይደርሳል ----------36
- ምን እየተካሄደ እንደሆነና ወዴት እንደምንሄድ
  የምናውቀው እንዴት ነው? አንተስ የት
  እየወሰድከን ነው? ----------38

2. የሰብዓዊ መብት ድንጋጌ
   ያልሰጠነ ህብረተሰብ ግብዝነት
- ብቸኛው መሰረታዊ መብት አምላክ የመሆን
  መብት ነው ---------- 44

3. አራት ነጥቡ ፈፅሞ አይመጣም
- በዓለም የሰዎችን ህይወት የለወጡ ሁለት ዓይነት
  የአስተሳሰብ ተፅዕኖዎች አሉ ---------- 84

t.me/OLDBOOKSPDF

- ፍጹም ርግጠኛ የሚኮነው መጀመሪያ ሳይሆን መጨረሻ ነው ---------- 95
- አንተ ከኔ ጋር ነህ ወይስ እኔ ከአንተ ጋር? አንተስ ማነህ? እኔ ወይስ አንተ ---------- 98
- የጥፋተኝነት ስሜት አይለወጥም ---------- 99

## 4. ፍቅር ግልፅ ራዕይ ይሻል

- እውነተኛ የፍቅር ፈተና ያለው በሰዎች ዘንድ ነው፤ ሁለቱም ሲያገኙት ይፈልጋሉና ---------- 108
- ማንም እውነትን አስቀድሞ አያውቅም፤ ሁሉም ሰው መጀመሪያ የሚያውቀው ውሸትን ነው ----------119
- ማንም አለመሆን ታላቁ ድል ነው! ---------- 124
- ወሲብ ሲጠፋ ወደታች ይወርድ የነበረው ኃይል ወደ ላይ መውጣት ይጀምራል ----------127

## 5. ሰብዓዊ መብቶች

### ለአዲሱ ሰው

- ሁሉም የሰው ልጅ እስረኛ ነው፤ ሰፊ እስር ቤት በመሆኑ መታሰሩን ይዘነጋዋል እንጂ ----------130
- ለማንኛውም ህይወት ክብር መስጠት
- ፍቅር፣ የሌሎች መሰረታዊ መብቶች መንገድ ጠራጊ
- ሦስቱ መሰረታዊ መብቶች - ህይወት፣ ፍቅርና ሞት
- እውነትን መፈለግ
- በተመስጦ ማሰብ
- ሁለ - ገብ ነፃነት
- አንድ ምድር፣ አንድ ህዝብ
- የእያንዳንዱ ግለሰብ ልዩ መሆን መቀበል
- የዓለም አንድ መንግስት
- ሜሪቶክራሲ


t.me/OLDBOOKSPDF

# የአወዛጋቢው ኦሾ
# አጭር የሕይወት ታሪክ

ባግዋን ሽሪ ራጅኒሽ (ኦሾ) የተወለደው በ1931 (እ.ኤ.አ) ህንድ ውስጥ ኩችዋዳ በምትባል አነስተኛ መንደር ነው። የመጀመሪያ መጠሪያው ራጆኔሽ ቻንድራ ሞሀን ነበር። በአሁኑ ጊዜ ከስጋው ተለይቷል፣ ወይም ሞቷል።

ኦሾ ገና ከልጅነቱ ጀምሮ በርካታ ጥያቄዎችን መጠየቅ ያዘወትር ነበር። ይህ ሁኔታም ዕድሜው ሃያ አንድ ዓመት ደርሶ እውነት እስኪገለጽለት (ባለ ራዕይ እስከሚሆን) ወይም የመጨረሻው በንቃተ - ህሊና ደረጃ (በራስ የማወቅ ደረጃ) ላይ እስኪደርስ ድረስ ቀጥሏል። ይህንን የማወቅ ደረጃም «የሁላችንም የተፈጥሮ መብት ነው» ይለዋል።

ኦሾ የቤተሰቡ እምነት ጃይኒዝም ይሁን እንጂ፣ ከልጅነቱ አንስቶ ይሄንን ኃይማኖት ሲጋፋና ሲተች ነው የኖረው። ይህ በቤተሰቡ ላይ የጀመረው የለውጥና የአመፅ ህይወትም ቀጥሎ ከብዙ የዓለም ህግጋትና እምነቶች ጋር አላትሞታል። እሱ ግን እስከ መጨረሻው «ዓለም በኔ የለውጥ ሂደት ካልተመራች እራሷን በራሷ እንድትለውጥ በሚያስገድድ ጥልፍልፎሽ ትጠፋለች» ከማለት ወደ ኋላ አላለም።

የኖረ ስህተት የመንቀስ ባህሪው ከቤተሰብ ወደ ማህበረሰብ፣ ከማህበረሰብ እስከ አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ድረስ ተሸጋግሯል። ለዚህም ፍልስፍና መማሩና አያሌ መጻህፍትን እያደነ ማንበቡ የበለጠ ጉልበት ሆኖታል።

የረኛም ዘመን ትምህርትን ገና በሃያ አንድ ዓመቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ አጠናቅቆ ከሳውጋር ዩኒቨርስቲ በፍልስፍና የማስተር ዲግሪውን ካገኘ በኋላ ወዲያውኑ ነበር ፍልስፍና ማስተማር የጀመረው። እንደ



t.me/OLDBOOKSPDF

እውነቱ ግን ክፍያ የሚያገኘው በጣም የሚወደውን ተግባር በማከናወን፣ ማብራሪያ በመስጠት እና ጥያቄዎችን በማቅረብ ነበር።

ኦሾ ከ13 ዓመታት በኋላ የዩኒቨርስቲ መምህርነቱን ሳንዱና ለመጨረሻ ጊዜ ተሰናብቶ በ1966 «እምነቴ» ብሎ በሚያራምደው ሃሳብ የሚያደንቁትን ምዕመኖቹ በማድረግ ጠቅልሎ እምነቱን ወደመስበክና ወደማስፋፋት ተግባር ተሰማራ። እናም ኑሮውን በህንዷ የቦምቤ ከተማ ውስጥ ሲመሰርት፣ እሱን ለማየት ከመላው ዓለም የሚጐርፉ ሰዎች ከዓመት ዓመት እጅግ እየተበራከቱ መጡ። በዚህ የተከታዮቹ ቁጥር መብዛት ምክኒያት በ1974 ቦምቤ ውስጥ የተከራየውን አነስተኛ አፓርታማ ለቆ አንድ መቶ ማይሎች ርቃ ወደምትገኘው በዛፎች ወደተከበበችው ኮሪጋአን ፓርክ ባለችው ፑና እንዲዘዋወር ተገደደ። የቦታው ዝውውሩ የታየው በሁለት መንገድ ነበር። አንዱ ተከታዮቹ ስለበረከቱለትና የማስተማሪያ ቦታው (አሽራም) አመቺ ባለመሆኑ ቀየረ ሲሉ፣ ሌሎች ግን አስተምህሮቱ እጅግ ተቀናቃኝ በመሆኑ የአካባቢው ነዋሪና አስተዳዳሪ አላኖር ስላሉት ነው ቦታ ለመቀየር የተገደደው ይላሉ።

ያም ሆኖ ይህ ፑና ውስጥ ኦሾ ተዘጋጅቶ የጠበቀው ስፍራ እጅግ ሰፊና ለመንፈሳዊ ሥነ - ሥርዓቱ የተመቸ ነበር። ከ50 ሺ ያላነሱ ምዕራባውያን ተከታዮቹን በቋሚነት ከማስተናገዱም በተጨማሪ ብዙ እንግዶቹን በጊዜያዊነት ይቀበል ነበር። ከነዚህ ውስጥ ትልቅ ስም ያላቸው ሀኪሞችን ጨምሮ በበርካታ ሺህ የሚቆጠሩ የተለያዩ ሙያ ያሏቸው ሰዎች ሊያዩት ይመጡ ነበር።

አዎን፣ በሚያደርገው ያልተለመደ ንግግር ስሙ ቢጐድፍም በርካታ ህዝብ ከጐኑ ማሰባሰብ ችሎ ነበር። ፑናም በተከታዮቹ ዘንድ «በምድር ላይ ታላቅ እና ከፍተኛ ለውጥ የሚካሄድባት ቦታ!» እስከ መባል በቅታለች።

በአንድ ወቅት ኦሾ ንግግሩን ለማድመጥ የሚመጡት ሰዎች በሚፈልገው መልኩ እየተለወጡ አለመሆናቸውን ሲረዳ የማስተማር ዘዴውን ለውጦ የቅርብ ደቀመዝሙሮችን የያዘ ቡድን መስርቶ ነበር።



t.me/OLDBOOKSPDF

እነኚህ ደቀመዛሙርትም በእሱ የተመሰጠ ማሰላሰል የሚሳተፉ እና በህይወታቸው ላይም ሊተገብሩት ፈቃደኛ የነበሩ ናቸው።

ከዚህ ሌላ ተቀባይነቱ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሲደርስ፣ በድንገት ሁሉንም ሰው ትቶ ራጂኒሽፑራም የተባለውን ትልቁን ተግባራዊ ሙከራውን ለመተግበር በኦሪጎን በረሃ ወደምትገኝ የአሜሪካን ከተማ ተጓዘ። ራጂኒሽፑራም የተለያዩ መጠሪያዎች የነበሩት ሲሆን ከነዚህ ውስጥ፡- የኦሪጉንን የመሬት ህጎች ነቃፊ፣ ካለወትቱ የቆደረገ የሥነ - ምህዳር ሃይል፣ የፋሽስቶች ማጉሪያ ካምፕ፣ የማሽነፍ/መሽነፍን የማወቅ ችሎታን ማዳበር የሚያስችል የአራት ዓመት የህክምና ቡድን . . . ወዘተ ነበሩ። ለዚህ የከተማ ላይ ሙከራ በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ ፈሷል፤ በርካታ ሰዎችም ተሳትፈውበታል።

ይሁንና በዚህ መሀል የብሔራዊ ዘብ ሊያስረው እንደሆነ እና የዋኮ ዓይነት ጭፍጨፋ ሊደርስ እንደሚችል ጭምጭምታ የተሰማ ጊዜ ኦሾ ተከታዮቹን ትቶ ሄደ። ጭፍጨፋ ባይደርስም እሱ ግን ሶስት ሺ ማይሎች ርቃ በምትገኘው ሰሜን ካሮላይና ውስጥ ከመታሰር አልዳነም። የዋስ መብት ስላልተፈቀደለት እና ከማንም ጋር እንዳይገናኝ ስለተከለከለም ለአስር ቀናት ብቻውን በእስር ለማሳለፍ ተገድዷል። ይህ ሁሉ የደረሰበት የስደተኞች ህግን (የኢሚግሬሽን ደንብን) ተላልፈሃል በሚል ነበር።

ከዚያ በኋላ ነበር በተሳካ ሁኔታ ዓለምን ዞሮ ወደ ህንድ የተመለሰው። ስኬቱ የሚለካውም የፑና ማስተማሪያ ቦታን (ተቋምን) ዳግመኛ በማስጀመሩ በአሜሪካን መንግስት ጫና በራቸውን በዘጉበት ሃያ አንድ ሀገራት ጭምር ነበር። በተደጋጋሚ ተከታዮቹን ትቶ መሄዱ ደቀመዛሙርቱን እንዲበታተኑ ቢያደርግም፣ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ የፑና አባላት ቁጥር መጀመሪያ ከነበረው በሶስት እጥፍ ጨምሮ ነበር። እንደ አድናቂዎቹና ተከታዮቹ አባባል፣ «የዜን ጥበብ ሃይለኛነት እነሱ እንዲነቁ ለማድረግ መሆኑ በገባቸው ፈላጊዎች ይበልጥ ተጨናነቁ።»

ተቋሙ በኦሾ «እምነት» ተብሎ አይጠራ እንጂ ጥናት ያደረጉ እንዳረጋገጡት ከሂንዱዝም፣ ከጃይኒዝም፣ ከዜን ቡድሒዝም፣


t.me/OLDBOOKSPDF

ከታአይዝም፣ ከክርስትና እና ከቀድሞ የግሪክ ፍልስፍና ተዳቅሎ የተፈጠረ ነው ይሉታል። ኦሾ በዚህ ማጠቃለያ እንደማይስማማ ከመግለፁም በላይ «እኔም ሆንኩ ተከታዮቼ አላማችን ከሀይማኖት ሆነ ከባህል እና ከፖለቲካ ነፃ የሆነ ትውልድ መፍጠር ነው» ሲል በግልፅ ተናግሯል። «ተቋማችን ኃይማኖታዊ ነው ከተባለም የፀረ - ኃይማኖት - ኃይማኖት ነው» በማለት ያክላል።

ኦሾ በ1979 ዓ.ም የተቋሙን አላማ ግልፅ ሲያደርግ «በዚህ 20 ዓመት ውስጥ <አዲሱን ሰው> መፍጠር ካዳገተን የዓለም ፍፃሜ እርግጥ ይሆናል» በማለት የመላው ዓለም ተስፋ ሙሉ በሙሉ በእርሱ የመዳን እሳቤ ላይ መንተራሱን በሙሉ ልብ ተናግሯል።

እንዲህ ያለው የኦሾ ንግግር ወደ የትኛው አቅጣጫ እንዲያመራ ሊያስገድደው ይችላል በሚል በብዙ ሀገሮች በጥርጣሬ እንዲታይ አድርጎታል። በተለይ ከተላታሚነቱ ጋር ተያይዞ «አዲሱ ሰው» (New Man) ላይ ተስፋ የመጣል አዝማሚያ ማሳየቱ ከጀርመናዊው ፈላስፋ ከፍሬዲሪክ ኒች «ታላቁ ሰው» (Superman) ጋር ተዛምዶ በዳግም አዶልፍ ሒትለርነት አስጠርጥሮታል።

ኦሾ «አዲሱ ሰው» የሚለውን የወደፊት የሰው ልጅ ተስፋ የሚመለከተው ከተለያየ ጎንዮሽ ነው። ከርዕዮተ - ዓለም ውጭ በማህበራዊ እሳቤም ምን መምሰል እንዳለበት ደጋግሞ ያስረዳል። «I am the gate» በሚለው መፅሐፍ ውስጥ እንዲህ ይላል፦

«አዲሱ ሰው የቡድሃም ሆነ የክርስቶስ፣ የመሃመድ ሆነ የአብርሃም ሊንከን ቅጂ አይደለም፣ እርስቶትልንም አይመስልም። በእርግጥ ይቺ ዓለም ህይወትን በቅጂ ለሚያስተናግድ የተመቻቸች ነች። የኑሮ ቅጂ ኑሮ ያላቸው ኑሮዋቸው በሌሎች አይበጠበጥም፤ የእምነት ቅጂ እምነት ያላቸው እምነታቸው በሌሎች አይነቀፍም። የባህል ቅጂ ባህል ያላቸው ባህላቸው በሌሎች አይጣጣልም፤ የልምድ ቅጂ ልምድ ያላቸው ልምዳቸው በሌሎች አይብጠለጠልም። ስለዚህ የይስሙላ ኑሯቸው የሰለጠ ይሆናል። ነገር ግን ሌሎችን ሆነህ እየኖርክ አንጡራው አንተነትህ ሥፍራው የት ይሆን? አንተን ለመሆን የተወለደው ጫቅላው



t.me/OLDBOOKSPDF

እንተነትነህ በመጎልበት ጊዜ የት አደረስከው? ቡድሃን፣ ክርስቶስን፣ መሃመድን፣ ሲጉከንን፣ ኣርስቶትልን. . . ስመቅዳት የተፈጠርክ ተራ ሴንኪሎ መሆንህን እስበኸው ይሆን? <አዲሱ ሰው> ግን ይህንን የሚያሸንፍ የራሱ ሰው ነው።»

ኦሾ ከዛፍቸውና ንግግሮቹ ተገልብጠው ከሰፈሩባቸው ከ700 በላይ መፅሐፎቹና የድምፅ መልዕክቶቹ ደጋግሞ ስለሰው ልጅ መንፈሳዊ ነፃነት እንዲህ ይላል. . .

«ህይወት፣ በምድር ላይ ከተቀደደ መንገድ ይልቅ ወዳሰኘህ አቅጣጫ የምትበርበትን ሰማይ ትመስላለች። የምድር ላይ ሀያላን በቀደዱልህ መንገድ ላይ በካርታቸው እየተመራህ መንገድ ተጓዥ አያሰኝም፤ ኑሮህም ኑሮ አይሆንም። ገና ወዳልተዳሰሰው ድንግል ሰማይ ለመንጎድ የምታስችልህን ክንፍ አነቃቃ። የራስህ የሆነም ካርታ ከአሻራዎችህ ላይ ቅዳ።»

ኦሾ በአመዛኙ የሚታወቀው ላልመሰለው ነገር በሀይለ - ቃል አስጣአገባ ውስጥ በመግባቱ ነው። በወላጆቹ ያሟሸው ኃይማኖትንና ልምድን በሰላ ሒስ የመሞረድ ልምድ ወደ ማህበረሰብም ተሸጋግሮ ነበር። በተለይ እንደ ቡድሃ እና ማሃቪራ የመሳሰሉትን የኃይማኖት መስራቾች አቃሎ መመልከቱና አልፎ ተርፎም ለማረም መሞከሩ በአብዛኛው የህንድ ማህበረሰብ ጥላቻን እንዲያተርፍ አድርጎታል። አንድ ጊዜ የፒና ነዋሪ ነቅሎ ወጥቶ ኦሾ «ባግዋን» በሚለው መጠራት የለበትም! ስሙን ይቀይር በሚል ሰላማዊ ሰልፍ ያካሄዳል። ህንዶች እንደተለመደው ሰላማዊ ሰልፋቸውን ያካሄዱት አህያ ላይ የተሰጠፈ መፈክር አስቀድመው ነበር። ኦሾ ስለጉዳዩ ምን ትላለህ? ተብሎ ሲጠየቅ፤

«ጥሩ ነው፤» አለ። «ጥሩ ነው። የኔ ሥም ባግዋን (የተባረከ ሰው) የሚለው ቢቀየር እኔነቴን አይጎዳውም። የሚያሳዝነኝ ግን ሰልፈኞቹ በአህያ መመራታቸው ነው» ሲል አሽሟጠጣቸው። ለዚህ ምላሹ ከሒንዱ እምነት አክራሪ በተሰነዘረበት የስለት ጥቃት ቆስሎ እንደነበር ታሪክ ያስረዳል።



t.me/OLDBOOKSPDF

እሾ ግጭቱ ከቤተሰቡ ወደ ህብረተሰቡ እንዳደገ ሁሉ አገራዊ አተካራ ውስጥም ገብቶ ነበር:: በተለይ ከአሜሪካ ጋር እስጥአገባው እጅግ በርትቶ ዘብጥያ እስከ መውረድ ደርሶ ነበር:: በእሾ አቋምና አስተምህሮት ጥርጣሬ የዘለቃት አሜሪካ ከራሷ አልፋ በአውሮፓና በህንድ ተፅዕኖ እንዲደረግበት እጇን ስታስረዝም እንደነበር እሾ ደጋግሞ ገልጿል::

«ፖለቲካ ላይ ያለኝ ዝንባሌ ዜሮ ነው:: የትኛውንም ሥልጣን ለመቆናጠጥ ፍላጎት የለኝም:: ሀገሮች በኔ ላይ ጥርሳቸውን እንዲነክሱ ያደረጋቸው የፖለቲካ መሪዎቻቸው በአስተውሎት መጓደል ያልተመለከቱትን እውነት እንዳለ በማቅረቤ ነው:: በተለይ አሜሪካ ከግዛቷ አልፋ በአውሮፓ በአውስትራሊያና በህንድ ላይ ጭምር ተፅዕኖ በማድረግ እያስገለለችኝ ትገኛለች:: የህንድ ተወካዮች ምክር ቤት ለህንድ ጋዜጠኞች ባስተላለፈው ትዕዛዝ መሰረት የትኛውም እንቅስቃሴዬ በጋዜጣም ሆነ በሬዲዮ እንዳይዘገብ ማዕቀብ ተጥሎብኛል::»

እሾ ይሄን ይበል እንጂ በዓለም መስተጋብር ውስጥ ገብቶ የአገራቱን አቋም ከመንቀፍ ወደኋላ እንዳላለ ነው በተለይ አሜሪካና ተመራማሪዎቿ የሚያስረዱት:: እሾ በ1981 ዓ.ም ገደማ ከህንድ ወደ አሜሪካ በማሸጋገር ተከታዮቹ በገዙት 65 ሺህ ሔክታር መሬት ላይ አርሳን ውስጥ ከፑኒ ጋር ተመሳሳይነት ያለው መንፈሳዊ ማዕከል አቋቁሟል:: በዚህ መንፈሳዊ ማዕከል ውስጥ በሚካሄደው ህገወጥ ግንባታና ያልተለመደ አኗኗር በተለይ ከአካባቢው አስተዳደር ጋር አለመግባባት በመፈጠሩ የአስተዳደሩ ቢሮ በቦምብ እስከመጋየትና አንድ አስተዳዳሪ ህይወታቸውን እስከማጣት ደርሰዋል:: ይሄንን አሜሪካ የእሾ እና የተከታዮቹ የኃይል እርምጃ ነው በሚል ትወነጅላለች:: በዚህ የተፈጠረው አለመግባባት በተለይ እሾ አሜሪካ ውስጥ የነበረው የመኖሪያ ፈቃድ ተነፍጎ ክልከላውን በተላለፈበት ጊዜ ለሳምንት ያህል ዘብጥያ እንዲወርድ ተደርጓል::

የእሾን አሟሟት ከዚሁ ከአሜሪካ እሰጣአገባ ጋር የሚያያይዙት አሉ:: ዘብጥያ በወረደበት ወቅት በሲ.አይ.ኤ በተወጋው ታሊየም



t.me/OLDBOOKSPDF

(Thallium) የተባለ መርዝ ምክንያት ህይወቱ አልፏል የሚል ጭምጭምታ ቢኖርም ጎን ለጎን ደግሞ በልብ ድካም በሽታ ምክንያት ነው የሚሉ አሉ። ያም ሆነ ይህ ኦሾ በተወለደ በ59 ዓመቱ በ1990 ዓ.ም ህንድ ውስጥ ህይወቱ አልፎ በሒንዱ ኃይማኖታዊ ሥነ-ሥርዓት መሰረት እንደተለመደው አስከሬኑ ተቃጥሎ አመዱ ወደ ወንዝ ተበትኗል።

ያልተለመደው ግን ሞቱን ተከትሎ የመጣው በዓል ነበር። አስከሬኑ በተመስጦ ማሰላሰያ አዳራሽ ውስጥ እየተቃጠለ ባለበት ሰዓት በሺ የሚቆጠሩ ደቀመዛሙርቱ ከመቼም ጊዜ የበለጠ ጨፈሩ፣ ዘፈኑ። ከዚህ በኋላ ነበር አመዱ ወደ ተከታዮቹ የተወሰደው።

ይህም የእሱ እንቅስቃሴ ቀጣይነትን መሰረት የጣለ ነበር። ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ቁጥሩ የበዛ ህዝብ ወደ ፑና መጉረፍ ጀመረ። በተለይ ምሽት ላይ ነጭ ካባ ተለብሶ በሚደረገው በዓል ላይ ሁሉም ኦሾ በህይወት አብሯቸው ያለ ያህል ይሰማቸዋል። ስለዚህ የተከታዮቹ ቁጥር እንደገና በእጥፍ ጨመረ። ቦታው አምስት የእምነ - በረድ ፒራሚዶች፣ አስራ ሁለት ኤከር ስፋት ያለው የዜን ፓርክ እና እጅግ አስደናቂ የመዋኛ ገንዳ ሲኖረው በርካታ የህክምና፣ የፈጠራ፣ የሥራ እና በተመስጦ የማሰላሰል ፕሮግራሞች አሉት። ከሁሉም ፕሮግራሞችና ድርጊቶች መሀል ላይ የሚገኘው በተመስጦ ማሰላሰል ነው። የቦታው ድባብ በራሱ አንድ ሰው ወደ ውስጡ እንዲመለከት፣ በውስጡ ያለውን እውነት እንዲፈልግ የሚያደርግ ነው ይባላል። ይህንን የተመሰጦ ተግባር የትም ሆኖ ማከናወን እንደሚቻል የሚገልፁት ተከታዮቹ፣ ይሁንና ባለራዕዩ የነበረበት ቦታ ላይ ማድረጉ የተሻለ ነው ብለው ያምናሉ። የፑና አባላት «በዓለም ላይ ካሉ ሁሉ እጅግ ታላቅ መንፈሳዊ ሰላም የሚገኝበት ቡድን ነው» በማለትም ይገልጹታል።

ለእነሱ ቁልፉ የኦሾ መኖር ነው። በዚያ ቦታ ኦሾ አሁንም በህይወት ያለ ያህል ነው።

ኦሾ የህይወት ዘመኑን በሙሉ ያሳለፈው በአስተዳደጋችን የሰረፁብንን ነገሮችን፣ ተስፋ አድርገን የመጠበቅ እና የማመን አቋሞችን


t.me/OLDBOOKSPDF

ለማጥፋት በመሞከር ነው። እንደ ኦሾ አባባል፣ «ብቸኛው መንገድ ራስን መሆን ነው።»

ይህ ጽሑፍ ሰ·ዴቫ ሳርሶ የተባለው የኦሾ ተከታይ "The Real osho - a short biography" በሚል ርዕስ ... ካሰፈረው ጽሑፍ እና አስማየሁ ገላጋይ «ኦሾ - የአወዛጋቢ ሃሳቦች ሰርጥ» በማለት በኔሽን ጋዜጣ ካቀረቡት ጽሑፍ አንድ ላይ ተዋህዶ የቀረበ ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF

ባግዋን ሽሪ ራጅኒሽ አሁን «ኦሾ» ተብሎ ነው የሚታወቀው፡፡ ኦሾ እንደተናገረው ስሙ የመጣው «ዊሊያም ጀምስ» ከሚለው ቃል ነው፡፡ «ኦሺኒክ» የሚለው ቃል ውቅያኖስ ውስጥ መሟሟት የሚል ትርጓሜ አለው፡፡ ኦሽኒክ የሚለው ቃል የሚገልፀው ተግባሩን ነው፣ ይላል፡፡ ግን ተግባሩን ፈፃሚውስ? ይህን ለመግለፅ «ኦሾ» የሚለውን ቃል እንጠቀማለን፡፡ በኋላ ላይ እንደተገነዘበው «ኦሾ» የሚለው ቃል ጥንት ሩቅ ምስራቅ አካባቢ አገልግሎት ላይ ይውል ነበር፡፡ «የተባረከው»፣ ከሰማይ አበባ የሚረግፍለት የሚል ትርጓሜ አለው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# መግቢያ

ከውስጥ የሚገኙትን ገፆች ሲያነብቡ ይነሳሳሉ፣ ይበሳጫሉ፣ ይደስታሉ፣ ይነካሉ፣ በብዙ መንገዶች አሁን ያለዎትን ማንነት ይለውጣሉ። ይህ መፅሃፍ ከእርስዎ ተነስቶ ወደ መለኮታዊው የህይወት ምሉዕነት የሚመጥቅ በታሪኮች፣ በቀልዶች እና በሱትራዎች የተሞላ የልብ ሰረገላ ነው።

በዚህ መፅሃፍ ውስጥ ከሚገኙት ቃላት ጀርባ ኦሾ በቀን ለሃያ አራት ሰዓታት ተጣብቆት የሚኖረው ፍፁም ፀጥታ ይገኛል። ልብዎ የተጠማች ከሆነች በእነዚህ ቃላት መካከል አስደሳቹን የፀጥታ ትንፋሽ መስማት ይችላሉ።

ይህን መፅሃፍ እያነበቡ ቢያንስ አንድ ጊዜ በሆድዎ ካልሳቁ ምንም ተስፋ የለዎትም፤ በሮችዎና መስኮቶችዎ መዘጋት ብቻ አይደለም ተቆልፈዋል። በእነዚህ ገፆች ውስጥ የባለ ራዕዩ ጠቢብ ኦሾ የተለየ፣ ውብ፣ ሰርስሮ የሚገባ ምልከታ እና ግልፅነት በግልፅ ይታያል። ኦሾ ይቅርታ አይጠይቅም፣ አስታራቂ ሃሳብ አይፈልግም፣ ሃሳቡ ተቀባይነት እንዲያገኝ ወይም እንዲከበርም አይጠይቅም። አዕምሮዎን ሰርስሮ፣ ልብዎን ሰንጥቆ «አዎ፣ ልክ ነው!» የሚያስብልዎትን እውነት እየነገረዎት ነው። እውነት በሌላ መንገድ ይገለጥ ይሆን?

«ወደ ማለዳ ፀሃይ እየቀረብን ነው» ይላል ኦሾ፣ ንግግሩን ሲቀጥል። «ከትንሽ ጥረት ጋር ዓለማችን ከዚህ በፊት ሆና እንደማታውቀው እጅግ ውብ ስፍራ ትሆናለች - የሰው ልጅ ሁልጊዜ እንደሚያልማት አይነት።»

ስለዚህም አዕምሮዎን ከጉን አስቀምጠው የልብዎን መጋረጃ ትንሽ ይክፈቱና ይጠባበቁ፣ ያስተውሉ. . . ለውጡ ተጀምሯል።



t.me/OLDBOOKSPDF

# መጀመሪያ ጥበብን የተመለከተ ሰው፣ የመጀመሪያው አዋቂ (ጥበበኛ) እና ቅዱስ ነው

# 1

**ታህሳስ 29 - 1986፣ ቦምቤ**



t.me/OLDBOOKSPDF

# ልዩ ተሰጥዖ ያለው ሰው ተራ እንደሆነ የሚሰማውና ተራ የሚሆነው እንዴት ነው?

**ተወዳጁ ባግዋን፣**

**ስእኔ ማሰብ ከምችለው በላይ እጅግ ልዩ ተሰጥዖ ያለህ ሰው ነህ:: ይሁን እንጂ ተራ እንደሆንክ እንደሚሰማህ አውቃለሁ:: ተሰጥዖ ያለው ወይም ምጡቅ የሆነ ሰው ተራ እንደሆነ የሚሰማውና ተራ የሚሆነው እንዴት ነው? ሁልጊዜ የተለየሁ እንደሆንኩ ሳስብ አንድ መጥፎ ነገር እንደሚከሰት አስተውያለሁ:: ይሁን እንጂ አሁን ድረስ የእውነተኛ ትሁትነት እና ቀላል ኑሮ የሚገኝበትን የቅንነትን መንገድ አላገኘሁትም:: እባክህን ስለዚህ ጉዳይ ጥቂት የምትነግረኝ ነገር ይኖራል?**

ተራ እንደሆንኩ መሰማት ብቻ አይደለም - ተራ ነኝ::

ተሰጥዖ ያላቸው እና ምጡቅ የሆኑ ሰዎች መላው ህይወት ተራ እንደሆነ ስለሚዘነጉት የእንተን አይነት ችግር ይገጥማቸዋል:: አንተ የምትሰቃየውን ስቃይ ይሰቃያሉ::

የፀሃይ ውጣት ምንም ውብ ቢሆን ንፁህ ተራ ክስተት ነው:: በከዋክብት የተሞላ ሰማይ በምንም አይነት መንገድ የተለየ ነገር የለውም:: በተዋቡ አበቦችና ግሩም መዓዛ ባላቸው ዕፅዋት የተሞላ አፀድ የአንድ ተራ ህልውና አካል ነው::

ተሰጥዖ ያላቸው ሰዎች ከህይወት ጋር ያላቸውን ግንኙነት ስለሚዘነጉት ችግር ውስጥ ይገባሉ:: በዚያች ሚጢጢዬ ተሰጥዖዋቸው ውስጥ ታጥረው እስረኛ ይሆናሉ::

የአንተ ተሰጥዖ ወይም ችሎታ ምንድነው? መሳል ስለቻልክ ብቻ ምጡቅ ልትባል ትችላለህን? እስኪ ሁላችሁም ቢራቢሮዎችን፣ አበቦችን፣



t.me/OLDBOOKSPDF

ፀሃይ ስትጠልቅ የሚፈጠረውን የሰማይ አስደናቂ ትዕይንት ልብ ብላችሁ ተመልከቱ፤ መላው ህልውና በቀለማት ህብር የደመቀና የተዋበ ነው። እናንተ አንድ አነስተኛ ሽራ ላይ አንድ ስዕል ስለሳላችሁ ብቻ ልዩ ሰው ልትባሉ ነውን? ለመሆኑ የሳላችሁት ምንድነው?

ህልውና መታወስ አለበት። ይሄንን ካደረጋችሁ «እኔ ልዩ ነኝ» በሚለው የራስ ኩራት (ለራስ የሚሰጥ ከፍተኛ አመለካከት) ስሜት አትተብተቡም። «ልዩ ነኝ» የሚል ስሜት በተሰማችሁ ቅፅበት ከህይወት፣ ከፍቅር፣ ከመላው ዓለም ጋር ያላችሁ ግንኙነት ይቋረጣል - ብቻችሁን ትቀራላችሁ።

እውነተኛ ብልህ (ምጡቅ ችሎታ ያለው ሰው) ልዩ መሆኑን አያውቅም፣ ልዩ እንደሆነም አይሰማውም። ይህ ነው የእውነተኛ ምጡቅ መመዘኛው። ልዩ እንደሆነ ከተሰማው እሱ እውነተኛ ችሎታ ያለው ብልህ አይደለም። ልዩ የመሆን ስሜት የሚመነጨው ከበታችነት ስሜት ነው። የበለጠ የበታችነት ስሜት በተሰማችሁ ቁጥር የበለጠ ልዩ ሰው ሆናችሁ ለመቅረብ ትሞክራላችሁ።

የህልውናን ስፋት፣ የትየለሌነት እና ዘላለማዊነትን ማስተዋል ከቻልን፣ በማለዳ የጠዋት ፀሃይ ብቅ እንደሚል ጤዛ መሆናችንን እንረዳለን። በውበቱ የዛፍ ቅጠሎች ላይ እንደ ዕንቅ እናንፀባርቃ ይሆናል። ነገር ግን በጥቂት ነፋስ ጤዛዎቹ ተንሸራተው ውቅያኖስ ውስጥ በመውደቅ ይጠፋሉ። ውቅያኖሱ ሁልጊዜም አለ። ህያው ነው። እናንተም አሁን እና እዚህ መኖር ወይ መታወስ ከፈለጋችሁ ራሳችሁን ከአንዷት ጤዛ ጋር አታመሳስሉ። የፈለገ ውብ ብትመስሉም፣ ውበታችሁ የላይ ብቻ ነው።

ከውቅያኖሱ ጋር ብትዋሀዱ፣ ውስጡ ገብታችሁ ብትሟሙ ግን ከውቅያኖሱ ጋር መቼም አትነጣጠሉም። እንዲህ ሲሆን ጤዛው ሞተ ማለት አይደለም፤ በተቃራኒው ጤዛው ውቅያኖስ ሆነ ማለት እንጂ።

እውነተኛ ትህትናን፣ እውነተኛ ቀናነትን እና ቀላል ኑሮን እንዴት ሊገኝ እና ሊተገበር እንደሚችል ጠይቀኸኛል። እነዚህን ነገሮች ፈፅሞ መተግበር አይቻልም፣ ፈፅሞ አይገኙም። እነኚህ ነገሮች በእናንተ



t.me/OLDBOOKSPDF

እጅ ውስጥ ያለ አይደለም። ግንዛቤው ካላችሁ ብቻ ነው የሚከሰቱት። የዚህ ምስጢራዊ ዓላም አንድ አካል መሆናችንን ብቻ መገንዘቡ ይበቃችኋል። ዓለም ደግሞ እጅግ ሰፊ ናትና ተራ ከመሆን ውጪ ታድያ ምን መሆን ትችላላችሁ?

ጥያቄው ተራነትን የማግኘት ወይም የመተግበር አይደለም። ጥያቄው «ተራ ከመሆን ውጪ ሌላ ምን ልሆን እችላለሁ?» የሚል የግንዛቤ ጥያቄ ነው። አንድ ቀን ተራ ላትሆኑ ትችላላችሁ። በሌላ ቀንም በድጋሚ ላትሆኑ ትችላላችሁ። ነገር ግን ተራ እና ትሁት ለመሆን እየሞከራችሁ ነውን? በህይወታችሁ ተራ እና ቀላል ኑሮን ለመኖር እየጣራችሁ ነው ወይ?

እንግዲህ ህይወት ቀላል ናት። ልታወሳስቧት ከፈለጋችሁ ግን ትችላላችሁ። በጭንቅላታችሁ ስትቆሙ የዚያኔ ህይወት ትወሳሰባለች! የደነዘ መጥፎ ተግባራትን በሙሉ ስትሰሩ ያን ጊዜ ህይወት ውስብስብ ትሆናለች።

ስለዚህ ምንም ነገር አታድርጉ። ንቁ ሁኑ እና ከተዓምራዊና ሚስጥራዊ ዓለም ጋር መዛመድ አለመዛመዳችሁን ለማስተዋል ሞክሩ። እንዲህ ካደረጋችሁ ልክ እንደ ህፃን ልጅ ንፁህ እና ቀላል ኑሮ የምትኖሩ እንደሆናችሁ በድንገት ይገለጽላችኋል።

ህፃን ልጅ ተራ የሚሆነው ተራነትን በተግባር ለመተግበር ሞክሮ ሳይሆን፣ ከመላው ሁኔታ ጋር ቅኝቱን ተከትሎ በአንድ መንገድ በተራነት ስለሚጓዝ ነው። በእናቱ ማህፀን ውስጥ ሳለም ከምሉዕነት ጋር ህብር ነበረው። ህፃን ሆኖም ይህንን ገና አልረሳውም ማለት ነው።

አንድ እውነት ልብ ብላችኋል? ወደ ኋላ መለስ ብላችሁ ለማስታወስ ስትሞክሩ ምን ያህል ርቀት በትውስታ መጓዝ እንደምትችሉ አስተውላችሁ ታውቃላችሁ? የሶስት ወይም የአራት ዓመት ህፃን ሳላችሁ የነበረው ሁኔታ ትዝ ይላችኋል? ሆኖም ከዚያ በላይ ወደኋላ ተመልሳችሁ ማስታወስ አትችሉም። የሶስት ዓመት ህፃን ሳላችሁ ግን ፍፁም ንቁ ነበራችሁ። ህይወትን ከየትኛውም ጊዜ በበለጠ ትደስቱባት ነበር። ሁሉም ነገር የሚያስደስት ውብ ነበር፣ የተለያየ ቀለም ያላቸው



t.me/OLDBOOKSPDF

መጫወቻዎቻችሁ፣ ትናንሽ ድንጋዮች፣ በባህር ዳርቻ የሚገኙ የባህር ዛጎሎች በሙሉ ድንቅ ነበሩ:: እጅግ በጣም ትልቅ ሀብቶቻችሁ ነበሩ::

ከሶስት ዓመት በፊት፣ እስከተወለዳችሁበት ጊዜ ድረስ ወደኋላ ዞር ብላችሁ ማስታወስ የማትችሉበት ምክንያት በእነዚያ ሶስት ዓመታት ንፁህና ተራ ስለነበራችሁ ነው - ትውስታ መሰብሰብ የማትችሉ ተራ:: ይህን ማድረግም አያስፈልጋችሁም ነበር:: ልክ እንደ መስታወት የምታንፀባርቁ ነበራችሁ:: ያቺ ቅፅበት ትደሰቱባታላችሁ እንጂ አታስቡዋትም:: ምንም የምትሰበስቡት ትውስታ አልነበረም:: ስቁንቁንም አልነበራችሁም:: ለራሳችሁ ያላችሁ ከፍተኛ አመለካከት (ego) ገና አልተፈጠረም ነበር:: ማህበረሰቡ ለራስ ያለ ከፍተኛ አመለካከትን ለወንዶች ለማስለመድ ቢያንስ አራት ዓመት፣ ሴቶችን ለማስለመድ ደግሞ ሶስት ዓመት ይፈጅበታል::

ይህ ጥያቄ ሁልጊዜ ግራ ያጋባኛል፣ ለሴቶች ሶስት ዓመት፣ ለወንዶች አራት ዓመት እንዴት ሊሆን ቻለ?

ይህ የሚሆነው ሴቶች የበለጠ የራስ ንቃት ስላላቸው ነው::

ሙላ ናስሩዲን ሁለት ቢራቢሮዎችን ለመያዝ ለሁለት ሰዓታት ያህል መልፋት ነበረበት:: በመጨረሻም መያዙ ተሳካለትና ለሚስቱ «ያዝኳቸው:: አንዱ ወንድ፣ ሌላኛዋ ደግሞ ሴት ናት» አላት::

«እምላኬ! ወንድና ሴት መሆናቸውን በምን ለየህ?» በማለት ሚስቱ ጠየቀችው::

«በጣም ቀላል ነው» አለ:: «ሴቷ ለሁለት ሰዓታት ያህል ያለ ማቋረጥ ከመስታወቱ ፊት ተቀምጣ ነበር:: ወንዱ ደግሞ ለሁለት ሰዓታት ያህል ጋዜጣ ሲያነብ ነበር:: በዚህም ማን ምን እንደሆነ መለየት ቀላል ነበር::»

ሴት ከወንዱ የበለጠ በአካሏ የምትመራ ናት፣ አካሏ ላይ ታተኩራለች . . . ስለ ውበቷ ታውቃለች፣ ሌሎች ውበቷን እንደሚያውቁም ታውቃለች:: ለዛም ነው ለራሷ ያላት ከፍተኛ አመለካከት ከወንዱ አንድ ዓመት ቀደም ብሎ የሚፈጠረው::

ሴት ከወንዱ በበለጠ በራሷ አጥር ውስጥ የታጠረች ናት::



t.me/OLDBOOKSPDF

ወንድ ግን ራሱን ሙሉ በሙሉ ረስቶ አካባቢውን ያማትራል፣ በዚህም ምክንያት ወደ ራሱ ለማትኮር ከሴቷ ለጥቂት ጊዜ ያህል ይዘገያል። የራስ ከፍተኛ አመለካከት እንዴ ከያዘው በኋላ ግን ከሴቷ የበለጠ ጠንካራ እና መርዛማ ይሆናል። ሴቷ ለራሷ ያላት ከፍተኛ አመለካከት በውብ አይኖቿ፣ በውብ ፀጉሯ፣ በውብ አካሏ ላይ የተወሰነ ነው። በቀላሉም የሚጎዳ ነው። የምትፈልጋቸው ነገሮችም ቢሆኑ ትላልቅ (ብዙ) አይደሉም።

ወንድ ግን ታላቁ አሌክሳንደርን፣ ናፖሊዮን ቦናፓርትን፣ አስፈሪው ኢቫንን መሆን ይፈልጋል። ለራሱ ያለው ከፍተኛ አመለካከት ወሰን የለውም። ወሰኑ መላው ዓለም ነው።

በከፍለ - ዘመኑ መባቻ አካባቢ የመጀመሪያዎቹ ተራራ ወጪ ቡድኖች ወደ ሂማሊያ ተራራ ጫፍ ለመውጣት ሲሞክሩ (ጉሪሻንካር በዓለም ዘንድ ኤቨረስት ተብሎ ነው የሚታወቀው) «ህይወታችሁን ለምን አላስፈላጊ አደጋ ላይ ትጥላላችሁ?» የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር። ምክንያቱም ምንም የሚገኝ ነገር አልነበረም. . . መቼም የማይቀልጥ ዘላለማዊ ከሚመስለው ግግር በረዶ በቀር ሌላ የሚያገኙት ነገር አልነበረም።

መሪው ሲመልስም «ዋናው ነገር ኤቨረስት ላይ አንድ ነገር ማግኘቱ አይደለም። ዋናው ጥያቄ የሰው ልጅ ከዚህ ቀደም ወጥቶበት የማያውቀው ይህ ተራራ ካልወጣነው ለራሳችን ያለን ከፍተኛ አመለካከት መጉዳቱ ነው» ብሎ ነበር።

አስገራሚ ነው - ምስኪኑ ኤቨረስት ለማንም ምንም አይፈይድለትም። በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ግን በአንድ ቀላል ምክንያት ሳቢያ የኤቨረስት ተራራን ለመውጣት ሲሞክሩ ህይወታቸውን አጥተዋል - ምክንያቱም ተራራው እዚያ ስላለ ነው። አናቱ ላይ ሳይወጣ ደግሞ ሊቀር አይችልም። የሰው ልጅ ሊያሸንፈው የግድ ነውና።

ጨረቃዋስ ምን አላት? ምንም። መኖሯ በራሱ ግን ችግር ነው። በማርስስ ላይ ምን አለ? ምንም ባይኖርም ማርስ ራሷ እዚያ አለች። ሌሎች በሚሊዮን የሚቆጠሩ ከዋክብትም አሉ። ወዘተ . . . ወዘተ . . .



t.me/OLDBOOKSPDF

የሰው ልጅ ለራሱ ያለው ከፍተኛ አመለካከት ወሰን የለውም፡፡

ሰፊና ሁሉም እየሰፋ እና እያደገ የሚሄድ ነው፡፡

አንዲት ሴት በውብ ልብሶቿ፣ ጌጣጌጦቿ፣ በውቡ መናፈሻዋ፣ የመዋኛ ገንዳዋ . . . ስለምትረካ ከዚህ የበለጠ ብዙ አትጠይቅም፡፡ ለዛም ነው አንዲትም ሴት ጉተማ ቡድሃን መሆን ያልቻለችው፡፡ ይገርማል አይደል? ግንኙነቱን ብታውቁ ትደነቃላችሁ፡፡ ለመሆኑ ሁለቱ ምን ዓይነት ግንኙነት አላቸው?

ጉተማ ቡድሃን ለመሆን ትልቅ ተራራ የሚያህል የራስ ላይ ከፍተኛ አመለካከት ያስፈልጋችኋል፡፡ ይህን ሸክም ወይ ታወርዱታላችሁ፣ አሰበለዚያ ይገድላችኋል፡፡

የሴቶች የራስ አመለካከት ግን አነስተኛ ስለሆነ የተራራን ያህል ሸክም አይሆንም፡፡ ለእነሱ ሸክሙን ለመጣል ወይም ለመታገል መሞከር አስፈላጊ አይደለም፡፡ ለዛም ነው ሴቶች ከንቃት ጫፍ ያልደረሱት፡፡ በትናንሽ ነገሮች በቀላሉ ይረካሉና፡፡

ወንድ ግን እርካታ አያውቅም፡፡ ይህ አለመርካት ደግሞ አስቸጋሪና ከባድ ስቃይ ስለሚፈጥርበት ከዚህ ችግር የሚወጣበት መንገድ የግድ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

ተራነት እንዴት ይገኛል ብለህ ጠይቀህኛል፡፡ ከውጪ የሚገኘው ተራነት የይምሰል ነው፣ ምክንያቱም በውስጥህ ተራ እንዳልሆንክ ታስባለህና፡፡ ከውጪ የምታገኘው ትሁትነትም የውሸት ይሆናል፣ ምክንያቱም በልብህ ውስጥ ይህ የምትኖርበት ህብረተሰብ ደንብ እና አጉል ልማድ መሆኑን በጥልቀት ታውቃለህና፡፡ በዓለም ላይ ትሁት እና ቀና መሆን ጭምብሎች ናቸው፡፡ ካለነዚህ ጭምብሎች በቀር ቀናነት እና ትሁትነት ዋጋ ያስከፍላሉ፡፡

ከጠየቅከኝ ግን እነግርሀለሁ፣ እነዚህን የማግኘት ሃሳብህን ተወው፡፡ የማግኘት ሃሳቡ ራሱ የራስ ከፍተኛ አመለካከት ያለበት ነው፡፡ ስስታምነት ነው፡፡

እናንተ ተራ እና ትሁት ናችሁ፡፡

እስኪ ዙሪያችሁን ተመልከቱ፡፡

ውቅያኖሱን፣ ሰማዩንም ተመልከቱ፡፡

እናስ፣ ተራ እና ዝቅ ያለ አለመሆን እንዴት ይቻላችኋል?



t.me/OLDBOOKSPDF

# የሁሉንም ጥያቄዎች የተሟላ መልስ ማግኘት ይቻል ይሆን?

★

## ሰይጣን መጀመሪያ ወደ ወንድ ያልሄደው ለምንድነው?

ተወዳጁ ባገዋን፣

አንድ ጥያቄ በማፍኩልህ ቁጥር ከእያንዳንዱ ቃል ጋር በውስጠ ብዙ፣ ብዙ ጥያቄዎች ይነሳሉ:: በጥያቄዎች ደን ውስጥ ሳይጠሩ እንደ ቀላል ዓረፍተ ነገር መፃፍ የማይቻል ከባድ ሆኖብኛል::

አንዱን ጥያቄ ፅፌ ስጨርስ ፍጹም ተዳክሜ ነበር:: መምህር፣ ሁሉን ማወቅ በጣም ስለምፈልግ እንባ በአይኖቼ ግጥም ይላል:: በተሳሳተ መንገድ ጀምሬው ሲሆን ይችላል፣ ነገር ግን ሁሉን ማወቅ እፈልጋለሁ:: ሁሉንም ነገር መጠየቅ፣ የሁሉንም ጥያቄዎች የተሟላ መልስ ማግኘት እሻለሁ::

ውዱ የመልሶች አባት፣ በዚህ ጉዳይ አስተያየትህን ልትሰጠኝ ትችላለህ?

አዕምሮ ልክ እንደዛፍ ነው:: ጥያቄዎችም ልክ እንደ ዛፍ ቅጠሎች በየአቅጣጫው ያድጋሉ:: አንዱን ቅጠል ብትቀጥፉት ዛፉ ቢያንስ በሶስት ቅጠሎች አባዝቶ ይተካዋል:: አትክልተኛ ዛፉ እንዲያድግለት እና ቅጠሎቹ እንዲያቆጠቁጥለት የሚከተለው ይህን መንገድ ነው::

ጥያቄዎችንም በተመለከተ አዕምሮ ልክ እንደ ዛፍ ነው:: በርካታ ጥያቄዎችን የማፍለቅ ችግር የለበትም:: በጣም ፍሬያማ ነው፤ ጥያቄዎችን ብቻ ያመርታል:: ከእያንዳንዱ መልስ ተነስቶም በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ጥያቄዎችን ይፈጥራል:: አዕምሮን ጥያቄ ከማፍለቅ ማስቆም



t.me/OLDBOOKSPDF

የሚችል በቂ መልስ የለም። ስለዚህ አንተ የተከተልከው የተሳሳተውን መንገድ ነው ማለት ነው። ሙሉ በሙሉ ተሳስተሃል። ሁሉንም ነገር አውቀህስ ምን ትጠቀማለህ? አምላክን መሆን ትፈልጋለህ ወይ?

አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር ህይወትን በመፍጠሩ ስህተት ሰርቷል ብለው ያምናሉ። እግዚአብሔር ምክራቸውን ቢቀበል ዓለም የተሻለች ስፍራ ትሆን ነበር ብለው የሚያምኑ ሰዎች አሉ። እነዚህ ሰዎች የተወሰነ እውነት አላቸውና እንዲሁ በቀላሉ ገሸሽ ልታደርጋቸው ወይ ችላ ልትሏቸው አትችሉም።

ምክንያቱም ህይወትን ብትመለከቱ እግዚአብሔር የሰራቸውን በርካታ ስህተቶች ታገኛላችሁ። ጥቂት ምሳሌዎች ላቅርብ፦

እንደመፅሐፍ ቅዱስ ትረካ እግዚአብሔር መጀመሪያ አዳምን እንጂ ሄዋንን አልፈጠረም። ሄዋን እግዚአብሔር የፈጠራት ሁለተኛዋ ሴት ናት። ከሄዋን በፊት ሌላ ሴት ፈጥሮ ነበር። ይህ ጉዳይ በርካታ ጥያቄዎች ስለሚያስነሳ ክርስቲያኖች ምንም አይሉም። አይሁዶችም አይናገሩትም። የመጀመሪያዋ ሴት ምን ሆነች?

ገና በመጀመሪያው ሌሊት እግዚአብሔር አንድ አነስተኛ አልጋ ብቻ በመስራት የመጀመሪያውን ስህተት ፈጠረ። አልጋው ሁለት ሰዎችን ማስተኛት የሚችል ሰፊ አልነበረም። እግዚአብሔር ወንድን እና ሴትን ፈጥሮ እንዴት ጠባብ አልጋ ይሰጣቸዋል።

እናም በመጀመሪያው ሌሊት እናንተ አሁን ድረስ የምታደርጉት ጠብ ተጀመረ። ሴቷ አልጋው ላይ መተኛት ፈለገች። ወንዱም አልጋው ላይ መተኛት ፈለገ። የትራሱም ነገር ሌላው የሚያወዛግባቸው ጉዳይ ነበር። ከሁለቱ መሬት ላይ ለመተኛት ፈቃደኛ ስላልነበር ሌሊቱን በሙሉ መተኛት አልቻሉም።

ተራ አናጺ ከዚህ የተሻለ መስራት ይችላል። አዳም ወደ እግዚአብሔር ሄዶ «ፈጣሪዬ፣ ምን አይነት ህይወት ነው የሰጠኸኝ? በዚህ አይነት መስማማት የምንችል አይመስለኝም። ለምንድን ነው ጠባብ አልጋ የሰራህልን?» አለ።



t.me/OLDBOOKSPDF

እዚህ ጋር እግዚአብሔር ሁለተኛውን ስህተት ፈጠረ:: ሁለት ሰው የሚያስተኛ ሰፊ አልጋ አያደለም ዓለምን መፍጠር የቻለው አምላክ፣ ሴቷን ጠሰዳት:: ያቺ ሴት ትክክለኛዋ ሴት ነበረች:: ምክንያቱም በጥንካሬ፣ በአካል፣ በአዕምሮ ችሎታዋ . . . በሁሉም ነገሯ ከወንድ እኩል ነበረች::

ለሺ ዓመታት ወንዶች ሴቶች ላይ ያደረሱት በደል ሁለት ሰዎችን የሚያስተኛ ሰፊ አልጋ በመስራት ሊወገድ ይችል ነበር:: ነገር ግን እግዚአብሔር ሌላ ሴትን ፈጠረ:: ይህችኛዋ ግን እንደቀድሞዋ ከወንድ እኩል አልነበረችም:: የመጀመሪያዋ ሴት የተፈጠረችው አዳም ከተፈጠረበት አፈር ነበር:: ሁለተኛዋ ሴት የተፈጠረችው ግን ከአዳም የጐን አጥንት::

በመሆኑም እኩል መሆን አልቻለችም - የጐን አጥንት ነች!

አዳም ውጪ አምሽቶ ወደ ቤቱ ከገባ በኋላ እንቅልፍ ሲወስደው፣ የሄዋን የመጀመሪያ ስራ የጐን አጥንቶቹን መቁጠር ነበር ሲባል ሰምቻለሁ:: ማን ያውቃል? ሌላ ቦታ ሌላ ሴት ተፈጥራለት ሊሆን ይችላል:: ይህንን ደግሞ እሱን መጠየቅ አያስፈልግም . . . የጐን አጥንቶቹን መቁጠር ይበቃል::

ደካማ አስተሳሰብ ያለው ሰው እንኳን ቢሆን አንድ ነገር መከልከል ማለት የጉጉት እና የማወቅ ፍላጐት መፍጠር መሆኑን ይረዳል:: እግዚአብሔርም አዳም እና ሄዋንን ገደብ ጣለባቸው:: መከልከል ብቻ አይደለም ለአዳም እና ለሄዋን ሁለት ዛፎችን አሳያቸው . የመጀመሪያው ጥበብ የሚገኝበት፣ ሌላኛው ዘላለማዊ ህይወትን የሚሰጥ ዛፍ:: ከዚያም «የእነኚህን ዛፎች ፍሬዎች መብላት አትችሉም!» አላቸው:: የአትክልት ቦታው እጅግ ሰፊ ነበር:: አዳም እና ሄዋን ብቻቸውን እዚያው ቢተዉ ኖሮ እኛ ራሳችን በአሁኑ ጊዜ እነኛን ሁለት ዛፎች ማግኘት የምንችል አይመስለኝም::

እግዚአብሔር ዛፎቹን አሳይቶ «ይህ ጥበብን የሚያስገኝ ዛፍ፣ ይህኛው ደግሞ ዘላለማዊ ህይወትን የሚሰጥ ዛፍ ነው:: ከቀሩት ከሌሎቹ ዛፎች ግን እንደልባችሁ መብላት ትችላላችሁ» ማለቱ ትክክል



t.me/OLDBOOKSPDF

አይመስለኝም፡፡ የአዳም እና የሄዋን ቀልብ እነኛ ዛፎች ላይ ቢያርፍ አይደንቅም፡፡ እናንተም ብትሆኑ አዳም እና ሄዋን ካደረጉት የተለየ ነገር አታደርጉም፡፡

እኔ ትክክለኛ ነገር አድርገዋል እላለሁ፡፡

ምክንያቱም ጥበብ ጉጂ ነገር አይደለም፡፡ ጉዳት የሚያደርሰው አላዋቂነት ነው፡፡ ዘላለማዊ ህይወት ልጆቻችሁን የምትነፍጓቸው ነገር አይደለም፡፡ እግዚአብሔር ግን የሥነ - ልቦና መሰረታዊ መርሆችን የሚያውቅ አይመስልም፡፡

ሁሉንም ነገር አውቃችሁ ምን ታደርጋላችሁ?

የጥበብ እና ዘላለማዊ ህይወት የሚሰጡትን የሁለቱን ዛፎች ፍሬዎች ብትበሉ ይበቃል፡፡ እኔም ለተከታዮቼ የማቀርብላቸው ሁለቱን ዛፎች ብቻ ነው፡፡

እነኛ ሁለት ዛፎች የሚገኙት በአትክልት ሥፍራ (ገነት) ውስጥ ሳይሆን በእናንተ ውስጥ ነው፡፡ በተመስጦ ውስጥ ስትሆኑ፣ ፀጥ ብላችሁ ውስጣችሁ ስታዳምጡ፣ ሰላማዊ ስትሆኑ . . . ጥበብ ከውስጣችሁ ይመነጫል፡፡

ጥበብ ከፀጥተኛ ጥልቅ አሳቤ መንጭቶ የሚያንፀባርቅ ብርሀን ነው፡፡

አንድ ጊዜ ውስጣችሁ በብርሀን ከተሞላ ወዲያውኑ ህይወታችሁ ዘላለማዊ መሆኑን ትረዳላችሁ፡፡ ሞት ልብ ወለድ ይሆንባችኋል፡፡

እግዚአብሔር የሰው ልጅ ውስጡን እንዳይመለከት ከልክሎታል፡፡ የሰው ልጅ ወደ ሰፊው የገነት የአትክልት ስፍራ መሄድ፣ ማለትም ሁሉንም ዓለም ማሰስ ይችላል . . . ነገር ግን ወደ ውስጡ እንዳይመለከት ተከልክሏል፡፡

መፅሀፍ ቅዱስ፣ ሄዋን የጥበብን ፍሬ እንድትበላ ያታለላት (ያባበላት) ሰይጣን እንደሆነ ይነግረናል፡፡ እናንተ ግን ከዚህ ጀርባ ትክክለኛ ሳይንስ መኖሩን ልብ በሉ፡፡

ሰይጣን «መጀመሪያ የዘላለማዊ ህይወት ከሚያስገኘው ፍሬ ብሉ» አላለም፡፡ ዘላለማዊ ህይወት ከሚያስገኘው ዛፍ መብላት



t.me/OLDBOOKSPDF

አትችሉምና:: ዓይናችሁ ስለታወረ ወደ ዛፉ መቅረብ አትችሉም:: በመጀመሪያ ዓይናችሁ መገለጥ (መብራት) አለበት::

በመሆኑም ሰይጣን በመጀመሪያ ያሳመናት ጥበብን የሚያስገኘውን ዛፍ እንድትበላ ነው:: ያቀረበላትንም ምክንያት እዚህ ጋር ማንሳቱ ጠቃሚ ነው:: ሰይጣን ያቀረበላት ምክንያት፣ «እግዚአብሔር ከዚህ ዛፍ እንዳትበሉ የከለከላችሁ ማንም ሰው ከእሱ እኩል እንዲሆን ስለማይፈልግ ነው:: ጥበበኛ ከሆናችሁ እና ዘላለማዊ ህይወት ከተጐናጸፋችሁ አምላክን ትሆናላችሁ:: እግዚአብሔርም ከእናንተ የበለጠ ጥበብ (ኃይል) አይኖረውም:: ፍሬውን እንዳትበሉ የከለከላችሁም ለዚህ ነው» የሚል ነበር::

በነገራችን ላይ በተለያዩ የዓለም ክፍል የሚኖሩ በርካታ ሰዎች፣ «ለምንድን ነው ብዙ ሴቶች የሚከተሉህ? የሴት ተከታዮችህ ቁጥር ከወንዶች የበለጠበት ምክንያት ምንድን ነው?» እያሉ ይጠይቁኛል:: ምክንያቱ ከላይኛው ጋር ተመሳሳይ ነው፣ ሰይጣን መጀመሪያ ወደ ወንድ ያልሄደው ለምንድን ነው?

ወንድ ተከራካሪ ነው፣ ከልቡ አያዳምጥም:: የሚያደምጠው በውስጡ ያለውን ነው:: ሰይጣን የኋላ ኋላ ወንዱን ሊያሳምነው ቢችልም፣ የሚወስድበት ጊዜ ግን ረጅም ነው:: እንዲያውም እሱን ከማሳመኑ በፊት እግዚአብሔር ሊደርስበት ይችል ነበር:: ስለዚህ ሰይጣን ማድረግ የፈለገውን በአጭር ጊዜ ማድረግ ነበረበት::

ሴቷ የምታደምጠው ከልቧ ነው:: ልብ ደግሞ ፈጣን ነው:: አዕምሮ ቀርፋፋ ከመሆኑ በተጨማሪ በርካታ ማሳመኛዎችን ይፈልጋል:: እጅግ ሲበዛ ተጠራጣሪም ነው:: በዛ ላይ የሚያቀርባቸው ጥያቄዎች ማብቂያ የላቸውም:: ሰይጣን መጀመሪያ የተገናኘው ከተጠራጣሪው ጠያቂ ጋር ቢሆን ኖሮ ጠያቂው (ወንዱ) ሁሉንም ነገር ግልፅልፅ እስኪልለት ድረስ ማወቅ ስለሚፈልግ እስካሁን ድረስ እንኳን ጥያቄውን አይጨርስም ነበር::

ሄዋን ግን ሁሉንም ነገር የማወቅ ፍላጐት አልነበራትም:: ጥበብን ለማግኘት ይህ በቂ ነው:: ጥበብ ማለት ሁሉንም ነገር



t.me/OLDBOOKSPDF

ታውቃላችሁ ማለት አይደለም:: ጥበብ በአጭሩ ንጹህ የማመዛዘን ችሎታ ነው:: በብርሀን የተሞላ ልቦ ማለት ነው:: በውስጣችሁ በየትኛውም ሥፍራ ላይ የጨለመ ክፍል አለመኖር ነው:: ጥበብ የእናንተ ሙሉ በሙሉ መስወጥ ነው:: እውቀት ማለት ግን ይህን አይደለም::

እናንተ እውቀትን ትሻላችሁ:: እጅግ ሰፊ የሆነ እውቀትም ልትቀስሙ ትችላላችሁ:: ይሁን እንጂ ባወቃችሁ ቁጥር ጥያቄዎቻችሁም የዚያኑ ያህል እየጨመሩ ይሄዳሉ:: የመጨረሻ ውጤቱም እብደት ነው::

እናም በዚህ በኩል ሴቷን ማሳመን በጣም ቀላል ነበር:: ሰይጣን የሚነግራትን አዳመጠችው:: ያቀረበላት ሀሳብም ግልፅ ሆኖ ታያት:: በቃ!

አንድ ተጨማሪ ነገር ላስታውሳችሁ:: እየሱስ በምድር ላይ ሳለ በተናገረባቸው የሂብሩ እና አራማይክ ቋንቋዎች <ሰይጣን> የሚለው ቃል <Sanskrit> ከሚለው ቃል እንደመጣ አያውቁም:: ሰይጣን እና የተቀደሰ ነገር (devil and divine) የሚሉት ቃላት የመጡት ከአንድ ቃል ነው:: ሰይጣን የሚለው ቃል ቅዱስ (divine) ማለት ስለሆነ በጭፍን አታውግዙት:: ከዛም ታሪኩ የተሰየ መልክ ይይዛል::

እግዚአብሔር ከሰብአዊ ፍጡራን በተፃራሪ ነው:: እግዚአብሔር ብልህ (ጠቢብ) እንድትሆኑ፣ ዘላለማዊ ፍቅር እና ዘላለማዊ ህይወትን የሚያስገኙላችሁን ፍሬዎች እንድትበሉ አይፈቅድም:: መጀመሪያ ጥበብን የተመለከተውን ሰው . . . የመጀመሪያውን አዋቂ (ጥበበኛ) እና ቅዱስ ከማለት ሌላ ምን ማለት እንችላለን?

እግዚአብሔር አዳም እና ሄዋን ጥበብን የሚያስገኘውን ፍሬ መብላታቸውን ሲያውቅ ወዲያውኑ ከገነት አባረራቸው:: አሁን ስለፈራ የግድ ሁለተኛ እርምጃ መውሰድ ነበረበት:: ይህም ዘላለማዊ ህይወትን የሚያስገኘውን ፍሬ የያዘ ዛፍ ነው:: ያንን ዛፍ ከመብላታቸው በፊት ከገነት መባረር ነበረባቸው::

ሀሳቡ ሊኖራችሁ ወይም ላይኖራችሁ ቢችልም ሁሉም የሰው ልጅ ረጅም ህይወት፣ ከዚህ የተሻለ እና ጤናማ ህይወት ለማግኘት እንደሚጥር ማወቅ አስፈላጊ ነው:: ለምን? ምክንያቱም ያ ቁስል እስካሁን አልዳነም:: አሁን ድረስ እያሳደደን አለን::



t.me/OLDBOOKSPDF

ሁሉም ሳይንሳዊ ምርምሮች እና የፍልስፍና ጥናቶች ሁለተኛ ውን ዛፍ ማግኘት ላይ ያተኮሩ የመሆናቸው ምስጢርም ይህ ነው።

ምናልባት ሳይንስ በመጠኑ እድሜን ማስረዘም ችሎ ሊሆን ይችላል። ዘላለማዊ ህይወትን ግን መስጠት አይችልም፣ ለምን ቢባል ሳይንስ የሚያተኩረው አካል (ሰውነት) ላይ ነው። አካል (ሥጋ) ደግሞ ዘላለማዊ ሊሆን አይችልም። ፍልስፍናም ቢሆን ጠንካራ አስተሳሰቦችን ሊሰጣችሁ ይችላል። እነዚያ የሚሰጣችሁ ጠንካራ ሀሳቦች ግን እንደ ሳሙና አረፋ ናቸው። ዘላለማዊ ህይወትን ለያጐናጽፏችሁ አይችሉም።

ይሁንና ይህን ለማድረግ አንድ ሌላ መንገድ አለ። ይኸውም በተመስጦ ማሰብ ነው። ይህ በቀጥታ ዘላለማዊ ህይወት ወደሚያስገኘው ዛፍ የሚወስድ መንገድ ነው።

በመሆኑም ጊዜአችሁን በጥያቄ እና መልስ ከምታባክኑ ዛፉን መፈለግ ይሻላችኋል። ሁለቱም ዛፎች የሚገኙት ደግሞ እናንተ ውስጥ ነው። እነሱ ጋ የሚደረስበት መንገድም ከባድ ጥረትን የሚጠይቅ አይደለም። እንዲውም ከነጭራሹ ጥረት ማድረግ አያስፈልግም። የሚያስፈልገው ጥረት የማይጠይቅ ዘና ማለት ብቻ ነው።

ስለዚህ ጊዜ ባገኛችሁ ቁጥር ዓይናችሁን ጨፍናችሁ ዓለምን እርሷት እና ዘና በሉ። ሀሳብ ልማድ ስለሆነ አይቆምም።

አንድ ቀላል ሚስጥር ልብ በሉ። ሚስጥሩ ነገሮችን ያለምንም መደምደሚያ እና ማዳላት (ብይን ወይም ዳኝነት ሳትሰጡ) እንዲሁ መመልከት ነው። ሀሳባችሁ ልክ በአንድ የፊልም ስክሪን ላይ እንዳለ ምስል እንዲፈስ (እንዲንቀሳቀስ) አድርጉት። በፀጥታ አስተውላችሁ ተመልከቱ እንጂ ብይን አትስጡ። ይህ ከሆነ ቀስ በቀስ ጭንቅንቁ፣ መዋተቱ እየቀነሰ ይሄዳል። ከዚያ በኋላ አንድ ቀን በድንገት አዕምሯችሁ ከሀሳብ ነፃ ሆኖ ታገኙታላችሁ።

ይህ በአንድ ሰው ህይወት ውስጥ ወሳኝ ምዕራፍ ነው። ምክንያቱም ወደ ተለያዩ ሀሳቦች ይዋትት የነበረው ሀይል ምንም ነገር ሳያገኝ ሲቀር በመጨረሻ ወደ ዋነኛ ምንጩ ይመለሳል።

የክቡ ቅርፅም ሙሉ በሙሉ ይገጥማል።



t.me/OLDBOOKSPDF

በዓለም ላይ በርካታ ሚስጥራዊ ማህበረሰቦች ጭራውን አፉ ውስጥ የከተተ እባብ ምስልን ለምልክትነት ሲጠቀሙበት አይታችኋል፡፡ ያ ምልክት የራሳችሁ ሀይል ወደ ምንጩ ተመልሶ ሲገባ እና የክብ ቅርጹን ሙሉ ሲያደርግ (ሲገጥም) የሚያሳይ ነው፡፡

ምንም አይነት መልስ ስለማታገኙ እባካችሁን እኔን <የመልሶች አባት> እያላችሁ አትጥሩኝ፡፡ እኔ የእናንተ መልስ አይደለሁም፡፡ ጥያቄአችሁ ላይ የሆነ ማብራሪያ ብሰነዝርም መልስ አልሰጥም፡፡

እንዲያውም የእኔ ጥረት በተቃራኒው ነው፡፡ ጥያቄአችሁን ከመመለስ ይልቅ አጠፋቸዋለሁ፡፡ መልስ በመስጠት ስም ጥያቄአችሁን እያጠፋሁት ነው፡፡ ከእናንተ እየወሰድኩባችሁ ነው፡፡ ምክንያቱም ለአንዱ ጥያቄአችሁ መልስ መስጠት ሌሎች በርካታ ጥያቄዎችን መፍጠር መሆኑን አውቃለሁ፡፡ እኔ የእናንተ ጠላት አይደለሁም እና ከዚህ በላይ ምንም ነገር ልጭንባችሁ አልሻም፡፡ ከተጫኑባችሁ የራሳችሁ ሀይማኖቶች፣ ፍልስፍናዎች እና ባህሎች ሌላ ምንም ነገር ልጭንባችሁ አልወድም፡፡ ሸክሞቻችሁ የሚቃለሉበት ሰዓት ደግሞ አሁን ነው፡፡ በዝምታችሁ ውስጥ ብቻችሁን ልትተዉ ይገባል፡፡ እናም ምንም መልስ እንደማታገኙ፣ ነገር ግን ጥያቄዎቻችሁ እንደሚጠፉ አስታውሱ፡፡

ሁሉም ጥያቄዎች ሲጠፉ በቃል ከሚሰጥ መልስ የበለጠ ነገር አገኛችሁ ማለት ነው፡፡ የእናንተ መኖር በመላው ዩኒቨርስ ውስጥ በጥልቀት የሰረፀ ነው፡፡ መላው ዓለም በእናንተ እጅ ውስጥ ነው፡፡

የራሳችሁን ውስጠት ብቻ አግኙ፤ ያን ጊዜ የመላውን ዓለም ውስጠት አገኛችሁ ማለት ነው፡፡

ነገር ግን ከጥያቄዎች ተጠንቀቁ፡፡ ጥያቄዎች የእናንተ ወዳጆች አይደሉም፡፡ በጥያቄዎች ጥቅጥቅ ደን ውስጥ ገብታችሁ ትጠፋላችሁ፡፡ በመጠየቅ የላቀ እውቀትን ልታገኙ ትችላላችሁ፡፡ ነገር ግን ዕውቀቱን በጥልቀት ስታዩት የምታገኙት ጨለማን እና ሞትን ብቻ ነው፡፡

ስለዚህ በውስጣችሁ ብርሀን፣ ህይወት እና ፍቅር እንዲኖራችሁ እፈልጋለሁ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# ራስን አሳልፎ መስጠት የሚቻለው እንዴት ነው?

ተወዳጁ ባግዋን:-

ሁሉም ደቀ - መዝሙር ራሱን መስዋት የሚያደርግ ይሆናል ወይ? ትምህርት ስትሰጥ ሙሉ በሙሉ በአንተ እመሰጣለሁ:: ውስጤ ከአንተ በቀር ባዶ ይሆናል:: ከአንተ ስለይ እና ውስጤ ሲጨልም ምስልህ ብርሀን ይሆነኛል:: በቴፕ ካሴት የተቀረፀ ድምፅህን መስማት ከእንቅልፌ ያነቃኛል:: ስነቃም እንዳንቀሳፋ ያደርገኛል:: አንተ የእኔ ደም እና አጥንት ነህ::

መምህር፣ ከዚህ በላይ ደግሞ ራሴን ራሱን አሳልፎ እንደሚሰጥ አማኝ አልመለከተውም:: ለአንተ ራስህን መንከባከብ የሚጨነቁትን ስመለከት ሙሉ በሙሉ ራስን ከመውደድ የፀዳ እንደዛ አይነት ነገር እንዴት ማድረግ እንደምችል ማወቅ ባልችልም በውስጤ ግን አንድ ቀን በሙሉ ፍቅር ተሞልቼ አገልግሎት እንደምሰጥ ይታወቀኛል:: አንተ ራሱን አሳልፎ የሚሰጥ የምትለው አይነት ሰው እንኳን ባልሆን ከአንተ የሚነጥለኝ ሀይል ይኖር ይሆን?

ሳቪታ (ልጄ) :- ሁሉም ደቀመዝሙር ራሱን አሳልፎ ወደሚሰጥ አማኝ ያድጋል:: ሌላ ቦታ የሚኬድበት ምንም መንገድ የለም:: እናንተ ግን ራስን አሳልፎ የመስጠትን ትርጉም አልተረዳችሁም::

በመላው ዓለም አንድ ሚሊዮን የሚሆኑ ተከታዮች አሉኝ:: ሁሉም ራሳቸውን ትተው እኔን ለመቅረብ የሚያስቡ ከሆነ፣ ጠቢብ (አዋቂ) መሆን ስህተት ነው እላለሁ::

ራስን አሳልፎ መስጠት ልክ እንደ አበባ መአዛ ማለት ነው:: አበባ ደቀመዝሙር ነው፤ ራስን አሳልፎ መስጠት ደግሞ መአዛው ነው:: አበባውን ማየት ትችላላችሁ፤ መአዛውን ግን ማየት አትችሉም:: አበባውን መንካት፣ መዳሰስ ትችላላችሁ፤ መልካም መአዛውን ግን በእጅ መጨበጥ አትችሉም::

የአበባው መአዛ ዕጣ - ፈንታ የሚባል ነገር የለውም::



t.me/OLDBOOKSPDF

ዕጣ - ፈንታ ያላቸው ማሽኖች ብቻ ናቸው::

እናንተ አዕምሮ ያለው የሰው ልጅ ናችሁ:: እናንተ የራሳችሁ አለቃ (ጠቢብ) ስለሆናችሁ ዕጣ - ፈንታ የላችሁም::

ዕጣ - ፈንታ ያላቸው ባሪያዎች ብቻ ናቸው::

የአበባው መአዛ የአበባው ነጻ መንፈስ ነው::

አበባው አካሉ ሲሆን መአዛው ደግሞ ነፍሱ ነው:: አበባው ሲያብብ መልካም መአዛው ከውስጡ ይፈልቃል:: መአዛው ወጥቶ በመላው ዓለም ይናኛል:: ነፋስ መጥቶ ሲወስደውም ያለ ተቃውሞ አብሮት ይጓዛል::

ራሱን አሳልፎ የሚሰጥ ሰው ህይወትም፣ ሂደት ነው:: ለእኔ ወይም ለሌላ ሰው ሳይሆን ለመኖር (ለሕይወት) ሙሉ በሙሉ እጅ መስጠት ነው:: ለህይወት ሙሉ በሙሉ እጅ ስትሰጡ የተዋቡት ተራሮች፣ ዛፎች፣ ወንዞች . . . እንደው በአጠቃላይ ዓለም በሞላ የእናንተ መኖሪያ ቤት ትሆናለች::

ራሱን አሳልፎ የሰጠ ሰው ለራሱ ያለው ከፍተኛ ስሜት (ego) የሞተ ነው:: ለራሱ ከፍተኛ አመለካከት ያለውን ሰው በተመለከተ ግን፣ ምንም ውስጥ የሌለበት እና በጥልቅ እሳቤ ውስጥ ያለ ነው::

በእርግጥ በዙሪያዬ ጥቂት ሰዎች እንዲኖሩ እፈልጋለሁ:: ሰነፍ ሰው ራስን አሳልፎ ከመስጠት ጋር ምንም የሚያገናኘው ነገር የለም:: ከእኔ ጋር ግን የሚያዛምደው ነገር አለ:: እኔ በህይወቴ ምንም አይነት ነገር ያልሰራሁ ሰው ነኝ::

አንድ ወዳጄ ከቀድሞዋ ሶቭየት ህብረት መጥቶ፣ «በፍጹም ወደ ሶቭየት ህብረት እንዳትሄድ !» አለኝ::

እኔም «በመጀመሪያ ደረጃ አገራቸው እንድገባ አይፈቅዱልኝም:: ጣሊያን እና ጀርመን ያልፈቀዱልኝ ሶቭየት ትፈቅዳለች የሚል ግምት የለኝም!» አልኩት::

አከል አድርጌ፣ «ለምንድን ነው ይህን ያልከው?» ብዬ ጠየቅኩት:: «በእጆችህ ምክንያት ነው:: እጆችህን የሚጨብጥ ማንኛውም ሰው እጆቹን ከአንተ ያሸሻቸዋል» አለኝ::



t.me/OLDBOOKSPDF

«እጆቼ ላይ ምን ችግር አለ?»

«እጆችህ ካራ የማይሰራ (የጨቋኝ) እጆች ናቸው። ምንም አይነት ስራ ሰርተህ አታውቅም፣ ሶቭየት ህብረት ደግሞ ዝቅተኛው የማህበረሰብ ክፍል የበዛባት አምባገነን ናት!» አለኝ።

«እሱስ ልክ ነህ፣ ስራ ሰርቼ አላውቅም። እኩለ ሌሊት ላይ እንኳን የምጠጣው ቀዝቃዛ ውሃ አጠገቤ የተቀመጠልኝ ቢሆንም የመጥሪያ ደውል በመጫን ሰው እጣራለሁ። የመጥሪያ ደወሉ እንኳን የሚገኘው አልጋዬ አጠገብ ነው። በመሆኑም አንድ ሰው መጥቶ አንድ ብርጭቆ ቀዝቃዛ ውሃ ይሰጠኛል . . .

«በእርግጥ እንክብካቤ የሚያደርጉልኝ ሰዎች <ልትሰብራቸው ስለምትችል ብርጭቆ እና ጠርሙሱን አትንካ> ይሉኛል። ታዲያ ምን ማድረግ እችላለሁ? . . .

«በእጭሩ ሰነፍ ነኝ።»

ሳቢታ፣ ራስን አሳልፎ ወደ መስጠት ደረጃ እያደጋችሁ በአለመሆናችሁ ተስፋ መቁረጥ የለባችሁም። ራስን አሳልፎ ወደ መስጠት ደረጃ ለማደግ ጥቂት ጊዜ ይወስዳል።

እናም ለጥቂት ጊዜ ታገሱ። የፀደይ ወቅት (መልካም ጊዜ) እንዲመጣ አድርጉ። ያን ጊዜ የአበባው እምቡጥ ፈክቶ መልካም መዐዛው ይናኛል።

እውነተኛ ነጻነት ደግሞ ይህ ነው።

ነገር ግን እያንዳንዱ ደቀመዝሙር ጊዜው ይረዝም እንደሆነ እንጂ ራሱን አሳልፎ የሚሰጥ ይሆናል። ደቀመዝሙር ከሆነ በፍጹም ወደኋላ መመለስ አይችልም።

አንድ ጊዜ ራሱን አሳልፎ የሰጠ፣ የዚህንም ጣፋጭነት እና መልካምነት የቀሰመ ሰው፣ በፍጹም ወደ ኋላ መመለስ አይቻለውም። ሰዎች ወደ ኋላ ሲመለሱበት የሚችሉትን መስመር አልፏልና።

ሁሌም ወደኋላ መመለስ የማይቻልበት ነጥብ አለ። በሺ የሚቆጠሩ የእኔ ተከታዮችም ያንን ነጥብ አልፈዋል። ከእንግዲህ መመለስ ቢፈልጉ እንኳን አይችሉም። ይህም ልክ አዲስ እንደተወለደ ህጻን ልጅ



t.me/OLDBOOKSPDF

ማለት ነው። ህጻኑ በእናቱ ማህፀን ውስጥ እያለ የሚኖረው በገነት ውስጥ ነበር። ከእናቱ ማህፀን ሲወጣ የውጪው ዓለም ፍጹም እንግዳ ይሆንበታል። ወደ እናቱ ማህፀን መመለስ ቢፈልግም አይችልም። እንደገና ሊመለስበት የማይችለውን መስመር አልፎታልና። ከአሁን በኋላ ያለው ዕድል ወደፊት መቀጠል (መጓዝ) ብቻ ነው።

አንድ ደቀመዝሙር ረጅም ርቀት ተጉዞ መጥቷል። ስመጨረሻው ወሳኝ ምዕራፍ በጣም ተቃርቧል።

ይህ የመጨረሻ ወሳኝ ምዕራፍ ራስን አሳልፎ መስጠት ነው። ነገር ግን የእኔን ራሴን ከመንከባከብ ጋር ምንም የሚያገናኘው ነገር የለም።

የሚገናኘው የአንተን በአትኩሮት ማሰብን ከመንከባከብ ጋር ነው። ስለዚህ የተቻለህን ያህል በምሉዕነት እና አጠቃላይነት ወደ ህይወት ማዕከላዊ ነጥብ፣ ወደ የህይወት አውሎ ነፋስ ማዕከላዊ ክፍል ለመጓዝ (ለመጠጋት) ሞክር። ያን ጊዜ ራስህን ታገኛለህ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ዕብደት ያለበት ነጥብ ጋር ስንደርስ ንቃታችን በከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ ይደርሳል

**ተወዳጁ ባገዋን:-**

**እብደት ያለበት ነጥብ ጋር ስንደርስ ንቃታችን በከፍተኛ የእድገት ደረጃ ላይ ይደርሳል:: እባክህን ከእብደት ወደ በጥልቀት ማሰብ የሚወስደውን ማርሽ እንዴት እንደምንቀይር ንገረን?**

ልጄ ራድሀ:- ጥያቄው መንገድ ላይ ላለ ሰው በሙሉ እጅግ ወሳኝ ጥያቄ ነው::

እኔ መስታወት ነኝ - ባዶ መስታወት::

እናንተ ጥያቄ ይዛችሁ ትመጣላችሁ፣ ይህም መልካችሁን (ፊታችሁን) ይዛችሁ ትመጣላችሁ ማለት ነው:: የእኔ መስታወት ደግሞ አንፀባርቆ ፊታችሁን ያሳያችሁ እና ገና ተመልሳችሁ ከመሄዳችሁ መስታወቱ ተመልሶ ባዶ ይሆናል:: የእናንተ መምጣት እና መሄድ በእኔ መስታወት ላይ ምንም የሚተወው ምልክት (አሻራ) የለም::

ይህ በሚገባ ግልፅ መሆን አለበት:: ምክንያቱም ስለ እኔ የተሳሳተ ግንዛቤ ካላችሁ ያንን መስመር (መንገድ) መከተል ትጀምራላችሁ:: ሰፊ እውቀት ማካበት እና በርካታ ቅዱስ መፅሐፍት መሰብሰብ ልትጀምሩ ትችላላችሁ:: እኔም ከዚህ ቀደም ያንን አስቀያሚ ስራ ሰርቻለሁ:: በእናንተ የተቀደሱ መፅሐፍት እና ትምህርቶች ላይ ብዙ ጊዜ አባክኛለሁ:: ነገር ግን ሁሉም ቃላት ብቻ ናቸው:: በእርግጥ ሁሉንም ነገር ከመፅሐፍት መጠበቅ ስህተት ነው:: መፅሐፍት የሞቱ ቃላት ስብስብ ናቸውና::



t.me/OLDBOOKSPDF

እኔ እዚህ እስካለሁ ድረስ ህይወት ያላቸውን ቃላት የማድመጥ እድል አላችሁ፡፡ አንድ ጊዜ ከሄድኩ ግን በመፅሐፍት ላይ የምታነቡት ተመሳሳይ ቃላትን ነው፡፡ እነሱም ቢሆኑ ታድያ ይሞታሉ፡፡ የእኔ የጋለ ስሜት፣ ፍቅር እና የልብ ምቴ ውስጣቸው የለምና፡፡

እኔ ከቃላቶቼ ጀርባ ሆኜ ልትረዷቸው ካልቻላችሁ፣ እኔ በሌለሁበት መፅሐፍትን አንብባችሁ ልትረዷቸው አትችሉም፡፡ ስለዚህ እኔ የምናገረውን ስታደምጡ ሌሎች ተጨማሪ ጥቂት ነገሮች ማወቅ ይኖርባችኋል፡፡ ትምህርቴ ተራ ትምህርት አይደለም፡፡ ለእናንተ መረጃ ማስተላለፍ ብቻ አይደለም፡፡ እናንተም ማስታወስ የሚኖርባችሁ ነገር አይደለም፡፡ ሙሉ በሙሉ ከዚህ የተለየ ድርጊት ነው፡፡

እኔን ማድመጥ ቃላቶቼን ማድመጥ ማለት አይደለም፡፡

በእርግጥ ቃላቶቹን ትሰማላችሁ፡፡

ቃላቶቹን ብትሰሙም እኔን ግን አድምጡኝ፡፡ እኔን ስታደምጡኝም፣ ውሃ እንደመጠጣት፣ ምግብ እንደማብላት እና ከአካል ጋር እንደማዋሀድ እንጂ በአዕምሯችሁ የትውስታ ማህደር ውስጥ እንደሚቀመጥ ነገር አይሁን፡፡

እኔን ስታደምጡኝ ልክ እንደ እኔ ባዶ ሁኑ፡፡

መልስ የሚገኘው ከባዶነት ነውና፡፡

የዚህ አይነት መልስ መገንዘብ የሚቻለው በባዶነት ማድመጥ ሲቻል ብቻ ነው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምን እየተካሄደ እንደሆነ እና ወዴት እንደምንሄድ የምናውቀው እንዴት ነው? አንተስ የት እየወሰድከን ነው?

**ተወዳጁ ባገዋን፡-**

ከስድስት አመታት በፊት ልከተልህ ስነሳ እንዴት መራመድ፣ መዘመር እና መደሰት እንዳለብኝ አላውቅም ነበር:: ዛሬ ግን፣ በከዋክብት ስር ሆኜ መጨፈር እና መሳቅ፣ መዘመር እና መጫወት እንደዚሁም መደሰት እችላለሁ:: በመንገዱ ላይ ግን ብዙ ነገሮች ገጥመውኛል:: ምን እየተካሄደ እንደሆነ ወይም የት እየሄድኩ እንደሆነ አላውቅም:: የማውቀው ቢኖር ልቤ ውስጥ በዚህ የተደናገረ ጉዞ ከአንተ ጋር አብሮ የመጓዝ ከባድ ፍላጎት እንዳለኝ ብቻ ነው:: ተወዳጁ ባገዋን፣ ስለመሆኑ የት እየወሰድከን ነው?

የምወስዳችሁ ወደ ራሳችሁ ነው::

ከራሳችሁ ርቃችሁ ብዙ ተጉዛችኋልና::

ምናልባትም ወደ ኋላ የመመለሻ መንገዳችሁን ሙሉ በሙሉ ረስታችሁት ይሆናል:: የማሳምናችሁ ውስጣችሁን ካላገኛችሁት በስተቀር በስቃይ ውስጥ እንደምትቆዩ ነው::

የትም መሄዳችሁን አቁሙ:: ጉዟችሁን አቁሙ::

ሀይል (ጉልበት) ወደ ቁሶች እና ግቦች አቅጣጫ የማይንቀሳቀስ ከሆነ ያ ሀይል (ጉልበት) ወደ ራሱ መዞር ይጀምራል:: ይህም ማወቅ፣ መንቃት፣ ሳናድሀ፣ ሳም ቦድሂ ይባላል::

ዘወትር አንድ ቦታ መሄድ ትፈልጋላችሁ:: ሰዎች በመላው ዓለም ያለ እረፍት ይንቀሳቀሳሉ:: ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ፣ ከአንዱ ከተማ ወደ ሌላ ከተማ ይሄዳሉ:: የሚፈልጉበት እንደርሳለን በሚል ተስፋ



t.me/OLDBOOKSPDF

በየቦታው ይኳትናሉ፡፡ የት መድረስ እንዳለባቸው ግን አያውቁትም፡፡ መድረስ ያለባቸው ቦታ እንዳለ እንኳ እርግጠኞች አይደሉም፡፡ የሚደርሱበት ቦታ አስፈላጊ ስለመሆኑም እርግጠኞች አይደሉም፡፡

እኔ ግን እናንተ የትም መሄጃ ቦታ እንደሌላችሁ እነግራችኋለሁ፡፡ የተወለዳችሁት በትክክል እዛው ቦታ ነው፡፡

የእኔ ጥረት እናንተን በቃላቶቼ ሳይሆን በዝምታዬ እና ከእናንተ ጋር አብሬ በመኖሬ፣ በፍቅሬ እና በደስታዬ ማሳመን ነው፡፡ ሁላችሁም በዮኒቨርስ እምብርት ላይ እንዳላችሁ ማሳመን ነው፡፡ ምክንያቱም ያለው አንድ ማዕከላዊ ቦታ (እምብርት) ብቻ ነው፡፡ የምንለያየው ድንበሩ (ዳር ላይ) ስንሆን ብቻ ነው፡፡ በማዕከላዊው ቦታ ግን ሁላችንም አንድ ነን፡፡

እናንተም ልታብቡ የምትችሉት እምብርቱ ላይ ስትሆኑ ብቻ ነው፡፡

ሰዎች ግን በተለያዩ አቅጣጫዎች ይጓዛሉ፡፡ የተለያየ አይነት ስራዎችንም ይሰራሉ፡፡ በዚህ ሂደት የሚያባክኑት ሀይል እጅግ በጣም አስገራሚ ነው፡፡ እንስሳት ከሰው የተሻሉ ብልሆች ናቸው፡፡ ከጥቂት ቀናት በፊት አውሮፓ ውስጥ ከእንስሳት ጋር ወሲብ ሲፈፅም እጅ ከፈንጅ የተያዘ የሀይማኖት አባት አለ፡፡ ለፍርድ ቤት ቃሉን የሰጠ ጊዜ፣ ለአስራ ሁለት አመታት ከእንስሳት ጋር ወሲብ እንደፈፀመ አምኗል፡፡ «ይህን የማደርገው እኔ ብቻ አይደለሁም» በማለትም አክሎ ተናግሯል፡፡

ተፈጥሯዊው የወሲብ ድርጊት ስለተከለከለ፣ አሁን ጤነኛ ወዳልሆነ የወሲብ ፍላጐት ተሸጋግሯል፡፡ ከእንስሳት ጋር ወሲብ መፈፀም ቀላል ነው፡፡ ምክንያቱም ምስኪኖቹ እንስሳት የሀይማኖት አባቱ የፈፀመውን ድርጊት ለማንም መናገር አይችሉም፡፡ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሄደው አቤቱታ አያቀርቡም፡፡ ስለዚህ የተፈፀመውን ነገር በሰዎች ዘንድ ሳይታወቅ ሚስጥር ሆኖ ይቀራል፡፡

አንዲት መናገር የሚችል ፓሮት ወፍ ያላት ቆንጆዬ ሴት አለች ሲባል ሰምቻለሁ፡፡ ሴትየዋ ሴተኛ አዳሪ ነበረች፡፡ ፓሮቱ የተሳሳተ ወዳጅ በማግኘቱ ፀባዩ ተበላሽቷል፡፡ ሴትየዋ አንድ ወንድ ይዛ ወደ ቤቷ ስትገባ



t.me/OLDBOOKSPDF

ፓሮቱ የብልግና ስድቡን ማንጎድጎድ ይጀምራል:: በመጨረሻም «ዛሬ ደግሞ ከሌላ ሰው ጋር ልታደርግ ነው፣ ልታደርግ ነው» ይላል:: ይህ አባባሉ ሴተኛ አዳሪዋን ተከትሎ ለሚመጣው ወንድ ሁሉ ግራ ያጋባዋል:: ለሴትየዋም በጣም አሳፋሪ ይሆንባታል::

ሴትየዋ ምን ማድረግ እንዳለባት ምክር ለመጠየቅ ወደ የቤት እንስሳት መሸጫ ሱቅ ሄደች:: እዛ ያገኘችው ሰውም «ምንም ችግር የለውም፣ መፍትሔው በጣም ቀላል ነው:: እንደአንቺ አይነቷ ሴት እንኳን ችግሩን ማወቅ አትችልም:: የሚያስፈልገው ሴት ወፍ ነው:: አሁን ሴት ፓሮት ወፍ የለኝም:: ግን በአስቸኳይ አንዲት ሴት ፓሮት እንድትመጣልሽ አዛለሁ:: በሁለት ሳምንት ውስጥም አስረክብሻለሁ:: እስከዛ ድረስ ይህችን የተዋበች ጉጉት ውሰጂ እና ፓሮቱ አጠገብ አስቀምጫት:: ለአመታት በሴተኛ አዳሪ ቤት ውስጥ ታቅቦ እንደመቆየቱ ምናልባት ይቺን ቆንጆ ጉጉት ሲያገኝ ሊወዳት ይችላል!» አላት::

ሴትየዋ በሃሣቡ ተስማምታ ጉጉቷን ይዛ ወደ ቤቷ ሄደች እና በብረት ጉጆው ውስጥ ከፓሮቱ አጠገብ አስቀመጠቻት:: መጀመሪያ ላይ ፓሮቱ ወደ ጉጉቷ ዞር ብሎ ስላላየ ሴትየዋ ሃሳቧ የማይሳካ መስሏት ነበር:: ምሽት ላይ አንድ ወንድ ደንበኛዋን ይዛ ስትመጣ ግን እንደ ወትሮዋ የፓሮቱ ነገር አላስጨነቃትም:: እስከዛ ሰአት ድረስ ወፎቹ እንደሚለማመዱ ገምታለች::

ይሁንና የቤቷን በር ከፍታ እንግዳዋን ገና ከማስገባቷ ፓሮቱ «አሃ፣ እንደገና ሊጀመር ነዋ!» ብሎ የብልግና ንግግሩን ጀመረ:: በመጨረሻም «ዛሬ ደግሞ ከሌላ ሰው ጋር ልታደርግ ነው፣ ልታደርግ ነው!» አለ፣ እንደተለመደው::

ሴቷ ጉጉትም አስከካች::

ፓሮቱ ግን «አንቺ የውሻ ልጅ፣ ከአንቺ ጋር የዚህ ዓይነቱ ነገር እንደማይደረግ ሙሉ በሙሉ አረጋግጥልሻለሁ!» አለ::

እንስሳት ሳይቀሩ ፓሮት ወፍ፣ በጉጉት ወፍ እንደማይሳብ መገንዘብ ይችላሉ:: የሀይማኖት አባቶች ግን ያስቡታል፣ ያደርጉታልም::



t.me/OLDBOOKSPDF

በዓለም ላይ እንደታፈነ (እገዳ እንደተጣለበት) አዕምሮ አስቀያሚ ነገር የለም:: ለሺ. አመታትም አዕምሯችሁን ባማፈን ቆይታችኋል:: አሁን አዕምሯችሁንን ሙሉ በሙሉ አፍናችሁታል::

እኔ ግን ሙሉ በሙሉ ባዶ ነኝ::

በቃላቶቼ ውስጥ እውነት ካለ ያ እውነት የሚመነጨው ከባዶነቴ ውስጥ ነው:: እኔ ውስጥ የለም፣ እኔ መተላለፊያ (ቱቦ) ነኝ:: እኔ፣ ህልውና ከእናንተ ጋር እንዲገናኝ አደርጋለሁ:: ይህንን ማድረግ የምችለው ደግሞ ሙሉ በሙሉ ባዶ ከሆንኩ ነው::

ከእንቅልፌ ስነቃ ጠዋት ወይም ከሰአት በኋላ መሆኑን ማሰብ አለብኝ:: ምክንያቱም ከሰአት በኋላ ባለው ጊዜም እተኛለሁ:: አንዳንድ ጊዜ ነገሮች ግራ ያጋቡኛል:: አንድ ቀን ከሰአት በኋላ ባለው ጊዜ፣ ስአት ላይ ጠዋት እንደሆነ እያሰብኩ ወደ መታጠቢያ ቤት ሄድኩኝ:: ከዛም እናንተ እንደምትመጡ በማሰብ መዘጋጀት ጀመርኩ::

ከመታጠቢያ ቤት ስወጣ ሲኒርቫኖን ስጠይቃት «ከእንግዶች ጋር ለመገናኘት የመዘጋጃ ሰአት አይደለም» አለችኝ::

ወዲያውኑ ሰአት አይቼ «ወይ አምላኬ አሁን ለሶስተኛ ጊዜ ገላዬን መታጠብ አለብኝ!» አልኩ::

ይህ ሁላችንም የምንኖርበት ዓለም ነው:: ለዕብደት የተቃረበ ነው:: የእብደቱ ዋነኛ ምክንያትም ሁሉም ሰው የሚሄድበትን እና ለምን እንደሚሄድ አለማወቁ ነው:: ከየት እንደመጣ አያውቅም:: የሁሉም ትርጉም ምን እንደሆነ አያውቅም::

የህይወት ትርጉም እና የህልውና አስፈላጊነት ካልተረዳችሁ በስተቀር ራሳችሁን ጤነኛ ነኝ ብላችሁ ማለት አትችሉም::

አማኞች በምድር ላይ ካሉ ሰዎች ሁሉ የበለጡ ጤነኞች እንዲሆኑ እፈልጋለሁ:: ምድር ጤነኛ ሰዎችን ተጠምታለችና::



t.me/OLDBOOKSPDF

t.me/OLDBOOKSPDF

# የሰብዓዊ መብት ድንጋጌ፤

# ያልሰለጠነ ህብረተሰብ ግብዝነት

# 2

ታህሳስ 25 1986 ቦምቤ



t.me/OLDBOOKSPDF

# ብቸኛው መሰረታዊ መብት አምላክ የመሆን መብት ነው

**ተወዳጁ ባግዋን፣**

**መሳው ዓለም በአንድ በኩል መሳ ሃይሉንና አቅሙን አሰባስቦ በተገኘው መንገድ ሁሉ የሰው ልጅ ሰው እንዳይሆን ሲጥር፣ በሌላው በኩል ደግሞ «የሰብዓዊ መብት ቀንን ሳከብር» ብሎ ሲጠይቅ ማየት እጅግ አስገራሚ ስሜት ይፈጥራል፡፡ የተከበርከው፣ ምን እየተካሄደ ነው? ተወዳጁ ጠቢብ፣ ይህን ሁኔታ ልታብራራልኝ ትችላለህ?**

ማኒሻ፣ በግብዝ ህብረተሰብ ውስጥ እየኖርን እንደሆነ ከሁሉም ነገር በፊት መታወቅ አለበት፡፡

በአንድ ወቅት ለአንድ ታላቅ ፈላስፋ «ስለ ስልጣኔ ያለህ አመለካከት ምንድን ነው?» የሚል ጥያቄ ቀርቦለት ነበር፡፡

ፈላስፋው ሲመልስም «ሃሳቡ ጥሩ ነው! ግን አንድ የሆነ ሰው ሃሳቡን ወደ ተግባራዊ እውነት መለወጥ አለበት፡፡ አሁን ስልጣኔ የለም፡፡ ወደፊት ይመጣል ተብሎ የሚታሰብ ህልም ነው» ብሎ ነበር፡፡

ፖለቲካዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ማህበራዊ ስልጣን ያገኙ ሰዎች እዚያ ስልጣን ላይ የተቆናጠጡት ስልጣኔ ስለሌለ ነው፡፡ የሰለጠነ ዓለም እና የበሰለ ሰው ግን ሃገር አያስፈልገውም - እነዚህ ሁሉ ወሰኖች የሃሰት ናቸው - ሁሉም ሃይማኖቶች ተራ ፈጠራዎች ናቸውና ሃይማኖትም አያስፈልገውም፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

በሺ ለሚቆጠሩ ዓመታት በስልጣን የቆዩት ካህናት፣ ፖለቲከኞች፣ ሃብታሞች የሰውን ልጅ ለውጥ ለማስቆም የሚችል ሃይል አላቸው:: ይህን አዝጋሚ ጉዞውን ለማስቆም ቀላሉ መንገድ ደግሞ «ስልጡን ነህ»፣ «ሰብአዊ ፍጡር ነህ:: ከዚህ ሌላ ለውጥ አያስፈልግህም:: መለወጥም አስፈላጊ አይደለም» ብሎ ማሳመን ነው::

የሰው ልጅ ድክመቱ ደግሞ ከስልጣኔ በላይ ምንም ነገር የለም ማለቱ፣ እንደ ስሜታዊነት ምንም ነገር የለም ብሎ ማመኑ፣ በሃሰተኛ የፖለቲከኞች ንግግር፣ የካህናት ስብከት፣ በመምህራን ትምህርት ማመኑ ነው:: እነዚህ ሁሉ በቀላሉ የሚታመኑ በመሆናቸው ሌላ ምንም ነገር ማድረግ አትችሉም::

ሰው አለመሆንን መገንዘብ በራሱ ፍርሃት ይፈጥራል:: በእግር የረገጡት መሬት ይከዳል::

እውነት፣ ውሸቶችን በሙሉ አወላልቆ፣ የግብዝነት ሃሳቦችን በሙሉ ጠራርጐ ዕርቃን ያስቀራል:: ለዛም ነው እውነት የማይፈለገው፤ እንደዚያም ሆኖ ሁሉም እውነትን እንደጨበጠ ያምናል::

ሥነ - ልቦናዊ ዳራውን አስተዋላችሁት? ለአንድ የሆነ ሰው የሆነ ነገር መስጠት ካልፈለጋችሁ፣ «ይሄ ነገር እኮ አለህ» በማለት ታሳምኑታላችሁ፤ ታደነዝዙታላችሁ:: ደግማችሁ ደጋግማችሁም ትነግሩታላችሁ:: ወላጆቻችሁን፣ መምህራኖቻችሁን፣ ካህናቶቻችሁን፣ መሪዎቻችሁን ጨምሮ በዙሪያችሁ የሚገኙት በሺ የሚቆጠሩ ሰዎች በሙሉ በዚህ ሃሳብ ሲያምኑ፤ ወደዚህች ዓለም የሚመጡት ህፃናት በዚህ ሺህ ዓመታትን በፈጀ ሃሳብ አያምኑም ማለቱ ፍጹም የማይታሰብ ይመስላል:: በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች ስልጣኔ አለ ብለው ኖረው ሞተዋል::

ስለዚህ ከሁሉም ነገር በፊት እንድትገነዘቡልኝ የምፈልገው አሁንም ያልሰለጠንን እንደሆንን ነው:: እኛ በሺዎች ለሚቆጠሩ ዓመታት ስናደርገው የቆየነውን የሚያደርጉ ሰብዓዊ ፍጡራን ሳይሆኑ ያልሰለጡ ኋላቀሮች ብቻ ናቸው:: በሶስት ሺ ዓመታት አምስት ሺ ጦርነቶች ተካሂደዋል. . . እና ይህ ስልጣኔ ነወይ?



t.me/OLDBOOKSPDF

በሃያኛው ክፍለ ዘመን - በሃያኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ - አዶልፍ ሂትለርን፣ ጆሴፍ ስታሊንን፣ ቤኒቶ ሞሶሊኒን፣ ማኦ ሴ - ቱንግን መፍጠር ችላችኋል! ታዲያ የሰው ልጅ ሰልጥኗል ሊባል ይችላል?

አዶልፍ ሂትለር ብቻውን ስድስት ሚሊየን ሰብአዊ ፍጡራንን ፈጅቷል:: በዚህም ሳይንስና ቴክኖሎጂ ጥቅም ላይ ውሏል:: አንድ ሚሊየን የሚሆኑ አይሁዶች በጋዝ ተቀቅለዋል - በጥቂት ሰኮንዶች ውስጥ በሺ የሚቆጠሩ ሰዎች በጢስ መውጫዎች ውስጥ የሚትጉለጉሉ ጢሶች ሆነዋል:: እያንዳንዱን ሰው በስርዓት መቅበር እስኪያዳግት ድረስ እጅግ ብዙ ሰዎችን ገድሏል::

ሰው ድሃ ሆኖ አያውቅም - ለማኞች እንኳን መቃብር ይቆፈርላቸዋል:: እሱ ለገደላቸው አያሌ ሰዎች መቃብር ይቆፈር ቢባል ግን. . . መላዋ ጀርመን የመቃብር ስፍራ በሆነች ነበር:: ስለዚህም ጥልቅ ጉድጓዶችን አስቆፈረና ሰዎቹን እዚያ ውስጥ ወርውሮ ጭቃ አለበሳቸው:: አስከሬኖቻቸውን ወደ ጉድጓዶቹ ከመወርወሩ በፊት እንኳን ክብራቸውን አጥፍቶ ነበር:: ልብሶቻቸውን በሙሉ እንዲወልቁ ተደርገዋል፤ ፊታቸው ታይቶ እንዳይታወቅም ራሳቸውን፣ ፂማቸውን እንዲላጩ ተደርገዋል:: ጭንቅላቶቻቸውን ቆርጦ እጅና እግሮቻቸውን በተለያየ ቦታ ቀብሯል:: በሺ የሚቆጠሩ ሰዎችን ማንነት ለመለየት ፍፁም የማይቻል ነበር::

ይህ ሁሉ ለምን አደረገ? ይህን ያደረገው ሰዎቹ እንዳይታወቁ ነበር:: አንድ ሰው አስክሬኖቹን ቢያገኝ እንኳ የማን እንደሆኑ መለየት አይችልም:: ለነገሩ ጠቅላላውን ሰውነትም ማግኘት አይቻልም:: ታዲያ ይህን ሰው ስልጡን ትሉታላችሁን?

ታሪኩ በዚህ አያበቃም:: የሁለተኛውን የዓለም ጦርነት የተመለከተ ሰው ትንሽ ብልህነት ቢኖር የሁለተኛው የዓለም ጦርነት የመጨረሻው መሆን በቻለ፣ የሰው ልጅ በሰው ልጅ ላይ እንዲያ አይነት ተግባር መፈፀሙን ባቆመ ብሎ ማሰቡ አይቀርም:: እኛ ግን ለመጨረሻው የሶስተኛው የዓለም ጦርነት እየተዘጋጀን ነው::



t.me/OLDBOOKSPDF

«በሶስተኛው የዓለም ጦርነት ምን ሊከሰት እንደሚችል የምትነግረን ነገር አለ?» የሚል ጥያቄ ለአልበርት አይንስታይን ቀርቦለት ነበር።

እሱም ሲመልስ «ይቅርታ አድርጉልኝ፣ ስለ ሶስተኛው የአለም ጦርነት ልነግራችሁ አልችልም። ስለ አራተኛው ግን ልነግራችሁ እችላለሁ» ብሎ ነበር።

ጥያቄውን ያቀረበው ሰው የሰማውን መልስ ሊያምን አልቻለም። «ስለ ሶስተኛው ምንም መናገር አትችልም። ግራ የሚያጋባ ነው። ስለ አራተኛው ለመናገር ግን ዝግጁ ነህ። ይህ ደግሞ የበለጠ ግራ የሚያጋባ ነው!»

«አልተረዳኸኝም» አለ አይንስታይን። «ስለ አራተኛው ለይቼ አንድ ነገር በእርግጠኝነት ልነግርህ እችላለሁ። ሶስተኛው የዓለም ጦርነት በምድር የሚገኝን የሰውና የእፅዋትን ህይወት በሙሉ ስለሚያጠፋ አራተኛው አይከሰትም። በምድር ላይ የሚኖር ሁሉ ይጠፋል።»

ታዲያ የሰው ልጅ ሰልጥኗል ማለት ይቻላል?

በፍፁም፣ ተታላችኋል ማለት ነው። ይህ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ያወጣው የሰብአዊ መብት ድንጋጌም ተመሳሳይ ግብዝነት የሚታይበት ነው።

ጆርጅ ጉርዲፍ ስለ ስብዕና የሚያወራ አንድ አጭር ታሪክ አለው። ታሪኩ ስለ አንድ አስማተኛ ነው። ይህ በተራሮችና በደኖች መሃል የሚኖር አስማተኛ በሺዎች የሚቆጠሩ በጐች ነበሩት። ነገር ግን አስማተኛው ለቁርሱ አንድ፣ ለምሳው ደግሞ ሌላ በግ ያርድ ነበር እና በጐቹ በሙሉ ይፈሩታል። ከአስማተኛው ለማምለጥ ቢሞክሩም ደኑ የተጠቀጠቀ በመሆኑ ማምለጫ መንገድ ሊያገኙ አልቻሉም። አስማተኛ በመሆኑ አስማቱን ይጠቀማል። አንዳንዶቹን በጐች ለየብቻ እየጠራ «እናንተ ሰው ስለሆናችሁ ፍርሀት የለባችሁም። እናንተ ሳትሆኑ በጐች ብቻ ናቸው ታርደው የሚበሉት። እናንተ ልክ እንደ እኔ ናችሁ» በማለት ያታልላቸው ነበር።


t.me/OLDBOOKSPDF

ሌሎቹን ደግሞ ይጠራና «እናንተ አንበሳ ናችሁ - ፍርሃት የለባችሁም። በጐች ናቸው የሚፈሩት። ሰነፎች ስለሆኑ ሊያመልጡ ይሞክራሉ። እናንተ አንበሶች ስለሆናችሁ ከምትሮጡ ይልቅ ብትሞቱ ትመርጣላችሁ። እናንተ የነዚህ በጐች ወገን አይደላችሁም። ስለዚህ እነሱ ቢገደሉ የእናንተ ችግር አይደለም። እነሱ መሞት አለባቸው። እናንተ ግን በዚህ ጫካ ውስጥ የምወዳችሁ ወዳጆቼ ናችሁ» ይላቸዋል።

ይህን ከነገራቸው ዕለት ማግስት አንስቶ ሮጦ ለማምለጥ የሚሞክር በግ ጠፋ። የራሳቸው ወገን የሆኑ በጐች ሲገደሉ እና ሲተለተሉ ቢያዩም፣ ጭንቀታቸው አልነበረም። አንዱ አንበሳ፣ አንዱ ነብር፣ አንዱ ሰው፣ ሌላኛው ደግሞ. . . ነበሩ። ከሚሞተው በቀር ሌሎቹ በጐች አልነበሩም።

በዚህ መንገድ ምንም እረኛ ሳያሰማራ በሺ የሚቆጠሩ በጐችን ለመጠበቅ ቻለ። ምግብና ውሃ ፍለጋ ወደ ጫካ ወጥተው ተመልሰው በሚመጡበት ጊዜ ሁሉ፣ «እኔ ሳልሆን አንድ በግ ነው የሚገደለው። እኔ የእነሱ ወገን አይደለሁም። እኔ የዚህ ታላቅ አስማተኛ የተከበረ ጓደኛ አንበሳ ነኝ» በማለት እያሰቡ ነው። በዚህም የአስማተኛው ችግሮች በአስተማማኝ ሁኔታ ተፈተዋል።

ታሪኩን የምነግራችሁ የእናንተም ታሪክ ስለሆነ ነው። የተነገራችሁን ነገር በሙሉ ዞር፣ ዞር እያላችሁ ሳታጣሩ፣ እውነት መሆኑን ሳታረጋግጡ ትቀበላላችሁና።

የመጀመሪያው ነገር. . . ግዴታ በሌለበት፣ መብት ይኖራል ብዬ ስለማላምን የተባበሩት መንግስታትን የሰብዓዊ መብት ድንጋጌ እቃወማለሁ። ግዴታ ስር ሲሆን መብት አበባ ነው። ያለ ግዴታ መብት ሊኖር አይችልም። የሰብአዊ መብትን ቀን እያከበሩ. . . መቅደም የነበረበትን የግዴታ ቀን አያከብሩም።

ለምንድነው ስለ ሰብአዊ ግዴታ የማያወሩት? ምንም ጥርጥር የለውም፤ ሰብአዊ መብት ሊሰጥዋችሁ ስላልፈለጉ ነው። ግዴታ የሌለበት መብት ከወሬ አያልፍም። እነዚህ ፖለቲከኞች ግዴታን በተመለከተ



t.me/OLDBOOKSPDF

ምንም ግድ የላቸውም። ስለዚህም ጥቂት ምሳሌዎችን ልሰጣችሁ እችላለሁ።

ሁሉም ሰብአዊ ፍጡር እኩል ነው - ይላሉ። ይህ አስተሳሰብ የሁሉንም የራስ ከፍተኛ አመለካከት ስለሚያጠናክረው የሚቃወመው የለም። ለሰው ልጅ ከተነገሩት ውሸቶች መሃል እጅግ አደገኛው ይህ ነው።

እኩልነት መሰረተ - ቢስ ተረት ነው።

በማንኛውም መንገድ፣ በማንኛውም መስኪያ ሁለት ሰዎች እንኳን እኩል ሊሆኑ አይችሉም። እኩል አይደሉም ግን እያልኩ አይደለም። የተለያዩ እና የማይነፃፀሩ በመሆናቸው የእኩልነት እና እኩል ያለመሆን ጥያቄ መነሳት የለበትም እያልኩ እንጂ። እናንተ በአንድ አዳራሽ ውስጥ ከሚገኙ አምዶች ጋር እኩል መሆን ትችላላችሁን? አምዶቹ የተዋቡ ሊሆኑ ቢችሉም ከእነሱ ጋር እኩል አይደላችሁም። ይህ ማለት ግን ከአምዶቹ ታንሳላችሁ ማለት ነውን? አይደለም። እናንተ አምድ አይደላችሁም - አምዶች፣ አምዶች ናቸው፤ እናንተ ደግሞ እናንተ ናችሁ። እያንዳንዱ ሰው ከራሱ ጋር ነው የሚመደበው።

የእያንዳንዱን ሰው ልዩነት ካልተገነዘብን ሰብአዊ መብት፣ የሰለጠነ ዓለም - ፍቅር፣ ደስታ ሊኖሩ አይችሉም።

በድንጋጌው ውስጥ ሁሉንም ሰብአዊ ፍጡር እንድትወዱ ደንጋጊዎቹ ደጋግመው አፅንኦት ሰጥተውበታል፤ «ሁላችሁም ወንድማማቾች ናችሁ» ይላሉ። ግን የሚዋደዱ ወንድማማቾችን አይታችሁ ታውቃላችሁ? ጓደኛሞች የሆኑ ወንድማማቾች አይታችሁ ታውቃላችሁ?

ወንድማማቾች እንደሚጣሉት ማንም አይጣላም።

«ወንድማማቾች ናችሁ» ማለቱ ብቻ እውነታውን አያሳይም። እነዚህን ሰብአዊ መብቶች የደነገጉት ሰዎች ምን ስልጣን አላቸው? እነሱ ማናቸው? ፖለቲከኞች. . . ፖለቲከኞች ደግሞ የዚያ ሁሉ ጦርነት፣ የዚያ ሁሉ ነውጥ መንስኤዎች ናቸው።


t.me/OLDBOOKSPDF

እነዚህ ሰዎች የህብረተሰቡ ግማሽ አካል የሆኑትን ሰብአዊ ፍጡራን - ሴቶችን በባርነት ያስቀመጡ ናቸው።

ስማቸው (ዖታዊ መጠሪያቸው) እንኳን በመጽሐፉ አልተጠቀሰም።

እነዚህ ፖለቲከኞች አፈ - ጮሌዎች፣ ታታሪዎች፣ ብልጦች. . . በአብዛኛውም ከህግ ሙያ የመጡ ናቸው። በወንድና በሴት፣ በጥቁርና በነጭ መካከል ልዩነት የለም ይላሉ። በዘር፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ ርዕዮተ - ዓለማት መካከል ልዩነት እንደሌለ ይሰብካሉ። ግን ማነው ልዩነት እየፈጠረ ያለው? እነዚሁ ናቸው። ድንጋጌውንም የደነገጉት እነሱ ናቸው።

የሴቷን መብት ለዘመናት የነፈጉት እነዚሁ ሰዎች ናቸው። በእነሱ ድንጋጌ መሰረት መሰረታዊ ሰብአዊ መብት የሆነውን ነፃነት ሊሰጧት ግን ፈቃደኞች አይደሉም።

ጥቁሮች የሚታዩት እንደ እንስሳት ነው። እስከ ክፍለ ዘመኑ መጨረሻ ድረስ በገበያ እንደ ዕቃ ለሽቀጥ ሲቀርቡ ነበር። ዛሬም ቢሆን የነጮችን ያህል ክብር የላቸውም።

ይህን የሚያደርጉት ነጮች ናቸው - እነዚህ ሁሉ ፖለቲከኞች ነጮች ናቸው። እነዚህ ነጮች ለሶስት መቶ ዓመታት ያህል መላውን የሰው ዘር ወደ ባርነት መርተዋል። ሁሉም የራሳቸው ግዛት አላቸው። ሰፊ ግዛት ያላት እንግሊዝ ናት፤ በእንግሊዝ ግዛት ፀሃይ አትጠልቅም እየተባለም ይነገራል። በእንግሊዝ ግዛት የትኛውም ክፍል ፀሃይ ታበራለች፣ ሁሌም ቀን ነው - በመላው ዓለም። ሌሎችም ነጮች ብዙ አልራቁም። ፈረንሳውያን፣ ፓርቱጋላውያን፣ ስፔናውያን . . . እነዚህ ሁሉ መላውን ዓለም የሚበዘብዙበት ሰፋፊ ግዛቶች አሏቸው። እነዚህ ሀገራት ደግሞ ራሳቸው ጥገኞች ነበሩ፤ ዛሬ የሰብአዊ መብት ደንጋጊ መሆናቸው ደግሞ የሚያስቅ ነው።

ይህ ሁሉ ማታለል ነው። የሚናገሩት ከልባቸው አይደለም። ከማንም ጋር እኩል እንደሆናችሁ፣ ከማንም ጋር ወንድማማች



t.me/OLDBOOKSPDF

እንደሆናችሁ፣ የሰብአዊ መብት ሁሉ እንደሚጠበቅላችሁ ይናገራሉ:: ግን ውሸት ነው፣ ማታለል ነው::

> ለሰው ልጅ ከተነገሩት ውሸቶች መሀል እጅግ አደገኞቹ «ለልጡን ነህ» እና እንዲሁም «ሁሉም ሰብአዊ ፍጡር እኩል ነው» የሚባሉት አስተሳሰቦች ናቸው:: ምክኒያቱም በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች ስልጣኔ አለ ብለው ኖረው ቢሞቱም፣ የሰው ልጅ ግን ገና አልሰለጠነም:: በተጨማሪም ይህ እኩልነት የሚባለው ነገር መሰረተ - ቢስ ተረት ነው:: ሴሳው ቀርቶ በማንኛውም መንገድ፣ በማንኛውም መስኪያ ሁለት ሰዎች እንኳን እኩል ሲሆኑ አይችሉም::

እኔ ከህይወት ልምዴ የማውቀው ነገር አለ::

በዚህ ድንጋጌ ውስጥ የተዘረዘረ አንድ ሰብአዊ መብት አለ፣ «ማንም ሰው ያለ ማዘዣ አይታሰርም» ይላል:: ይሁንና አሜሪካ ውስጥ ያለ ምንም የእስር ማዘዣ፣ ያለ ምንም የፍተሻ ማዘዣ ታስሬ አውቃለሁ:: በአፋቸው እንኳን ፈፀምከው ስለሚሉት ወንጀል አልነገሩኝም:: «ወንጀሌ ምንድነው? ቢያንስ ይህን ማወቅ አለብኝ» ስላቸው ጥይት የጐረሱ መሳሪያዎች ናቸው የጠበቁኝ - የተሳፈርኩባት የግል የራሴ አውሮፕላን በአስራ ሁለት ጥይት የጐረሱ መሳሪያዎች ተከብባ ነበር::

መልስ የሚሰጠው በዚህ ዓይነት ሁኔታ በመሳሪያ ከሆነ ስልጣኔ ገና ሩቅ እንደሆነ እርግጠኛ መሆን ትችላላችሁ::

ምንም የእስር ማዘዣ ሳይዙ ነበር የያዙኝ:: መያዝ ብቻ አይደለም ቢያንስ ለሁለት ቀን እስር ቤት እንድቆይ አድርገውኛል:: ፍርድ ቤቱ የሚከፈተው ሰኞ ዕለት ብቻ በመሆኑ ከእስር የምወጣውም በዚያ



t.me/OLDBOOKSPDF

ቀን ብቻ ነበር። እነሱ ራሳቸው ያለ ምንም ምክንያት እንዳሰሩኝ ስለሚያውቁ በዚያውኑ ቀን ከእስር እንደምወጣ እርግጠኛ ነበሩ፤ በእኔ ላይ ምንም ማስረጃ አልነበራቸውም። እኔን ለሁለት ቀናት በማሰር እርካታ ሲያገኙ ስላሰቡ ግን፣ ፍርድ ቤቱ የሚዘጋበትን ወቅት ጠብቀው ያዙኝ። በሶስተኛው ቀን. . . ፍርድ ቤቱ ሳይለቀኝ ሲቀር አልገረመኝም ነበር።

አምባገነንዋ ዳኛ፣ ጠበቃዎቼ ያለ ምንም የእስር ትዕዛዝ የታሰርኩበትን ምክንያት እንዲጠይቁ እንኳን ዕድል አልሰጠቻቸውም። በዓለም ትልቋ ዲሞክራሲያዊት እንደሆነች በሚነገርላት ሃገር፣ ፍርድ ቤቱ ጠበቆቼ እንዲከራከሩ እንኳን መፍቀድ አልቻለም። ይህን ቢያደርጉ እንደሚጋለጡ ያውቃሉ። ሌላው ቢቀር ከሶስት ቀናት በኋላ እንኳን የእስር ማዘዣውን ሊያዘጋጁ አልቻሉም - የመፈታቴ ጉዳይም አልተነሳም፤ የዋስ መብት አልተሰጠኝም። አዎን፣ የሚታሰርበትን ምክኒያት ሳይነግሩ አንዱን ያስራሉ፣ ያንገላታሉ።

እነዚሁ ፖለቲከኞች አሜሪካ ውስጥ ተቀምጠው በእነዚያ ሰብአዊ መብቶች ውስጥ «ማንም ሰው ያለ ፍርድ ቤት ማዘዣ መታሰር የለበትም» ብለው ይናገራሉ፣ «ይህ መሰረታዊ ሰብአዊ መብት ነው» በማለት ይለፍፋሉ። እኔ ባልታሰር ኖሮ እውነቱን አላውቀውም ነበር።

ማንም ሰው በሌላ ሰው ፍልስፍና፣ ሃይማኖት፣ ፖለቲካዊ አስተሳሰብ ጣልቃ መግባት እንደሌለበት፤ ይህ የማንኛውም ሰው ተፈጥሯዊ መብት እንደሆነ ነጋ፣ ጠባ ይጮሃሉ። ይሁንና በክርስትና ሳቢያ፣ ነጭ ባለመሆኔ፣ አለማቀፋዊ በመሆኔ ምክንያት አሜሪካ ውስጥ ለችግር ተዳርጌያለሁ. . . አሜሪካ ቀለማቸው ጥቁር የሆኑ ሰዎች እንዲሁም ከመላው ዓለም የመጡ የተለያዩ ሰዎች አሉ። ማንኛውም አይነት ልዩነት የማይታይበት ስፍራ ነበር። ዳሩ ምን ያደርጋል? ይህን ሰብአዊ መብትን በማንኛውም መልኩ የሚያረጋግጠውን ስፍራ አጥፍተውታል።

ከላይ ሲታይ ፣ሰው ልጅ ሰልጥኗል። በውስጡ፣ ንቁ ባልሆነው ጨለማው የአዕምሮ ክፍሉ ግን ገና አልሰለጠነም።



t.me/OLDBOOKSPDF

* * *

በዚህ ድንጋጌ መግቢያ ላይ እንዲህ ይላል፡- «በሃይማኖት ወይም በእምነት ሳቢያ የሚከሰቱ ማናቸውንም አይነት አለመቻቻሎች እና ልዩነቶች ለማጥፋት ቆርጠን ተነስተናል፡፡»

ይህ ድንጋጌ ግን በየትኛውም ሃገር ሲተገበር አይታይም፡፡ ሃይማኖቶች ሁልጊዜ እርስ በርሳቸው እንደተፋጠጡ ነው፡፡ በአንድ መንግስት ውስጥ ወግ አጥባቂ ሃይማኖተኛ ሰዎች ስልጣን የሚሰጣቸው ከሆነ - ሌላው ህዝብ ይጨፈለቃል፣ ይጨቆናል፡፡ ምኞቱ መልካም ቢሆንም ተመኚዎቹ ግን በሙሉ ትክክል አይደሉም፡፡

| |
|---|
| ከሳይ ሲታይ የሰው ልጅ ሰልጥኗል፡፡ በውስጡ፣ ንቁ ባልሆነው ጨለማው የአዕምሮ ክፍሉ ግን ገና አልሰለጠነም፡፡ |

የመንግስታቱ ድርጅት እነዚህን መሰረታዊ መብቶች ለውይይት ባቀረበበት የስምምነት መድረክ ላይ ሶቭየት ህብረት አልተገኘችም ነበር፤ ሌሎች ስምንት ኮሚዩኒስት ሃገራትም በፊርማው አልተገኙም፡፡

አሜሪካ ግን በስምምነቱ ጊዜ ነበረች፡፡ ድንጋጌው ሲፀድቅ አንድም ወገን የተቃውሞ እጁን አላነሳም፡፡ ይህን ያነሳሁት፣ ይህ ድንጋጌ እንዲወጣ ከፍተኛውን ሚና የተጫወተችው አሜሪካ ስለሆነች ነው፡፡ እያንዳንዱን ሰብአዊ መብት የምትጥሰውም አሜሪካ ናት፡፡

ይህቺው አሜሪካ ልክ እንደ ኩባ ከኮሚኒስቶች ጦራ በተቀላቀለችው ትንሽዬ ሃገር ኒካራጓ ለሚንቀሳቀሱ አሸባሪዎች ሁለት መቶ ሚሊየን ዶላር ሰጥታለች፡፡ ሃገሪቱን ለማጥፋትም በአሸባሪዎች አስወርራታለች፡፡ አሸባሪዎቹን በመሳሪያና በሌሎች ነገሮች ለማጠናከር በሚሊዮኖች የሚቆጠር ዶላር ወደዛች ሃገር አፍስሳለች፡፡ በዚህ ድንጋጌ ውስጥ ግን ሁሉም ሃገር ሉዓላዊ እንደሆነና በየትኛውም ሃገር ህልውና እና ሃይማኖት ውስጥ ማንም ጣልቃ መግባት እንደሌለበት ተገልጿል፡፡ አምን፣ ሀገራት እንዴት መኖር እንደሚፈልጉ፣ ማመን ወይም አለማመን የሚፈልጉት ነገር የእነሱ የግል ጉዳይ ነው፡፡ ይህ የሌላ የማንም ጉዳይ



t.me/OLDBOOKSPDF

አይደለም:: በአንዲት ትንሽ ሃገር የሚኖሩ ህዝቦች ኮሚዩኒዝምን እንደ ህይወት መመሪያቸው፣ እንደ ማህበራዊ ስልታቸው መጠቀም ከፈለጉ አሜሪካ ምን አገባት? ምንስ መብት አላት?

ይህን ጉዳይ በተመለከተ ኒካራጓ ለዓለም ፍርድ ቤት አቤት ብላ ነበር:: ፍርድ ቤቱ ደግሞ በአሜሪካውያን ዳኞች የተሞላ ነው:: እንደዚያም ሆኖ ይህ የዓለም ፍርድ ቤት አሜሪካን ወንጀለኛ በማድረግ «አሜሪካ የሰብአዊ መብት ጥሰት እንደፈፀመችና ወንጀል እንደሰራች» ውሳኔ አሳለፈ:: ሮናልድ ሬገን ግን «የአለም ፍርድ ቤት ውሳኔ አይመለከተንም፣ ግድም አይሰጠንም» ሲሉ ነበር መልስ የሰጡት:: አያችሁ፣ እነዚህ ሰዎች ናቸው ድንጋጌውን የደነገጉት:: በተለያዩ አካባቢዎች የሚነሱ ግጭቶችን ለመፍታትም የአለም ፍርድ ቤትን አቋቁመዋል:: ሆኖም እነዚሁ ሰዎች ራሳቸው የፍርድ ቤቱን ውሳኔ ለማድመጥም ሆነ ለመቀበል ፈቃደኞች አይደሉም::

ከጀርባው ያለውን ፖለቲካ አስተዋላችሁት? የዓለም ፍርድ ቤት እንዲሁም የተባበሩት መንግስታት ድንጋጌ. . . እነዚህ ሁሉ ጭምብሎች ናቸው:: አንዲት ትንሽዬ ሃገር ጥፋተኛ ሆና ከተገኘች፣ ወይ ጥፋተኛ ነች ከተባለች አሜሪካ የፍርድ ቤቱን ውሳኔ ተቀብላ ሃገሪቱን ታጠፋታለች::

አሜሪካ ጥፋተኛ ሆና በተገኘች ጊዜ ግን መሪዎቿ «ለፍርድ ቤቱ ውሳኔ ግድ የለንም» በማለት ያጣጥሉታል::

ታድያ የአለም ፍርድ ቤት ምን ማድረግ ይችላል? ጦር የለው፣ ሃይል የለው:: ለፖለቲከኞች የተሰጠው ሃይል ነው ያለው:: ታድያ እነዚያ ፖለቲከኞች ህጉን በጣሱ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ምን ማድረግ ይችላል?

የመንግስታቱ ድርጅት ፍርድ ቤቱ እየተሰደበበት፣ እየተዋረደበት ምንም ማድረግ አልቻለም:: በድርጅቱ ውስጥ የሚገኙት ወገኖች ከፍ ያለ ስልጣን ካላቸው ድርጅቱንም ሆነ ፍርድ ቤቱን ማፍረስ ይችላሉ - ምን ችግር አለ? ዛሬ አሜሪካ ይህን እያደረገች ነው:: ነገ ደግሞ ሌሎች ሃገራት ይህን ያደርጋሉ::

ሶቭየት ህብረት በዚህ ረገድ በጣም የተሻለች ናት:: በዚህ ድንጋጌ ላይ አልተሳተፈችም:: የትኛውም የኮሚኒስት ሃገር በዚህ ስምምነት



t.me/OLDBOOKSPDF

አልተሳተፈም። ከመነሻው ጀምሮ ሁሉም ነገር የሀሰት መሆኑ ገብቷቸው ነበርና «እናንተ ለማታለል የተፈቀደላችሁ እነማን ናችሁ?» ብለው ነበር።

* * *

ሁሉም መብቶች በመሰረታዊ ምክንያቶች የተደገፉ አይደሉም። ለምሳሌ፣ ስለ ሞት በሚጠቅሰው ድንጋጌ፣ «አንድ ሰው በምድር ላይ በቂ ጊዜ በህይወት ኖሮ ደካማ፣ ህመምተኛ፣ ሽማግሌ፣ ሽክም እና ጥቅም የሌለው ቢሆንም ገና በህይወት የመቆየት መብት አለው» ይላል. . . ግን ሰውየው አስፈላጊ ባልሆነ ሁኔታ እየተሰቃየ ሞትን እየጠበቀ ነው። ለምን ይጠብቃል? ይህ ሰው ባላስፈላጊ ስቃይ ውስጥ እንዲኖር ለምን ይፈረድበታል?

በየሆስፒታሉ፣ በየመንከባከቢያ ስፍራው ለሚሰቃዩ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ሃላፊነት ያለበት ህብረተሰቡ ነው። ይሁንና ጤነኛ ሆነው ወደ ህይወት በመመለስ ፍሬያማ መሆን የማይችሉ ሰዎች እየተሰቃዩ ነው። ሰዎቹ በዚህ ስቃይ ውስጥ ያለ ስራ እና እንቅስቃሴ ተቀምጠው እያሉ ህክምናውም በበኩሉ እያደገ ነው - ለዓመታት በሆስፒታል ውስጥ ሊያስቀምጧቸው ይችላሉ። ሰውየው የሞተ ቢሆንም ሆስፒታሎች አርቲፊሻል የመተንፈስ ስርዓትን በመጠቀም በህይወት እንዳለ አድርገው ሊያታልሉ ይችላሉ።

አዎን፣ በዚህ ረዥም ድንጋጌ ውስጥ አንድ አስፈላጊ (ወሳኝ) ሰብአዊ መብት ተዘልሏል - ከዚህ ዓለም የመሰናበት፣ ትኬቱን የመመለስ መብት። «ወደ ዘላለማዊ ቤቴ መመለስ እፈልጋለሁ። ይህን ከማድረግ የምትከለክሉኝ እናንተ ማናችሁ?» የማለት መብት።

ይህ መብት ዛሬ አስፈላጊ ነው፣ ምክንያቱም በበለፀጉ ሃገራት የአንድ ሰው የአማካይ እድሜ ከፍ በማለቱ በርካታ ሰዎች የሰማንያ፣ የዘጠና ዓመት ልጅ ሊኖራቸው ይችላል።

ሰዎቹ አራተኛው፣ አምስተኛው ወይም ስድስተኛው ትውልድ ደርሰዋል። አምስተኛው ወይም ስድስተኛው ትውልድ ደግሞ የአንድ


t.me/OLDBOOKSPDF

መቶ እና የአንድ መቶ ሃያ ዓመት እድሜ ካላቸው በሆስፒታል ከሚማቅቁ ሰዎች ጋር ምንም አይነት ግንኙነት ሊኖረው አይችልም:: እነዚህ አዲስ መጤዎች ከእነሱ ጋር ምንም አይነት ግንኙነትም ሆነ አክብሮት የላቸውም::

ወራት ባለፉ ቁጥር እነዚያ በሆስፒታል የሚገኙ አዛውንት አንድ ቀን አንድ ጓደኛቸው፣ ልጃቸው፣ የጥንት ወዳጃቸው መጥቶ ይጠይቀናል በማለት በተስፋ ይጠባበቃሉ:: ነገር ግን ማንም ብቅ አይልም:: ሰዎች ይዘነጓቸዋል::

በእርግጥ አዛውንቶች በተፈጥሮ አሰልቺ ናቸው:: ከነሱ ጋር መቀመጥ ልክ አምሳ አመት ያስቆጠረ ጋዜጣ እንደማንበብ ማለት ነው:: ምንም አዲስ ነገር አይኖራቸውም፤ ሁሉም ነገር ሃምሳ እና ስድሳ አመት ያስቆጠረ ነው:: ጠጋ ሲሏቸው ወጣት በነበሩበት ዘመን ያሳለፉትን ወርቃማ ህይወት መጠረቅ ይጀምራሉ:: ይህም መሰልቸትን ይፈጥራል:: በአምሳ ዓመት ውስጥ ሁሉም ነገር ተለውጧላ:: እነዚያ ሰዎች ግን የተለወጠ ነገር ያለም አይመስላቸው::

በአለም ላይ የሚገኝ አንድ መንግስት እንኳን በፈቃደኝነት የመሞት መብትን (የቴኔዥያ) አልተቀበለም:: በዚህ ረገርም ድንጋጌ ውስጥም የለም::

ፖለቲከኞች በጣም፣ እጅግ በጣም ብልጦች ናቸው:: አወዛጋቢ መሆን ስለማይፈልጉ እናንተ ወይም ሌላው ሰው መስማት የሚፈልገውን ብቻ ይናገራሉ:: እውነተኛውን ሁኔታ እና የሚያስፈልገውን ለውጥ ዞር ብለው አይመለከቱትም:: የእነሱ ስራ የሃሰት ቃላት በመደርደር ሰዎችን ደስተኛ እና ተስፈኛ ማድረግ ነው::

በዚህም በዓለም ላይ እስካሁን ድረስ መሰረታዊ መብቶች አልተተገበሩም::

* * *



t.me/OLDBOOKSPDF

በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ ድንጋጌ ውስጥ፣ «የሰብአዊ መብቶች መናቅና ክብር ማጣት የሰውን ልጅ ህሊና ጭካኔ በማሳበስ ስዐጡን ሳልሆኑ ተግባራት ዳርገውታል. . .» ይላል፡፡

በዚህ አንቀፅ ውስጥ ሁለት ፋይዳዎችን እናገኛለን፡፡ የመጀመሪያው ይህን ድንጋጌ ያወጡት ሰዎች የሰው ልጅ ሰልጥኗል ብለው የተቀበሉ መሆናቸው ነው፡፡ ለዛም ነው፣ «አንዳንድ ጊዜ ያልሰለጠነ ተግባር ሲፈፀም መላው የሰው ዘር ህሊናው የሚጎዳው፣ ህመሙና ጭንቀቱ የሚሰማው» የሚሉት፡፡ ነገር ግን ሁለቱም ውሸት ናቸው፡፡ እኔ በበኩሌ የሰው ልጅ በጠቅላላ ህሊና አለው ብዬ አላምንም፡፡

የመሃመድ ተከታዮች ሂንዱዎችን ሲገድሉ አንድም የመሃመድ ተከታይ ስህተት እንደሰራ አያምንም - የህሊና ጥያቄ ጉዳይ አይነሳም፡፡ በእርግጥም በሃይማኖታቸው መሰረት የተቀደሰ ተግባር ነው የፈፀሙት፡፡ የመሃመድ ተከታይ ካልሆኑ ወደ ገነት አይገቡም ተብሎ ስለሚታሰብ ሂንዱዎችን ወደ መሃመዳዊነት ለመለወጥ እየጣሩ ነው፡፡

አማኙ ትክክለኛ በሆነ ወይም ባልሆነ መንገድ ወደ ገነት ሊያስክብልላችሁ እየጣረ ነው፡፡ የምትገቡበት በር የፊተኛው ይሁን የኋለኛው ጉዳዩ አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ እናንተ ታመነታላችሁ፣ ወደ ገነት መግባት አትፈልጉም፣ ወደ ሲያል ለመግባት ቆርጣችኋል - ለዛም ነው መንገዳችሁ ላይ ቆሞ ሊመራችሁ የሚሞክረው፣ አሻፈረኝ ካላችሁም አንገታችሁን የሚቀላው፡፡ ወደ ሲያል ከምትወረወሩ በሃይማኖተኛው እጅ ብትሞቱ የተሻለ ነው፡፡ ስለዚህም አማኞቹ፣ ሰዎች ወደ ሲያል እንዳይወርዱ እየተከላከሉ ነው - ለምን ህሊናቸውን ይቆጠቁጣቸዋል?

ይህን ስሜት ሂንዱዎችም ሆኑ ክርስቲያኖች ይጋሩታል፡፡ ክርስቲያኖች ከማንም በበለጠ ብዙ ሰዎችን ገድለዋል፣ ሰዎችን ከነህይወታቸው አቃጥለዋል፡፡ እነሱን የማይመስሉ ሌሎችም ገድለዋል፣ አቃጥለዋል፡፡ ክርስትና አቋራጭ መንገድ አለው፡፡ ለምን ለሁለት ይከፈላል? መፅሃፉ በአንድ መፅሃፍ ተጠቃልሎ መታተም ከቻለ ሁለት ጥራዝ ማዘጋጀቱ ለምን አስፈለገ?



t.me/OLDBOOKSPDF

መጀመሪያ ገድሎ ከዚያ ማቃጠል? - በቀጥታ ማቃጠል አይሻልም! ለነገሩ ቦሺ የሚቆጠሩ ሰዎች ከእነ ህይወታቸው ተቃጥለዋል እኮ::

በዚህ ጉዳይ የተበሳጨ ግን፣ የትም አንድም አላገኘሁም::

ምክኒያቱም ሰዎች ከተበሳጩ ነገሮች ይለወጣሉ - ነገሮቹን የሚፈፅመው ማነው? እኛው ነን:: ስለዚህ ለምን እንበሳጫለን?

በድንጋጌው መግቢያ ላይ የሚገኘው ይህ ዓረፍተ ነገር የሃሰት ነው:: በመጀመሪያ «ስልጡን ላልሆኑ ተግባራት. . .» ይላል:: እርግጥ ነው በእነዚህ ሃምሳ አመታት ውስጥ ከጠቅላላው የሰው ልጅ ታሪክ በበለጠ ብዙ ስልጡን ያልሆኑ ተግባራትን ፈፅመናል:: በአስር ሺ ዓመታት ውስጥ ልክ በእነዚህ ሃምሳ ዓመታት ውስጥ እንዳደረግነው እጅግ ብዙ ስልጡን ያልሆኑ ተግባራትን ፈፅመናል:: ዘዴና ስልታችንን እየቀያየርን የበለጠ ያልሰለጠኑ እየሆንን ነው::

ስለ ሂሮሽማ እና ናጋሳኪ ምን ያስባሉ? ተግባራቱ ስልጡን ያልሆኑ ናቸው ወይስ የናጋሳኪንና የሂሮሽማን ውብ ህዝቦች በቀጥታ ወደ ገነት ለመላክ የታሰቡ?

ሁለት መቶ ሺ የሚሆኑ ሰዎች በአምስት ደቂቃዎች ውስጥ ጠፍተዋል፣ ዶግ አመድ ሆነዋል:: እንደዚህ አይነት ብዙ ህዝብ በገነት በር ላይ ይቆማል ብዬ አላስብም:: ለሂሮሽማ እና ናጋሳኪ ከተሞች ጉዳት ሃላፊነት ያለባት አሜሪካ ናት::

አሁን የወታደራዊ ሳይንስን ጠንቅቀው የሚያውቁ ሰዎች ሂሮሽማ እና ናጋሳኪ ላይ የአቶም ቦምብ መጣል አስፈላጊ እንዳልነበር አረጋግጠዋል:: ለምን ቢባል ጃፓን እጇን እየሰጠች ነበር - ጀርመን ተማርካ ስለነበር ጃፓን የምትዋጋበት ምክንያት አልነበረም:: ከአንድ ሳምንት በላይ የመዋጋት አቅም አልነበራትም::

ጀርመን መሸነፏን እየተመለከተች ጃፓን ብቻዋን የምትዋጋበት ምክንያት አልነበረም:: ሃገሪቱ አነስተኛ ብትሆንም ህዝቦቿ ደፋሮች ነበሩ:: ጀግና ህዝቦች፣ ግን አነስተኛ ሃገር:: በዋነኝነት በጀርመን የምትደገፍ ነበረችና ድጋፉ ሲቋረጥ. . . ጃፓን እጇን ለመስጠት ዝግጁ ነበረች::



t.me/OLDBOOKSPDF

የአሜሪካው ፕሬዝዳንት ትሩማን ጃፓን ነገ እንደምትማረክና የአቶም ቦምቦቹን የመጣል ዕድሉ ያመልጠኛል የሚል ፍራቻ አድሮባቸው ነበር፡፡ የአቶም ቦምቦቹን ለመገንባት ብዙ ገንዘብ፣ ጉልበት እና እውቀት ስላወጡ የሰሩትን ነገር የመሞከር ፍላጎት ነበራቸው፡፡ በጊዜው ትልቁ ጉዳይ የነበረው የሰው ልጅ ሳይሆን ገንዘብ ነበር. . . እናም ቦምቦቹ መሞከር ነበረባቸው፡፡

ታዲያ ሰዎች ስልጡን ባልሆኑ ተግባራት ሳቢያ የህሊና ጉዳይ ይሰማቸዋል ተብሎ ይታመናል? ፕሬዚዳንት ትሩማን ስልጡን ነበሩ ወይስ አልነበሩም? የራሳቸው ወታደራዊ አማካሪዎች ሳይቀሩ ህዝብን ማጥፋት ትርጉም የለሽ እንደሆነ መከረዋቸው ነበር፡፡ እሳቸው ግን በድርጊታቸው ገፉበት፡፡

በአለም ላይ ይህን ዓይነት ዘግናኝ ውድመት በሰው ልጅ ተፈፅሞ አያውቅም ነበርና በሚቀጥለው ቀን ጠዋት በመቶዎች የሚቆጠሩ ጋዜጠኞች ፕሬዝዳንት ትሩማንን ለማናገር ተሰብስበው ነበር፡፡ የመጀመሪያው ጥያቄያቸው «ሚስተር ፕሬዚዳንት፣ ምሽቱን በሰላም አሳለፉ?» የሚል ነበር፡፡ ይህ ጥያቄ የተነሳው ያለ ምክንያት አልነበረም፡፡ ፕሬዝዳንቱ ወደ አልጋቸው የሄዱት «ሂሮሽማ እና ናጋሳኪ ወድመዋል፣ ከመሬት ካርታ ላይ ተሰርዘዋል» የሚል መልዕክት ከደረሳቸው በኋላ ነበርና ነው፡፡ አልጋቸው ላይ ከመውጣታቸው በፊት የዜናውን መድረስ መጠበቅ ነበረባቸው፡፡

እሳቸውም፣ «አዎ፣ ሙከራችን ስኬታማ በመሆኑ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በሰላም ተኝቻለሁ፡፡ አሁን በዓለም እኛን የሚወዳደር የለም» ሲሉ ነበር የመለሱት፡፡

እና ስለ ህሊና ትናገራላችሁ?!

ከሁለት መቶ ሺ የሚበልጡ ሰዎች በሶስት ደቂቃዎች ውስጥ አልቀዋል፡፡ ሰዎቹ በጅምላ እንዲገደሉ ትዕዛዙን ያስተላለፉት ሰው ግን ከምንጊዜውም በበለጠ «በሰላም» እንቅልፋቸውን ለጥጠዋል፡፡ የፕሬዚዳንት ትሩማን «True - Man» (እውነተኛ ሰው) ጉዳይ እንዲህ ከሆነ እውነተኛ ያልሆኑ ሰዎችስ? ...


t.me/OLDBOOKSPDF

እንደ እኔ አስተሳሰብ ስልጣኔ ገና በህልም ያለ ተስፋ ነው፡፡ በአስማተኛ አስማት ካልተታለልን እና ስልጡን ህዝቦች መሆናችንን ማመን ካቆምን ተስፋው እውነት ይሆናል፣ ህልሙም ወደ ተግባር ይለወጣል፡፡

ህሊና ደግሞ ያለ ተመስጦ አይመጣም፡፡ ከህሊና ጋር አብራችሁ አልተወለዳችሁም፡፡ ህፃናትን በትኩረት መመልከት ትችላላችሁ፡፡ ህፃናት ጉንዳን ሲያዩ ይገድላሉ፡፡ ታዲያ ይህን የሚያደርግ ህፃን ህሊና አለው ሊባል ይችላል? ህፃኑስ ወንጀለኛ፣ ነፍሰ ገዳይ ነውን? በፍፁም፣ እንዲያ አይደለም፡፡ ህፃኑ ከመደነቅ አልፎ ዓለምን ለማወቅ እየጣረ ነው፡፡ አዲሱን ዓለም ለመገንዘብ እየሞከረ ነው፡፡ የህሊና ጉዳይ አይደለም፡፡ ያለ ምንም ምክንያት አንድን ውሻ ሲመታ ውሻው እንደሚያመው አያውቅም፡፡ ህፃናት የሰብዓዊ ፍጡር ዘር እንጂ ህሊና የላቸውም፡፡

እነዚህ ፖለቲከኞች ደግሞ «ህሊና አላችሁ» በማለት የሰውን ልጅ ለማሳመን እየሞከሩ ነው፡፡ እናንተ ግን ህሊና የላችሁም፡፡ ይህ ነገር በውስጣችሁ እንዲፈጠር ኮትኩታችሁ ልታሳድጉት ይገባል፡፡ ፀጥ ማለትን፣ የውስጣችሁን ድምፅ ማድመጥን መልመድ አለባችሁ፡፡

ይህን ድንጋጌ ያወጡት ፖለቲከኞች በሙሉ ህሊና ምን እንደሚመስል እና ምን እንደሆነ የሚያውቁ አይመስለኝም፡፡

ህሊና የሚመጣው ውስጣችሁን ለረዥም ጊዜ ስታከብሩ ከቆያችሁ ነው፡፡ ሁሉንም ነገር ስትወለዱ አላገኛችሁትም፡፡ ስትወለዱ ያገኛችሁት በህይወት እንድትቆዩ የሚያስችሉዋችሁን ነገሮች ብቻ ነው፤ ሌላው ነገር በዘር መልክ ነው የተሰጣችሁ፡፡ ህሊናችሁን እስከ ጫፍ ድረስ ማሳደግ ከፈለጋችሁ ግን ትችላላችሁ፡፡

ተፈጥሮ በህይወት እንድትቆዩ የሚያስችላችሁን ነገር እንጂ ህይወት፣ ደስታ፣ ፀጥታ፣ ፍንደቃ ወይም ፍቅር አትሰጣችሁም፡፡ ተፈጥሮ ከዝሙት ጋር መኖር ስለምትችል ፍቅር ምን ያደርጋል? ውስብስብ ነገሮች ለምን ያስፈልጋሉ? ራሳችሁ ፍቅርን ማግኘት፣ ህሊናችሁን ኮትኩታችሁ ማሳደግ ይኖርባችኋል፡፡ የራሳችሁ አትክልተኛ መሆን ይገባችኋል - ማንነታችሁ የአትክልት መብቀያ ስፍራ ነውና፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ይህ ማንነታችሁ በመፅሃፍ ቅዱስ ውስጥ የኤደን ገነት ተብሎ የተጠቀሰው ነው። የኤደን ገነት የትም ሳይሆን እውስጣችሁ ነው ያለው።

ተወርውራችሁ የወጣችሁት ከዚህ ገነት ነው። አሁን ደግሞ ለመግባት ፈልጋችሁ ዙርያውን ብትዞሩም አልገባችሁም። ወደ ራሳችሁ ውስጥ በገባችሁበት ቅፅበት ያኔ በኤደን ገነት ውስጥ ናችሁ።

አሁን ግን ይህ ጉዳይ ቀብ ካጣ በሺ የሚቆጠሩ ዓመታት አልፈዋል። ተመልሳችሁ ገብታችሁ አታውቁም። ሁሉም ነገር ገና በዘር ደረጃ ላይ ነው፤ የአበበ፣ የጐመራ፣ የሰመሰመ ነገር የለም። ይሁን እንጂ አቅሙ ስላላችሁ መልሳችሁ ህይወት ልትዘሩበት ትችላላችሁ።

እነዚያ ፖለቲከኞች ግን ህሊና የሚባለውን ነገር የሚረዱ አይደለም።

ቃላቱን ብቻ ነው የሚያውቋቸው።

አንድ የሰማሁት ታሪክ ነበር. . . አንድ ሳይኮሎጂስት የዶክትሬት ዲግሪውን ለማግኘት የቃል ፈተና መውሰድ ነበረበት። ፈታኞቹ ሶስት ነበሩ። የመጀመሪያው ጥያቄ «የእናት ጡት ወተት ሶስት ባህሪያት ምንድናቸው?» የሚል ነበር።

የሥነ - ልቡና ባለሙያው ትንሽ ግራ ተጋባ። «ሥነ - ልቡና ከእናት ጡት ወተት ጋር በምን ይገናኛል? እዚህ የመጣሁት ስለ ወተት ወጤቶች ኤክስፐርት ልሆን አይደለም። ግን ምን ያደርጋል፣ መልስ መመለስ አለብኝ. . .» ይላል።

ከዚያም ይቀጥልና «በመጀመሪያ፣ ለህፃኑ እድገት ጠቃሚ የሆኑት ንጥረ - ምግቦች አሉት - ፍፁም የሆነ ምግብ ነው። ሁለተኛ፣ የሚወጣው ከእናቲቱ ሰውነት ውስጥ በመሆኑ ሞቃት እና በቀላሉ የሚዋሃድ ነው፤ ከውስጥ ስለወጣም ኢንፌክሽን ወይም በሽታ አይኖረውም። በዚህ በኩል ህፃኑ ከጉዳት (ከህመም እና ከሞት) የተጠበቀ ነው» ብሎ ያብራራል።

«ትክክል! ሶስተኛውስ?» ይሉታል።

ባለሙያው መልሱን ስላላወቀው ለጥቂት ጊዜ ያህል ፀጥታ ይሰፍናል - ሶስተኛው ባህርይ ምንድነው? ሁሉቱን አውቋቸዋል።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሶስተኛው በአዕምሮው ደጋግሞ ቢመጣበትም እንዳይወጣ እየተጫነው ነው:: ሌላ አማራጭ አልነበረውምና ሲናገረው የግድ ሆነ:: እናም «በምርጥ መያዣዎች ውስጥ ነው ወተቱ የሚያልፈው!» አለ::

እነዚህ ደደቦች ናቸው ሳይኮሎጂስቶች የሚሆኑት! በአዕምሮው በመጀመሪያ የመጣው ነገር ይህ ነው - «ምርጥ መያዣዎች::» የእናቲቱን ጡቶች ማለቱ ነው::

ድንጋጌውን በተመለከትክ ጊዜ በመጀመሪያ የተሰማኝ ስሜት እነዚህ ሰዎች በቃላት መጫወት የሚችሉ ጥሩ ተናጋሪዎች እንደሆኑ ነው:: አዎን፣ ውብ የሆኑ ቃላት በመጠቀም እውነታውን ደብቀው ተፅዕኖ ሊያደርጉባችሁ እና ሊያታልሏችሁ ይችላሉ::

*   *   *

**እንቀፅ አንድ:- ሁሉም ሰብአዊ ፍጡራን ሲፈጠሩ ጀምሮ ነፃ ናቸው:: ፍፁም የማይመስል ነገር::**

ሁሉም ሰብአዊ ፍጡራን ሲፈጠሩ ጀምሮ ነፃ ከሆኑ ገና የተወለደ ህፃንም ነፃ ተዉት ማለት ነው:: እንዲህ ከሆነ ደግሞ በተወለደ በሃያ አራት ሰዓታት ውስጥ ይሞታል:: አንድ የሰው ልጅ ህፃን፣ በዚህ ዓለም ከሚኖሩ ፍጥረታት ሁሉ በበለጠ ረዳት የለሽ ነው - እና ምን ነፃነት ሊኖረው ይችላል? መራመድ አይችል፣ መናገር አይችል፣ መብረር አይችል. . .

አንድ ሳይንቲስት፣ «ህፃናት ከሚገባቸው ጊዜ ቀድመው ነው የሚወለዱት» ብሎ ያቀረበውን ሃሳብ እጋራለሁ:: አዎን፣ ምሉዕ ስላልሆነ እና ገና እያደገ ስለሆነ በእናቱ ማህፀን ውስጥ ቢያንስ ለተጨማሪ ዘጠኝ ወራት ያህል መቆየት ነበረበት:: የእንስሳት ግልገሎችን ተመልከቱ - ገና እንደተወለዱ መራመድ እና ራሳቸው ምግብ መፈለግ ይጀምራሉ:: ከሰው ልጅ የበለጠ ነፃ እና በራሳቸው ምሉዕ ናቸው:: አንድ ሰብአዊ ህፃን ግን ያለ እናቱ፣ ያለ አባቱ፣ ያለ ቤተሰቡ ወይም ያለ ሌሎች ሰብአዊ ፍጡራን እርዳታ በህይወት መቆየት አይችልም::



t.me/OLDBOOKSPDF

ታዲያ ምን ዓይነት ነፃነት ሊኖረው ይችላል?

ይህንን ነው በፖለቲከኞች አዕምሮ ውስጥ የሚመላለስ ብሎጥነት የምለው:: በተዘዋዋሪ ነፃነት እንደማያስፈልገን እየነገሩን ነው:: «ነፃነትን አትጠይቁ:: ስትወለዱ ጀምሮ ነፃ ናችሁ:: ሁሉም ሰብአዊ ፍጡራን ሲፈጠሩ ጀምሮ ነፃ ናቸው» ይላሉ::

ይሄ ቅጥፈት ነው! ሁሉም ሰብአዊ ፍጡራን ሲወለዱ ጀምሮ ረዳት አልባና ጥገኛ ናቸው:: ነፃ ለመሆን አመታት ይፈጅባቸዋል:: በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ደግሞ መቼም ነፃ አይሆኑም::

ይሄ ድንጋጌ ግን «ከተወለዱ ጀምሮ ነፃ ናቸው» ይላል::

እንዲያውም በሚሊየን የሚቆጠሩ ሰዎች ነፃ ሳይሆኑ ነው ኖረው፣ ኖረው አርጅተው የሚሞቱት:: እናንተም ብትሆኑ ህይወታችሁን ስለምታውቁት ነፃ እንዳልሆናችሁ ለመረዳት አይከብዳችሁም::

ባል እስካለ ድረስ ሚስት ነፃ አትሆንም:: ሚስት እስካለች ድረስ ባል ነፃ አይሆንም:: ባልና ሚስቶች በመንገድ ላይ እያወሩ ሲሄዱ ሁሌ እያለሁ - ባልየው እዚህና እዚያ ማየት እንኳን አይችልም! ልክ እንደ አንድ የቡድሃ መነኩሴ ወደፊት ለፊት ብቻ ነው መመልከት የሚችለው:: ሚስት በአይኗ ጥግ አትኩሮቱ ያረፈው የት እንደሆነ ትቆጣጠረዋለች:: ይህ ነፃነት ምን አይነት ነፃነት ነው? ባል ቤቱ እንደገባ መጀመሪያ የሚቀርብለት ጥያቄ «የት ነበርክ?» የሚል ነው:: ባልየው ግን እንደ እናንተ ሁሉ ነፃ ነኝ ብሎ ያስባል:: ሆኖም «የት ቆይተህ ነው?» ትባላላችሁ::

ተማሪ እያለሁ ብዙ ጊዜ አረፍድ ነበር:: ከትምህርት ቤቱ አጥር ውጭ የነበረው ህይወት ውብ ነበር:: በትምህርት ቤቱ ዙሪያ ብዙ የማንጐ ዛፎች ነበሩ:: ማንጐዎቹ የሚደርሱበት ወቅት ሲሆንማ - በዚያ መዓዛ፣ በዚያ ውበት መሃል መመላለስ በጣም ደስ ይላል:: ሌሎች የፍራፍሬ ዛፎች የነበሩ ቢሆንም፣ ለኔ ማንጐ የፍሬዎች ሁሉ ንጉስ ነው:: እናም ክፍል ከመግባት ይልቅ ወደ ማንጐዎቹ ሄጄ መዝናናት ያስደስተኝ ነበር::



t.me/OLDBOOKSPDF

በመጀመሪያው ቀን ትምህርት ቤት ስደርስ ግማሽ ሰዓት ያህል አርፍጄ ነበር። «ያዶረግከው ነገር ፍፁም ትክክል አይደለም። ቢያንስ እኔ አልታገስህም። የእኔን ትምህርት መማር ከፈለግክ እኔ ከመምጣቴ አምስት ደቂቃዎች በፊት እዚህ መድረስ ይኖርብሃል። ለመሆኑ ለምንድነው የዘገየኸው?» ነበር ያለኝ - መምህሬ።

«ያድምጡኝ - በዚህ ጥያቄ ምክንያት ነው ትዳር መመስረት የማልፈልገው!» አልኩ።

«ምን? የጋብቻ ጥያቄ?!»

«ካልገባዎት በደንብ አብራራልዎታለሁ» አልኩ። «በአካባቢዬ በየስፍራው የምሰማው ነገር ነው። ሚስቶች በሙሉ ባሎቻቸውን <የት ቆይተህ ነው? ለምን ዘገየህ?> በማለት ይጠይቃሉ። ባሎችም እንደዚያው። እኔ ደግሞ እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ዝግጁ አይደለሁም። በዚህ ጥያቄ ሳቢያ መላ ህይወቴን ሳላገባ ለመኖር ወስኛለሁ። እና ይህንን እጅግ የምጠላው ጥያቄ ሲጠይቁኝ በደስታ መልስ የምሰጥዎት ይመስልዎታል? ይህን አስጠሊታ ጥያቄ ከምመልስ ትምህርት ቤትን ብቀይር ይሻላል። ደህና ይሁኑ!»

«ይህ አስገራሚ ልጅ ነው። ስለ ትዳር አንስቶ በማያገባው ጉዳይ ገብቷል። ትዳርና የኔ ጂኦግራፊ ትምህርት ምን አገናኛቸው?» አላቸው ለክፍል ተማሪዎች።

ይሁን እንጂ በአነጋገሬ ተማርኮ ነበር። የትምህርቱ ክፍለ ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ እኔ ዘንድ መጥቶ እጄን ያዘኝና «እዚህ እንቀመጥ። ጉዳዩ ምን እንደሆነ መረዳት እፈልጋለሁ» አለኝ።

እኔም እንዲህ ስል መለስኩለት። «ለምን እንደዘገየሁና የት እንደነበርኩ የመጠየቅ መብት ያለው ማንም የለም። መናገር ካልፈለግኩ መብቴ ነው። የእርስዎ ስራ ጂኦግራፊ ማስተማር ብቻ ነው። እዚህ የተገኙት እንዲህ አይነት ጥያቄ እየጠየቁ የጥገኝነት ስሜት እንዲያድርብኝ አይደለም። እንደዚህ አይነት ጥያቄዎች ያስጠሉኛል። እንዲያውም በዚህ የተነሳ ከትምህርት ቤት መራቅ፣ ትምህርት ማቆም እችላለሁ፣ ምንም አስፈላጊ አይደሉም። ኢየሱስ ያለ ምንም ትምህርት



t.me/OLDBOOKSPDF

ራሱን መምራት ከቻለ፣ ካቢር ያለምንም ትምህርት ራሱን መግዛት ከቻለ በየትኛውም ስራ፣ በየትኛውም አገልግሎት፣ በማንኛውም ቅጥር ህይወቱን ብኖር ግድ የለኝም። ስለዚህ በክፍልዎ እንድማር ከፈለጉ ትንሽም ቢሆን ነፃነቱን ሳይጋፋ ሰብአዊ ሊሆኑ ይገባል።»

* * *

የመጀመሪያው አንቀፅ፣ «ሁሉም ሰብአዊ ፍጡራን ሲፈጠሩ ጀምሮ ነፃ ናቸው» ይላል።

እነዚህ ስብዕናን የሚያደነዝዙ እና እውነት ብሎ እንዲቀበላቸው የሚያለማምዱ አደገኛ ዘዴዎች ናቸው።

ከተወለዳችሁ ጀምሮ ነፃ እንደሆናችሁ እየነገሩዋችሁ ነው - አሁን ለነፃነታችሁ የምትታገሉበት፣ አካል አሳሪ ነውና ከአካላችሁ፣ ከሁሉም ነገር የእውነትም ነፃ ከሚያደርጋችሁ ውስጣዊ አብዮት ጋር የምትራመዱበት ምክንያት እንደሌለ እየገለፁላችሁ ነው።

የምስራቁ ዓለም በተሻለ እውነተኛ ነው። በዚህ ክፍለ ዓለም ሰዎች ሲወለዱ ነፃ ሳይሆኑ እስረኛ ሆነው ነው ተብሎ ይታመናል። አካላችሁ፣ አዕምሮአችሁ፣ አንጐላችሁ በሙሉ እስር ቤቶች ናቸው። ህሊናችሁ ታጥሯል። ነገር ግን ይህ ህሊናችሁ አጥሩን ሰባብሮ በመላው ዩኒቨርስ መሰራጨት ይችላል። ይህን የማድረግ አቅም እንዳላችሁ ስለማታምኑ ግን ይህቺን ታክል ብቻ ነኝ ብላችሁ ራሳችሁን ታሳምናላችሁ።

እንደ እኔ አስተሳሰብ ከሆነ እነዚህ ሰዎች መላውን የሰው ልጅ (ክርስቶስ) በመስቀል ላይ ከሰቀሉት እና ካታለሉት የበለጠ ወንጀለኞች ናቸው። የማታለያ ዘዴያቸው ደግሞ እጅግ ብልጥነት የታከለበት ነው። «ነፃ ሆናችሁ ነው የተወለዳችሁት» ይላሉ።

ነፃነት በተፈጥሮው የሚጠየቅ፣ የሚፈጠር፣ የሚሰጥ፣ የሚገኝ፣ በልገሳ የሚበረከት አይደለም። ይህ ሁሉ ሳይኖር ነፃ ናችሁ!


t.me/OLDBOOKSPDF

ጆርጅ ጉርዲፍ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ «ነፍስ የለንም» ብሎ ጠቃሚ ነገር የተናገረ ብቸኛው ሰው ነው። በዓለም ዙሪያ የሚገኙ ሃይማኖቶች በሙሉ ነፍስ አላችሁ፣ ከነፍስ ጋር ነው የተፈጠራችሁት ብለው ያምናሉ። በታሪክ «ሁሉም ሰዎች ነፍስ የላቸውም፣ የነፍስ ቦታ ባዶ ነው» ብሎ የተናገረ ጆርጅ ጉርዲፍ ብቻ ነው። እርግጥ ነፍስን የምትፈጥሩበት ዕድል አለ። ይሁንና ከነፍስ ጋር የተወለደ ማንም የለም።

ጉርዲፍ ሰዎች ከነነፍሳቸው እንደተወለዱ እንደሚያምን አውቃለሁ - ነገር ግን እሱ ለማለት የፈለገው <ከነፍስ ጋር ነው የተወለድነው ማለቱ ምንም አልፈየደልንም፤ እንድናንቀላፋ አድርጎናል> ነው። ከነፍስ ጋር ነው የተወለድነው፣ እግዚአብሔር በውስጣችን አለ፣ የእግዚአብሔር መንግስት በውስጣችን አለ። ግን ምን ማድረግ ይኖርብናል? እናንተ ጋ የሌሉ ነገሮችን - ገንዘብ፣ ስልጣን፣ ክብር - ለማግኘት በጣም ትጥራላችሁ። «ህፃን ሁሉ ከገንዘብ ጋር፣ ከፖለቲካ ስልጣን ጋር፣ ከክብር ጋር ነው የተወለደው» ያለ ሰው ግን የለም። ይህን የሚል ሰውም አይኖርም። እነዚህ ነገሮች የሚገኙ ናቸውና።

ነፃነት፣ ህሊና፣ እግዚአብሔር ወይም ሌላ ስም ስጡት ብቻ መገኘት አለበት። የተደበቀ፣ የተቀመጠ ነውና የሚንቀሳቀስ ህያው፣ ሙሉ በሙሉ የበሰለ እንዲሆን መደረግ አለበት። ሊያብብ እና ሊጎመራ ይገባል። ነገር ግን ሰዎችን «ስትወለዱ ጀምሮ ነፃ ናችሁ - በክብር እና በመብት እኩል ናችሁ. . .» ባልናቸው ቁጥር በነዚህ ቃላት ራሳቸውን እየሸነገሉ ተደላድለው ይተኙ እና በመጨረሻ ቃላቱ ትርጉም አልባ ይሆናሉ።

ማንም እኩል አይደለም።

ይህ ነው ስነ - ልቦናዊ እውነታው።

በአካልም፣ በአዕምሮም፣ በእውቀትም፣ በተሰጥኦም ከማንም ጋር እኩል አይደላችሁም - ማንም ከማንም ጋር እኩል አይደለም። ሲግመንድ ፍሪውድ፣ ሲግመንድ ፍሪውድ ነው፣ በርትራንድ ራሴል፣ በርትራንድ ራሴል ነው፤ ዲ.ኤች ላውረንስ፣ ዲ.ኤች ላውረንስ ነው። በቃ!

ሌላ ዲ.ኤች ላውረንስ የለም፤ አይኖርም።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሁሉም ግለሰብ የተለየ ነው።

ይህ የእኩልነት ሃሳብ አስቀያሚ ቢሆንም የዘመናዊው ሰው እምነት ሆኗል ማለት ይቻላል - <እኩልነት!>

ወደ ሰው ልጅ አዕምሮ ሰርስሮ የገባ እጅግ አፍራሽ የሆነ ሃሳብ እንደሆነ ልነግራችሁ እወዳለሁ። ልዩ ስለመሆናችሁ ሲነገራችሁ ይገባል።

*   *   *

በዚህ ድንጋጌ ውስጥ፣ «ሁሉም ሰብአዊ ፍጡራን የማሰብ ኃይልና ህሊና ተሰጥቷዋልና በወንድማማችነት መንፈስ አብረው ሊኖሩ ይገባል» የሚል አንቀፅ አለ።

እነዚህ ሁሉ ተገቢ ያልሆኑ የይሆናል አስተሳሰቦች ናቸው። ሁሉም ሰብአዊ ፍጡራን የማሰብ ሃይል አልተሰጣቸውም፣ ከማሰብ ሃይል ጋርም አልተወለዱም።

ለምሳሌ ያህል በርትራንድ ራሴልን የመሳሰሉ የማሰብ ሃይል ያላቸው ጥቂት ሰዎች አሉ። ጂ. ክሪሽናሙርቲም አለ. . . ተራው ህዝብ ግን በከንቱ ነገር አምኖ የሚኖር ነው።

ከንቱ እምነታችሁን በሙሉ ካላስወገዳችሁ በቀር በምክኒያት የሚመራ ሚዛናዊ ሰው ልትሆኑ አትችሉም።

የማሰብ ሃይል ምንድነው? ለሂንዱዎች ላም እናት ናት። ይህ ነው <አስተሳሰብ>።

ከአንድ የሂንዱ ሻንካራቻሪያ ጋር የማውራት አጋጣሚ አግኝቼ ነበር። ሻንካራቻሪያ ከሊቀ - ጳጳስ ጋር የሚመጣጠን ሹመት ነው። «ላም እናታችሁ እንደሆነች እርግጠኛ ነዎት?» ስል ጠየቅኳቸው።

«ምን ማለትህ ነው?» አሉኝ።

«ወደ ቤተ - መቅደስ ስገባ እናትዎን አግኝቻቸው ነበር። እናም ግራ ገባኝ። እናትዎት ሴትዮዋ ናቸው ወይስ ላሟ? ወይስ አንደኛዋ የእንጀራ እናትዎ ናት?»



t.me/OLDBOOKSPDF

«ስለምን እያወራህ ነው? ሴትዮዋ ባዮሎጂያዊ እናቴ ስትሆን ሳሚ ደግሞ መንፈሳዊ እናቴ ናት» ሲሉ መለሱልኝ::

«እምላኬ!» አልኩ:: «ኮርማውስ? ከኮርማው ጋርም ግንኙነት አለዎት፤ አይደለም እንዴ? መንፈሳዊ አባትም ነው? ታዲያ እርስዎ ማነዎት? ኮርማ? ወይስ የተከላሸ ኮርማ?»

ብዙ ሰዎች ከከንቱ እምነት ጋር እየኖሩ ስለ ማሰብ ሃይል ያወራሉ:: ይህ የሚቻል ነገር አይደለም:: ከከንቱ እምነት ጋር የሚኖር ሰው በመጀመሪያ ደረጃ ምክኒያታዊ አስተሳሰብ የለውም፤ ሊኖረውም አይችልም:: ያለ ምክንያታዊ አስተሳሰብ ደግሞ ስለ ማሰብ ኃይል በፍጹም ሊያወራ አይችልም:: ምክንያቱም እሱ ጅል ነው - ከከንቱ እምነት ነውና የሚኖረው:: የበሰጠ ጅል በሆናችሁ ቁጥር ነው የበለጠ አማኝ የምትሆኑት::

ደግሞም እንደ ቡድሂስት እምነት «ሰው ሁሉ ሲወለድ ጀምሮ የማሰብ ሃይል ነበረው» የሚባለው ነገር ፍፁም የማይመስል ነው:: ዓለም ራሷ ሚዛናዊ አትመስልም:: በማሰብ ሳይሆን ሚዛናዊ ባልሆኑ ነገሮች እየተመራን ነውና የምንኖረው::

የማሰብ ሃይል ተሰጥቶናል የሚሉት ጣፋጭ ቃላት ግን የሚታመኑ ናቸው::

> **ማንም እኩል አይደለም::**
>
> **ይህ ነው ስነ - ልቦናዊ እውነታው::**
>
> **በአካልም፣ በአዕምሮም፣ በዕውቀትም፣ በተሰጥዖም ከማንም ጋር እኩል አይደላችሁም - ማንም ከማንም ጋር እኩል አይደለም::**



t.me/OLDBOOKSPDF

«. . . ህሊና ተስፐቷቸዋልና በወንድማማችነት መንፈስ አብረው ሊኖሩ ይገባል።»

ይህን ድንጋጌ ያረቀቁት ፖለቲከኞች ምክንያታዊ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች አይደሉም። ምክንያቱም ህሊና የሚመጣው ከጥልቅ ተመስጦ በኋላ እንጂ በፊት አይደለም። ህሊና የተመስጦ አበባ ነው።

በመላው ዓለም፣ በመላው የሰው ልጅ ታሪክ ጥቂቶች ብቻ ናቸው ህሊና ያላቸው፣ በጥልቅ ማሰብ የቻሉ። ሁለቱ ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ቢኖራቸውም በሃይማኖት ሰዎች ሳቢያ ከፈረንሳይኛ ቋንቋ በቀር የተለያየ ትርጉም ነው የሚሰጣቸው።

ሃይማኖቶች ህሊናን በጥልቀት ከማሰብ ለይተው ያስቀምጡታል። በጥልቀት ማሰብ የሚመጣው ከጥልቅ ተመስጦ በኋላ ነው። እስከ መቼ ሃይማኖት ሃይማኖት እያታለላችሁ መኖር ትችላላችሁ?

ብርሃን ይዛችሁ ወደ አንድ ክፍል ስትገቡ መቼም ጨለማው ጨለማው እንደ ሚጠፋ ነው። በተመስጦ ውስጥ ስትሆኑም በጥልቀት ታስባላችሁ፣ ትነቃላችሁ።

እነሱ ደግሞ ህሊና የሚባል ቃል ፈጥረዋል። ህሊና የሚባለው ካህናቱ፣ ቤተ - ክርስቲያን፣ ሃይማኖቱ «ይሄ ጥሩ ነው፣ ይሄ መጥፎ ነው፣ ይህ በጐ ነው፣ ይህ ሃጢአት ነው» ብለው ያስተማሩዋችሁ ሁሉ ነው። ህሊናን ከጥልቀት እሳቤ ነጥሎ ማየት ሃይለኛ የሸወዳ ጥበብ የሚጠይቅ ነው።

ካለ ጥልቀት ማሰብ የሚኖር ህሊና የለምና።

እነሱ የፈጠሩት ህሊና ግን የሃሰት ነው።

ለምሳሌ እና የተወለድኩት እጅግ ጥንታዊ በሆነ ሃይማኖት ውስጥ ነው። ምናልባትም የሚቀድመው እምነት ላይኖር ይችላል። የተከታዮቹን ቁጥር በተመለከተ እጅግ ጥቂት ናቸው። ይሁን እንጂ የራሳቸው የሚያመልኳቸው ከንቱ እምነቶች አሏቸው።

አስራ ስምንት ዓመት እስኪሞላኝ ድረስ በቤታችን ውስጥ የቲማቲም ዘር አይቼ አላውቅም ነበር። ቲማቲሞች አደገኛ ናቸው ብላችሁ አስባችሁ ይሆን? ቲማቲም ወደዳር የተገፋው፣ የስጋ አይነት



t.me/OLDBOOKSPDF

ቀለም ስለነበረው ብቻ ነው። አስራ ስምንት ዓመት እስኪሞላኝ ድረስ በምሽት መብላት አልችልም ነበር - በሃይማኖቱ የተከለከለ ነው። ፀሃይ ወጥታ እስክትጠልቅ ብቻ ነው መመገብ የሚቻለው። በምሽት መመገብ የሆኑ ነፍሳት ወይም ጉንዳን መብላትን ሲያስከትል ስለሚችል አንድ ችግር ሲፈጥር ይችላል። ስለዚህ በቀን፣ በብርሃን መመገቡ ይመረጣል።

እድሜዬ አስራ ስምንት ሲደርስ ጓደኞቼ ጥቂት ማይሎች ራቅ ብሎ ወደሚገኘው አንድ ውብ ህንፃ ለመሄድ ሲዘጋጁ አየሁና እኔም ከእነሱ ጋር ሄድኩ። ምን ሊያዩ እንደሚሄዱ አላውቅም። ከረብታውን አልፈን ወደ ህንፃው መሄዳችንን ብቻ ነበር የማስበው. . . በጣም ብዙ የሚታዩ ውብና ጥንታዊ ነገሮች ስለነበሩ ምግብ የሚያዘጋጅ ሰው አልነበረም።

«አንድ ነገር እናድርግ - ፀሃይዋ ልትጠልቅ ተቃርባለች። ሁላችንም ረሃብ እየተሰማን ነው። ቀኑን ሙሉ ተራራውን ስንወጣ ነው የዋልነው. . . የሚያደክም ቢሆንም ደስ የሚል ነገር ነው» አልኩ።

«ፀሃይዋ ሳትጠልቅ የቀሩንን ነገሮች ብናይ ይሻላል» አሉኝ እነሱ።

እኔ ብቻ ነበርኩ በምሽት የመብላት ልምድ ያልነበረኝ። እነሱ በሙሉ በምሽት መመገብ ስለሚችሉ ይህ ነገር አላሳሰባቸውም። ከምሽቱ ሶስት ወይም አራት ሰዓት ሲሆን እጅ የሚያስቆረጥም ምግብ ሰሩ። ቀኑን ሙሉ ያደረግነው ጉዞ ረሃብ ስለሰቀቀብኝ ምን ማድረግ እንዳለብኝ እያሰብኩ አመነታሁ። ምን ላድርግ? ከዚያም «ትልቅ ችግር አለብኝ። በምሽት በልቼ አላውቅም። እኔ ያለሁበት ሃይማኖት በምሽት የተመገበ ሰው ወደ ሲኦል እንደሚወርድ ይናገራል። ለአንድ ምሽት ምግብ ብዬ ሲኦል መውረድ አልፈልግም። እንዲህ ርቦኝ መተኛት ደግሞ አልችልም። በዚያ ላይ የምግባችሁ መዓዛ ልዩ ነው!» አልኳቸው።

«ለቤተሰቦችህም ሆነ ለማንም አንነግርብህም። በምሽት መመገብህን ማንም አያውቅም» በማለት ሊያሳምኑኝ ሞከሩ።

«ችግሩ ይህ አይደለም» አልኳቸው። «ፍራቻዬ ቤተሰቦቼ ወይም ሌሎች ያውቁብኛል የሚል አይደለም። መላው ዓለም ቢሰማ ችግሬ



t.me/OLDBOOKSPDF

አይደለም። ይሁንና ከዚህ ሁሉ ዓመት በኋላ ራሴን ማታለል አልችልም።»

ነገር ግን ሳያሳምኑኝ አልቀሩም - እኔም ማመን ነበረብኝ። በመጨረሻ በሳሁና እንቅልፍ ሳይወስደኝ አደረ። ሌሊቱን በሙሉ አስመለስኩ።

ሌላ ያስመለሰ የለም። ከእኔ ጋር የነበሩት ሃያውም ጓደኞቼ ደከሟቸው ስለነበር ምግባቸውን በልተው እንቀላፍተዋል፤ በሰላም ተኝተዋል። እኔ ብቻ ሌሊቱን ሙሉ ንቁ ሆኜ ሳስመልስ ቆየሁ። ምግቡ ከውስጤ ጨርሶ ካልወጣ በቀር ማንቀላፋት አልችልም። ከንጋቱ አስራ አንድ ሰዓት አካባቢ ነበር የተኛሁት።

ይህም በምሽት መመገብ አደገኛ ሳይሆን አይቀርም ብዬ እንዳስብ አደረገኝ። አንድ ጊዜ ብበላ ሌሊቱን ሙሉ ስሰቃይ አደርኩ! ህይወታቸውን በሙሉ በምሽት ሲመገቡ የነበሩት ግን. . .

ምናልባት ወደ ሲኦል ይወርዳሉ የተባለው ትክክል ሳይሆን አይቀርም። ግን እኮ ዓለም በሙሉ በምሽት ይመገባል። የእኔ እምነት ትክክል ከሆነ መላው ዓለም ሲኦል ይገባል ማለት ነው። እነዚህ ሃያ ወዳጆቼ የሰላም እንቅልፍ ተኝተዋል - ሌላ ያስመለሰ ሰው ስለሌለ ምግቡ ወይም ሰዎቹ ምንም ችግር የለባቸውም ማለት ነው። ችግሩ ያለው በውስጤ ካለው እምነት ነው፤ የተሳሳተ ሃሳብ (እምነት) ይዤ ነበር ያደግኩት።

አንድ ነገር ከተቀበላችሁ በውስጣችሁ «ይህን አድርግ፣ ይህ አታድርግ» የሚል ሃሰተኛ ህሊና ትፈጥራላችሁ። ይህ ደግሞ በጥልቀት ማሰብ አይደለም።

በጥልቅ የሚያስብ ምን ማድረግ እንዳለበት እና ምን ማድረግ እንደሌለበት ያውቃል። የምርጫ ጥያቄ አይነሳም። የጥልቀት እሳቤ፣ ምርጫ የሌለበት ሁኔታ ነው - ዝም ብላችሁ እንዲሁ ትክክለኛው የቱ እንደሆነ ታውቃላችሁ።

ከህሊና ጋር አልተፈጠራችሁም። ህሊና የተፈጠረው በካይማኖቶች ነው። እነሱ ናቸው ህሊናን በመፍጠር የሰውን ልጅ


t.me/OLDBOOKSPDF

የበዘበዙት:: <ህሊና> የሚለው ቃል ካለፈው ጊዜ እና ከሃሰተኛ ሃሳቦች ጋር የተሳሰረ ነውና እንተወው::

ከዚያ ይልቅ <በጥልቀት ማሰብ> የሚለውን ቃል መጠቀም ይኖርባችኋል:: በጥልቀት ስታስቡ ፍፁም የተረጋጋችሁ ትሆናላችሁ፣ አብሯችሁ የሚወለድ አይደለም::

አዎ፣ በጥልቀት ካሰባችሁ አዲስ ህይወት ይኖራችኋል፤ ዳግም ትወለዳላችሁ:: ኢየሱስም ኒቆዲሞስን «ዳግመኛ ካልተወለድክ በቀር አታውቀኝም» ያለው ለዚህ ነው::

ሌላ ጊዜ ካልተወለድክ ማለቱ አይደለም:: ራስህን መቀየር፣ በጥልቀት ማሰብ አሰብህ ማለቱ እንጂ:: «ዳግመኛ ካልተወለድክ በቀር አታውቀኝም::»

በጥልቀት ካሰባችሁ፣ ከተረጋጋችሁ እና ከተመሰጣችሁ መላው የሰው ልጅ አንድ (እኩል) ነው ብላችሁ አታስቡም:: ይህን በልምድ ነው ያገኛችሁት:: አብሮ የሚኖረው በወንድማማችነት ብቻ ሳይሆን በእህትማማችነትም ነው! ይሄ ሁሉ ግን እርባና ቢስ ነው፤ ይህን መሰረታዊ መብት ነው ብሎ መደንገጉ አስፈላጊ አይደለም::

* * *

አንቀፅ ሁለት:- እያንዳንዱ ሰው በዚህ ድንጋጌ ውስጥ የተካተቱትን መብቶች እና ነፃነቶች በሙሉ ያለምንም የዘር፣ የፆታ፣ የቀለም፣ የቋንቋ፣ የሃይማኖት፣ የፖለቲካ ወይም የሌላ አስተሳሰብ፣ የሃገር ወይም የማህበራዊ እርከን፣ የሃብት፣ የውልደት ወይም የሌላ ሁኔታ ልዩነት የማግኘት መብት አለው::

ይህ ሁሉ የማይረባ ነው::

ወደ አሜሪካ ለመጀመሪያ ጊዜ ስገባ በመጀመሪያ የቀረበልኝ ጥያቄ በህግና በመንግስት የማላምን እንዳልሆንኩ እንድምል ነበር:: በህግና መንግስት የማላምን ከሆነ ወደ አሜሪካ መግባት አልችልም:: ይህ አይነቱ እምነት የፖለቲካ አስተሳሰብ ነው:: እኔ ደግሞ እነዚህ ሰዎች ይህን



t.me/OLDBOOKSPDF

አይነቱን ድንጋጤ ሲያወጡ ልታገሳቸው አልችልም። «በተግባር የምታውሏቸው መቼ ነው?» ብሎ የሚጠይቃቸው ማነው?

በየቦታው፣ በተለያዩ ሃገራት፣ በተለያየ ሁኔታ መድልዎ አለና።

የሰው ልጅ በእነዚህ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ላይ አንድ ነገር ማድረግ ይኖርበታል። እነሱ ትልቅ አገልግሎት እየሰጡ እንደሆነ የሚያስቡ ናቸውና።

ህንድ ውስጥ ለምሳሌ ሴቶች ከወንዶች ጋር አንድ ዓይነት ስራ እየሰሩ የሚከፈላቸው ግን አነስተኛ ነው። በዚህ ድንጋጤ ውስጥም ለተመሳሳይ ሥራ ሰራተኛው ወንድም ሆነ ሴት፣ ጥቁርም ሆነ ነጭ ተመሳሳይ ክፍያ ማግኘት እንዳለባቸው ይገልፃል። ይህ ግን እውነት አይደለም።

አሜሪካ ውስጥ በሰድስት እስር ቤቶች ታስሬያለሁ። በእነዛ ሁሉ እስር ቤቶች አንድም ነጭ እስረኛ አላጋጠመኝም። በእነዚያ ስድስት የፌዴራሉ ወህኒ ቤቶች - በእያንዳንዱ እስር ቤት ከስድስት መቶ እስከ ሰባት መቶ ሰው የሚታጐርባቸው መቀመቆች ውስጥ. . . ያሉት እስረኞች በሙሉ ጥቁሮች ናቸው። ታዲያ እንዴት ነው ልዩነት የለም የሚባለው? በነጮች ሃገር እስረኞቹ በሙሉ ጥቁሮች ናቸው።

ሁኔታው ይህ ብቻ አልነበረም። ሁሉም ይወዱኝ ነበርና ጥቂቶቹን ጥቁር እስረኞች ጠየቅኳቸው። ለአምስት ዓመታት በየዕለቱ በቴሌቪዥን ያዩኝ ስለነበር ራሳቸውም እነዚያን ጥያቄዎች ሲጠይቁ ነበር። መፃህፍቶቼን አንብበዋቸዋል። ቢያንስ አንድ ቀን አብሬያቸው በእስር ቤት ቆይቻለሁ - ያችን ቀን መቼም አይረሷትም።

«ምን ወንጀል ሰርታችሁ ነው?» በማለት ጠይቄያቸው ነበር።

«እነዚህ ሁሉ ሰዎች ምንም አይነት ወንጀል አልፈፀሙም። ሁላችንም እንደ አንተ ያለምንም የእስር ማዘዣ ነው የታሰርነው። በየዕለቱ <ነገ፣ በሚቀጥለው ሳምንት ፍርድ ቤት ትቀርባላችሁ> ይሉናል። ያቺ ነገ ግን መቼም የምትመጣ አልሆነችም» አሉና መለሱልኝ።


t.me/OLDBOOKSPDF

ከእስረኞቹ መሃል አንዱ ፍርድ ቤት ሳይቀርብ ለዘጠኝ ወራት ያህል እንደታሰረ ነግሮኛል። ይህ ድንጋጌ ግን ማንም ሰው ያለ እስር ማዘዣ መያዝ እንደሌለበት፣ ወንጀለኛ ካልሆነ በቀር ወህኒ ቤት መቀመጥ እንደሌለበት ይደነግጋል። ንፁህነት ምንም ማስረጃ አያስፈልገውም፤ አንድ ሰው ወንጀለኛ መሆኑ ከተረጋገጠ ብቻ ነው እስር ቤት መቀመጥ ያለበት። አለበለዚያ ወደ ወህኒ ሊወርድ አይገባውም። ነገር ግን ወጣቶች ያለ ምንም ፍርድ ለስድስት፣ ለስምንት፣ ለዘጠኝ ወር በእስር ቤት ይቆያሉ።

በኋላ በእስር የመቆየታቸው ሚስጥር ተገለጠልኝ። ወጣቶች እና ለውጥ ፈላጊ አብዮተኞች ስለነበሩ ነው የታሰሩት። ጥቁሮች እኩል መብት እንዲያገኙ ስለሚከራከሩ ነው። ይህ ነው ወንጀላቸው። ፍርድ ቤት ቢሄዱ ነፃ ስለሚሆኑ ወደዚያ አይወስዱም። ስለዚህ ዝም ብለው ወህኒ ያቆይዋቸዋል። የዩ.ኤስ መንግስት በዚህ በኩል ወንጀለኛ ነው።

ባየሁዋቸው ስድስት እስር ቤቶች ብቻ ሶስት ወይም አራት ሺ የሚሆኑ ወጣት ጥቁሮችን አግኝቻለሁ። ምናልባትም በሺ የሚቆጠሩ እስረኞች በሌሎች ወህኒ ቤቶች ይኖራሉ። «ከመላው ዓለም የሚመጣ ጫና ስላለ ነው ወደ እስር ያመጡዎት። ዓለም ፀጥ ቢልና የዜና ሚዲያዎች፣ መንግስት በንፁሃን ላይ ወንጀል እንደፈፀመ ባያስራጩ ኖሮ. . . መላው የዜና ሚዲያ ትኩረቱን በእርስዎ ላይ ስላደረገ ጫናው በዝቶባቸው ነው ለፍርድ ያቀረቡዎት። ሳይወዱ በግዳቸው ነው ፍርድ ቤት የወሰድዎት» ብለውኛ ነበር።

ይህ ሁሉ ሆኖ እንኳን እኔን ፍርድ ቤት ለመውሰድ አስራ ሁለት ቀናት ፈጅቶባቸዋል። ይህ ሰብአዊ መብትን ክፉኛ የሚፃረር ነው። በእስር ቤቱና በፍርድ ቤቱ መካከል ያለው ርቀት የአምስት ሰዓት በረራ ብቻ የሚፈጅ ነበር። የራሴም አውሮፕላን ነበር። «የራሳችሁን አብራሪዎች፣ የራሳችሁን ሰራተኞች በመጠቀም በግል አውሮፕላኔ ወደ ፍርድ ቤት ልትወስዱኝ ትችላላችሁ። እኔን እዚህ በማቆየት ምን ትጠቀማላችሁ?» በማለት ሃሳብ ሰጥቼያቸው ነበር።



t.me/OLDBOOKSPDF

በራሳቸው አውሮፕላን ብቻ ነው ሊወስዱኝ ፈቃደኛ የሆኑት፡፡ «ዛሬ አውሮፕላኑ ኣልመጣም. . . አውሮፕላኑ ችግር ገጥሞታል. . . አብራሪው ታሟል. . .» ሰበባቸው ብዙ ነበር፡፡ አንድ አውሮፕላን ብቻ ያላቸው ይመስላሉ፡፡ አንድ የአምስት ሰዓት ጉዞ ለማድረግ አስራ ሁለት ቀናት ወሰደባቸው፡፡ ሌሎቹን እስረኞች ስመለከት ግን «አስራ ሁለት ቀናት ብቻ. . . በፍጥነት ነው ለፍርድ ያቀረቡኝ» ነበር ያልኩት፡፡

እያንዳንዱ መንግስት ህገ - ወጥ እና ሰብአዊ መብት የሚፃረር ነገርን በሙሉ ይፈፅማል፡፡ እነዚሁ የመንግስት ሹማምንት ደግሞ ምንም ሳያፍሩ (ምናልባት ምን እያደረጉ እንደሆነ አይታወቃቸው ይሆናል) ድንጋጌውን ይቀበላሉ፡፡ አይናቸውን በጨው አጥበው ይዋሻሉ - ነጭ ውሸት!

* * *

አንቀፅ ሶስት፡- እያንዳንዱ ሰው በህይወት የመቆየት፣ ነፃ የመሆን፣ ደህንነቱ የመጠበቅ መብት አለው፡፡

በዚህ አንቀፅ ውስጥ አስፈላጊ የሆነው ሞት ግን አልተጠቀሰም፡፡ ውልደቱ በእጃችን ያለ ነገር አይደለም - ያለ ፍላጐታችን ነው የተወለድነው - በእጃችን ያለው ሞት ብቻ ነው፡፡ እናንተም ምርጫ አላችሁ፡፡ ያለ ፍላጐታችሁ ወይም በፈቃዳችሁ፣ ከስብዕና ክብራችሁ ጋር መሞት - ለሞት እድል ሳትሰጡ ራሳችሁ ይህን ማድረግ፡፡

ሁሉም ሃይማኖቶች እና የፖለቲካ ፓርቲዎች ግን ሞትን ወደዚያ ገለል እያደረጉት ነው - ምክንያቱም እንዲያ ካላደረጉ በራሳቸው ላይ ችግር ይፈጥራሉ፡፡ ሁሉም ነገር መፅናኛ ነው፤ <ህይወት> - ግን ምን አይነት ህይወት?

ባለፈው ዓመት፣ ከስድስት ወራት በፊት አውሮፓ ውስጥ በዓለም አቀፉ ገበያ ላይ ቅቤ እና ሌሎች የምግብ አይነቶች ተትረፍርፈው ነበር፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ በየዕለቱ አንድ ሺ ሰው እየረገፈ ነበር፡፡ አውሮፓውያኑ ትርፍ ምግብ ቢኖራቸውም ለኢትዮጵያ


t.me/OLDBOOKSPDF

አይሰጡም:: ያ ትርፍ ምግብ ወደ ውቅያኖስ ይወረወራል:: ምግቡን ወደ ባህር በመወርወር ሁለት ቢሊዮን ዶላር ያህል ይባክናል - ይህ የምግቡ ዋጋ ሳይሆን ምግቡን ለማጓጓዝና ባህር ውስጥ ለመጨመር የሚወጣው የሰራተኛ ጉልበት ክፍያ ነው:: ይህን የሚያደርጉት በየስድስት ወሩ ነው:: በየመንፈቀ - ዓመቱ ምርት ስለሚተርፍ ተጨማሪ መጋዘን መገንባት ሊያስፈልግ ነው:: አዲሱስ ምርት ምን ይደረግ? ግን ለኢትዮጵያ አይሰጣትም::

ህንድ ውስጥ ሃምሳ በመቶ የሚሆነው ህዝብ ማግኘት ከሚገባው የህክምና ደረጃ በታች ነው የሚኖረው:: ሃያ አምስት በመቶ የሚሆነው ህዝብ ደግሞ ይራባል:: ሃምሳ በመቶ የሚሆነው የገጠሩ ነዋሪ በቀን አንዴ ነው የሚመገበው - የሚመገበው ስላችሁ የታጅ መሃልን ሆቴል እንዳታስቡ:: አንድ ዳቦ፣ ጨው፣ ትንሽ የማንጎ ወይም የሌላ ፍራፍሬ ጭማቂ ማለቴ ነው - በቃ:: ይህ ደግሞ ምግብ አይባልም::

ዓለም አንድ ካልሆነች በቀር እያንዳንዱን ሰው በበቂ ሁኔታ መመገብ አይቻልም:: ታዲያ የመኖር መብት ምን ማለት ነው? ይህ የሚነሳው ሰዎች ስላሉ ብቻ ነው:: ሰዎች ግን እየሞቱ ነው፣ ሞተዋልም::

አሜሪካም ይህንኑ እየፈፀመች ነው፣ የስታሊን ራሺያም ተመሳሳይ ነገር እያደረገች ነው:: አውሮፓ ውስጥ ብቻ የሚፈፀም አይደለም::

አሜሪካ በየሶስት ወሩ በቢሊየን ዶላሮች የሚገመት ትርፍ ምርት ወደ ባህር ትጨምራለች:: በስታሊን ዘመን ሩሲያም ለባቡሮቿ ነዳጅ ከከሰል ይልቅ ስንዴን ትጠቀም ነበር:: በወቅቱ ስንዴ ከከሰል ይልቅ ርካሽ ነበር::

ሰዎች እየሞቱ ነው - አስፈላጊ ጉዳይ አይደለም::
ሰዎች እየተራቡ ነው - አስፈላጊ ጉዳይ አይደለም::

* * *



t.me/OLDBOOKSPDF

እንቀፅ ዘጠኝ፡- ማንም ሰው ቢሆን በዘፈቀደ መያዝ፣ መታሰር ወይም መጋዝ የለበትም፡፡

እኔም ህያው ምስክር ነኝና ይህ ድንጋጌ በየትኛውም መንግስት እንደማይተገበር አውቃለሁ - በተለይ ደግሞ የድንጋጌው የበላይ በሆነችው አሜሪካ፡፡

ያለ አንዳች ምክንያት እንግሊዝ ውስጥ ታስሬ አውቃለሁ፡፡ አብራሪዎቼ ስለደከማቸውና እረፍት ስለፈለጉ በአንደኛ ደረጃ መዝናኛ ውስጥ ለስድስት ሰዓታት ያህል ቆይቼ ነበር፡፡ በእነሱ ህግ መሰረት ከአስራ ሁለት ሰዓታት በላይ መብረር ክልክል ስለነበር መቆም ነበረብን፡፡

«ችግር ሊፈጥሩ ይችላሉ፤ የመጀመሪያ ደረጃ መዝናኛው ለመጀመሪያ ደረጃ መንገደኞች የተዘጋጀ ስለሆነ እርስዎ ደግሞ መንገደኛ አይደሉም ሊሉ ይችላሉ፡፡ እርስዎ የግል አውሮፕላን አለዎት፡፡ ታዲያ በየትኛው የበረራ ደረጃ ውስጥ ሊመደቡ ነው?» ብለውኝ ነበር አብራሪዎቹ፡፡

ስለዚህም ለጠዋቱ በረራ ሁለት የአንደኛ ደረጃ ትኬቶች እንዲገዙልኝ ነገርኳቸው፡፡ «የምንጓዘው በራሳችን አውሮፕላን ቢሆንም ለማንኛውም ትኬቶቹን ግዟቸው» አልኳቸው፡፡ የገመትነው አልቀረም፣ ችግሩ ተፈጠረ፡፡ እኛም ትኬቶቹን መዝዘን አሳየናቸው!

መኮንኑ ይህን ሲያይ ደነገጠ፡፡ እኛ ትኬት ይዘናል ብሎ አልጠረጠረም ነበር፡፡ «አሁንስ ምን ታስባለህ?» ስል ጠየቅኩት፡፡

«እኔ ምንም ማድረግ አልችልም፡፡ የበላዮቼን መጠየቅ ይኖርብኛል!» ብሎ መለሰልኝ፡፡ የበላይ አለቃው ማነው? ራሷ ጠቅላይ ሚኒስትሯ ሳይሆኑ አይቀሩም፡፡ ሰውየው ከሄደ በኋላ ፋይሉን ተመለከትኩት፡፡ ጠረጴዛው ላይ ትቶት ነበር፡፡ ትዕዛዙን ያስተላለፈው መንግስት ነበር፡፡

ወደ እንግሊዝ ለመግባት የመግቢያ ቪዛ አልጠየቅኩም ነበር፡፡ በዚህ መጨነቅም አይገባቸውም ነበር፡፡ ለማንኛውም መግባት ብፈልግ እንኳን እንዳልገባ ፓርላማው ውሳኔ አሳልፏል፡፡

ሰውየው ተመልሶ በመጣ ጊዜ፣ «መላው የእንግሊዝ ህዝብ ወደ ሀገሩ እንድገባ የሚፈልግ ቢሆንም ወደ እንግሊዝ መግባት አልፈልግም፡፡


t.me/OLDBOOKSPDF

እንግሊዝ ውስጥ ምንም ጉዳይ የለኝም፡፡ መዝናኛው ውስጥ ለማረፍ ፈልጌ ነው የመጣሁት፡፡ ከመዝናኛው ተነስቶ ወደ ሃገሪቱ መግባት ደግሞ አይቻልም፡፡ ዝግ ነው፣ አየር ማረፊያው ውስጥ ብቻ ነው ማረፍ የሚቻለው፡፡ አየር ማረፊያው ደግሞ አለማቀፍ ነው! እንግሊዝ አይደለም» አልኩት፡፡

«እኔ ምን ላድርግ? አለቃዬ ነው ያዘዘኝ፡፡ <ማረፊያ ቤት አቆዩት፣ ከዚህ ሌላ ምንም አማራጭ የለም፡፡ ሰውየው ለስድስት ሰዓታት በእስር ይቆይ> ያለው አለቃዬ ነው» አለኝ፡፡

እናም ያለ ምንም ምክንያት ለስድስት ሰዓታት በእስር ቆየሁ፡፡ ምንም ወንጀል አልፈፀምኩም፣ ትኬት ይዣለሁ፣ አውሮፕላን አለኝ፣ እረፍት ማድረግ ፈልጌያለሁ፡፡ ይሁን እንጂ ፖለቲከኞቹን ያለማቋረጥ ሳጋልጣቸው ስለቆየሁ በመዝናኛው ውስጥ ለስድስት ሰዓታት በመተኛቴ የእንግሊዝን ስብዕና እና ልማድ እንዳልነካ ፈርተው ነበር፡፡ በመዝናኛው ውስጥ በመቀመጥ ብቻ ወጣቱን ላበላሽ እችላለሁ!

እነዚህ ሰዎች የሰብአዊ ፍጡራን አፍቃሪዎች አይደሉም፡፡
ለሰው ልጅ ስብዕናም ምንም ክብር የላቸውም፡፡

* * *

አንቀፅ አስራ ስምንት፡- ማንኛውም ሰው ነፃ ሃሳብ፣ ህሊና እና ሃይማኖት የማራመድ መብት አለው፤ ይህ መብት ሃይማኖትን ወይም እምነትን የመቀየር እና በግልም ሆነ ከሌሎች ጋር በመሰባሰብ በአደባባይ ወይም በድብቅ ሃይማኖቱን ወይም እምነቱን የማስተማር፣ የመተግባር፣ የማምለክ እና የመካፈል መብትን የሚያካትት ነው፡፡

«ሃሳብን የመግለፅ መብት» - እኔ ሃሳቤን ከመግለፅ በቀር ምንም አላደረግኩም፡፡ ይህ ሰብአዊ መብት ከሆነ የትኛውም መንግስት ባልተቃወመኝ ነበር፡፡

በማንኛውም ፖለቲካ ውስጥ ካለመሳተፌ በተጨማሪ የስልጣንም ፍላጎት የለኝም፡፡ እነኚህ እውር ፖለቲከኞች ማየት ያልቻሉትን በግልፅ ስላየሁ እና ይህንንም በመናገሬ ብቻ ነው ይህ ሁሉ እንግልት፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ፍርሃቱን ምን አመጣው?

ሊቀ - ጳጳሱ የሃይማኖቶች አለማቀፋዊ ኮንፈረንስ እንዲጠራ አዝዘዋል። ዋና ቀሳውስት እና የሃይማኖት መሪዎችም ተጋብዘዋል።

በኢጣሊያ የሚገኙ ወዳጆቹ እንዲህ ብለው ፃፉልኝ:- «ጳጳሱን አጥብቀን እየጠየቅናቸው ነው - ፀሃፊው በአንተ በመሳባቸው ግብዣውን ሊሰጡህ ፈቃደኛ ናቸው። ሊቀ - ጳጳሱ ግን መምጣትህን ይቃወማሉ።»

እርግጥ ነው የኢጣሊያ መንግስት የሶስት ሳምንት የቱሪስት ቪዛ በመስጠት ወይም ባለመስጠት ላይ ሲያስብ ስምንት ወራት አልፈዋል። የዚህ ሁሉ መዘግየት ተጠያቂው ጳጳሱ ናቸው።

ታዲያ እነዚህ ሰዎች እንዲህ አይነት ተግባር እየፈፀሙ «ሃሳብን በነፃ የመግለፅ መብትን እንደግፋለን» ይላሉ። ማንም ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትን የሚደግፍ የለም። ከደገፉትኋቸው ብቻ ይቀበሏችኋል።

«ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት. . .» ሊቀ - ጳጳሱ መፃህፍቶቼን በጥቁር መዝገብ ላይ ስላሰፈሯቸው ማንም ካቶሊክ አያነባቸውም።

ጥቁር መዝገብ አላቸው። በመካከለኛው ዘመን አንድ መፅሃፍ በጥቁር መዝገብ ላይ ከሰፈረ በመላው አውሮፓ ይቃጠል ነበር። በአሁኑ ዘመን ማቃጠል ባይቻልም ማንም እንዳያነበው መከልከል ይቻላል።

ካቶሊኮች ደግሞ ጥቂት የሚባሉ አይደሉም - በዓለም ላይ ሰባት መቶ ሚሊየን የሚሆኑ ተከታዮች አሉ።

ይሁንና እነዚህ ሰዎች እንዳያነቡት መከልከል ማለት ሽንፈትን መቀበል፣ መልስ ማጣት ነው።

ታዲያ ያን ሁሉ የሰብአዊ መብት ዝባዝንኬ ምን አመጣው?

* * *

እንቀፅ አስራ ዘጠኝ:- እያንዳንዱ ሰው ሃሳቡን በነፃነት የመግለፅ መብት አለው፣ ይህ መብት ሃሳብን ያለማንም ጣልቃ - ገብነት መያዝን፣



t.me/OLDBOOKSPDF

መረጃዎችንና ሃሳቦችን ያለ ምንም ገደብ በማንኛውም የማስተላለፊያ ዘዴ መፈለግን፣ መቀበልን እና መስጠትን ያጠቃልላል::

ይህ ትክክል አይደለም:: የህንድ ፓርላማ የህንድ ጋዜጠኞች እና የዜና ማሰራጫ ሚዲያዎች ለእኔ ሃሳቦች ቦታ እንዳይሰጡ አዝዟል:: የአሜሪካ መንግስት ከምዕራብ የመጡ የሚዲያ ሰዎች ቃለ - ምልልስ እንዳያደርጉልኝ በህንድ መንግስት ላይ ተፅዕኖውን አሳርፏል::

የአሜሪካ መንግስት ሁለት ነገሮችን አድርጓል:: ለአውሮፓ እና ለአውስትራሊያ መንግስታት እኔ ወደ ሃገራቸው እንዳልገባ እንዲከለክሉ እና በተያዝኩበት ሃገር ተይዤ ወደ ህንድ እንድላክ ነግሯቸዋል:: እናም ሁሉም የአውሮፓ ሃገራት በሃገራቸው ለሰባት ሳምንት እንኳን በቱሪስትነት እንዳልቆይ ውሳኔ ላይ ደርሰዋል::

አሜሪካ፣ እኔ ወደ ሌላ ነገር እንዳልገባ እና እኔን ማግኘት የሚፈልጉ ሰዎችን ወደ ህንድ እንዳይገቡ ትፈልጋለች:: ይህን ሲያደርጉ የነፃነት ፈላጊዎቹን እንቅስቃሴ የገቱ ይመስላቸዋል::

ይህ በእውነት ያለ ነው:: በቃላት ሲቀመጡ. . . ውብ እና ታላቅ መፈክሮች ይመስላሉ፣ ነገር ግን ባዶ ናቸው::

* * *

አንቀፅ ሃያ ሁለት:- እያንዳንዱ ሰው ስብዕናውን በነፃነት የማዳበር መብት አለው::

ስብዕናችሁን በነፃነት ስታዳብሩ እስካሁን አላየሁም:: በመጀመሪያ ደረጃ ይህን የፃፉት ሰዎች ስብዕና የውሸት ሽፋን እንደሆነና እንደማይዳብርም አያውቁም::

እውነታችሁ ተፈልጎ መገኘት ያለበት በግለኝነታችሁ ውስጥ ነው::

እነሱ ግን ስለ ግለኝነት አያወሩም::

አስበውትም ላያውቁ ይችላሉ:: ያላቸው ስብዕና ብቻ በመሆኑ ግለኝነትን ንቁ አላደረጉትም::



t.me/OLDBOOKSPDF

እርግጥ ነው <ስብዕና> የሚለውን ቃል ይፅፉሱ:: <ስብዕና> አስቀያሚ ቃል ነው:: <ጭምብል> ማለት ነው፤ ስርወ - ቃሉ <ጭምብል> ነው::

እኛ ደግሞ፣ ሰዎች ጭምብል እንዲለብሱ አንፈልግም:: ሰዎች በራሳቸው ተፈጥሯዊና ምሉዕ መሆን አለባቸው::

* * *

ስንቀፅ ሃያ ስምስት:- ሁሱም ህፃናት በህጋዊ ጋብቻ የተገኙም ይሁኑ ወይም ስይሁኑ - ስንድ ዓይነት ማህበራዊ ክስሳ ሲደረግሳቸው ይገባል::

ይህ እውነት ቢሆን ጋብቻ ባልኖረ ነበር! በትዳር እና ከትዳር ውጪ የሚገኙ ልጆች አንድ አይነት መብት ቢኖራቸው ኖሮ ትዳር ትርጉም ባጣ ነበር::

የጋብቻ ትርጉም ምንድነው? እነሱ ይህን ለመመለስ ድፍረት የላቸውም::

ይህም እውነት አይደለም፤ ምክንያቱም ከጋብቻ ውጪ የሚወለዱ ህፃናት አይከበሩም:: በየአቅጣጫው ተቃውሞ ይደርስባቸዋል::

ለዚህ የማይረባ ነገር ብዙ ማብራሪያ ለመስጠት የተገደድኩት፣ ዓለምን የሚቆጣጠሩት እነዚህ ሰዎች በመሆናቸውና ጭንቅላታቸው መወቀር ስላለበት ነው::

የሰውን ልጅ በባርነት የያዙት እነሱ ናቸው - ከአሁን ወዲያ ግን በዚህ መልኩ መቀጠል የለብንም::

ድንጋጌ የማውጣት መብት የላቸውም::

እኛ ነን ድንጋጌ የማውጣት መብት ያለን::

እኛ ህዝቦች ነንና::

የእኔን ህዝቦች (ተከታዮቼን) በተመለከተ እኛ በነፃነት፣ በፍቅር፣ በመተሳሰብ ነው የምንኖረው:: በግለኝነታችን በልፅገን የሚጋብዘንና የሚቀበለንን ለመርዳት ዝግጁ ነን::

ብቸኛው መሰረታዊ መብት አምላክ የመሆን መብት ነው::



t.me/OLDBOOKSPDF

**በውስጣችሁ አምላክን ካላገኛችሁት በቀር ሁሉም ነገር አሰማዊ ይሆናል፡፡ በውስጣችሁ አምላክነትን ስትጐናጸፉ ሁሉም ነገር በየተራ ይመጣል፣ ይከሰታል፡፡**



t.me/OLDBOOKSPDF

# አራት ነጥቡ ፈፅሞ አይመጣም

# 3

ታህሳስ 27 ቀን 1986፣ ቦምቤ



t.me/OLDBOOKSPDF

# በዓለም የሰዎችን ህይወት የለወጡ ሁለት ዓይነት የአስተሳሰብ ተፅዕኖዎች አሉ

**ተወዳጁ ባግዋን፡-**

**የጀርመናዊውን ፈላስፋ የፍሬዲሪክ ኒቼን ፅሑፎችን ባነበብኩ እና ዘና የማለት ስሜት በተሰማኝ ቁጥር ህይወት ካለው መንፈስ ጋር ተገናኝቼ የምንነጋገር ይመስለኛል፡፡ እሱ ስለሞተም፣ በህይወት ያለ የቅርብ ወዳጅ ነው፡፡ ሁሉም ታላላቅ መንፈሶች በህይወት ሆነውም ሆነ ሞተው ጥልቀት ያለው ግንኙነት መፍጠራቸው የሚገርም አይደለም፡፡ አንተ ጋ ግን ሁሉም ሰዎች እና ቃላት ጠፍተው ንቁ እና ጥበብ የተገለጠለት ሰው እሆናለሁ፡፡ ከአንተ ጋር እንደዚህ መሆኔን እጅግ በጣም እወደዋለሁ፡፡ ሚስጥርህ ምንድን ነው?**

የእኔ ሚስጥር በጣም ቀላል ነው፡፡ እኔ ስም የለኝም፣ ቅርፅም የለኝም፡፡ ምንም አይነት መታወቂያ ወይም መለያ (ማንነት) የለኝም፡፡ እኔ ከሁሉም ጋር አንድ ነኝ፡፡ ስለዚህ ስለ እኔ ባሰብከበት ቅፅበት በህሊናህ መስታወት ውስጥ የምታየው ሰው አይኖርም፡፡ ከዛ ይልቅ ባዶ ሰማይ ታያለህ፡፡

ፍሬዴሪክ ኒቼ ወይም ሌሎች ፈላስፎች እጅግ በጣም ታላላቅ ሰዎች ናቸው፡፡ ነገር ግን ከሁሉም ጋር አልተዋሀዱም፡፡ እንደውም በተቃራኒው በከፍተኛ ደረጃ ስለራሳቸው ብቻ የሚያስቡ ናቸው - በተለይ ኒቼ፡፡ እኔ ራሴ ኒቼን በጣም እወደዋለሁ፡፡ ነገሮችን በከፍተኛ ደረጃ የመገንዘብ ችሎታ አለው፡፡ በአዕምሮው ታላቅ እውነት የተገለፀለት ሰው ነው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

በመላው ዓለም ችላ ከተባሉ ወይም ከተጠሉ ፈላስፎች እሱ ዋነኛው ነው:: የዚህም ምክንያት ፍርሃት ሊሆን ይችላል:: አንድ ጊዜ ኒቼን በጥልቀት ከተረዳችሁት የቀድሞው እናንተነታችሁ አይኖርም:: ኒቼ ይለውጣችኋል:: ሀሳቦቹ ምክንያታዊ ናቸው:: የማስተዋል ክህሎቶቹ በዓለም ላይ ተስተካካይ የላቸውም::

ቢሆንም ግን በተመስጦ የሚያስብ ሰው አልነበረም::

እንድታስታውሱ የምፈልገው የተሰየ ሀሳብ አለ:: በዓለም ላይ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን ህይወት የለወጡ ሁለት አይነት የአስተሳሰብ ተፅዕኖዎች አሉ:: አንደኛው አዕምሮ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳርፈው ነው:: ሁሉም ፈላስፎች እና የማሰብ ችሎታ ያላቸው እዚህ ውስጥ ይካተታሉ:: አዕምሮን በተመለከተ ታላቅ ችሎታ አላቸው:: ለበርካታ ሺ አመታት በሚሊየን የሚቆጠሩ ሰዎችን ያስደመሙ ሲሆን በአሁኑ ዘመንም ተቀባይነት አላቸው::

በሌላኛው ወገንም እንደ እነ ጉተማ ቡድሀ፣ ቦድሂድሀርማ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ላኦ ትዙ . . . አሉ:: እነኚህ ፈላስፎች አይደሉም:: የሚናገሩት ንግግር ከአዕምሮ የሚመነጭ አይደለም:: ከአዕምሮ በላይ ነው:: አዕምሮን ወደ ጐን ገሸሽ አድርገውታል:: እነሱን ለመረዳት ጥሩ የአዕምሮ ችሎታ መኖር ብቻ በቂ አይደለም:: እነሱን ለመረዳት እነሱ በተጓዙበት መንገድ መጓዝ ያስፈልጋል::

አዕምሮ ደግሞ የትም ቦታ አይሄድም::

ሁሉም ፈላስፎች የሚጫወቱት በቃላት ነው:: አንዳንድ ጊዜ በቃላት ውስጥ ድንቅ ውበት፣ ታላቅ ቅኔ እና አመክንዮ (ሎጂክ) መኖሩ አይካድም:: ኒቼ፣ ሄግል፣ ካንት፣ በርትራንድ ራሴል፣ ጀን ፖል ሳርተር፣ ጃስ ፒርስ ወይም ማርቲን ሂዴገር ከፍተኛ የማሰብ ችሎታ አላቸው:: በእነሱ ልትደመሙ ትችላላችሁ፣ ነገር ግን አትለወጡም:: መደመም ደግሞ ባሪያ መሆን ነው:: መለወጥ ከሌለ በቀር ባርነታችሁ የበለጠ በጥልቀት ስር እየሰደደ ይሄዳል::



t.me/OLDBOOKSPDF

ፍሬዴሪክ ኒቼ በህይወት ባይኖርም በመንፈስ እንደሚኖር ተናግረሀል። ይህን ብቻ ሳይሆን እንደምታነጋግረውም ነግረኸኛል። በጥያቄህ ውስጥ ባትገልፀውም እሱም መልስ የሚሰጥህ ይመስለኛል።

ሁለቱም ነገሮች፣ ማለትም ጥያቄው እና መልሱ የሚከናወኑት በአናንተ ነው። እስኪ የፍሬዴሪክ ኒቼን ለእውነት ያለውን ፍልስፍናውን ብቻ ሳይሆን ህይወቱንም ተመልከቱ። ህይወቱ በከፍተኛ ስቃይ የተሞላ ነበር።

የፍሬዴሪክ ኒቼ ህይወት ምን እንደሚመስል ብታውቁ ፈፅሞ እሱን መሆን አትመኙም። በከፍተኛ ደረጃ ራስ ወዳድ ስለነበር ህይወቱን ያለምንም ጓደኛ በብቸኝነት የኖረ ሰው ነው። ከእሱ ጋር ወዳጅነት መመስረት ፈፅሞ የሚቻል አልነበረም። ራሱን የበላይ አድርጐ እናንተን የሚያያችሁ መሬት ላይ እንደሚድህ ህጻን ነው። ይህ ምን አይነት ጓደኝነት ነው? ሌላው ቢቀር እንደ ሰው እንኳን አያያችሁም። የሚያያችሁ ከፊል የሰው ዝርያ እንዳለው ፍጡር ነው። የእሱ አጠቃላይ ፍልስፍና <ልዕለ ሰብ> እያለ የሚጠራውን ትክክለኛ ሰው መፍጠር ላይ ያተኮረ ነው። እሱ ራሱ ግን ተራ እንኳን የሚባል አይነት ሰው አልነበረም። ታዲያ እንዴት ስለ ልዕለ ሰብ (Superman) መናገር ይችላል? መልኩ እጅግ አስቀያሚ ነበር። ይህ እንኳን ይቅር ሊባል ይችላል። ለእሱ ፍቅር ማለት አገዛዝ ስለነበር በህይወቱ ሙሉ ሴት ልጅን ማፍቀር አልቻለም ነበር። የሚፈልገው የሚያፈቅረው ሳይሆን የእሱን ቅኝት ተከትሎ የሚያዜም አሽከር ነበር።

ህይወቱን የሚመለከት ሰው ጥልቅ ፍቅር እንዳሰበት ይሰማዋል። ህይወቱን ሙሉ ያሳለፈው ከእህቱ ጋር በብቸኝነት ነበር። እህቱ የኒቼን ህይወት የሚንከባከብ ሰው የግድ ያስፈልገው ስለነበር ህይወቷን ለእሱ ሰውታለት ነበር። በመጨረሻም አበደ።

ልብ በሉ፣ ማንም በድንገት ተነስቶ አያብድም። እብደት ቀስ እያለ የሚያድግ፣ ደረጃ በደረጃ የሚከሰት ነገር ነው። ትልቅ ደረጃ ላይ የደረሰ ጊዜ በሁሉም ሰው ዘንድ ይታወቃል። ኒቼ ከመጀመሪያው ጀምሮ እብድ ቢሆንም እብደቱ በይፋ አይታወቅም ነበር። በመደበኛ የሰው ልጅ



t.me/OLDBOOKSPDF

የአብደት ደረጃ ውስጥ ነበር:: ያንን መስመር አልፎት የሄደው ግን በአጭር ጊዜ ውስጥ ነበር::

በመጨረሻ አብደቱ ይፋ ሲወጣ ከአንዱ በቀር ሁሉንም ፍልስፍናዎቹን ረሳቸው:: አብዶ እንኳን ያልረሳው ነገር ነበር:: ምን ይሆን? ብላችሁ መጠይቃችሁ አይቀርም:: ያልረሳው ነገር ምን መሰላችሁ? ዘወትር ፊርማ ሲፈርም ስሙን <ፀረ ክርስቶሱ ፍሬዴሪክ ኒቼ> ብሎ መጻፍን ነበር:: ይህ <ፀረ - ክርስቶስ> የሚለው አመለካከቱ አብዶም ቢሆን አብሮት የኖረ ነው::

ከስሙ በፊት <ፀረ ክርስቶስ> ብሎ ሳይፅፍ አንድም ፊርማ ፈርሞ አያውቅም:: የተወለደው ህንድ ቢሆን ኖሮ <ፀረ ጉተማ ቡድሀ> ይሆን ነበር:: ቻይና ቢወለድ ኖሮ <ፀረ ቱዋንግ ዙ> ይሆን ነበር::

ዋናው ነጥብ እነኚህ ስሞች አይደሉም:: ኒቼ ለምን ፀረ ክርስቶስ ሆነ? ምክንያቱም ክርስቶስ ፈላስፋ አልነበረም:: ክርስቶስ ለንግግሮቹ ምንም ምክንያቶችን አያቀርብም:: የሚናገረው በራሱ ስልጣን ነበር:: ውስጡ ስላለው እውነት ይናገራል እንጂ ምንም አይነት ክርክር አያቀርብም:: እንደውም ክርክር የሚያስፈልገው ለውሸት ነው:: ፍርድ ቤቶች ውስጥ ክርክር የምታዩት ለዚህ ነው::

እውነት እርቃኑን ነው:: እናንተን ለማሳመን እውነት መኖሩ በራሱ በቂ ነው:: እውነት በራሱ ተቀባይነት ከሌለው እና በክርክር ላይ የሚመሰረት ከሆነ እውነት አይደለም:: ክርክሮች ሊለወጡ ይችላሉ:: ከእናንተ የበለጠ ማሳመኛ ሃሳብ ያለው ሰው ያጋጠማችሁ ጊዜ ሊለወጡ ይችላሉ::

እዚህ ጋ ኬሻብ ቻንድራ የሚባል ታላቅ የሆነ ምክንያታዊ አስተሳሰብ ያለው (ሎጂክያን) ሰው ትዝ አለኝ:: ምናልባትም በዚህ ባለፈው ክፍለ ዘመን ህንድ ውስጥ የእሱን ያህል የሰላ አዕምሮ ያለው እና እንከን የማይወጣለት ክርክር የሚያቀርብ ሰው አልተፈጠረም:: ራማክሪሽና ከካልካታ ውጪ በሚኖርበት ዘመን ኬሻብ ቻንድራ በካልካታ ይኖር ነበር::


t.me/OLDBOOKSPDF

ኬሻብ ቻንድራ ጥቂት የተማሩ ተከታዮች ቢኖሩትም ሁሉም ግራ ተጋብተው ነበር፡፡ «በሺ የሚቆጠሩ ሰዎች ወደ ኑዛ ደደብ ራማክሪሽና ይሄዳሉ! እሱ መፈረም እንኳን የማይችል መሀይም ነው፡፡ እነኚህ ሰዎች ወደዚህ እብድ የሚሄዱት ለምንድን ነው?» ይሉ ነበር፡፡ በመጨረሻ ኬሻብ ቻንድራ፣ ራማክሪሽናን ሄዶ በአይኑ በብረቱ የመመልከት ፍላጎቱ እያለ መጣ፡፡ በጥቂት የማሳመኛ ክርክሮች ሰውየውን ራመጨረሻ ጊዜ እንደሚያጠፋው አውቋል፡፡

እናም «ከአንተ ጋር መከራከር ስለምፈልግ መቼ ልምጣ?» የሚል መልዕክት ወደ ራማክሪሽና ላከ፡፡

ራማክሪሽና ይህን ሲሰማ «ኬሻብ ሊመጣ ነው? እሱን ሌላ ጊዜ መቅጠር አያስፈልግም፣ ዛሬ መምጣት ይችላል፡፡ ወደ እሱ ሄዳችሁ <ወደ እኔ መጥተህ የፈለከውን ያህል ተከራከር!> በሉት» አለ፡፡

ኬሻብ ቻንድራ አንድ የረሳው ነገር ነበር፡፡

መልዕክቱን (ጥያቄውን) ሲያስተላልፍ ያለው፣ «ከአንተ ጋር መከራከር እፈልጋለሁ» የሚል ነበር፡፡ ሌላው ሰው ዝም ብሎ እያዳመጠ «ተከራከር!» ቢል ይህን ክርክር አይባልም፡፡

አንድን ሰው እንዲከራከራችሁ ማስገደድ አትችሉም፡፡ ኬሻብ ቻንድራ ግን እንደዚህ አይነት ሰው አጋጥሞት ስለማያውቅ ይህን አልተረዳም ነበር፡፡

ራማክሪሽና በቤተ መቅደስ ውስጥ ይኖርባት ወደነበረችው ዳክሺንሽዋር ሄደ፡፡ የኬሻብ ቻንድራ ክርክሮች እንደ ጦር ልብ ላይ ተሰክተው የሚገድሉ ስለነበሩ ደቀመዛሙሮቹ በጣም ፈሩ፡፡ ራማክሪሽና ደግሞ መከራከር እንኳን የማያውቅ በጣም የዋህ ሰው ነበር፡፡ ምናልባት የመፎካከርን (የመወዳደርን) ትርጉም ሁሉ ላያውቅ ይችላል፡፡

ራማክሪሽና በተደጋጋሚ ከቤተ መቅደሱ እየወጣ «ኬሻብ አልመጣም ወይ?» እያለ ይጠይቅ ነበር፡፡ በመጨረሻ ኬሻብ ቻንድራ የቅርብ ተከታዮቹን አስከትሎ ከተፍ አለ፡፡ ራማክሪሽና ሄዶ ሲያቅፈው ወደ ኋላ ሸሸ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ራማክሪሽና በዚህ ተገርሞ «ኬሻብ፣ ሰዎችን እንዴት እንደምታቅፍ አታውቅም እንዴ? የምታውቀው መከራከር ብቻ ነውን? የሰው ልጅ የጋለ ስሜት እና ፍቅርን የሚያክል ትልቅ ነገር አጥተሀል:: መምጣትህ ግን ትልቅ ነገር ነው:: ክርክሮችህን መስማት እፈልግ ስለነበር በመምጣትህ ደስ ብሎኛል» አለ::

ይህ ንግግር ለኬሻብ ቻንድራ ምንም ስሜት ሊሰጠው (ስላልገባው) አልቻለም:: ወዲያውኑ «እግዚአብሔር የለም» በማለት መናገር ጀመረ::

«እንዴት ዓይነት ቆንጆ ዓረፍተ ነገር ነው! እንደገና ላቅፍህ እችላለሁ?» ብሎ ራማክሪሽና በድጋሚ አቀፈው::

ኬሻብ እጅግ አፈረ:: ተከታዮቹም በጣም አፈሩ:: ምን እየተካሄደ ነው?

«መልዕክቴን ተቀብለሀል ወይስ አልተቀበልክም?» አለ ራማክሪሽና::

«ምንም ነገር አልተናገርከም:: ምንም ነገር ሳትናገር እንዴት ነው መልዕክትህን የምቀበለው? ዝም ብለህ ነው ያቀፍከኝ» አለው ኬሻብም::

«ይህማ መናገር የማይቻሉ ነገሮችን መናገር የሚቻልበት መንገድ ነው:: <እግዚአብሔር የለም> አልከኝ:: እኔም አንተ የእግዚአብሔር መኖር ማረጋገጫ ነህ እልሀለሁ:: አለበለዚያ እንዲህ አይነት የማመዛዘን ችሎታ ከየት ይመጣል?» አለ ራማክሪሽና::

ከእንደዚህ አይነት ሰው ጋር እንዴት መከራከር ይቻላል?

ከአስር ደቂቃዎች በኋላ ኬሻብ ቻንድራ፣ በራማክሪሽና እግሮች ስር ወድቆ «ይቅር በለኝ፣ በሀሳብ (በአዕምሮ) ሳይሆን በህልውና እየኖረ ስላለ ሰው ምንም አይነት ሀሳብ አልነበረኝም:: አሁን በደንብ ግልፅ አድርገህልኛል:: አንተ የማሳመኛ ሀሳብ፣ የአመክንዬ ሰው ሳትሆን የፍቅር ሰው ነህ:: ማሳመኛ ምክንያት (ሎጂክ) ተራ ሲሆን፣ ፍቅር ግን እጅግ በጣም ሀያል ነው:: እባክህን ደቀመዝሙርህ አድርገኝ» አለው::


t.me/OLDBOOKSPDF

ኒቼ ታላቅ የማሳመን ብቃት ያለው እና ታላቅ ፈላስፋ ቢሆንም ስለ እውነታ የሚያውቀው ነገር አልነበረም:: የሚናገረው በአዕምሮ ላይ ብቻ የሚቀር ግምት እና አስተያየት ብቻ ነው:: በክርክር የተደገፉ መላምቶች ሰዎችን ሊያታልሉ ይችላሉ፣ የሚያውቅ ሰውን ግን አያታልሉም::

ኒቼ አያውቅም ነበር:: ነገር ግን ጥሩ አድርጎ መጻፍን ተክኖበታል:: ከፍተኛ የመከራከሪያ ነጥብ ላይ የደረሱ ፅሑፎችን በተከታታይ ፅፏል:: እነኚህ ግን እውነተኛ እና ትክክለኛ ዋጋ የላቸውም::

ትልቅ ዋጋ ያለው ነገር ክርክር ሳይሆን ልምድ (ተሞክሮ) ነው:: ኒቼ ደግሞ ምንም አይነት ልምድ (ተሞክሮ) አልነበረውም:: በተመስጦ ውስጥ ቆይቶ አያውቅም:: በራሱ ውስጥ ጠልቆ ገብቶ አያውቅም:: ዙሪያችንን ከከበበን እጅግ በጣም ሰፊ እና የተዋበ ዩኒቨርስ ጋር ተገናኝቶ አያውቅም:: ዩኒቨርስ የእኛ ማህፀን ነው - እኛ በውስጡ ሆነን ያለማቋረጥ የምናድግበት::

ምዕራባዊያን ጥቅም የሌላቸውን ነገሮች በተመለከተ ሀብታሞች፣ እውነተኛ ዋጋ ያላቸው ነገሮች በተመለከተ ደግሞ ድሆች ናቸው:: ኒቼ «ፀረ ክርስቶስ» የነበረበት ዋነኛ ምክንያት በሚሊየን የሚቆጠሩ ሰዎች ኢየሱስን በመከተላቸው እና ኢየሱስም ፍልስፍናውን ለማረጋገጥ አንድም የመከራከሪያ ሀሳብ ባለማቅረቡ ነበር:: እናም ኒቼ፣ የክርስቶስን ፍልስፍና ውድቅ ለማድረግ በመቶ የሚቆጠሩ ያማሩ እና የጠሩ የክርክር ሀሳቦችን አቀረበ:: ግን ምን ያደርጋል፣ ክርክሮች በቃ ክርክር ብቻ ናቸው::

በህይወታችሁ ሙሉ ስለፍቅር መከራከር ትችላላችሁ፣ ይህ ግን የፍቅርን ተሞክሮ አይሰጣችሁም::

ምዕራባውያን ያፈሩት ፈላስፎችን ብቻ ነው:: የምስራቅ አገራትም የሚያውቁት በጾም እና በፀሎት አምላክን ስለሚያገኙበት ሀይማኖት እንጂ ስለፍልስፍና አይደለም:: ሀይማኖታቸውም የተመሰረተው <ተሞክሮ፣ ክርክር አያስፈልገውም> በሚል ቀላል አመለካከት ነው::



t.me/OLDBOOKSPDF

ተሞክሮ የራሱ መሰረት ነው።

ወደ ውስጥ የሚጠልቅ ነው።

ውስጣችሁን ስታገኙ በውስጣችሁ በሺ የሚቆጠሩ መልካም መአዛ ያላቸው ፅጌረዳ አበቦች የፈነዱ ይመስል የብርሀን፣ የውበት እና የደስታ እርካታን ታገኛላችሁ።

ኒቼን ስለመሳሰሉ ፈላስፎች ስታስብ ልክ በህይወት ያሉ ይመስል በአካል የመገናኘት ያህል እንደምትቀርባቸው፣ ለእኔ ግን የተለየ ስሜት እንዳለህ ገልጸህልኛል።

እኔን ስታስታውሱ የሚሰማችሁ ዝምታ ነው። ደስታ ነው። ጮክ ብላችሁ ልትዘምሩ፣ ከልባችሁ ልትደሰቱ ወይም ዋሸንት ልትጫወቱ ትችላላችሁ።

እኔን ግን እዛ አታገኙኝም። እዛ የምታገኙት ህልውና (መላው ህይወት) በረከቱን በሙሉ ሲያፈስባችሁ ነው።

በፀሎት እና በመመስጥ ከአምላካቸው ለመገናኘት በሚሞክሩ እና በፈላስፎች መሀከል ያለው ልዩነት ይኸው ነው። ፈላስፎች በቃላት ሲኖሩ፣ በፀሎት እና በመመስጥ ከአምላካቸው ለመገናኘት የሚሞክሩ ግን በእውነተኛ ተሞክሮ ውስጥ ይኖራሉ።

ፍልስፍና ለምዕራባውያን እርግማን ነበር። ከጥንታዊ ግሪኮች ጀምሮ እስካሁን ያሉት ታላላቅ ምሁራን ፊታቸውን የሚያዞሩት ወደ ፍልስፍና ነው። ምክንያቱም ሁሉም ልማድ(ባህል) የፈላስፎች ነበር። ፈላስፎች በሰው ልጅ ዝግመታዊ ለውጥ ውስጥ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሱ ይመስላሉ። ሆኖም ይህ ሙሉ በሙሉ ትርጉም የለሽ ነው! ፈላስፋው የሚጫወተው የአዕምሮ ጨዋታ ነው። በህሊናው ግን የእናንተን ያህል ደካማ ነው።

ይሁንና የምስራቅ አገሮች እዚህ ወጥመድ ውስጥ አልገቡም። ምስራቃውያኑ አለማዊ ነገሮችን በተመለከተ ድሆች ናቸው። ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰን መንፈሳዊ ተሞክሮን በተመለከተ ግን የሚደርስባቸው የለም። የመጨረሻውን እውቀት ለማግኘት የሚያስፈልገው ብቸኛ ነገርም ይኸው ነው። ስንት ቤት እንዳላችሁ አትጠየቁም። ስለ ክርክራችሁም

t.me/OLDBOOKSPDF

ጥያቄ አይቀርብላችሁም። የምትጠየቁት «ልባችሁ ተከፍቶ አብቧል ወይ? የደስታ ጊዜያችሁ (የፀደይ ወራት) ደርሷል ወይስ አልደረሰም?» የሚሉ ጥያቄዎችን ነው።

ምስራቃውያን ሰዎችን እንደ አበቦች የሚያሳብበውን የፀደይ ወቅትን አይተዋል።

ኒቼን፣ ሄግልን፣ ካንትን፣ ፍዮርባችን፣ ካርል ማርክስን. . . ማንበብ በጣም ጥሩ ነገር ነው። አሪስቶትልን እና ፕላቶን የመሳሰሉትን የታላላቅ ፈላስፎች ፅሑፎችም ማንበብ ትችላላችሁ። ከባዶ ቃላት ውጪ ግን ምንም የምታገኙት ነገር የለም።

ቃላትም እናንተ የምትፈልጉትን ትርጉም መስጠት ይችላሉ።

**ፈላስፋው የሚጫወተው የአዕምሮ ጨዋታ ነው። በህሊናው ግን የእናንተን ያህል ደካማ ነው።**

ስለ አንድ ማስኪስት (ዱላ የሚወድ) የሰማሁት ነገር አለ። ማስኪስት ማለት በራሱ ላይ ስቃይ ሲደርስበት የሚደሰት ማለት ነው። ሳዲስት ደግሞ ሌሎችን በማሰቃየት ይደሰታል። ጥቂት ራሳቸውን በማሰቃየት እና ሌሎችንም በማሰቃየት የሚደሰቱ ውስብስብ ሰዎችም አሉ። እነኚህ ሳዶማስኪስት ይባላሉ።

አንድ ማስኪስት ከውብ ሀይቅ አጠገብ ተቀምጧል። ሳዲስት የሆነ ጓደኛውም አብሮት የተቀመጠ ቢሆንም አንድም ቃል አልተናገረም። በዚያ የሚያልፍ አንድ ሰው ሳዲስቱን «እናንተ ጓደኛሞች ሆናችሁ ሳለ የተቀመጣችሁት እንደ ጠላት ጀርባ ለጀርባ ነው። አንተም አንድም ቃል አልተናገርከም» አለው።

እሱም «እሱ (ማስኪስቱ) የሚወደው ይህንን ነው. . . ስቃይ!» አለው።

አንድ ሰው አብሯችሁ ተቀምጦ ምንም የማይናገር ከሆነ፣ ይህ የረቀቀ ስቃይ ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF

ስለ አንድ ተስፈኛ የሰማሁት አለ፡፡ ተስፈኛ ማለት በሁሉም ነገር ውስጥ ውበት የሚያይ ነው፡፡ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ መልካም ነገር የሚያይ ነው፡፡ ይህኛው ልብወለድ ታሪክ አይደለም፡፡ አንድ ቀን ተስፈኛው ከፀለምተኛ ጓደኛው ጋር ፓርክ ውስጥ ቆሞ ነበር፡፡ ፀለምተኛ ማለት በመልካም ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ችግሮች ብቻ የሚታዩት ሰው ነው፡፡ ሁለቱ ሰዎች ጓደኛሞች ነበሩ፡፡

ተስፈኛው «የምንኖርባት ዓለም ሊኖሩ ከሚችሉት ዓለሞች በሙሉ የተሻለች ነች» አለው፡፡

ፀለምተኛው «ልክ ነህ!» አለ፡፡

መልሱ በመጠኑ ረቂቅ ነው፡፡ ምላሹን በእኩለ ለሊት ጭር ሲል አተኩራችሁ ልታስቡበት ይገባል፡፡

**አንድ ሰው አብሯችሁ ተቀምጦ ምንም የማይናገር ከሆነ፣ ይህ የረቀቀ ስቃይ ነው፡፡**

አንድ ቃል ወይም አረፍተ ነገር በሌላ ሁኔታ ውስጥ ወይም በሌላ ሲነገር የተለየ መልክ እና የተለየ ትርጉም ይይዛል፡፡ በርካታ ፈላስፎች የተዋቡ አረፍተ ነገሮች ቢፅፉም ህይወት ግን የላቸውም፡፡

ኢየሱስ፣ ወይም ቡድሀ፣ ወይም በድሂ ዱሀርማ፣ አሊያም ካቢር የተናገሯቸው የተለመዱ ቃላት ግን በፍራፍሬ ጭማቂዎች የተሞሉ ናቸው፡፡ ሞልቶ በሚፈስ እውነት የተሞሉ ናቸው፡፡

የፈላስፎችን ፅሑፎች ማንበብ አዕምሮን ለማዳበር ስለሚጠቅማችሁ አንብቡ፡፡ ነገር ግን ሙሉ በሙሉ ውስጣቸው አትግቡ፡፡ ምክኒያቱም እየሰመጡ ናቸው፤ ወይም ሰምጠዋል፡፡ በራሳቸው ቃላት የራሳቸውን ብርሀን አጥተዋል፡፡

የሀሊናን ከፍተኛ ብርሀን የደረሱት በፀሎትና በመመስጥ ከአምላክ ለመገናኘት የሚሞክሩት ስለሆነ እነሱ ውስጥ በጥቂት ግቡ፡፡ ለዓለም የሚያስፈልጉት ሰዎች እነሱ ናቸው፡፡

ተከታዮቼ ሀመረ ኖህን እንዲሆኑ እፈልጋለሁ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ዓለም በውሀ ስትጥለቀለቅ ሀመሬ ኖህ አስፈልጓት ነበር፡፡

በተመስጦ አስቡ፡፡

...ይህን ስታደርጉ የራሳችሁን የህይወት ምንጭ ታገኙታላችሁ፡፡ የህይወታችሁን ምንጭ ስታገኙም በአካባቢያችሁ (በዙሪያችሁ) ልታዩት ትችላላችሁ፡፡

ዩኒቨርስ በጣም አስደናቂ እና ተአምራዊ ነው፡፡ ከተአምራቱ ጋር መገናኘት ከቻላችሁ፣ የተአምራቱ አካል መሆን ትችላላችሁ፡፡ ህይወት የደስታ፣ እያንዳንዱ ትንፋሻችሁም የእርካታ ይሆናል፡፡

ፈላስፎችን እየተቃወምኩ አይደለም፡፡ በቦታቸው መቀመጥ እንዳለባቸው በግልፅ እየተናገርኩ እንጂ፡፡

አምላካቸውን በፀሎት እና በተመስጦ ለማግኘት የሚሞክሩት ሰዎች ተከራካሪ ባለመሆናቸው ብቻ ተረስተዋል፡፡ እነሱ ብዙ አያወሩም፡፡ የሚናገሩትም የላቸውም፡፡

እነሱ ያላቸው በግልፅ የሚያሳዩት ነገር ነው፡፡ ከአምላካቸው ጋር በፀሎት እና በተመስጦ ለመገናኘት የሚሞክሩት ሰዎች እጆች ላይ እጃችሁን የማስቀመጥ ድፍረት ያላችሁንም፣ ማመን የማይቻለውን ወደምታዩበት ቦታ ይወስዷችኋል፡፡

ከዚያ በኋላ በህይወታችሁ ውስጥ ስቃይ፣ ስጋት፣ ጭንቀት እና ሞት አይኖሩም፡፡ የዘላለማዊ የህይወት ፍስት አካል ትሆናላችሁ፡፡

የትኛውም ፈላስፋ ደግሞ ይህን ሊሰጣችሁ አይችልም፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# ፍጹም እርግጠኛ የሚኮነው መጀመሪያ ሳይሆን መጨረሻ ነው

**ተወዳጁ ባገዋን፡-**

**ለአስራ አምስት ዓመታት ያህል የተለያዩ መንፈሳዊ ዘዴዎችን (ቴክኒኮችን) ከተከታተልኩ እና ለሁለት ዓመታት ያህል በቡድን ተግባራት ከተሳተፍኩ እንደዚሁም የአንተን ተመስጦ ከተከታተልኩ በኋላ አሁን ተከታይህ ለመሆን ወሰኛለሁ፡፡ ቢሆንም ግን እስካሁን ድረስ ስጠብቀው የኖርኩትን ፍጹም የሆነ ውስጣዊ እርግጠኛነት አላገኘሁም፡፡ መምህር፣ ደጋፊ በመሆን እና ተከታይ በመሆን መሀከል ስላለው ልዩነት ጥቂት ነገር ትነግረኛለህ?**

ደጋፊ ማለት ተከታይ ለመሆን በመንገድ ላይ ያለ ነው፡፡ በመሀከላቸው ልዩነት የለም፡፡ ተከታይ የደረሰ (የበቃ) ሲሆን ደጋፊ ደግሞ እየደረሰ ያለ ነው፡፡

ተከታይ ለመሆን ፍጹም እርግጠኛ እስከምትሆን አስራ አምስት አመታትን መጠበቅህ የሚገርም ነው፡፡ ሌሎች ነገሮችንም ያን ያህል ጊዜ ትጠብቃለህን? ለጋብቻ ወይም በፍቅር ለመውደቅ አስራ አምስት አመታት ትጠብቃለህ?

እስኪ ህይወታችሁን ልብ ብላችሁ ተመልከቱ፡፡ አስራ አምስት አመታት መጠበቅ እኮ በጣም ረጅም ጊዜ ነው፡፡ ሲርባችሁ ምግብ የምትበሉት ምግቡ እንደማይመርዛችሁ ፍጹም እርግጠኛ ስትሆኑ ብቻ ነውን? ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ስትሆኑ!

አሁን የተቀመጣችሁበት ቤት ላይ ያለው ጣራ እንደማይወድቅባችሁስ እርግጠኛ ናችሁ? ጣራው አስተማማኝ መሆኑን ለማረጋገጥ አስራ አምስት አመታትን ጠብቃችኋል?



t.me/OLDBOOKSPDF

አሁን ወደ ውስጥ በጥልቀት የመግቢያው ጊዜ ነው።

ምንም እንኳን ፍጹም እርግጠኛ ባትሆኑም መኖር ካልጀመራችሁ በቀር ህይወት በጣም አጭር ነች።

ስላልሞከራችሁት ነገር እንዴት ፍጹም እርግጠኛ መሆን ትችላላችሁ? በምን መንገድስ እርግጠኛ መሆን ትችላላችሁ?

አንድ ጊዜ ሙላ ናስሩዲን ውሃ ዋና ለመማር ተነሳሳ። ከዛም ወደ ውሃ ዋና አስተማሪ ዘንድ በመሄድ አብረው ወደ ወንዝ ወረዱ። ውሃው ጋር ሲደርሱ ግን ናስሩዲን ወደዚህ አደገኛ ውሃ ለመግባት ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ስላልነበር ፈራ። አስተማሪውስ እምነት የሚጣልበት ታማኝ መሆኑን እንዴት ማረጋገጥ ይቻላል? በፍጥነት አሰበ እና ከውሃው ዳር ተነስቶ ፊቱን አዙሮ ወደ ቤቱ መሮጥ ጀመረ።

አስተማሪው «የት እየሄድክ ነው? የመጣኸው እኮ ውሃ ዋና ለመማር ነው» አለው።

«ሁሉንም እርሳው። ፍጹም እርግጠኛ ስሆን ተመልሼ እመጣለሁ» አለው ሙላ ናስሩዲን።

«እንዴት ፍጹም እርግጠኛ መሆን ትችላለህ?» አስተማሪው ጠየቀው።

«መጀመሪያ አልጋዬ ላይ መለማመድ እጀምራለሁ። እዛ ምንም አይገጥመኝም። ሙሉ በሙሉ ስረካም አንተ ዘንድ እመጣለሁ» አለ፣ ሙላ ናስሩዲን።

ናስሩዲን ተመልሶ ወደ ውሃ ዋና አስተማሪው አልሄደም። ምክንያቱም አንድም ሰው አልጋ ላይ ሆኖ ዋና መማር አይችልም። ውሃ ዋና መማር የፈለገ ሰው የግድ ውሃ ውስጥ መግባት አለበት። ውሃ ውስጥ የምትገቡትም አደጋ እንደማይደርስባችሁ ፍጹም እርግጠኛ ሆናችሁ አይደለም። የምትሄዱት በጀብደኝነት መንፈስ መሆን አለበት። ራሳችሁን ለአደጋ እንደምታጋልጡ እና ውድቀት ሊኖር እንደሚችል ማወቅ አለባችሁ።

የእኔ ተከታይ ስትሆኑ በመላው ህይወት (ህልውና) ግዛት ውስጥ በጥልቀት ትገባላችሁ። ልክ በዚህች ሰአት ግን እንዴት ፍጹም እርግጠኛ



t.me/OLDBOOKSPDF

መሆን ትችላላችሁ? የግድ አንድ ሰውን ማመን አለባችሁ:: መንገዱን የሚያውቀውን እና በመንገዱ ላይ የተጓዘውን ሰው ማመን አለባችሁ::

ግለሰቡ እውነተኛ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ ለማወቅ አስቸጋሪ አይደለም:: አይኖቹን ተመልከቱ፤ እንቅስቃሴውን ተመልከቱ፤ የቃላቱን ጥንካሬ አድምጡ:: አብሯችሁ መኖሩ በጥልቀት ይሰማችሁ::

አለበለዚያ ግን አስራ አምስት አመታትም ሆነ አስራ አምስት ተደጋጋሚ ህይወቶች የሚያመጡት ለውጥ የለም:: ካላችሁበት ሁኔታ መውጣት አትችሉም:: ፍጹም እርግጠኛ መሆን የሚመጣው መጀመሪያ ሳይሆን በመጨረሻ ነው::

ጅማሬው. . . መጀመር ያለበት ፍጹም እርግጠኛ በመሆን ሳይሆን ለመማር (ለመለወጥ) ሙሉ በሙሉ ፍላጐት በመያዝ ነው::

ስለራሳችሁ ለማወቅ እና የህይወትን ሚስጥራት ለመረዳት ከልባችሁ ቆርጣችሁ ከተነሳችሁ ይበቃል:: እርግጠኛ መሆን የሚመጣው ተሞክሯችሁ እየዳበረ ሲሄድ ነው::

ነገር ግን ፍጹም እርግጠኛ መሆን አስቀድሞ እንዲመጣ ከፈለጋችሁ. . . አይሆንላችሁም:: ስለማይሳካላችሁም እርሱት::

**ጅማሬው. . . መጀመር ያለበት ፍጹም እርግጠኛ በመሆን ሳይሆን ለመማር (ለመለወጥ) ሙሉ ፍላጐት በመያዝ ነው::**


t.me/OLDBOOKSPDF

# አንተ ከኔ ጋር ነህ ወይስ እኔ ከአንተ ጋር? አንተስ ማነህ? እኔ ወይስ አንተ?

ተወዳጁ ባግዋን፡-

ከአንተ ጋር ስሆን ማዕበሉ በተነሳበት ሰፊ ውቅያኖስ ላይ እንዳለ ጀልባ የምንሳፈፍ ይመስለኛል:: ጥያቄዬ አንተ ከእኔ ጋር ነህ ወይም እኔ ከአንተ ጋር ነኝ?

የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ነን:: ሁለቱም ትክክል ናቸው:: ይህንን ጐን ወይም ያኛውን ጐን ማየት ትችላለህ:: እንደ ማዕበል ወደ ላይ ከፍ ብለህ በተነሳህ ቁጥር ወደ እኔ እየቀረብክ ትመጣለህ::

በከፍተኛው ነጥብ ላይ ስትደርስ ይህ ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም:: አንተ ማነህ? - እኔ ወይስ አንተ? በእርግጥ እነኛ ሁለት አካላት ወደ አንድ ሙሉ ህያውነት ውስጥ ገብተው ጠፍተዋል::

ይህንንም ራስን አሳልፎ መስጠት እያልኩ እጠራዋለሁ:: የደቀ መዝሙርነት የመጀመሪያ ደረጃ ነው::



t.me/OLDBOOKSPDF

# የጥፋተኝነት ስሜት አይለወጥም!

ተወዳጁ ባገዋን፡-

ራሴን መገሰፅ ስፈልግ የጥፋተኛነት ስሜት ይሰማኛል፡፡ በመጨረሻ ራሴን በድፍረት ስገስፅ ለእኔ ከሚሰጠኝ የአምንታ ስሜት ይልቅ ስሴሎች የእሱታ ስሜት የሚሰጥ ይመስላል፡፡ በዚህ ምክንያትም የጥፋተኝነት ስሜቱ ተመልሶ ይሰፍርብኛል፡፡ ከዚህ የማመልጥባቸው ሁለት መንገዶች ለሴላ ቀን ማስተላለፍ ወይም መከላከል (መቃወም) ናቸው፡፡ እነኚህም ቢሆኑ የችግሩ አካል ይመስላሉ፡፡ ተወዳጁ መምህር፣ የጥፋተኛነት ስሜትን መለወጥ የሚቻልበት መንገድ አለ?

ወይ ፈጣሪዬ! የጥፋተኝነት ስሜት መለወጥ የቻለ አንድም ሰው የለም! በአጭሩ መተው ያለበት ነገር ነው፡፡ መለወጡ ለምን አስፈለገ? በአንድ ወይም በሌላ መልኩ አብሮህ እንዲኖር ትፈልጋለህን?

የጥፋተኝነት ስሜት አብሯችሁ የተወለደ ነገር አይደለም፡፡ ተፈጥሯዊ አይደለም፡፡

የጥፋተኝነት ስሜት የሚፈጠረው በምትኖሩበት ማህበረሰብ ነው፡፡

ለምሳሌ ሁሉም ሀይማኖት በተለያየ መንገድ የጥፋተኝነት ስሜትን ይፈጥራል፡፡ ዘዴው ግን ተመሳሳይ ነው፡፡

ሁሉም ሀይማኖቶች የሚኖሩት እና የሚስፋፉት የጥፋተኝነት ስሜት በሚሰማቸው (ሀጢያተኛ) ሰዎች ነው፡፡ መጀመሪያ ሰዎቹን የጥፋተኝነት ስሜት እንዲሰማቸው አድርጉ፡፡ ሰውን አንድ ጊዜ የጥፋተኝነት ስሜት እንዲሰማው ማድረግ መቻል መንፈሱን የመግደል ያህል ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ነፍስ የሌለው ባሪያ ይሆንላችኋል፡፡


t.me/OLDBOOKSPDF

እኔን በተመለከተ አጠቃላዩ ተልዕኮዬ እናንተን እንዴት ከጥፋተኝነት ስሜት ነፃ እወጣለሁ እንጂ የጥፋተኝነት ስሜትን እንዴት እለውጠዋለሁ የሚል አይደለም::

የተወለድኩት የጃይና ሀይማኖት በሚከተል ቤተሰብ ነው:: ሀይማኖቱ ሲበዛ ወግ አጥባቂ ነው:: ቀላል ነገሮች እንደ ሀጢአት ይቆጠራሉ:: የሀይማኖቱ ተከታዮች በምሽት ምግብ መብላት አይችሉም፣ ይህን ማድረግ ትልቅ ጥፋት ነው:: በምሽት ምግብ ከተመገባችሁ ወደ ገሀነም አቅጣጫ እየተጓዛችሁ ነው ማለት ነው:: ወደ ገሀነም የሚወስደውን ደረጃ አንድ እርምጃ ወደታች ወረዳችሁ ማለት ነው::

እኔ ምንም አይነት ችግር አላይበትም:: ሀይማኖቱ ጥንታዊ ነው:: በዛን ጊዜ መብራት እና ኤሌክትሪክ ስላልነበር ሰዎች በምሽት ምግብ እንዳይበሉ ቢከለከሉ ላይገርም ይችላል:: ነገር ግን ጥፋት (ሀጢአት) ማድረጉ ለምን አስፈለገ?

እዚህ ላይ ምክንያታዊ የሆነ ማብራሪያ በቂ ቢሆንም፣ ሀይማኖቶች ግን ለምክንያታዊ ማብራሪያ ቁብ አይሰጡም! እናንተን ጥፋተኛ (ወንጀለኛ) የሚያደርጉበት አንድም እድል እንዲያመልጣቸው አይፈልጉም:: የጥፋተኝነት ስሜት በእናንተ ላይ ሀይል እንዲኖራቸው የሚያደርግ ነው::

**ሁሉም ሀይማኖቶች የሚኖሩት እና የሚስፋፉት የጥፋተኝነት ስሜት በሚሰማቸው (ሀጢያተኛ) ሰዎች ነው::**

ከሰው ልጅ ውስጥ ሁሉንም ጥፋት (ሀጢአት) ማስወገድ ከቻልን ሁሉም ቤተክርስቲያናት እና ቤተ መቅደሶች ባዶአቸውን ይቀሩ ነበሩ:: የሚፀልይ ሰው አይኖርም ነበር:: ቅዱስ መፅሐፍትን የሚሸከም አይኖርም ነበር::

የጥፋተኝነት ስሜት በመፍጠር ግን ማንኛውንም ነገር ማድረግ ይቻላል:: ሁኔታው አንዳንድ ጊዜ አዝናኝ ነው::



t.me/OLDBOOKSPDF

እድሜዬ አስራ ስምንት አመት እስከሚሞላ ድረስ በምሽት ምግብ ተመገቡ አላውቅም ነበር፡፡ በዚህ ምግባሬም መገሳ ይቀርብልኝ ስለነበር በአካባቢዬ ካሉት ሂንዱዎች የበላይ እና ቅዱስ እንደሆንኩ አስብ ነበር፡፡ እነኛ ሰዎች በምሽት ይመገቡ ነበር፡፡ እንዴት ያሳዝናሉ፣ ሁሉም ገሀነም መውረድ አይቀርላቸውም፡፡

እኔ ከቅጣት ተርፌ እነኚህ ሰዎች በቅጣት የሚጠፉ በመሆናቸው ከፍተኛ ደስታ ይሰማኝ ነበር፡፡ የትም ቦታ ሆነን ምግብ ብንመገብ መቼም አንድ ሌላ ቦታ ጨለማ መሆኑ አይቀርም! ታዲያ ምሽቱ እዚህ ወይም ለንደን መሆኑ ምን የሚያመጣው ለውጥ አለ? መምሸቱ እንደሆነ አይቀርም፡፡

በሲክ ሀይማኖት አንድ የሀይማኖቱ ተከታይ አምስት መርሆዎችን መከተል ይጠበቅበታል፡፡ አምስቱም እስቲኝ ናቸው፡፡ አንድ ሲክ ፀጉሩ ረጅም መሆን አለበት፡፡ በፑንጃቢ ቋንቋ እነኚህ መርሆች አምስቱ 'K' ዎች ይባላሉ፡፡ የመጀመሪያው 'K' ትርጉሙ Kesh ፀጉር ማለት ነው፡፡ የሰውነታችሁን ፀጉር በፍጹም መቁረጥ አትችሉም፡፡ ሁለተኛው 'K' Katar ነው፡፡ ካታር ማለት ልዩ አይነት ጉራዴ ነው፡፡ እንዴ . . . ደግሞ ጉራዴን እና ሀይማኖትን ምን አገናኛቸው? ትሉ ይሆናል፡፡ ቢሆንም ሁሉም ሲክ ጉራዴ መታጠቅ አለበት፡፡

የበለጠ የሚያስገርመው ሶስተው 'K' ነው፡፡ የዚህን ሀይማኖታዊት ለመረዳት ሞክሬ እስካሁን አልሆነልኝም፡፡ ካችቻ Kachchhc ይባላል፡፡ ካችቻ ማለት ከውስጥ የሚለበስ ልብስ (ሙታንታ እና ካራቴራ) ማለት ነው፡፡ ከውስጥ የሚለበስ ልብስ ካልለበሳችሁ አበቃላችሁ፡፡

ወይ ፈጣሪ! እኔ እስከማውቀው ድረስ እግዚአብሔር ራሱ ልብስ የለውም፡፡ የትኛውም ቅዱስ መፅሐፍ እግዚአብሔር ልብስ አለው አይልም፡፡ እነኚህ ምስኪን ሲኮች ግን ከውስጥ የሚለበስ ልብስ እንዲለብሱ ይገደዳሉ፡፡ ብዙ ጊዜ ይህ ምን ችግር አለው? እያልኩ ራሴን እጠይቃለሁ፡፡ ለምን ከውስጥ የሚለበስ ልብስ እዚህ ውስጥ ገብቶ የሀይማኖት መርህ ለመሆን በቃ?


t.me/OLDBOOKSPDF

እነኛ ቀናት ለሲክ ሀይማኖት (ሲኪዝም) የተወለደባቸው ጊዜያት ነበሩ:: ሀንድ በመሐመድ ተከታዮች አገዛዝ ስር ነበረች:: በጦርነት ወቅት የሚወድቅ ነገር ይዛችሁ የምትሮጡ ከሆነ እና ወገባችሁ ላይ ያገለደማችሁት ጨርቅ ቢወድቅ - ያን ጊዜ ካችቻ ያስፈልጋል:: አለበለዚያ የያዛችሁት ጉራዴ ምንም የሚፈይደው ነገር የለም:: እናንተም መሳቂያ ትሆናላችሁ::

አሁን ግን ጦርነት የሚባል ነገር የለም:: ችግርም የፈጠረ ነገር የለም:: ካችቻውን ማስቀመጥ ይቻላል!

አንድ ሲክ ፀጉሩን መቆረጥ አይችልም:: ፀጉሩን ከተቆረጠ የጥፋተኝነት ስሜት ይሰማዋል:: እናንተ ፀጉራችሁን ስትቆረጡ ወይም ፂማችሁን ስትላጩ የጥፋተኛነት ስሜት አይሰማችሁም:: ኧረ እንዲያውም የጥፋተኛነት ስሜት ራሱ ውል አይልባችሁም:: እንዴት ሆኖስ የጥፋተኛነት ስሜት ሊያጭርባችሁ ይችላል?

ነገር ግን አንድ ጊዜ ሀሳቡ አዕምሯችሁ ውስጥ ከሰረፀ፣ እንደዚሁም ከልጅነታችሁ ጀምሮ በዚህ መንገድ ካደጋችሁ ይህን ማድረግ አስቸጋሪ ይሆንባችኋል::

አንድ መኪና የሚያሽከረክርልኝ የሲክ ሾፌር ነበረኝ:: አንድ ምሽት ተኝቶ ሲያንኩራፋ ፀጉሩን ቆረጥኩት:: ጠዋት ሲነሳ በሩጫ እያለቀሰ ወዳለሁበት መጥቶ «ስራዬን በፈቃዴ ለትቄአለሁ» አለኝ::

«ምን ተፈጠረ?» አልኩት::

«አታዩትም እንዴ? ፀጉሬን የቆረጠኝ ሰው አለ:: ሀይማኖቴን፣ መንፈሳዊነቴን አጥፍቶብኛል» አለ::

«እስኪ ቁጭ በል:: ፀጉርህ በመቆረጡ ሀይማኖትህ የሚጠፋው እንዴት ሆኖ ነው?» አልኩት::

«ምንም ነገር መስማት አልፈልግም:: ይህ በቅዱሳን መፅሐፍት ላይ የተጻፈ ነገር ነው:: የእኔን ቅዱስ መፅሐፍ የሚጻረር አንዳችም ነገር ማድመጥ አልፈልግም:: ስለዚህ እባክዎን ካችቻዬን ስጡኝ እና ልሂድ::»

ፀጉሩን ስቆርጠው ካችቻውም መውሰዱ ጥሩ ነው ብዬ አስቤ ነበር:: በጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ ስለነበር ካችቻውን አውልቄበት ነበር::



t.me/OLDBOOKSPDF

«ካቾቻ? ካችቻህማ ማን ወሰደብህ? ገላህን ታጥበህ አታውቅም:: ሾፌሬን በአንድ ማይል ራዲየስ ውስጥ ሆኖ በጠረኑ በቀላሉ መለየት እችላለሁ:: ካችቻህ እኮ አስቀያሚ መአዛ ይረጫል:: የወሰደብህ ሰው ካለ ይዞት ጥርግ ይበል!» አልኩት::

«አይሆንም፣ ይህ ሀይማኖቴ ነው! መጀመሪያ ማን እንደወሰደብኝ ማወቅ አለብኝ::»

ጉራዴውን በእጁ ይዞ ስለነበር «ረጋ በል:: አዲስ ካችቻ አመጣልሀለሁ» አልኩት::

«ፀጉሬስ?» ብሎ ጠየቀኝ::

«የውሸት (አርተፊሻል) ፀጉሮች ሞልተዋል::»

«እሱስ ጥሩ ነው::»

እንዲህ አይነት የጥፋተኝነት ስሜት የሚሰማቸው ቂሎች በመላው ዓለም ሞልተዋል:: እናንተም የጥፋተኝነት ስሜትን ስነልቦና (ሳይኮሎጂ) መረዳት አለባችሁ:: አንድ ጊዜ ከተረዳችሁት ከዛ በኋላ የጥፋተኝነት ስሜቱ ይወገዳል::

ሰዎች እናንተን የመንፈስ ባሮች ለማድረግ «እነኚህን ነገሮች ስህተት ናቸው:: እነዚህን ነገሮች ካደረጋችሁ እግዚአብሔር ተቆጥቶ ወደ ገሀነም ይወረውራችኋል» የሚሉ ሀሳቦችን አዕምሯችሁ ውስጥ አስቀምጠውባችኋል:: ከእኔ በስተቀር ሰው በተፈጥሮው ሲኦል መግባት አይፈልግም:: እኔ ለሲኦል ከፍተኛ ፍቅር አለኝ:: ወደ ገነት መሄድ የማልፈልግበት ምክንያት እዛ ያሉት የደረቀ አጥንት ያላቸው፣ አስቀያሚ ጻድቃኖች፣ ካችቻ የያዙ ሰዎች ብቻ ስለሚገኙ ነው:: በሲኦል ግን በጣም ምርጥ የሚባለውን ወዳጅ ታገኛላችሁ:: ሁሉም ታላላቅ ጥበበኞች እና ባለቅኔዎች የሚገኙት እዛ ነው:: ሁሉም አምላካቸውን በተመስጦ እና በፀሎት ለማግኘት የሚሞክሩ ታላላቅ ሰዎች ያሉት እዛ ነው:: እንደውም እዚህ ምድር ላይ የተከሰተ ሁሉም የሚያምር ነገር የምታገኙት በገነት ውስጥ ሳይሆን በሲኦል ነው::

በገነት ውስጥ የምታገኙት ምድር ላይ የሚሰቃዩትን አስቀያሚ ጻድቃንን ነው:: ገነት ለመግባት ይህን ያህል የጣሩት ለምንድን ነው?


t.me/OLDBOOKSPDF

ሁኔታውን የበለጠ ግልፅ የሚያደርግ ነገር ልብ በሉ፡፡ ይህም ገነት ከገቡ በኋላ መውጫ የለም፡፡ አንድ ጊዜ ከገባችሁ፣ አበቃላችሁ፡፡ በሲኦል ግን የመግቢያ እና መውጫ የሆኑ ሁለት በሮች አሉ፡፡ መሄድ ከፈለጋችሁ መሄድ ትችላላችሁ፡፡ እዚያ ገብቶ የሚወጣ ሰው ግን የለም፡፡ ሁሉም የተዋቡ ሴቶች፣ ሁሉም መልከ መልካም ወንዶች ያሉት እዛ ነው፡፡ ሀያ አራት ሰአት ፌስታ ነው፡፡

በመሆኑም ለሹፌሬ «አትጨነቅ፡፡ ገሀነም ከገባህ እኔም አብሬህ እመጣለሁ፡፡ እዛም ሾፌር ትሆነኛለህ!» አልኩት፡፡

«እኔ ግን እዛ መሄድ አልፈልግም» አለ፡፡

«አልገባህም፣ ገነት እኮ መኪና የለም፡፡ እዛ ምን ትሰራለህ?» አልኩት፡፡

«ይህ ጥሩ ጥያቄ ነው፡፡ መስራት የምችለው አንድ ስራ ብቻ ነው፡፡ ገነት መኪና አለመኖሩን እርግጠኛ ነዎት?» ብሎ ጠየቀኝ፡፡

«እኔ ሰምቼ አላውቅም፣ ሁሉም ቅዱስ መፅሐፍትን ማየት ትችላለህ፡፡ የሁሉንም ሀይማኖት ቅዱስ መፅሐፍትን አንብብ፡፡ ምንም መኪና የሚባል ነገር የለም፡፡»

«ወይ ፈጣሪዬ! እንደሱ ከሆነ ካችቻው (የውስጥ ልብሱ) እና ኬሽ (ፀጉሬ) ቢቀሩብኝ ይሻላል፡፡ ከእርስዎ ጋር እሄዳለሁ፤ ሲኦል የሚሄዱ ከሆነ አንድ ነገር አሰው፡ ማለት ነው፡፡»

የጥፋተኝነት ስሜት ውጅቅ መደረግ አለበት፡፡

የቆሳል ግንዛቤ መኖር በቂ ነው፡፡

አንድ ነገር እንድትለማመዱ ተደርጐ ተታላችኋል፡፡ ይህ ነገር ትርጉም የለሽ መሆኑን በተረዳችሁበት ቅፅበት ከውስጣችሁ አስወግዱት፡፡ መለወጥ ግን አስፈላጊ አይደለም፡፡

በዛ ላይ መለወጥ የሚቻል ነገር አይደለም፡፡ ምክንያቱም የጥፋተኝነት ስሜት እውነተኛ (ትክክለኛ) ነገር አይደለም፡፡ በአዕምሯችሁ በግድ እንዲሰርፅ የተደረገ ሀሳብ ነው፡፡

ልክ በስህተት ሁለት ሲደመር ሁለት፣ አምስት ይሆናል ተብሎ እንደተማረ ሰው ነው፡፡ እዚህ ላይ መለወጥ የሚያስፈልግ ይመስላችኋል?



t.me/OLDBOOKSPDF

ለተሳሳተው ሰው «ሁለት ሲደመር ሁለት አምስት ሳይሆን አራት ነው» ማለት ይበቃል፡፡

አራት ወንበሮች ከፊት ለፊቱ አስቀምጡ፡፡ ሁለቱን በአንድ ጐን ሁለቱን ደግሞ በሌላው በኩል አድርጓቸው፡፡ ከዛም አንድ ላይ ቀላቅሏቸው እና አራት ወይም አምስት መሆናቸውን ለማረጋገጥ እንዲቆጥራቸው ንገሩት፣ አምስት የሚለውን ሀሳብ ለመጣል የሚቸገር ይመስላችኋል? ሁለት ሲደመር ሁለት፣ አራት መሆኑን ባወቀበት ቅፅበት አምስት የሚለውን ነገር ያበቃለታል፡፡

የጥፋተኝነት ስሜትም ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

የጥፋተኝነት ስሜት በሀይማኖተኛ ሰዎች በሰው ልጅ ላይ የተፈፀመ ከባድ ወንጀል ነው፡፡ በፍጹም ይቅር ሊባሉ አይችሉም፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# ፍቅር ግልፅ ራዕይ ይሻል

# 4

## ታህሳስ 26፣ 1986፣ ቦምቤ



t.me/OLDBOOKSPDF

# እውነተኛ የፍቅር ፈተና ያለው በሰዎች ዘንድ ነው፤ ሁለቱም ሊያገኙት ይፈልጋሉና

**ተወዳጁ ባገዋን፦**

**የጥበብ ሰው እንደመሆኔ የፍቅር እና የደስታ ስሜቴን በፅሁፍ ማስፈር እችላለሁ። በፅሁፎቼ ገለፅ እንደምሆነው ስምንድን ነው ስሜቴን በገለፅ ለሰዎች መንገር የማልችለው?**

ፅሁፎች ህይወት አልባ ነገሮች ናቸውና ፀሃፊ መሆን ቀላል ነው። ውብ የሆኑ ሃውልቶችን መገንባት ብትችሉም ሃውልቶቹ ሙት ናቸው። እናንተ ግን ህያው ናችሁና ከእነሱ ጋር ልትመደቡ አትችሉም። በህይወትና በሞት መካከልም ንግግር የለም።

ልታደንቁ፣ በዚህም ልትደሰቱ ትችላላችሁ - ፈጠራችሁ ስለሆነ። ስራው ስለተሳካላችሁ በፈለጋችሁ ጊዜ የምሉዕነት ስሜት ሊሰማችሁ ይችላል። ነገር ግን አንድ ነገር አትዘንጉ፣ በዚያኛው ወገን ማንም የለም። ብቻችሁን ናችሁ።

በዚህ ሁኔታ ምክንያት ውሾቻቸውን፣ መናፈሻዎቻቸውን፣ መኪናዎቻቸውን፣ በአጭሩ ከሰው በቀር በዓለም ላይ የሚገኘውን ሁሉ የሚወድዱ አሉ።

ሰው ካለ ብቻችሁን አይደላችሁትም፤ ሌላ ወገን አለ፤ ንግግር አለ። ከሃውልት ጋር ግን የብቻ ውይይት ነው። ሃውልቱ ምንም አያናግራችሁም፣ አይተቻችሁም፣ በንብረትነት አይዛችሁም - እናንተ ንብረታችሁ ታደርጉታላችሁ እንጂ። ገበያ አውጥታችሁ ልትሸጡት



t.me/OLDBOOKSPDF

ትችላላችሁ፡፡ ይህንን ግን ሰብአዊ ፍጡራን ላይ ልታደርጉት አትችሉም፡፡ ችግሩ ይህ ነው፡፡

ከሰዎች ጋር ግንኙነት መመስረት ስትጀምሩ፣ ሰብአዊ ፍጡራኑ ተራ ነገሮች ሳይሆኑ ማሰብ የሚችሉ መሆናቸውን ከግምት ማስገባት ይኖርባችኋል፡፡ ምንም እንኳን ሁሉም ሰው ይህን ለማድረግ እየሞከረ ቢሆንም ልትጫኑዋቸው አትችሉም፡፡ በሰዎች ላይ የበላይ ለመሆን በምትሞክሩበት ቅፅበት ጠላት ፈጠራችሁ ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም የበላዩ ለመሆን የምትሞክሩት ሰውም የበላይ የመሆን ፍላጐት አለውና፡፡

ፍቅር ወይ ጓደኝነት ብላችሁ ልትጠሩት ትችላላችሁ፡፡ ነገር ግን ከጓደኝነት፣ ከፍቅር እና ከወንድማማችነት መጋረጃ ጀርባ የበላይ የመሆን ጥልቅ ፍላጐት አለ፡፡ የበላይ እንጂ የበታች መሆን አትፈልጉም፡፡

ከሰብአዊ ፍጡራን ጋር ባላችሁ ግንኙነት ሁልጊዜም ግጭት ውስጥ ናችሁ፡፡ ይበልጥ በቀረባችሁ ቁጥር ግጭቱ ይበልጥ ይጐዳችኋል፡፡ በሰብአዊ ግንኙነት ተጐድተው መላውን የሰው ልጅ ፍቅርና ጓደኝነት እርግፍ አድርገው የተዉ በሺ የሚቆጠሩ ሰዎች አሉ፡፡ ትኩረታቸውን ወደ ነገሮች መልሰዋል፡፡ ይህ መንገድ ደግሞ በጣም ቀላል ነው - ምክንያቱም ሌላኛው ወገን የፈለጋችሁትን ብታደርጉበት ፈቃደኛ ነው፡፡

እናንተ የጥበብ ሰው ናችሁ፣ ሃውልት ትቀርፃላችሁ፡፡ ግን ስለምትሰሩት ስራ አስባችሁ ታውቃላችሁ? እምነ በረድ እየቀራረጣችሁ ነው - ሆኖም አንድ ሰው መፍጠር አትችሉም፡፡ ሰዎች ግን እንዲያ እያደረጉ ነው፡፡ ወላጆች የልጆቻቸውን ክንፍ፣ ነፃነት፣ ግለኝነት ልክ እንደ ሃውልቱ እየቆረጡ ነው፡፡ ፍቅረኛሞችም እርስ በርሳቸው ይከፋፈላሉ፣ ይሰያያሉ፡፡

የዚህ ምክንያቱ ከሰው ልጅ ጋር በፍቅር መውደቅ ቀላል አለመሆኑ ነው፡፡ የፍቅር ጉዳይ ሁለት ህያው ወገኖች ላለመሸነፍ የሚፍጨረጨሩበት ስለሆነ በዓለም ላይ ከሚገኙት ጉዳዮች ሁሉ አስቸጋሪው ነው፡፡


t.me/OLDBOOKSPDF

ወላጆች ለልጆቻቸው «ይህን አታድርጉ!» ብለው ሲመክሯቸው እንኳን ህፃናቱ የተሰደቡ፣ የተንቋሸሹ፣ የተጐዱ ያህል ይሰማቸዋል። እነሱም በተራቸው ድፍረቱን ሲያገኙ ተመሳሳይ ነገር ይፈፅማሉ።

እኔ ከተወለድኩባት መንደር አስር ማይሎች ያህል ራቅ ብላ በምትገኘው መንደር ከናርማዳ ወንዝ ዳር አንድ ትልቅ ሃይማኖታዊ በዓል ይከበራል። ወንዟ በህንድ ውስጥ ከሚከበሩት ወንዞች መሃል አንዷ ናት። ምናልባትም በአፈ - ታሪክ ደረጃ እጅግ የተከበረችው ሳትሆን አትቀርም። ሌሎቹ ወንዞች በሙሉ የተጋቡ ሲሆኑ ናርማዳ ብቻ ድንግል ናት . . .

ናርማዳ ከተራሮቹ መሃል ወጥታ በውብ ፏፏቴ መልክ ወደ መሬት የምትፈስበት አንድ ቆንጆ ስፍራ አለ። ብዙ ፏፏቴዎችን ያየሁ ብሆንም ያ ፏፏቴ ግን አንድ የራሱ የሆነ የተለየ ነገር አለው። ድንጋዩ ጥቁር፣ በተለየ ሁኔታ የጠቆረ ነው . . . ናርማዳ አንድ ሺ ጅረት ሆና ትፈሳለች። አንድ ፏፏቴ ሳይሆን ተራራውን የመላ አንድ ሺ ፏፏቴዎች ነው።

ናርማዳ በፈጠረችው አንድ ሺ የቋጥኝ ክፍሎች ሳቢያ በአፈ - ታሪክ አንድ ሺ አመት እንደሞላት ይታመናል። አንድ በጣም የከበረ ንጉስ ነበር። ከናርማዳ ጋር መጋባት ይፈልግ ነበር። ምክንያቱ ደግሞ፣ «ሁሉም ወንዞች አግብተዋል። እናም ናርማዳ በግዛቴ ውስጥ ሳታገባ እንድትኖር አልፈቅድም» የሚል ነበር።

በዚያም ከናርማዳ ጋር ሊጋባ ይሄዳል። ነገር ግን ድንግልና፣ ንፅህና ነውና . . . የናርማዳ እርግማን ወደ ድንጋይነት ለወጠው። እነዛ አንድ ሺ የቋጥኝ ክፍሎች ምንም ሳይሆኑ የዛ ጭራቅ አንድ ሺ እጆች ናቸው። በእነዚያ እጆቹ ናርማዳን ሊያቅፉት ይሞክራል፣ እሷ ግን ታመልጠዋለች።

በየዓመቱ ይህ ውብ በዓል ይከበራል። እኔም እነዚያን አንድ ሺ እጆችና ናርማዳ በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ዓመታት እንዴት ድንግል ሆና እንደቆየች ለማየት ፈለግሁ። ናርማዳ የምትፈስበት መሬት ከዓለም ሁሉ ጥንታዊ እንደሆነ ብታዩ ትደነቃላችሁ። በመጀመሪያ ከውትያናስ



t.me/OLDBOOKSPDF

ውስጥ ነው የምትወጣው - ናርማዳ በምትፈስበት ተራራማ አካባቢ የሞቱ የባህር እንስሳትን ማየቱ ለዚህ ምስክር ነው። በናርማዳ እና በባህሩ መካከል በሺ የሚለኩ ማይሎች ርቀት አለ። በአንድ ወቅት ተራራው ከውቅያኖሱ ስር እንደነበር እርግጥ ነው። ውቅያኖሱ ሲቀንስ የመጀመሪያው የዓለት ቁራጭ ብቅ አለ። በዓለም ላይ ጥንታዊው ቋጥኝ እሱ ነው።

እጅግ ጥንታዊ የሆነውን ተራራ ልመለከት ፈለግኩ . . . ነገር ግን ወላጆቼን ብጠይቃቸው እምቢ እንደሚሉኝ አውቅ ነበር። በእነዚያ ሁሉ ቋጥኞች ሳቢያ አካባቢው አደገኛ ነውና። ብዙ ሰዎች ሞተውበታል። ወንዟ በድንጋዮች የተሞላች በመሆኗ ለመዋኘት አስቸጋሪ ነው። «እዚያ ከደረስክ የመዋኘት ፍላጎትህን መቋቋም ያቅትሃል» ብለውኝ ነበር።

ስለዚህም ወላጆቼን ሳልጠይቃቸው ዝም ብዬ ሄድኩ። የኔ መጥፋት ስላሳሰባቸው ለፖሊስ ከማመልከታቸውም በተጨማሪ እኔን ፍለጋ ሰዎች አሰማሩ፣ በየባቡርና በየአውቶብስ ጣቢያው እየዞሩ ጠየቁ። ሆኖም ሊያገኙኝ አልቻሉም። ከሶስት ቀናት ቆይታ በኋላ ተመለስኩ። በጣም ተናድደውብኝ ነበር። «የት ሄደህ ነው?» አሉኝ።

«የት?! ወደ በዓሉ ሄጄ ነበር» ስል መለስኩላቸው።

«ቢያንስ ልታስፈቅደን ይገባ ነበር» አሉኝ።

«መሄድ ስለፈለግኩ ነው ያልጠየቅኋችሁ። መሄድ ባልፈልግ ኖሮ እጠይቃችሁ ነበር። መልሳችሁ አይሆንም እንደሚሆን ስለማውቅ የማልፈልገው ነገር ብቻ ነው እንድትፈቅዱልኝ የምጠይቃችሁ። አንድ ነገር ማድረግ ስፈልግ ግን ሳልነግራችሁ አደርገዋለሁ። አሁን የፈለጋችሁትን ልታደርጉኝ ትችላላችሁ። ልትገርፉኝ ከፈለጋችሁ ትችላላችሁ። በሌላ መንገድ ልትቀጡኝ ከፈለጋችሁም ትችላላችሁ። እኔ ግን በዚሁ መልክ ነው የምቀጥለው። የምፈልገውን ነገር ፍፁም አልጠይቃችሁም። ለማድረግ በምፈልገው ነገር ላይ የማንንም ምክር አልጠይቅም» ብዬ እቅጩን ነገርኳቸው።

«አብደሃል ወይስ ምን ሆነሃል? የማትፈልገውን ነገር ብቻ ነው የምትጠይቀን?»


t.me/OLDBOOKSPDF

«በጣም ግልጽ እኮ ነው:: እግዜር እንኳን ይህን አላሰበውም:: ነገሩ ግልፅ ቢሆንም አምላክ እንኳን ዘንግቶታል:: ለአዳምና ሔዋን ፍጹም የጥበብ እና የሀላም ሀይወት ፍሬ እንዳትመገቡ> ብሏቸው ነበር:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሁሉም አባት ይህን መልስ ያስተጋባል:: ሁሉም አዳምና ሔዋን ደግሞ ይቃወማል::»

እናንተም አንድ ነገር ማድረግ ከፈለጋችሁ ሌላ ሃሳብ ከሌላችሁ በቀር ያለ ምንም ችግር ልትፈፅሙት ትችላላችሁ::

ነገሮችን፣ ቁሶችን እየሰራችሁ ነው:: እነሱ እሺም፣ እምቢም ሊሉ አይችሉም:: የፈለጋችሁትን ነገር ልታደርጓቸው ትችላላችሁ:: በሰው ልጅ ላይ ግን ይህን ማድረግ አትችሉም::

የፍቅር ግንኙነት እንዲኖራችሁ ከፈለጋችሁ የፖሊቲካ ስልጣናችሁን በሙሉ መርሳት እንዳለባችሁ ለመገንዘብ በሳል መሆን እንዳለባችሁ አለማወቃችሁ የራሳችሁ ስህተት ነው:: ሌላውን ልትጫኑ ወይም ጫና ሳይደረግባችሁ እንዲሁ ጓደኛ መሆን ትችላላችሁ:: በህይወታችሁ በጥቂቱ የተመሰጠ ልምድ ካላችሁ ይህን ማድረግ ትችላላችሁ:: እስከዚያ ግን አይቻልም::

አንድን ሰው መውደድ እጅግ አስቸጋሪ ነው፤ ምክንያቱም ፍቅራችሁን ማሳየት በጀመራችሁበት ቅፅበት ሌላኛው ወገን የበላይ መሆን ይጀምራል:: በእሱ ወይም በእሷ ላይ ጥገኛ እንደሆናችሁ ይሰማችኋል:: በአካልም በመንፈስም ተገገር ልትሆኑ ትችላላችሁ - መገዛት የሚፈልግ ደግሞ ማንም የለም:: ነገር ግን ሁሉም ስብእዊ መስተጋብሮቻችሁ ወደ ባርነት ይለወጣሉ::

ሆኖም አንድም ሃውልት ተገገርው ሊያደርጋችሁ አይችልም:: ከዚህ ይልቅ ጥበበኛ፣ ፈጣሪ፣ አርቲስት ያደርጋችኋል:: በመሀላችሁ ምንም ግጭት አይኖርም::

እውነተኛ የፍቅር ፈተና ያለው በሰዎች ዘንድ ነው::

የስብእዊ ግንኙነቱን ሚዛን ጠብቆ የሚመራ እሱ ብልህ ነው - ትልቅ ተሰጥኦ ይጠይቃልና:: አንድ ሃውልት መፍጠር ወይም አንድ ውብ ስዕል መሳል አንድ ነገር ነው፤ እነዚያ ስዕሎች «በሸራው ጥግ ላይ



መሆን አልፈልግም!» አይሉም:: ደግሞም ስዕሉን በፈለጋችሁበት ቦታ ብትሰቅሉት በዓት ታገኙታላችሁ:: በሰዎች ላይ ይህን ማድረግ ግን ቀላል አይደለም::

እያንዳንዱ ሰው የማንም ጥገኛ ያለመሆን ተፈጥሯዊ መብት አለው፤ ነገር ግን ሌሎችን ጥገኛ ለማድረግ ያለመሞከር ግዴታም አለበት:: ይሄን ጊዜ ጓደኝነት ያብባል::

ፍቅር ግልፅ ራዕይ ይሻል::

ፍቅር በአዕምሮአችሁ የሚገኙ ቅናት፣ ቂም፣ ሌሎችን የመጫን ፍላጎት የመሳሰሉ መጥፎ ነገሮችን በፍፁም አይሻም::

አንድ ታሪክ ሰምቼ ነበር . . . ሁለት ጥንዶች ሊጋቡ ፈልገው ወደ አንድ የጋብቻ ውል መፈፀሚያ ቢሮ ያመራሉ:: እናም ቅፆቹን ሞሉ:: ሴቷ ጓደኛዋን ተመለከተችው - ፍቅረኛሞች ናቸው፤ ነገር ግን የቤተሰቦቻቸውን ግፊት ተቋቁመው ነው ወደዚህ ቢሮ የመጡት:: በሀገራችን ጋብቻ የሚፈፀመው በጋብቻ ውል ቢሮ ውስጥ አይደለም:: በሀንድ፣ ጋብቻ የሚፈፀመው በጋብቻ ውል ቢሮ ውስጥ አይደለም:: ቤተሰብን፣ ማህበረሰቡን አንድ ነገር ካደረጉ ብቻ ነው በህጋዊ መንገድ የሚፈፅሙት::

እነዚያ ሁለት ሰዎች በጥልቅ ፍቅር ውስጥ ሳይሆኑ አይቀሩም:: ለዚያም ነው የማህበረሰቡን፣ የሃይማኖታቸውን፣ የወላጆቻቸውን፣ የቤተሰቦቻቸውን ጫና ተቋቁመው እዚህ የተገኙት:: ሁሉንም ነገር ተጋፍጠው ሊጋቡ ነው::

ሴቷ ቅጹን ከሞላች በኋላ ፍቅረኛዋ ቅፁን ሲሞላ እየተመለከተችው ቆየችና በድንገት ወደ ውል አስፈፃሚው ዞራ «እሁትን ፍቺ እፈልጋለሁ» አለች::

«ምነው? የጋብቻውን ቅፅ ሞልተሻል:: የሚገርሙ ጊዜያችሁ እንኳን ገና አላሳለፋችሁም:: በእርግጥ ማህተም በሚያስፈርጉበት ጋብቻውም አልተፈፀመም:: እንዲህ በድንገት ፍቺ የፈለግሽበት ምክንያት ምንድነው?» ሲል ጠየቃት::

«ይህን ሰው አልወደውም!» አለች::



t.me/OLDBOOKSPDF

«የሚደንቅ ነው! - እንድትጋቡ እዚህ ድረስ ያመጣሽው እቺ አይደለሽም እንዴ?»

«አዎ፣ እኔ ነኝ ያመጣሁት። እወደው ነበር፣ ሆኖም ግን ቅዑን ሳየው . . . በትልልቅ ፊደላት ነው የፈረመው! እኔም ስፈርም ሲያየኝ ነበር። እኔ እንደ ሁልጊዜው ነው የፈረምኩት። እሱ ግን ከተሰመደ ፊርማው በሶስት እጥፍ አሳድጐ ነው የፈረመው - የቅፁ ግማሽ በፊርማ የተሞላ ነው። ተዕዕኖውን፣ ሃይሉን ሊያሳየኝ ፈልጓልና ከዚህ ሰው ጋር መኖር አልሻም» በማለት መለሰችለት።

«ስለዚህ ፍቺ እያስፈልግም ማለት ነው» አለ ሙላ አስፈፃሚው። «ቅፃቹ ላይ ስላልፈረምኩባቸው እዚያ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ውስጥ ጨምሯቸውና ወደምትሄዱበት ሂዱ።»

ያ ትንሽ ነገር፣ የሰውየው ፊርማ፣ አንድ አመልካች ነበር፣ ሰውየው በወንድነቱ እንደሚኩራራ ያሳያል።

የእናንተስ ህይወት እንዴት ነው? ያው ሁሉም ነገር ችግር፣ ሁሉም ነገር ግጭት ነው። ምክንያቱ ደግሞ «እንዴት ማፍቀር እንደምንችል እናውቃለን» የሚለው የተሳሳተ እምነታችን ነው። ግን እናውቅም። ከእንስሳት ነው የመጣነው፣ እንስሳት ደግሞ አያፈቅሩም።

ፍቅር በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ አዲስ ክስተት ሆኖ የመጣ ነገር ነው። እንስሳት የሚራቡ ቢሆንም አይፋቀሩም። በጉሾች ውስጥ ሮሚዮና ዡልየትን፣ ለይላና ማጅኑን፣ ሺሪን እና ፋርሃድን፣ ሶኒና ማሂቫልን ፈልጐ ማግኘት አይቻልም። ጉሾች በእንደዚህ አይነቱ የፍቅር ነገር የታደሉ አይደሉም። በምድር የሚኖሩት እየተራቡ ነው። ተፈጥሮ ደግሞ በጉሾች ፍፁም ትረካለች። ተፈጥሮ የሰውን ዘር ለማጥፋት ብትጥርም ጉሾችን፣ አህዮችን እና ዝንጀሮዎችን ለማጥፋት አትሞክርም። እነሱ ከነጭራሹ ችግር አይደሉም።

ፍቅር በሰው ልጅ ጥልቅ እሳቤ የመጣ አዲስ ክስተት ነው። በትምህርት ነው የሚገኘው።

የተዋቡ ስዕሎችን፣ ግጥሞችን፣ ሃውልቶችን፣ ሙዚቃዎችን፣ ዳንሶችን መፍጠር ትችላላችሁ። ወደ ሰው ስትመጡ ግን በሌላኛው ወገን



ሌላ አይነት አስተሳሰብ እንዳለ ልትረዱ ይገባል። የምታፈቅሩትን ሰው ልታዝዙት ይገባል። ስላም ነው ከሰዎች ጋር ጥብቅ ቁርኝት የማትፈጥሩት።

ስለዚህ ስለ ሰዎችና ፍቅር ረስታችሁ ተመሰጡ። ይሄን ጊዜ ባለ ራዕይ፣ ግልፅ እና በሃይል የተሞላ ሰው ትሆናላችሁ።

ፍቅር መጠን ብዙ ሃይላችሁን ማጋራት ነው። ብዙ ሃይል ተሸክማችኋል። ከምትወዷቸው ሰዎች ጋር ይህን መካፈል አለባችሁ።

የአሁኑ ፍቅራችሁ - እናንተ ፍቅር የምትሉት - መጋራት ሳይሆን መናጠቅ ነው።

እያንዳንዱ ሰው የበለጠ ፍቅር መንጠቅ ይፈልጋል። ሚስት «አትወደኝም!» ማለቷን ትቀጥላለች። ባልም በበኩሉ «የምትወጂኝ አይመስለኝም!» ይላል።

ሙላ ናስሩዲን ከሚስቱ ጋር ወደ አንድ ፊልም ቤት አምርቶ ነበር። በፊልሙ ላይ ጀግናው ጀግናይቱን በፍቅር ሲስማት ሚስቱ ባየች ጊዜ ባሏን ጉንተል አደረገችውና «እንዲህ አድርገህ አታውቅም» አለችው።

«አትረብሺኝ። ያቺ ሴት ሚስቱ አይደለችም» ሲል መለሰላት፣ ሙላ ናስሩዲን።

«ተሳስተሃል! ጥንዶቹን አውቃቸዋለሁ። ያቺ ሴት የጀግናው ሚስት ናት» አለች የናስሩዲን ሚስት።

«እመቤቴ፣ ሰውየው እኮ ተዋናይ ነው! እንዲህ ማድረግ የሚችለው ተዋናይ ብቻ ነው። እኔ ተዋናይ ስላልሆንኩ ይቅር ልትይኝ እፈልጋለሁ። ሚስቱ ከሆነች . . . ሌላ ናት ማለት ነው። እኔም የሌላ ሰው ሚስት እንዲህ መሳም እችላለሁ። የራሴን ሚስት ግን . . . ? የራሱን ሚስት እንዲህ የሚስም በሃገራችን እንዲህ ያለ ታላቅ ተዋናይ የለም» አላት፣ ሙላ ናስሩዲን።

እናንተም ፍቅርን በዚህ መልኩ የምታዩት ከሆነ የፍቅርን ትርጉም መለወጥ አለባችሁ። ከሌላው የምታገኙት ነገር አይደለም።

የፍቅር ታሪክ ያለ ነው - ሁሉም ሰው በተቻለው መጠን ከሌላው ሊያገኝ የሚፈልገው ነው። ሁሉም ሊያገኙት ስለሚፈልጉት ማንም አያገኘውም።

ፍቅር የምትሰጡት እንጂ የምትቀበሉት አይደለም።

ግን ያላችሁን ብቻ ነው የምትሰጡት።

ለመሆኑ በውስጣችሁ ፍቅር አለን? ይህን ጥያቄ አንስታችሁ ታውቃላችሁ? ወርቃ ተቀምጣችሁ አስተውላችሁት ታውቃላችሁ፣ ለሌሎች ልትሰጡት የምትችሉት የፍቅር ሃይልስ አላችሁን?

የላችሁም፣ ማንም የለውም። ይህ ሳይኖራችሁ ግን በፍቅር ግንኙነት ውስጥ ትገባላችሁ። ሁላችሁም አስመሳይ ናችሁ። ካትን መፍጠር የሚችሉ ይመስል ያስመስላሉ። «አንዴ ከተጋባን አንድ ሺው የአረብ ምሽቶች ይረሱና የእኛው ምሽት ወርቃማ ይሆናል» ይባባላሉ።

የምትሰጡት ምንም ነገር እንደሌላችሁ ግን አታውቁም ... እነዚህን ሁሉ ነገሮች እንደምትሰጡ ብትናገሩም። ሌላኛውም ወገን እንዲሁ ያስባል። አንዴ ከተጋባችሁ በኋላ ከአንዲት የሀንዳውያን ምሽት ይልቅ አንድ ሺ የአረብ ምሽቶችን ስለምትጠብቁ ችግር ይፈጠራል! ይኼን ጊዜ ብስጭት ይከሰላል። ጥላቻው ቀስ በቀስ መርዛማ ይሆናል።

> **ፍቅር የምትሰጡት እንጂ የምትቀበሉት አይደለም።**
> **ግን ያላችሁን ብቻ ነው የምትሰጡት።**

ሁሉም ሰው የመከዳት ስሜት ስለሚሰማው ፍቅርን በቀላሉ ወደ ጥላቻ መለወጥ ይቻላል። በባህር ዳርቻዎች፣ በፊልም አዳራሾች፣ በዳንስ ቤቶች እንደኛው ፊታችሁን ታሳያላችሁ። ለግማሽ ወይም ለአንድ ሰዓት ያህል እጅ ለእጅ ተያይዞ በባህር ዳርቻዎች በመቀመጥ ስለ ህይወት ውበ ውበቱን ማሰብ ቀላል ነው። አንዴ ከተጋባችሁ በኋላ ግን የጠበቃችሁት ያለማችሁት ነገር በሙሉ መቅንን ይጀምራል።

የሁለት ጥንዶች ታሪክ ሰምቼ ነበር። «መልካም ጋብቻ» የሚል ጽሑፍ የሰፈሩባቸው ሻንጣዎችን ይዘው ወደ አንድ ሆቴል እየገቡ ነበር። የጫጉላ ጊዜያቸውን እያሳለፉ ነው። ሰውየው ወደ አልጋው እንደገባ ነበር



ይቶን በአንሶላ የሸፈነው። ሚስት ለእንቅልፍ ለመዘጋጀት ወደ መታጠቢያ ቤት እያመራች ነው።

«አስቤን መብራቱን አጥፋው። መብራት በርቶ መተኛት አልችልም» አለ ባል።

«አምስት ደቂቃ ቆየኝ። መጣሁ፣ አጠፋዋለሁ» ስትል መለሰች ሚስት።

«መጀመሪያ አጥፋው!»

ጭቅጭቁ ተጀመረ። «ምነው! . . . አምስት ደቂቃ እንኳን መታገስ አትችልም? ለአምስት ዓመት ያህል ጠብቀኸኛልኮ»

«ሁሉንም ለጊዜው ረስተሽ በመጀመሪያ መብራቱን አጥፋው!»

«እንዲህ ማድረግ አልችልም። አልጋው ውስጥ ከገባሁ በኋላ ነው የማጠፋው።»

«ይገርማል . . ምን ሆንሽ ነው?»

«ምክንያታዊ ሰው ከሆንክ በመጀመሪያ ያንተን ምክንያት ንገረኝ - አምስት ደቂቃ ብትታገስ ምን ይጎድልብሃል?» በማለት ሚስት ጠየቀች።

«እውነቱን ብነግርሽ የተሻለ ነው . . . አብረን መኖር ከጀመርን ሃያ አራት ሰዓታት ሊሞላን ነው። በብርድ ልብስ ተሸፍኜ እስከመቼ እበልቀጥላለሁ?»

«ምን ማለትህ ነው?» አለችው።

«አንዱ እግሬ የሀሰት (አርቴፊሻል) ስለሆነ ነው እንዳታይብኝ ጨለማውን የፈለግኩት» ብሎ መለሰላት።

«ይህማ ጥሩ ነው። የእኔም ፀጉር፣ ጥርሶች እና ጡቶች አርቴፊሻሎች ናቸው. . . አሁን እንግዲህ በግልጽ ስለተነጋገርን ችግር የለም። ይብራ ወይስ ይጥፋ?»

ሰውየው ፀጉሯ፣ ጥርሶቿ፣ ጡቶቿ የሃሰት መሆናቸውን ሲሰማ ብሎ በመሳሳት ፈረጠጠ። ከዚያ በኋላ እምጥ ይግባ ስምጥ ያየው ሰው አልተገኘም። ይህቺን ሴት ለማግባት ያልፈነቀለው ድንጋይ ግን አልነበረም



t.me/OLDBOOKSPDF

ሰብአዊ ግንኙነቶች መግባባትን ይጠይቃሉ።

የእኔ ምክር ተመስጦ ነው፣ የበሰጠ ፃጥታማ፣ የተረጋጋ፣ የሰከነ መሆን። ርጋታ በውስጣችሁ ይስፈን።

ይህም በብዙ መንገዶች ይጠቅማችኋል። ከፍቅር ባሻገር የተሻሉ ጥበቦችን መፍጠር እንድትችሉ ያስችላችኋል። ሰብአዊ ፍጡራን መውደድ ያልቻለ ሰው . . እንዴት ሊፈጥር ይችላል? ምንስ ሊፈጥር ይችላል?

ፍቅር የሌላት ልብ መፍጠር አትችልም። ማስመሰል እንጂ መፍጠር አትችልም።

ሁሉም ነገር የሚፈጠረው ከፍቅር፣ ከመግባባት እና ከፀጥታ ውስጥ ነው።



# ማንም እውነትን አስቀድሞ አያውቅም፤ ሁሉም ሰው መጀመሪያ የሚያውቀው ውሸትን ነው

ተወዳጁ ባግዋን፦

ምንም ነገር ግልፅ ባይሆንልኝም እውነት አንተ ዘንድ እንዳለች እንዴት ግልፅ ሲሆንልኝ ቻለ? እንዴት… እንደሆነ ባላውቅም አይኖችህ ውስጥ ይታየኛል። በማንነትህ ውስጥ ይሰማኛል።

እጅግ መሰረታዊ ከሆኑ ጥያቄዎች መካከል አንዱ ይህ ነው። እውነት ምን እንደሆነች አስቀድሞ የሚያውቅ የለም።

እውነትን ያወቀ ግን ነገሮች ይገለፁለታል። እስካሁን እውነት ነው ብሎ ሲያምነው የቆየው ነገር እውነት እንዳልሆነ ይገነዘባል። ለአይኖቹ አስተዋይነትን፣ ለማንነቱ እርጋታን፣ ለቃላቱ ሃይልን፣ ለህይወቱ ትኑን አልሰጠውምና።

ውሸት ባዶ ነው።

እውነት ምን እንደሆነ ባታውቁም፣ እውነትን ስትረዱት ወዲያውኑ ውሸት ምን እንደሆነ ትረዳላችሁ። ውሸት ምን እንደሆነ ስትገነዘቡ ደግሞ በውስጣችሁ እውነታው ብቻ ይልባችኋል። በእኔ ዓይኖች ውስጥ የምታዩትን እውነት በእናንተም ዓይኖች ውስጥ አለ - አልቀሰቀሳችሁትም እንጂ።

መጀመሪያ ውሸትን አባርሩት። ከዚያ ዓይኖቻችሁ ያንኑ እውነት ያያሉ ቃላቶቻችሁ ተመሳሳይ ዜማ፣ ማንነታችሁም ተመሳሳይ ድባብ ይኖራቸዋል።

ማንም ሰው እውነትን አስቀድሞ አያውቅም። ሁሉም ሰው መጀመሪያ የሚያውቀው ውሸትን ነው። ውሸት፣ ውሸት በመሆኑ



t.me/OLDBOOKSPDF

ምክንያት ስታስወግዱት፣ የቢያኔ ዘእሾችሁ ይወጣል። ውሸት ከሌላ ደግሞ የሚቀረው እቡነት ነው።

ውበትን አሳያችሁ ይሆናል። ነገር ግን ፀሀይዋ ከአድማሱ ማዶ ከነድምቀትዋ ስትጠልቅ ስትመለከቱ . . . ትዕይንቱ ውብ ነው ብሉ ከመናገር ይልቅ አንዳች የመደመም ስሜት ይሰማችኋል። አንድ የሆነ ነገር ልባችሁን እንደነካ፣ ምናልባትም ማንነታችሁ ውስጥ ጠልቆ እንደገባ ይሰማችኋል። ይህን ስታስተውሉ ማሰብ ትጀምራላችሁ - ትዕይንቱ አስደማሚ፣ ውስጥን ዘልቆ የሚነካ፣ ደንሱ፣ ዝፈኑ የሚያስኛችሁ ከሆነ ያለፈው መላው ህይወታችሁ ምን ነበር ማለት ነው? ከዚህ በፊት የምትደንሱ ቢሆንም ያኛው ማህበራዊ (የጋራ) ዳንስ ነበር። ዳንሱ ከውስጣችሁ የወጣ ሳይሆን የማህበረሰቡ ልማድ ነበር።

ሰዎች እንድትዘፍኑ ይጠይቁዋችኋል . . . እናንተም የዘፈኑን ወይም የሙዚቃውን ቴክኒካዊ ጉን የምታውቁ ቢሆንም ቴክኒካዊ ጉኑ እውነተኛ ነገር አይደለም። አፋችሁ ቢዘፍንም ልባችሁ እየዘፈነች አይደለችምና። ጓደኞችሁን ለማስደሰት ብቻ በጨዋነት እየተንቀሳቀሳችሁ ነው። ፀሃይዋ ስትጠልቅ አይታችሁ መዝፈን በጀመራችሁ ጊዜ ግን . . . ማንም ጠይቆአችሁ አይደለም፣ ፀሃይዋ አልጠየቀቻችሁም፣ አጠገባችሁም ማንም የለም። ራሳችሁም ዘፈኑ ከየት መጣ?! ብላችሁ ትደነቃላችሁ። እንድትደንሱ ያስገደዳችሁ ምንድነው? ይህን ዳንስና ዘፈን እንዳወቃችሁ ዳንሱና ዘፈኑ የውሸት ይሆኑባችኋል። እናም ለመጀመሪያ ጊዜ እውነት ምን እንደሆነ ትረዳላችሁ።

በምስራቃውያን ዘንድ የጉተማ ቡድሃን ወይም የማሃቪራን አይኖች ለማየት ብዙ ማይሎች በእግር መጓዝ ጥንታዊ ልማድ ነው። ለሁለት ደቂቃዎች ያህል ከጉተማ ቡድሃ ጉን ተቀምጣችሁ እግሮቹን በእጆቻችሁ ለመደባበስ በሺ የሚቆጠሩ ማይሎችን ትጓዛላችሁ።

ሰዎቹ በሙሉ ሞኞች ሆነው አይደለም ይህን የሚያደርጉት - እነዚህ ሁለት ደቂቃዎች ህይወታቸውን እንደሚለውጧቸው ስለሚያውቁ እንጂ። በነዚህ ሁለት ደቂቃዎች እውነተኛ ሰው ማለት ምን እንደሆነ ያውቃሉ። እግሮቹን በመንካት መንፈሱ ተሰምቷቸዋል፣ በፍቅሩ



t.me/OLDBOOKSPDF

ውሃ ታጥበዋል፤ በአይኖቹ ውስጥ መላው ዓለም ሲከፈት አይተዋል፤ እናም ለወራት ያህል የተጓዟቸው እነዚህ አንድ ሺ ማይሎች ዋጋ ነበራቸው::

ጉተማ ቡድሃ በሞተበት ዕለት ከመላው ሃገሪቱ የተውጣጡ አስር ሺ የሚሆኑ አማኞች መጥተው ነበር:: እሱን የሚያዩበት የመጨረሻዋ ዕለት እሷ ነበረች:: እሱ ካለፈ በኋላ ግን እንዲህ አይነት ሰው ከነመኖሩም አያምኑም:: ጉተማ ቡድሃ ታሪካዊ ሰው መሆኑን አይቀበሉም::

አናንዳ ከጉተማ ቡድሃ ጋር ለአርባ አመታት ያህል በወዳጅነት ቢቆይም እስካሁን ድረስ አልተገለፀለትም:: ከእሱ በኋላ የመጡ ግን ተገልፆላቸዋል:: አናንዳ አንድ የሆነ ቦታ ላይ ተቀርቅሮ ነበር:: ይህንን ጥያቄም ብዙ ጊዜ ሲያነሳ ነበር::

«የት ጋ እንደቆምክ አውቃለሁ:: ለመጀመሪያ ጊዜ እዚህ ስትመጣ ነው ያወቅኩት» በማለት ጉተማ ቡድሃ መልሶለት ነበር::

አናንዳ የጉተማ ቡድሃ አጎት - ወንድም ቢሆንም በዕድሜ ይበልጠዋል:: ሰተመሰጠ በመጣ ጊዜ ቡድሃን «ከተመሰጥኩ በኋላ ደቀ መዝሙርህ እሆናለሁ:: ያልከኝን ሁሉ ያለ ምንም መጠራጠር አፈፅማለሁ:: ከዚያ በፊት በመጀመሪያ ሶስት ነገሮችን ቃል እንድትገባልኝ እፈልጋለሁ:: ታላቅ ወንድምህ እንደመሆኔ አሁኑኑ ቃል እንድትገባልኝ እሻለሁ:: እስከዛው ደቀ - መዝሙርህ አይደለሁም» ብሎ ይጠይቀዋል::

ጉተማ ቡድሃም ይስቅና «እሺ! ምንድናቸው ቅድመ ሁኔዎችህ?» ይለዋል::

«ይሄን ያህልም ከባድ አይደሉም:: ቀላል ናቸው:: አንዱ ሁልጊዜ አብሬህ መሆን መፈለጌ ነው:: ወደ ሌላ ዓለም፣ ወደ ሃገሪቱ ራቅ ያለ ክፍል በፍፁም እትልከኝም:: ሃያ አራት ሰዓት ከአንተ ጋር እሆናለሁ ... በምሽት እንኳን በአንተ ክፍል ውስጥ አብሬህ ነው የምተኛው:: ትቀበላለህ?»

«እሺ» ይላል ጉተማ::

«ሁለተኛው ቅድመ - ሁኔታዬ ደግሞ ጥያቄዬ ምንም የማይረባ ቢሆን መመለስ ይኖርብሃል የሚል ነው:: ‹ይህማ ትርጉም አልባ


t.me/OLDBOOKSPDF

የማይረባ ነው» ማለት አትችልም። ጥያቄዬን አለመመለስ፣ ርዕስ - ጉዳዩንም መቀየር አትችልም። የግድ መመለስ ይኖርብሃል። ለስተኛው ደግሞ፣ እንቅልፍ ላይ ሆነህ እንኳን ሰው ይገድ ብመጣ አንተን እንዲያገኝህ እና እንዲያይህ ነውና ያመጣሁት እምቢ አትልም።»

ቡድሃም «በጣም ጥሩ» ይልና አናንዳ ደቀ - መዝሙር እንዲሆን ይደረጋል።

ከአርባ ዓመታት በኋላ ቡድሃ በህይወቱ የመጨረሻ ዕለት «በጠቢብነትህ ላይ ቅድመ - ሁኔታ በማስቀመጥህ - የአጉት - ወንድም ተራ ግንኙነት ስለመሰረትክ ነው እዚያው ተሰንቅረህ የቀረኸው። የጉተማ ቡድሃ ታላቅ ወንድም መሆንህን መርሳት ስላልቻልክ ነው» አለ።

«ደቀ - መዝሙር ብትሆንም በውስጥህ እንደ ታላቅ ወንድም ነህ። ህንድ ውስጥ ደግሞ እድሜ ይከበራል። ግን አታስብ። በሞትኩ በሃያ አራት ሰዓታት ውስጥ ይገለፅልሃል። በመሞቴም ትጠቀማለህ...

«ለአርባ አመታት እንዲገለፅልኝ ስትጥር ነበር - ግን ምንም አልተከሰተም። ለአንተ ስል ሙት ቢሉኝ እንኳን እሞታለሁ።» አናንዳ አለቀሰ።

«ጊዜ አታባክን። እንባህንም አትርጭ። ታላቅ ወንድሙ ነኝ የሚለው ኩራትህ አይኔን እንኳን እንድታይ አላስቻለህም። እግሮቼን በእጆችህ ብትዳስስም ምንም አይነት ግንኙነት አይታየኝም» አለው ቡድሃ።

ቡድሃ ሞተ። በሃያ አራት ሰዓታት ውስጥም አናንዳ ተገለፀለት። ለአርባ ዓመታት ከወንዝ ዳር ተቀምጦ ሲጠማ ነበር።

እናንተም እኳሴን ሳይሆን እኔን ማየት ከቻላችሁ ... አይኖቼን ማየት፣ ህሊናዬን መረዳት ከቻላችሁ፣ በልባችሁ አንድ ነገር የሚሉ ከሆነ እስካሁን የኖራችሁት ህይወት የውሸት እንደሆነ ትገነዘባላችሁ።

አንዴ ትንሿን እውነት ካገኛችሁ ወደኋላ መመለስ አትችሉም። ያለው መንገድ አንድ ብቻ ነውና በዚያ መንገድ መጓዝ ትቀጥላላችሁ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከእኔ አይኖች ውስጥ ያያችሁትን ሌሎችም በእናንተ ውስጥ ይመለከቱታል፡፡ በእኔ መኖር የተሰማችሁን ሌሎች በእናንተ አይኖች መኖር ይሰማቸዋል፡፡ እኔ ያገኘሁትን ሁሉ ታገኛላችሁ፡፡ አሁን ግን ሸንጣዎቻችሁ ተቆልፍዋል፤ አልተከፈቱም፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# ማንም አለመሆን ታላቅ ድል ነው!

**ተወዳጁ ባገዋን፣**

**በራስ እርግጠኛ መሆን፣ የበለጠ ጠንካራ መሆንና በተመለጦ ዘና ማለት እመኛለሁ። በተቃራኒው ደግሞ ብዙ ስጋት ባይኖርብኝም የበለጠ ባዶነት፣ እርግጠኛ ያለመሆን እና የበለጠ ተጋላጭ የመሆን ስሜት ይሰማኛል። ይህ እንዴት ሲሆን ቻለ?**

ሁሉም ፍላጎት ወደታሰበው ግብ አያደርስም፣ በተቃራኒው አቅጣጫ ይወስዳል እንጂ። ልዩ መሆን ይፈልጋሉ? ተራ መሆንዎን ተቀብለዋል ማለት ነው። ልዩ የሆነ ሰው ልዩ መሆን አይፈልግም፣ ልዩ መሆኑን እንኳን አይገነዘብም።

የፈለጉትን ቢፈልጉ አንድ ነገር እርግጥ ነው፣ እርስዎ ያን አይደሉም። እነዚህ ፍላጎቶች እና ምኞቶች ታድያ ከየት መጡ? ከማስመሰል። በዙሪያዎ ብዙ አይነት ሰው ያያሉ። አንዱ ሃብታም ነው፣ አንዱ ምሁር ነው፣ አንዱ የትግል ስፖርተኛ ነው፣ አንዱ በክሰኛ ነው። እርስዎ ግን ምንም ባለመሆንዎ ይጉዳሉ። ስለ ህይወት ባለዎ የተሳሳተ አመለካከት ሳቢያ ይጉዳሉ።

ስለዚህ በውስጥዎ የተወሰኑ ጥቂት ነገሮችን ማስቀመጥ ይኖርብዎታል። አንደኛ፣ አሁን ከሆኑት ሌላ ምንም ሊሆኑ አይችሉም። ከማንነትዎ ውጭ ሌላ መሆን የሚጥሩ ከሆነ መሆን ያለብዎትን ሳይሆኑ ይቀራሉ።

አንድ የጽጌረዳ አበባ አንድ የባህር ተክል መሆን እንደሚፈልገው ማለት ነው። መላ ሃይሉን ይህን ተክል በመሆን ላይ ያውለዋል፣ ስለ ጽጌረዳ አበቦች ይረሳል። መላ ሃይሉን በተቃራኒ አቅጣጫ ላይ ያውለዋል። ዘርና የባህር ተክል የመሆን አቅም ስለሌለው የባህር ተክል አይሆንም። አንድ ነገር እርግጥ ነው፣ የጽጌረዳ አበባ እንኳ መሆን አይችልም።

የባህር ተክል ከጽጌረዳ አበባ ይበልጣል ያለው ደግሞ ማነው? ሁለቱም ውብ እና ተፈላጊ ናቸው። ትንሿ የሳር ሰበዝ እንኳን በሰማይ የሚገኘውን ትልቅ ኮከብ ያህል ትፈለጋለች። መላው ዩኒቨርስ አንድ ሆነው ቅንጅት ነው። እዚህ የማይፈለግ ነገር የለም። በጣም የሚፈለጉ ሰዎች ራሳቸውን የተቀበሉና በሌሎች ሳይሆን በራሳቸው የሚኮሩ ናቸው።

ነገር ግን ማንም አለመሆን ታላቅ ደስታ የሚያጎናፅፍ ነው። እናም ልዩ ለመሆን አትሞክሩ። ተፈጥሮ በወሰደቻችሁ ተጓዙ። ወደ ላይ አትውጡ። ይህን ካደረጋችሁ ውድቀታችሁን ታረጋግጣላችሁ። ከፍሰቱ ጋር ፍሰሱ፣ ጭራሽ አትዋኙ፣ ጅረቱ እያስደሰተ፣ እያስደነሰ ወደ ውቅያኖሱ ይወስዳችኋል።

እኔን በተመለከተ፣ ከልጅነቴ ጀምሮ አንድ ነገር እየተነገረኝ ነው ያደግሁት . . . ሁሉም ሰው ይህን ሲለኝ ነበር፣ «ጠባይህ፣ አኗኗርህ፣ መላው ነገርህ ወደ ማንምነት የሚለውጥህ ነው።»

ትክክል ነበሩ! አሁንም ቢሆን ማንም አልሆንኩም። እኔም ማንም መሆን አልፈልግም ነበር። ማንም በመሆኔ ስለማልሰጋ እና ስለማልጨነቅ ማንም መሆን አልፈለግኩም። ጫና ስለሌለብኝ ህልም እንኳን የለኝም።

ከቅፅበት ወደ ቅፅበት እየኖርኩ ነው። ህይወት ደግሞ ደስታ ናት።

ማንም ባለመሆኔ መላውን ዩኒቨርስ በውስጤ መያዝ እችላለሁ። ማንም፣ ማንም ያለመሆን ወሰን የለውምና።

የበለጠ ልዩ በሆናችሁ ቁጥር ግን የበለጠ ውስን ትሆናላችሁ፣ የበለጠ ትኮማተራላችሁ። የበለጠ ልዩ በሆናችሁ ቁጥር የበለጠ አስቸጋሪ ትሆናላችሁ። የበለጠ ልዩ በሆናችሁ ቁጥር የበለጠ ከህይወት ጋር ትጣረሳላችሁ - ህይወትን የሚያሸንፍ ደግሞ የለም።

አንድ ብቻ ድል አለ፡፡ ማንም ያለመሆን፣ መላውን ዮኒቨርስ በውስጥ አቅፎ የመያዝ ድል፡፡ እናንተ ባለድል ናችሁ፡፡ እናንተ ባታውቁትም አዕዋፋቱ በዝማሬያቸው ይመሰክሩላችኋል፡፡ አበቦች «አዎ፣ ሆን» ይላሉ፡፡ ከእናንተ በቀር መላው ዮኒቨርስ ያውቀዋል፡፡

ስለዚህ ልዩ አለመሆናችሁ ይመረጣል - እንዲያ ከሆናችሁ የተባረካችሁ ትሆናላችሁ፡፡

አሁን መንገዱን ሞክሩት፡፡ አቋራጭ በመሆኑ የትም መሄድ አያስፈልጋችሁም - አሁን እዚህ በመቀመጥ ብቻ ማንም አለመሆን ትችላላችሁ፡፡

ስለነገ ምንም ቃል አልገባላችሁም፡፡

ስለዚህ ቅፅበት ብቻ ነው ቃል የምገባላችሁ፡፡

ማንም ሳትሆኑ ረጋ በሉ እና ውበቱን፣ እውነቱን፣ ክብሩን ተመልከቱ፡፡



# ወሲብ ሲጠፋ ወደታች ይወርድ የነበረው ኃይል ወደ ላይ መውጣት ይጀምራል

ተወዳጁ ባገዋን፡-

በሁለት መንገድ (መልኩ) ጉድተኸኛል፡፡ በአርባ ሁለት አመቴ ስሪ ፈት የመሆኔ ነገር እኔን እና ፍቅሬን የፈላ ውሃ ውስጥ ከትኖል፡፡ የሁሉንም ፀባይ (ባህሪ) ዋስትና እና ማረጋገጫ በፅሑፍ እንድሰጣት ትፈልጋለች፡፡

በሌላ በኩል ተጨማሪ ዘጠኝ አመታት ካለኝ ያ የነገርከኝ ቁርጥ ቀን የወሲብ ህይወቴ ብቻ ሳይሆን የእኔ መጨረሻ ነው፡ አራት ነጥብ ነው!

ተወዳጁ መምህር፣ ከከተትከኝ ከዚህ አጣብቂኝ ልታወጣኝ ይገባል፡፡

ሚላሬፓ፣ የእኔ ስራ ሰዎችን አጣብቂኝ ውስጥ መክተት ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ ሰዎችን ማውጣት የእኔ ስራ አይደለም፡፡ የአንተን ጉዳይ ግን በተለየ ሁኔታ እየዋለሁ፡፡ በጥያቄህ ውስጥ ያልገባህ አንድ ነገር ብቻ ነው፡፡ ይህም አራት ነጥብ የሚለው ነው፡፡

አራት ነጥብ ሳይሆን፣ ነጠላ ሰረዝ ነው፡፡

ሁሉም ነገር ይቀጥላል፡፡ የሚቀጥለውም በከፍተኛ እና በተሻለ ደረጃ ነው፡፡

ወሲብ በጠፋበት ቅፅበት ህይወት አይኖርም ማለት አይደለም - ወሲብ እና ህይወት አንድ ናቸው የሚል የተሳሳተ ሀሳብ ከሌለህ በቀር፡፡

ወሲብ እና ህይወት አንድ አይደሉም፡፡

ወሲብ መጥፋት በሚጀምርበት ቅፅበት በውስጣችሁ ታላቅ መንፈሳዊ ለውጥ(አብዮት) መካሄድ ይጀምራል፡፡ ወደታች ይወርድ የነበረው ሀይል ወደላይ መውጣት ይጀምራል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

ይህ ሀይል እናንተን ወደ ምድር ያመጣ ሀይል ነው:: ወደ ሌላ ዓለምም የሚወስዳችሁ ሀይል ነው:: በተለያዩ ሀይማኖቶች የተለያየ መጠሪያ አለው:: ፍጹም የደስታ መንፈስ ውስጥ መግባት፣ ገነት፣ የፈጣሪ አገር. . . ወዘተ በሚሉ የተለያዩ ስያሜዎች ይጠራል::

ያለው ሀይል ግን የወሲብ ሀይል ብቻ ነው::

ልታጠፉት፣ ልታበላሹት፣ አሽቀንጥራችሁ ልትጥሉት፣ ወይም የበለጠ ልታስተካክሉት፣ የበለጠ ብልህ ልትሆኑበት እና ልትሰውጡት ትችላላችሁ::

የጥፋተኝነት ስሜት የእናንተ አካል (ክፍል) ባለመሆኑ ሊለወጥ አይችልም ብያለሁ:: እናንተ የተሰራችሁት ከወሲብ ሀይል በመሆኑ ወሲብ ሊለወጥ ይችላል:: በሰውነታችሁ ውስጥ ያሉት ሴሎች በሙሉ የወሲብ ሴሎች ናቸው::

ስለዚህ አትጨነቅ:: እኔን ስታይ ጭንቀትህን መጣል ትችላለህ:: እኔ አልሞትኩም:: አንተ የተናገርከውን አራት ነጥብ ያሰፍኩት ሲሆን ነጠላ ሰረዝ መሆኑንም ተረድቻለሁ::

አራት ነጥብ ሊለወጥ አይችልም:: ያለው ንኡስ ሰረዝ ወይም ነጠላ ሰረዝ ነው:: ህይወትም ያለ አራት ነጥብ ሂደቷን ትቀጥላለች::

በአርባ ሁለት አመትህ የወሲብ ህይወትህ ያበቃል ብላ ስለምትጨነቀው አፍቃሪህስ?

የምትፈልጋቸውን ሰነዶች በሙሉ ስጣት:: ምክንያቱም የአንተን አፍቃሪ አውቃያታለሁ:: ከአንተ አስቀድማ ነጠላ ሰረዙ ጋ ትደርሳለች::

እንደውም ችግር ውስጥ የምትገባው አንተ እንጂ እሷ አይደለችም:: አፍቃሪህ ሌላ ሰው ሳትሆን ሹንዩ ናት:: ምንም ሳትጨነቅ የትኛውንም አይነት ማረጋገጫ፣ የትኛውንም አይነት ማህተም! ፊርማ እና የፅሑፍ ማስረጃ ልትሰጣት ትችላለህ::

በእርግጥ ለአንተ «የፅሑፍ ማስረጃ ስጠኝ. . .» ብላ እንድትጠይቅህ የገፋፋኋት እኔ ነኝ::

ምስኪኗ ሹንዮ በራሷ እንዲህ አይነት ነገር ማድረግ አትችልም:: ይህ የኔ ሥራ ነው::



# ሰብዓዊ መብቶች ለአዲሱ ሰው

# 5

ታህሳስ 28፣ 1986፣ በምቤ

## ... ነው፤ ሰፊ እስር ቤት በመሆኑ መታሰሩን ይዘነጋዋል እንጂ

ተወዳጁ ብንዋን፡-

ታህሳስ 25 ቀን ስለ ሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ አብሬርተህልን ነበር። ያቀረብከውም፤ የሰውን ልጅ አሁን ባለበት ሁኔታ በአካል እና በአዕምሮ ብርታ አድርጎ የሚያቀይ የፖለቲካ መሳሪያ እና የሰው ልጅ እውነተኛ የአምላክነት ዕምቅ ሀይሉን እንዳያውቅ እንደሆነ አድርገህ ነበር። ዛሬ አንተ ለአዲሱ ሰው የራስህን የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ ልታቀርብበት ትችላለህ?

የሰው ልጅ አሁንም በበርካታ የባርነት ዓይነቶች በግልጽ የሚያሳየን ይኼ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌ ነው። ይህ ድንጋጌ ነው፤ የድንጋጌው መሰረታዊ አስፈላጊነትም ሰዎችን ማታለል ነው። የሰው ልጅ የተታሰሰበት ዘዴ እጅግ ረቂቅ ስለሆነ ግን ከሰው ሰውነት በላይ ወደ ላይ ከፍ ካላላችሁ በስተቀር የታሰረበትን ሰውር ሰንሰለቶች ማየት አትችሉም። ሁሉም ሰው የታሰረበትን የማይታዩ እስር ቤቶች ማየት አትችሉም።

የእኔ የሰብአዊ መብት ድንጋጌ አስር መሰረታዊ ህጎችን (ደንቦችን) ይዟል።

የመጀመሪያው ህይወት ነው፡-



የሰው ልጅ ጤናማ የመሆን እና በታላቅነት ስሜት የመኖር መብት አለው። ወደ መጨረሻው የዕድገት ደረጃ እንዲያብብም የማደግ መብት አለው።

ይሁንና ለህይወታችሁ የምትጨነቁለት ያህል ለሌሎች ፍጡራን የመጨነት ግዴታ አለባችሁ። ስለ ሌሎች ሰዎች ህይወት የማትጨነቁ ከሆነ፤ የእናንተ መብት እንዲከበር እንዴት መጠየቅ ትችላላችሁ?

ሰዎች ለአደን ወጥተው እንስሳትን ያለምንም ጥቅም ይገድላሉ። በማሀራጃ ጃምናጋር ቤተ መንግስት እንግዳ ሆኜ ተጋብዤ ነበር። ንጉሱ በመቶ የሚቆጠሩ የአንበሶች እና የአጋዘን ጭንቅላቶችን አሳየኝ። የእንስሳቱ ጭንቅላቶች ቤተ መንግስቱን አጣበውት ነበር። የሚያስጉበኘኝም በኩራት «እነኚህ እኔ ራሴ የገደልኳቸው ናቸው!» እያለ ነበር።

«ጥሩ ሰው ትመስላለህ። የዚህ ሁሉ ምክንያት ምንድን ነው? እነኚህ እንስሳት ምን በደሉህ?» ብዬ ጠየቅኩት።

«ጥያቄው የምክንያት እና ውጤት! ወይም እንስሳቱ እኔ ላይ ምን በደል አድርሰዋል? የሚል አይደለም። ዝም ብሎ ደስ የሚል ጨዋታ ነው» አለኝ ንጉሱ።

«እሺ በሌላ መልኩ እየው። አንበሳ አንተን ቢገድልህ ጨዋታ ነው ይባላልን? ከሚስትህ፤ ከልጆችህ፤ ከወንድሞችህ . . . መሀል ደስ የሚል ጨዋታ ነው ማለት የሚችል ያለ ይመስልሀል? በጭራሽ! ቤተሰቦችህ ከባድ ሀዘን ይወድቅባቸዋል። አንተ እንስሳቱን ስትገድል ጨዋታ፤ እንስሳቱ ሲገድሉህ ግን አደጋ ይሆናል። ይህ አድሏዊነት የአንተን ብልጥነት እና ቅን አለመሆንን ያሳያል።»

«በዚህ መልኩ አስቤው አላውቅም» አለኝ።

የሰው ልጅ በሙሉ ጤና ባለ ነው። ሁሉም በሌላ ወገን ያለን ህይወት ይመገባል። ለህይወት ምን ያህል ክብር እንሰጥም።

ለህይወት የከበሬታ ስሜት ካልፈጠረ እና ክብር ካልሰጠ በስተቀር፤ ማንም የሰው ልጅ የህይወት መሰረታዊ መብትን የመጉናጸፍ አላማን አይረዳውም።

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የመንግስታቱ ድርጅት፣ «በህይወት መኖር የሰው ልጅ ሁሉ መሰረታዊ መብት ነው» ብሎ መደንገጉ አላግባብ ጥቅም ላይ ውሏል። ጳጳሱ፣ ማዘር ቴሬሳ እና እነሱን የመሳሰሉ ሰዎች የእርግዝና መከላከያ መጠቀምን፣ ውርጃን ለማገድ የተጠቀሙበትን ያህል ተጠቅመውበታል። የሰው ልጅ አዕምሮ ብልጥ ነው። ጥያቄው የሰው ልጆች መብት መሆኑን ተጠቅመውበታል። «የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎችን መጠቀም ህይወትን መጻረር በመሆኑ ልትጠቀሙበት አትችሉም፣ ያልተወለደው ህጻንም እንደ እናንተ በህይወት የመኖር ሙሉ መብት አለው» እያሉ ያስተምራሉ።

ለእኔ የእርግዝና መከላከያ እንክብል የሰው ልጅ መብቶችን አይፃረርም። እንደውም ለህይወት መሰረት ይጥላል። ምድር ከሚገባው በላይ በሰዎች ከተጨናነቀች በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች በረሀብ ያልቃሉ፣ ጦርነቶች ይበዛሉ። ይህም የሰው ልጅ ኢ ሰብአዊ ሁኔታ ውስጥ ዘሎ እንዲገባ ያደርገዋል።

በቤንጋል እናቶች ልጆቻቸውን እስከመብላት የደረሱበት አስከፊ ረሀብ ተከስቶ ነበር። ወላጆች አንድ እና ሁለት ሩፒ (የህንድ ገንዘብ) ለማግኘት ሲሉ ልጆቻቸውን ሸጠዋል። ህጻናቱን የገዙ ሰዎች ሰብአዊ ፍጡር የሸመቱ ይመስላችኋል? በፍጹም ሰው አይደለም የገዙት! ምግብ መግዛታቸው ነበር።

ጳጳሱ እና ማዘር ቴሬሳ ለዚህ ተጠያቂ ናቸው። የእርግዝና መከላከያ እንክብሉ፣ ህጻን በእናት ማህፀን ውስጥ እንዳይፈጠር ያደርጋል። ካልተፈጠረ ደግሞ የሰው ልጆች መብት ጥያቄ አይነሳም። በቅርቡም ሳይንስ ወንዶችም ሊጠቀሙበት የሚችሉ የወሊድ መከላከያ መድሀኒት ፈጥሯል። ስለዚህ ሴቷ ብቻ መድኃኒት እንድትወስድ አትገደድም፣ ወንዱም ሊወስደው ይችላል። በመሆኑም በማንኛውም መልኩ ህጻኑ ሊፈጠር አይችልም። ባለመፈጠሩም ይህ መሰረታዊ መብት የሚባል ነገር ተግባራዊ ሊሆን አይችልም። ነገር ግን የህንዱ ሸንካራ ቻሪያስ እና የኢራኑ አያቶላህ ሆሚኒን. . . የመሳሰሉ በመላው ዓለም የሚገኙ የሀይማኖት መሪዎች እና ሁሉም ሀይማኖቶች የትኛውንም



አይነት የእርግዝና መከላከያ ዘዴን አይቀበሉም። የሰው ልጅ ስልጡን እንዳይሆን የሚያደርገውም የእነሱ መንገድ ብቻ ነው።

እኔ ሙሉ በሙሉ የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎችን እደግፋለሁ። ህጻኑ እንደ ሰው መታየት ያለበት ሲወለድ ብቻ ነው። የተወለደ ጊዜ ላይም ቢሆን የተወሰነ ገደብ አለኝ።

ህጻኑ ሲወለድ አይነ ስውር፣ አካለ ስንኩል፣ ደንቆሮ ወይም ዲዳ ከሆነ ምንም ነገር ልናደርግለት አንችልም። ህጻኑ መወገድ (መሞት) ስለሌለበት ብቻ በእናንተ የማይረባ ሀሳብ ለሰባ እና ለሰማንያ አመታት ሊሰቃይ ይኖራል። ታዲያ አላስፈላጊ ስቃይ መፍጠር ለምን አስፈለገ? ወላጆቹ ፈቃደኞች ከሆኑ ዘላለማዊ እንቅልፍ ማግኘት አለበት። ይህ በራሱ ምንም ችግር የለበትም። አካሉ ወደ መሰረታዊዎቹ ንጥረ ነገሮች ተመልሶ ሲሄድ ነፍሱም ወደ ሌላ ማህፀን በራ ትሄዳለች። ምንም በከንቱ የሚጠፋ ነገር የለም።

ህጻኑን የምትወዱት ከሆነ ሰባ አመታትን በስቃይ፣ በበሽታ እና በእርጅና እንዲገፋ አትፈቅዱም። ህጻኑ ቢወለድ እንኳን ህይወቱ ሙሉ በሙሉ በጤንነት ሊያጣጥማት እንደማይችል ከተረጋገጠ ዘላለማዊ እንቅልፍ ቢያሸልብ እና ሌላ ቦታ በተሻለ ሰውነት ቢወለድ ይሻላል።

የህይወት መብት እጅግ ውስብስብ የሆነ ነገር ነው። አንድም ሰው ሌላ ሰውን የመግደል መብት የለውም - በሀይማኖት ስም ጭምር። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ግን እግዚአብሔርን ለማገልገል በሚል በሀይማኖት ስም ተገድለዋል።

አንድም ሰው በፖለቲካ ሳቢያ መገደል የለበትም። ተጨባጩ እውነታ ግን ተቃራኒው ነው። ጆሴፍ ስታሊን ብቻ በስልጣን ዘመኑ አንድ ሚሊዮን የራሱን ዜጎች ገድሏል። አዶልፍ ሂትለር ስድስት ሚሊዮን ሰዎችን ፈጅቷል። በሺ የሚቆጠሩ ጦርነቶችም ተካሂደዋል።

እዚች ምድር ላይ አንድ ተግባር ብቻ የምናከናውን ይመስላል። ልጆችን የምንወልደው ጦርነቶች ስለሚያስፈልጉን ወታደሮች እንድናገኝ ብቻ ይመስላል። ነብዩ መሐመድ የሰውን ቁጥር ለመጨመር ባዘዙት መሰረት፣ ሁሉም የመሐመድ ተከታዮች አራት ወይም ከአራት የበለጡ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሚስቶች ነበሩዋቸው። ምክንያቱ ደግሞ ጦርነት ነው። አንድ ሰው ዘጠኝ ሚስቶችን ካገባ በአንድ አመት ውስጥ ዘጠኝ ልጆች መውለድ ይችላል። ዘጠኝ ሴቶች አንድ ወንድ ቢያገቡ ችግር የለበትም። ነገር ግን በተቃራኒው ዘጠኝ ወንዶች አንዲት ሴትን ቢያገቡ በአንድ አመት አንድ ልጅ እንኳን ሳይወልዱ ይችላሉ። ሁሉም ነገር ይበላሻል። እንደውም እየተፈራረቁ ሴቲቱን በድካም ሲገድሏት ይችላሉ፡

እናም የሰው ቁጥር መብዛት የሚያስፈልገው ለተጨማሪ ውድመት እና በርካታ ጦርነቶችን ለማካሄድ ይመስላል።

የሰው ልጅ ኩራቱ፣ ክብሩ እና የመኖር መብቱ እንዲጠበቅለት ከፈለገ የህዝብ ቁጥር መቀነስ አለበት። ህይወት መሰረታዊ መብት ነው ስል በዘፈን እና በጭፈራ፣ በደስታ እና በበረከት የተሞላ ህይወት ማለቴ ነው።

* * *

ሁለተኛው ትኩረቴ ፍቅር ነው።

**2፦ ፍቅር፣ የሌሎች መሰረታዊ መብቶች መንገድ ጠራጊ፦**

ከሰው ልጅ መሰረታዊ መብቶች ውስጥ በዋነኛነት መጠቀስ ያለበት ፍቅር መሆን ነበረበት። ሁሉም ማህበረሰቦች ግን አጥፍተውታል። ያጠፉትም ጋብቻን በመፍጠር ነው። ጋብቻ የፍቅር የውሸት ምትክ ነው።

በቀድሞ ዘመን ህጻናት ልጆች ይጋቡ ነበር። እነኚህ ህጻናት ፍቅር ወይም ጋብቻ ምን እንደሆነ የሚያውቁት ነገር የለም። ታዲያ ህፃናቱ የሚጋቡበት ምክንያት ምን ነበር? ምክንያቱ ግልፅ ነው። ህጻናቱ የአፍላነት እድሜ ላይ ከመድረሳቸው በፊት፣ የፍቅር ስሜት በልባቸው ውስጥ ከማቆጥቆጡ በፊት በሮቹ መዝጋት ነው። ፍቅር አንድ ጊዜ ልባቸውን ከሞላው በጣም አስቸጋሪ ይሆናል።

ህፃናትን ማጋባት ፊልሞ ሰብአዊ ድርጊት አይደለም። አንድ ወንድ እና አንዲት ሴት ያሹዋቸውን ተጓዳኞች የመምረጥ፣ ከፈለጉም



በፈለጉበት ጊዜ ግንኙነታቸውን ማቋረጥ መቻል አለባቸው። እዚህ ጉዳይ ውስጥ መንግስት እና ማህበረሰቡ ምንም የሚመለከታቸው ነገር የለም። ይህ የሁለት ሰዎች የግል ጉዳይ ነው። የግል ጉዳይ መሆኑም በራሱ የተቀደሰ ቅዱስ ነው።

ሁለቱ ተጓዳኞች የጋራ ህይወት ለመመስረት ከፈለጉ ከየትኛውም የሀይማኖት አባት ወይም መንግስት ፈቃድ ማግኘት የለባቸውም። ፈቃድ ማግኘት ያለባቸው ከልባቸው ብቻ ነው። የመለያየት ጊዜያቸው እንደደረሰ ከተሰማቸውም ያለማንም ፈቃድ መለያየት አለባቸው። አስደሳች የፍቅር ጊዜአቸውን እያስታወሱ እንደ ጓደኞች ተለያይተው መኖር ይችላሉ።

ወንዶች እና ሴቶች አብረው ለመኖር የሚያስፈልጋቸው ፍቅር ብቻ መሆን አለበት። ሌላ ስርአት (ህግ) አስፈላጊ አይደለም።

በቀድሞ ዘመን የነበረው ዋነኛ ችግር፣ ልጆቹ ምን ይሆናሉ የሚለው ነበር። ለትዳር አስፈላጊነት የሚቀርበው የመከራከሪያ ሀሳብ ይህ ነበር። ነገር ግን ሲሉት እጅግ በጣም የተሻሉ አማራጮች አሉ። ልጆች መታየት ያለባቸው እንደ ወላጆቻቸው ንብረት አይደለም። ልጆቹ የሁሉም የሰው ልጅ አካል ናቸውና። ለህጻናት ገና በልጅነታቸው ግልፅ መደረግ ያለበት ነገር አለ። ይኸውም፣ »ሁሉም የሰው ልጅ እናንተን የሚጠብቅ ጋሻ ነው። አብረን ከሆንን እንንከባከባችኋለን፣ አብረን ባንሆንም እንጠብቃችኋለን። እናንተ የእኛ ደም፣ አጥንት እና ነፍስ ናችሁ« የሚል ነው።

በእርግጥ ወላጆች ልጆቻቸውን እንደ ግል ንብረታቸው መመልከታቸው ከሰው ልጅ ዘንድ ሲወገድ ያልቻለ በጣም አደገኛ አመለካከት ነው። ይህ የባለቤትነት አመለካከት መሰረት ነው። ልጆቻችሁን እንደ ግል ንብረታችሁ ማየት አትችሉም። የሁሉም ማህበረሰብ አካል ናቸው። የመጡት እናንተ ከመጣችሁበት ከሌላ ቦታ ነው፣ እናንተ መተላለፊያ ቱቦ ብቻ ናችሁ። ስለዚህ ስለራሳችሁ ከዚህ የበለጠ ስሜት አይሰማችሁ - ማድረግ የምትችሉትን በሙሉ አድርጉላቸው እንጂ።

ሁሉም ማህበረሰብ ልጆችን መንከባከብ አለበት። ማህበረሰብ በመቀላቀል ልጆችን መንከባከብ ሲጀምር፣ ትዳር ጊዜ ያለፈበት ይሆናል። ትዳር መሰረታዊውን የፍቅር መብት የሚያሳጣ ነውና።

የሰው ልጅ ፍቅር ነፃ ከሆነ ጥቁር ወይም ነጭ የሚባል ነገር አይኖርም። ፍቅር ድንበር ስለሌለው እነዚህ አሁን ያሉት አስቀያሚ አድሎዎች አይኖሩም። ከጥቁር ወይም ከነጭ ሰው ጋር በፍቅር ልትጠመዱ ትችላላችሁ። ፍቅር ምንም አይነት የሀይማኖት ማርክ አያውቅም። ፍቅር የሚያውቀው የልብ ምት ማድመጥ ብቻ ነው። ይህንንም በእርግጠኝነት ያውቀዋል። ፍቅር አንድ ጊዜ ነፃ ከሆነ ለሌሎች መሰረታዊ መብቶች መንገድ ይጠርጋል።

እንደውም ሳይንቲስቶችን ብትጠይቁ በፍቅር የሚጣመሩ ሰዎች የተቻለውን ያህል የተለያየ ዘር መሆን እንዳለባቸው ይነግሯችኋል። ይህን ካደረጉ የተሻለ አዕምሮ እና ጠንካራ ሰውነት ያለው ልጅ ይወለዳሉ። እኛ ይህን ተረድተን በመላው አለም በሚገኙ እንስሳት ላይ እየተገበርነው ነው። እንስሳትን ማዳቀል የተሻሉ ላሞችን፣ የተሻሉ ፈረሶችን እና ውሾችን አስገኝቷል። ሆኖም የሰው ልጅ አስገራሚ ፍጥረት ነው። ሚስጥሩን ያውቀዋል፣ ግን በራሱ ላይ አይተገብረውም።

**ትዳር መሰረታዊውን የፍቅር መብት የሚያሳጣ ነው**

ሁሉም ንጉሳዊ ቤተሰቦች ስቃይ ላይ ናቸው። የሚጋቡት እርስ በርስ ስለሆነ የሚወልዷቸው ልጆች የለየላቸው ደደቦች ናቸው። የንጉሳዊ ቤተሰብ ደም ከተራው ማህበረሰብ ደም ጋር አይቀላቀልም። በዚህ በሀያኛው ክፍለ ዘመን እንኳን ስለንጉሳዊ ቤተሰቦች ደም እናስባለን፣ እንጨነቃለን። ደም ያው ደም ነው። የማንም ደም ከማንም ደም አይበልጥም፣ የማንም ዘር ከማንም ዘር አያንስም። ነገር ግን በደርዘን የሚቆጠሩ ቤተሰቦች በተከታታይ ከትውልድ ወደ ትውልድ እርስ በርስ የሚጋቡ ከሆነ ብዙ አይነት በሽታዎች ይፈጠራሉ።

ከችግሮቹ አንዱ የአዕምሮ ዘገምተኝነት ችግር ነው። የቋልሱን አቡል ፎቶ ተመልከቱ እና የዚያኑ ዘገምተኛ አዕምሮ የልኩት ምን እንደሆነ ትረዳላችሁ። ቀበሉ ቆርጠዋል፣ ነገር ግን ከጠባቡ ድንበራቸው መውጣት አይችሉም። የንጉሳዊ ቤተሰብ አባል ሆኖ ብሩህ አዕምሮ ያለው ሰው አጋጥሞኝ አያውቅም። በአንድ ያሉት የንጉሳዊ ቤተሰቦች ሁሉንም ማለት ይቻላል አውቃቸዋለሁ። አዕምሯቸው ዘገምተኛ መሆኑ ብቻ አይደለም፣ አካላቸውም በርካታ የእንስሳት ፀጋዎችን አጥቷል።

**ፍቅር ምንም አይነት የሀይማኖት ሥርዓት - ደንብ አያውቅም። ፍቅር የሚያውቀው የልብ ምት ማድመጥ ብቻ ነው። ፍቅር አንድ ጊዜ ነፃ ከሆነ ለሌሎች መሰረታዊ መብቶች መንገድ ይጠርጋል**

መቼም ራስፑቲን የሚባለውን ስም ሰምታችሁት አልቀራችሁም። ከሩሲያ አብዮት በፊት አገሪቱ ውስጥ በጣም አስፈሪ ሰው ሆኖ ነበር። የዚህ ምክንያትም የዛሩ (የሩሲያ ንጉስ) ልጅ በድንገተኛ አደጋ ሰውነቱ ቢቆስል፣ ደሙ መፍሰሱን እንዳያቆም የሚያደርግ በሽታ ነበረበት። አንድ ጊዜ ከሰውነቱ ደም መፍሰስ ከጀመረ የትኛውም አይነት መድሀኒት የሚፈሰውን ደሙን ማስቆም አይችሉም። ደሙ ያለማቋረጥ መፍሰሱን ይቀጥላል። ይህ የቅርብ ቤተሰቦችን አባላት እርስ በርስ የማጋባት ጉዳት አንዱ ጥሩ ምሳሌ ነው።

ራስፑቲን ሰውን ሰመመን ውስጥ መክተት ይችል ነበር። ቅዱስ አልነበረም፣ ሀጢአተኛም አልነበረም። ነገር ግን ሰመመን ውስጥ በመክተት ከሆነ ያለማቋረጥ የሚፈሰውን ደም ማስቆም ይችል ነበር። ሀኪሞችም በዚህ አንድም የህክምና ባለሙያ ይህን ማድረግ አልቻለም ነበር። [illegible] የተገኘ ራስፑቲን ከመሳ የቃላቱ ማዝት ዘራች የሚዘን ነበር። ... ሰው መሆኑ አይደናቅፍም። ያለ እሱ የህጻኑ ህይወት ከፍተኛ አደጋ ላይ ይወድቅ ነበርና።



t.me/OLDBOOKSPDF

እንና የንጉሳዊ ቤተሰቦች ግዛታቸውን እና ስልጣናቸውን ካጡ በኋላም እርስ በርስ መጋባታቸውን አላቋረጡም:: ይህም እጅግ በጣም ደካማ በብዙና ፈጥሮባቸዋል::

ከዚ ቤተሰብ የወጣች ሴት በቁንጅና ውድድር ተሳትፋ የዓለም ቆንጆ ስትባል አይታችሁ ወይም ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? የእንግሊዝ ንግስት ኤልሳቤጥ በቁንጅና ውድድር አንደኛ የምትወጣ ይመስላችኋል? በመላዋ እንግሊዝ የሚወራ ሀሜት አለ:: እውነት መሆን አለመሆኑን አላውቅም እንጂ:: ሀሜቱ «የንግስት ኤልሳቤጥ ባለቤት ልዑል ፊሊፕ ግብረ ሰዶማዊ ነው» የሚል ነው:: ሰምስኪኑ ፊሊፕ በጣም አዝንለታለሁ::

እንደውም ንግስት ኤልሳቤጥን የሚያገባ ማንኛውም ወንድ ግብረሰዶማዊ ይሆናል፣ ስለዚህ ምንም የሚያስጨንቀው ነገር የለም:: ተፈጥሯዊ ነው::

ህንዳዊ የግድ ህንዳዊን፣ ብራህሚኑ የግድ ብራህሚኑን ማግባት አለበት የሚል ገደብ የለም:: እንደውም ሁሉ ህንዳዊ ከህንዳዊ ጋር መጋባት የለበትም የሚል መሆን አለበት:: ዓለም ሰፊ ስለሆነች የትዳር አጋራችሁን ከሩቅ ቦታ፣ ከሰባቱ ሰማያት (ከአድማስ) ባሻገር ሂዱችሁ ፈልጉ:: ይህን ካደረጋችሁ ይበልጥ የተዋቡ፣ ጤናማ፣ ረጅም እድሜ የሚኖሩ፣ የላቀ ብሩህ አዕምሮ ያላቸው ልጆችን ትወልዳላችሁ:: የሰው ልጅ መዳቀልን መልመድ (መማር) አለበት:: ይህ ሲሆን የሚችለው ግን ትዳር የሚባል ነገር ከጠፋ እና ለፍቅር ከፍተኛ ክብር ከተሰጠው ነው:: አሁን የምናየው ግን ፍቅር ሲወገዝ ነው::

* * *

ስስተኛው መሰረታዊ መብት. . . ሶስቱ መብቶች ለህይወት እጅግ በጣም አስፈላጊዎቹ ናቸው የሚል ነው:: እነኚህም ህይወት፣ ፍቅር እና ሞት ናቸው::



3:- ሦስቱ መሰረታዊ መብቶች - ሕይወት፣ ፍቅር እና ሞት:-

ሁሉም ሰው ከተወሰነ እድሜ በኋላ፣ ብቁ ዓመታትን ከኖረ እና በሉጥ ተዕዕኖ እየተጉተተ መኖርን ከጠላ መሰረታዊ መብት ሊሰጠው ይገባል:: ምክንያቱም ነገ፣ ከዛሬ ምንም ያልተለየ ድግግሞሽ ይሆንበታል:: ነገ የመኖር ጉጉቱንም ያጣል:: ስለዚህ አካሉን ትቶ፣ ከአካሉ ባሻገር ርቆ የመሄድ ሙሉ መብት አለው:: ይህ መሰረታዊ መብቱ ነው::

የሚኖረው የራሱን ህይወት ነው:: በሕይወት ለመኖር ካልፈለገ ማንም ሰው ጋሬጣ ሊሆንበት አይገባም:: እንደውም ሁሉም ሆስፒታሎች መሞት የሚፈልጉ ሰዎች ከእንድ ወር በፊት ሄደው የሚዝናኑበት፣ ህይወታቸውን ሙሉ ፈልገው ባጡት ነገር የሚደሰቱበት ክፍል ሊኖራቸው ይገባል:: ሙዚቃ፣ ስነፅሑፍ. . . ከፈለጉም ስዕል መሳል ወይም ቅርጻ ቅርፅ መቅረጽ ይኖርባቸዋል::

ዘኪሞችም እንዴት ሲያዝናኗቸው እንደሚችሉ ማወቅ አለባቸው:: እንደዚሁም ሆኖ ግን እስካሁን ድረስ ሞት እጅግ በጣም አስቀያሚ (መጥፎ) ነገር ነው::

የሰው ልጅ የጉዳት ሰለባ ሆኗል፤ ይህም የራሳችን ስህተት ነው - ሞትን አላከበርነውምና:: ሞት ሊከበር ይገባል፣ ሞትን በእርጋታ እና በፍጋ መቀበልን መማር አለብን:: በአንድ ጊዜ ውስጥ ወዳጅ ዘመዶቹ እየሄዱ ሊጠይቁት ይችላሉ:: ሁሉም ሆስፒታሎች ልዩ አገልግሎት መስጫ ሊኖራቸው ይገባል:: በህይወት ለሚኖሩት ሳይሆን ለሚሞቱት ይበልጥ የተሻሉ አገልግሎት መስጫዎች መዘጋጀት አለባቸው:: መሞት የፈለጉትን ቢያገኙ በአንድ ወር እንደንጉስ እንዲኖሩ ፍቀዱላቸው:: ይህን ካደረጋችሁ ህይወትን በደስታ እና በምስጋና ያለምንም ቅሬታ፣ ያለምንም ስሞታ ተሰናብተውት ይሄዳሉ::

* * *

በእነኚህ ሶስት መብቶች መሀል ሊነተት የሚገባው ሌላም ነገር አለ:: ይኸውም እውነትን መፈለግ ነው::

## 4:- እውነትን መፈለግ:-

ሁሉም ሰው ከልጅነቱ ጀምሮ በማንኛውም ርዕዮተ ዓለም፣ ፍልስፍና፣ ወይም የሀይማኖት ትምህርት መተብተብ የለበትም:: ይህን ካደረጋችሁ ሰውየው እውነትን የመፈለግ ነፃነቱን ታሳጡታላችሁ:: ሰውን ጠንካራ እንዲሆን እርዱት:: በዙሪያው ያሉ ሰዎች የሚያምኑትን እምነት የሚጠራጠር ጠንካራ ተጠራጣሪ እንዲሆን ድጋፍ አድርጉለት:: በፍጹም እምነትን እንዳያምን፣ ነገር ግን በዕውቀት ላይ እንዲያተኩር አግዙት:: ከፍተኛ ጥረት ቢጠይቅና ረጅም ጊዜ ሊወስድ ቢችልም እውነትን ለማግኘት የሚያደርገውን መንፈሳዊ ጉዞ ለብቻው ያድርግ:: ከዚህ መንገድ ውጪ እውነትን ማግኘት አይችልም::

ሌሎቹ ሁሉም ክርስቲያኖች፣ አይሁዶች፣ ሂንዱዎች ወይም የመሐመድ ተከታዮች እንደሆኑ የሚያስቡ ሰዎች በሙሉ አማኞች ናቸው:: አያውቁምና::

እምነት ወደር የሌለው ትክክለኛ መርዝ ነው::

ማወቅ ግን ቀስ በቀስ ያድጋል::

ስማንም ሰው እውነት ምን እንደሆነ ልታስተምሩ ስትችሉም:: ምክንያቱም እውነትን ማስተማር አይቻልም:: ሰው እንዲጠይቅ እገዛ ማድረግ ነው የሚኖርባችሁ - ጥያቄ መጠየቅ አስቸጋሪ ነውና::

እምነት እጅግ ቀላል ነው:: እውነት ግን በቀላሉ የሚገኝ ርካሽ አይደለም:: በአለም ላይ እጅግ በጣም ውዱ ነገር እውነት ነው:: እውነትን ከሌሎች ሰዎች ማግኘት አትችሉም:- ራሳችሁ መፈለግ ይኖርባችኋል እንጂ::

> **ስማንም ሰው እውነት ምን እንደሆነ ልታስተምሩ ስትችሉም:: ምክንያቱም እውነትን ማስተማር አይቻልም:: ሰው እንዲጠይቅ እገዛ ማድረግ ነው የሚኖርባችሁ - ጥያቄ መጠየቅ አስቸጋሪ ነውና::**

አስደናቂው ነገር ለማንኛውም እምነት ስለባ አልሆንም ባላችሁበት ቅፅበት ወደ እውቀት የሚወስደውን መንገድ ግማሹን ተጓዛችሁ ማለት ነው:: ቆራጥ የመንፈስ ፅናት ካላችሁ ወደ እውነት መሄድ አይኖርባችሁም:: እውነት ራሱ እናንተ ዘንድ ይመጣል::

ከእናንተ የሚጠበቀው እውነትን ለማግኘት በፀጥታ መጠበቅ ብቻ ነው:: እናንተ ጋባዥ ከሆናችሁ ግን እውነት እናንተ ጋ የሚመጣው ምንም የማይታወቅ እንግዳ ሆኖ ነው:: ምንነቱ አይገለጽላችሁም::

> **በዓለም ላይ እጅግ በጣም ውዱ ነገር እውነት ነው:: እውነትን ከሌሎች ሰዎች ማግኘት አትችሉም - ራሳችሁ መፈለግ ይኖርባችኋል እንጂ::**

አሁን መላው ዓለም የሚኖረው በእምነቶች ታጥሮ ነው:: እውነት በሰዎች አይኖች ውስጥ ብርሀን ያጣው፣ በሰዎች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ ግርማሞገሱ የተገፈፈው፣ በንግግራቸው ውስጥ ጥንካሬ እና ሀይል የሌለው የሆነው ለዚህ ነው:: እምነት የውሸት ማስመሰያ ነው:: ቤቱን የሚሰራውም ምድረ በዳ (አሸዋ) ላይ ነው:: ገና ነፋስ መንፈስ ሲጀምር የተገነቡት ህንጻዎች ይፈራርሳሉ::

እውነት ግን ዘላለማዊ ነው:: እውነት መፈለግ ማለት ደግሞ የዘላለማዊነት አንድ አካል መሆን ማለት ነው::

* * *

እምቢተኛ:- እውነትን ለመፈለግ ከመዋዕለ ህፃናት ጀምሮ እስከ ዩኒቨርስቲ ያሉ የትምህርት ስርአቶች በተመሰጦ ለማሰብ በተወሰነ ደረጃ የሚፈጥሩት አመቺ ሁኔታ እንዳለ ማወቅ ነው::

t.me/OLDBOOKSPDF

5፡- በተመስጦ ማሰብ፡-

በተመስጦ ማሰብ ከየትኛውም ሀይማኖት ጋር ትስስር የለውም፡፡ ተመስጦ እንዲያውቁም እምነትም አይደለም፡፡ ትክክለኛ የውስጥ አካል ሳይንስ ነው፡፡

ተመስጦን መማር፣ በደንብ ማስተዋልን መለማመድ፣ በጥልቀት ማሰብን መካን. . . እውነትን ለመቀበል ያዘጋጁዋችኋል፡፡

**እውነት ዘላለማዊ ነው፡፡ እውነት መፈለግ ማለት ደግሞ የዘላለማዊነት አንድ አካል መሆን ማለት ነው**

እውነት፣ በበርካታ ሰዎች ዘንድ እግዚአብሔር ተብሎ ይጠራል፡፡ በሌሎች ደግሞ ፍጹም የደስታ መንፈስ ይባላል፡፡ ሌሎችም ሌላ ስም ሰጥተውታል፡፡ ነገር ግን እውነት ስም የሌለው ፀጥታ፣ እርጋታ እና ሰላም ነው፡፡ ሰላም በጣም ጥልቀት ስላለው ውስጡ ትጠፋላችሁ፡፡ በጠፋችሁበት ቅፅበትም የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ውስጥ ትገባላችሁ፡፡

እጅግ የሚገርመው ነገር ሰዎች ስለ ፀጥታም ሆነ ስለመገናኛት፣ ሌላው ቀርቶ ስለራሳቸው ምንም ባለማወቅ አንድ ሶስተኛ የሚሆነውን ዕድሜአቸውን በትምህርት ቤቶች፣ ኮሌጆች እና ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ማባከናቸው ነው፡፡ ስለመላው አለም እያወቁ ራሳቸውን አለማወቃቸው ግራ የሚያጋባ ነው፡፡ ብቻ ለዚህ ምክንያት ያላቸው ይመስላል፡፡

በህንድ የሚነገር ጥንታዊ ታሪክ አለ፡፡ አስር አይነ ስውራን ሰዎች በወራጅ ውሃ ላይ ለማለፍ ይፈልጉና የውሀው ግፊት ሀይለኛ ስለነበር እጅ ለእጅ ይያያዛሉ፡፡

ወደ ሌላኛው የወንዙ ጥግ ሲደርሱ ከመሀከላቸው አንዱ «ብዛታችንን ስንት እንደሆን ለማወቅ መቁጠር አለብን፡፡ የውሀው ግፊት ኃይለኛ ስለነበር እኛ ሳናየው ውሃው ጠልፎ የወሰደው ሰው ሳይኖር አይቀርም» አለ፡፡ ሁሉም በዚህ ተስማምተው ብዛታቸውን መቁጠር



ጀመሩ፡፡ በቆጠሩ ቁጥር ቆጠራው የሚቆመው ዘጠኝ ቁጥር ላይ ሆነ፡፡ ሁሉም በየተራ ሞከሩ፣ ግን ብዛታቸው ያው ዘጠኝ ነው፡፡

ይህን በጽሞና የሚመለከት አንድ ወንዙ ዳር የተቀመጠ ሰው ከት ብሎ ሳቀባቸው፡፡ ምክንያቱም አስሩ ዓይነ - ስውራን ወንዙ ዳር ላይ ተቀምጠው አንድ ጓደኛቸውን በማጣታቸው ማልቀስ ጀምረው ነበርና፡፡ ሁኔታቸው እጅግ አስገራሚ ነበር፡፡

ሰውየው ወደእነሱ ቀረብ አለና፣ «ምን ሆናችሁ ነው?» ሲል ጠየቃቸው፡፡

እነሱም የደረሰባቸውን ነገሩት፡፡ ከዚያ ሰውየው፣ «መደዳውን በሰልፍ ቁሙ እና የመጀመሪያውን ሰው ስመታው <አንድ> ይበል፡፡ ሁለተኛውንም ሰው ሁለት ጊዜ ስለምመታው <ሁለት> ይበል፡፡ ሶስተኛውን ሰው እንደዚሁ ሦስት ጊዜ ስመታው <ሶስት> ይበል፡፡ በዚህ ሁኔታ እንቆጥራለን» አላቸው፡፡

በዚህ ሁኔታ የጠፋውን አስረኛውን ሰው አገኙት፡፡ ዓይነ - ስውራኑም እግሮቹ ላይ ወድቀው አመሰገኑት፡፡ «አንተ አምላካችን ነህ፡፡ አንድ ጓደኛችንን ያጣን መስሎን ስንጨነቅ ነበር፡፡ እባክህ እኛ ስንቆጥረው የጠፋውን ጓደኛችን በድንገት እንዴት ሊገኝ እንደቻለ ልትነግረን ትችላለህ?» ብለው ጠየቁት፡፡

«ይህ በቀላሉ ልትረዱት የማትችሉት ከባድ ሚስጥር ነውና ዝም ብላችሁ መንገዳችሁን ቀጥሉ» አላቸው ሰውየው፡፡

እዚህ ታሪክ ውስጥ ያለው ከባድ ሚስጥር ምንድን ነው? ሰው ራሱን የመርሳት ዝንባሌ እንዳለው የሚያሳይ ከባድ ምስጢር ነው፡፡ እንደውም ሰው ሁሉ ዕድሜውን ልክ የሚኖረው ራሱን ዘንግቶ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ሁሉንም ሰው ያያል፣ ሁሉንም ሰው ያውቃል፣ ራሱን ግን ይረሳል፡፡ ዞር ብሎ ራሱን አያይም፡፡

እናም ከገዛ ራሳችሁ ጀምሮ «አንድ» በማለት መቁጠር የሚቻልበት ብቸኛው መንገድ በተመስጦ ማሰብ ነው፡፡

በተመስጦ ማሰብ የየትኛውም ሀይማኖት አካል (ክፍል) ባለመሆኑ በመላው ዓለም፣ በሁሉም ትምህርት ቤቶች፣ ኮሌጆች እና

ዩኒቨርስቲዎች ሊሰሩ ይችላሉ፡፡ ትምህርቱን ጨርሶ ከዩኒቨርስቲ ወደ ቤቱ የሚሄድ ሰው የመመሰጥን ክህሎት ካዳበረ በኋላ መሆን ይኖርበታል፡፡ ከዩኒቨርስቲ ከመውጣቱ በፊት የተመሰጦን መንፈስ መያዝ ይገባዋል፡፡

አለበለዚያ ወደ ማሕበረሰቡ ተመልሶ ሲመጣ ይዞት የሚመጣው ነገር ፋይዳ቎ቢስ ትርኪ ምርኪ ይሆናል፡፡ ማለፊያ የጂኦግራፊ እውቀት ሊኖረው ይችላል፡፡ ቲም ቡክቱ ወይም ኮንስታንቲኖፕል የት እንደሚገኙ በትክክል የሚያውቅ ቢሆንም፤ እሱ ራሱ የት እንዳለ ግን አያውቅም፡፡

> **ሰው ራሱን የመርሳት ዝንባሌ አለው፡፡ እንደውም ሰው ሁሉ ዕድሜውን ሙሉ የሚኖረው ራሱን ዘንግቶ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ሁሉንም ሰው ያያል፤ ሁሉንም ሰው ያውቃል፤ ራሱን ግን ይረሳል፤ ዞር ብሎ ራሱን አያይም**

አንድ ሰው በህይወቱ በመጀመሪያ ደረጃ ማድረግ ያለበት ማን እንደሆነ እና የት እንዳለ ማወቅ ነው፡፡ ይህን ካደረገ ህይወቱና በህይወቱ ዙሪያ ያለው ሁሉም ነገር ይስተካከላል፤ በትክክለኛ አቅጣጫም ይጓዛል፡፡

* * *

### 6፡- ሁለ - ገብ ነፃነት፡-

እኛ የወፎች እና የእንስሳትን ያህል እንኳን ነፃ አይደለንም፡፡ አንድም ወፍ በህይወቱ ሙሉ ፓስፖርት ወደሚሰጥበት ቢሮ ሄዶ አያውቅም፡፡ ባሻው ሰዓት የመግቢያ ቪዛ ሳያስፈልገው ወደየትኛውም ሀገር በርሮ መሄድ ይችላል፡፡ የትም የመንቀሳቀስ መብቱ በእጁ ነው፡፡ የሰው ልጅ ግን አስገራሚ ፍጡር ነው፡፡ በአንድ መንግስት እና በዳር ድንበር ተከልሎና ተወስኖ ይኖራል፡፡ እስር ቤት ውስጥ ያለ እስረኛ ነው፡፡ ሀገሮቹ ሰፊ ግዛት በመያዛቸው ግን መታሰሩን እና እስር ቤት መሆን ይዘጋዋል፡፡ አዎን፣ መታሰራችሁን ስለምትዘነጉት ከዚያ ልትወጡ አትችሉም፤ ልትገቡበትም አይቻላችሁም - እጅግ በጣም ሰፊ እስር ቤት ነውና፡፡ መላው ዓለምም በሰፋፊ እስር ቤቶች የተሞላ ነው፡፡

በሁሉም ገፅታ (አቅጣጫ) ያለ ነፃነት ማለት ሰው የትም ቦታ ይወለድ የሰው ዘር አንድ ክፍል መሆን ነው ማለት ነው፡፡

መንግስታት እና ሀይማኖቶች ጠንካራ፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አስቂኝ ትስስር የሚፈጥሩ በመሆናቸው መወገድ አለባቸው የምለውም ለዚህ ነው፡፡

አንድ ጊዜ ዴቫስ ወደምትባል ከተማ ሄጄ ነበር፡፡ እዚያ የሚገኘው የጃይና ቤተመቅደስ ለሀያ አመታት ክፍት ሆኖ አያውቅም፤ እንደተዘጋ ነበር፡፡ ቤተመንግስቱ ሶስት ቁልፎች አሉት፡፡ አንደኛው ቁልፍ ዲጋምባራስ ከሚባሉ የጃይኒዝም ወገን፤ ሌላው ስቬታምባራስ ከሚባሉ ሌላ ወገን ሲሆን፣ ሶስተኛው የፖሊስ ነበር፡፡ ምስኪኑ ማሀቪራ ለሀያ አመታት ያህል ያለ ምግብ፤ ውሃ እና መብራት ቤተ መቅደሱ ውስጥ ኖሯል፡፡ ምንም ድምፅ አሰምቶ ስለማያውቅ በህይወት መኖር ወይም አለመኖሩን የሚያውቅ ማንም የለም፡፡ ቢያንስ እንኳን በሩን እያንኳኳ «ክፈቱልኝ እና ልውጣ» ማለት ነበረበት፡፡

እኔም ይህን ስመለከት «ምንድን ነው ችግሩ?» ብዬ ጠየቅኩ፡፡ በዚያ ሳልፍ በሶስት ትላልቅ ቁልፎች ተከርችሞ ነበር፡፡ ከዛም ታሪኩን ነገሩኝ፡፡

በዴቫስ ያለው የጃይና እምነት ቤተ መቅደስ አንድ ብቻ ነው፡፡ ያም ቤተመቅደስ ደህ ከላይ የነገርኳችሁ ብቻ ነበር፡፡ ጃይናዎች ቁጥራቸው ጥቂት ስለሆነ ሁለት ቤተመቅደሶችን ለመገንባት የሚያስችላቸውን በቂ ገንዘብ አልነበራቸውም፡፡ በመሆኑም አንድ ቤተ መቅደስ ብቻ ገነቡ እና የአምልኮ ጊዜአቸውን ከፋፈሉት፡፡ እስከጉኃቱ አስራ ሁለት ሰአት ድረስ ዲጋምባራስ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ያመልኩበታል፤ ከአስራ ሁለት ሰአት በኋላ ደግሞ ስቬታምባራስ ያመልኩበታል፡፡ ሆኖም ግን በየዕለቱ በመሀከላቸው ጠብ ይፈጠር ነበር፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

በስቬታምባራስ እና ዲጋምባራስ መሀል ያለው ጠብ በጣም ተራ የሚባል ዓይነት ነበር፡፡ እንደውም የህጻን ልጅ ጥል ነው የሚመስለው፡፡ ዲጋምባራሶች ማህቪራን የሚያመልኩት አይኖቹን ጨፍነው ሲሆን፤ ስቬታምባራሶች ደግሞ አይኖቹን ገልጠው ነበር፡፡ ዋነኛ ልዩነታቸው ይህ ነበር፡፡

የእምነበረድ ሀወልት አንድ ዘዴ ተጠቅማችሁ ማብሪያውን ስትጫኑ አይኖቹን እንዲገልጥ፤ እንደገና ስትጫኑት ደግሞ አይኖቹን እንዲጨፍን ካላደረጋችሁ በስተቀር፤ ሀውልቱ የተጨፈኑ ወይም የተገለጡ አይኖችን ብቻ ነው የሚኖረው፡፡ ነገር ግን በህንድ በማብሪያ እና በማጥፊያ አይኖቹን የሚገልጥ እና የሚጨፍን ሀውልት አሰራር ቴክኖሎጂ አልነበረም፡፡ ይህ ቢሆን ኖሮ ችግር አይፈጠርም ነበር፡፡ ይህን ጥበብ አሻንጉሊቶች ላይ ማየት ይቻላል፡፡ አንዲት የምታምር አሻንጉሊትን በጀርባዋ ስታስተኟት አይኖቿን ትጨፍናለች፡፡ ስታስቀምጧት ደግሞ አይኖቿን ትገልጣለች፡፡ ይህን ለማድረግ አንድ ነገር መስተካከል አለበት፡፡

እነሱም አንድ ያስተካከሉት ነገር ነበር፡፡ ኋላ ቀር ቢሆንም ተጠቅመውበት ነበር፡፡ ይህ መንገድ በመላዋ ህንድ ተስፋፍቶም ነበር፡፡ ስቬታምብራሶች አይኖቹ በተጨፈኑ ሀውልት ስር ሆነው በሚያመልኩበት ጊዜ የሀወልቱ አይኖች ላይ የሀሰት አይኖች ያስቀምጣሉ፡፡ ለጊዜው ያጣብቁበታል፡፡ ይህ በጣም ቀላል እና ልዩ ቴክኒክ የማይጠይቅ ነው፡፡ ከፍተኛ ቴክኖሎጂም የሚጠይቅ አይደለም፡፡

ነገር ግን ችግሩ በየዕለት መከሰቱን ቀጥሎ ነበር፡፡ ልክ አስራ ሁለት ሰአት ሲሆን ስቬታምብራሶች መጠበቅ ይጀምራሉ፡፡ አንድ ተጨማሪ ደቂቃ አልፎ፤ ዲጋምባራሶች ማምለካቸውን ከተጠሉ ስቬታምብራሶች ይመጡ እና የራሳቸውን አይን ሀውልቱ ላይ ያስቀምጣሉ፡፡ ይኼኔ ጠቡ ይጀመራል፡፡

ይህ ድርጊት በተደጋጋሚ መከሰቱ ያማረረው ፖሊስ በመጨረሻ ቤተመቅደሱን ቆልፎ «ወደ ፍርድ ቤት ሂዱችሁ አስወስኑ» አላቸው፡፡ ጉዳያቸውም በፍርድ ቤት መታየት ጀመረ፡፡ ፍርድ ቤቱ ታዲያ ማህቪራ

እንዴት በተጨፈኑ ወይም በተገለጡ አይኖች ያመልክ ነበር ብሎ መወሰን ይችላል?

እውነታው ግን እሱ በተመስጦ ውስጥ ይሆን የነበረው በከፊል በተገለጡ አይኖች ነበር፡፡

አንድም ህፃን፤ ህይወት ምን እንደሆነች በወላጆቹ ምንም አይነት ሀሳብ ሊሰጠው አይገባም፡፡ የትኛውም አይነት የሀይማኖት ትምህርት፣ ፍልስፍና እና ፖለቲካዊ አመለካከት ለልጆቹ መስጠት የለበትም - ህጻኑ በተቻለ መጠን የስላ እና ብሩህ አዕምሮ እንዲኖረው መደረግ አለበት እንጂ፡፡ ይህ ከሆነ እድሜው ሲደርስ እውነትን ራሱ መፈለግ ይጀምራል፡፡ ይህም የእድሜ ልክ ፍለጋ ነው፡፡

በባሬ ጊዜ ግን ሰዎች ሀይማኖትን የሚቀበሉት በተወለዱበት ዕለት ነው፡፡ በእርግጥ ስትሞቱ ሀይማኖታችሁን ማግኘት ከቻላችሁ በቶሎ አገኛችሁት ማለት ነው፡፡ ሀይማኖት እጅግ በጣም የከበረ ሀብት ቢሆንም ሊገኝ የሚችለው ግን በነጻነት ብቻ ነው፡፡ በሀይማኖት ብቻ ሳይሆን በሁሉም አቅጣጫ (ገፅታ) በሁሉም ነገሮች ውስጥ የሚገኝ ነጻነት ነው፡፡

የትኛውም አይነት መንግስታት እና ዳር ድንበሮች መኖር የለባቸውም፡፡ ሀይማኖቶችም መኖር አልነበረባቸውም፡፡ ሰው መታየት ያለበት እንደ ሰው ብቻ ነው፡፡ በበርካታ ተቀፅላዎች ማሰሩ ለምን አስፈለገ? በእሁኑ ጊዜ የሰው ልጅ በሁሉም ነገር ነጻ አይደለም፡፡

አንድ ጊዜ አሜሪካን አገር ታስሬ ነበር፡፡ አስካሁንም በሚገኝው እስር ቤት የነበረው የፖሊስ አዛዥ ስሜን ዴቪድ ዋሽንግተን ብዬ እንድፅፍ አዘዘኝ፡፡ እኔም «አንድ ሰው ስሜን ሲነግረኝ ይህ የመጀመሪያ ጊዜ ነው፡፡ አዕምሮ ማንበብ ትችላለህ እንዴ?» ስል ጠየኩት፡፡

በመጠኑ ግራ ተጋብቶ «ትክክለኛ ስምህ ነው አይደል?» ብሎ ጠየቀኝ፡፡

«እንዴታ!» ብዬ መለስኩለት፡፡

«እንደሱ ከሆነማ በሌላ ስም ይቀይሩት» አለኝ፡፡

«ትክክለኛ ስሜን ታውቀዋለህ፡፡ ዴቪድ ዋሽንግተን ስሜ አይደለም፡፡ ለምን ዴቪድ ዋሽንግተን ብዬ እፅፋለሁ? ይህችን ሀገር

t.me/OLDBOOKSPDF

ዲሞክራሲያዊት ሀገር ትሏታላችሁ፤ ግን አንድ ሰው የራሱን ስም እንኳን የመጻፍ ነጻነት የለውም። ያሏችሁ ነጻነቶች ምንድን ናቸው? በኮትህ ላይ በትልቁ <የፍትህ ሚኒስቴር፣ የዩ.ኤስ ፖሊስ አዛዥ> የሚል ፅሁፍ ይታያል። ቢያንስ እንኳ ኮትህን ብታወልቀው ምናለበት፤ ስሜ ዴቪድ ዋሽንግተን አይደለም፤ እኔም እንደዛ ብዬ አልፅፍም» አልኩና ቀጠል አድርጌም «በህይወቴ ዲሞክራሲ እንዴት እንደሚተገበር ስመለከት ይህ የመጀመሪያዬ ነው። ስሜን እንኳን የመጻፍ ነፃነት የለኝም። እና የዲሞክራሲ ትርጉም ምንድን ነው?» አልኩት።

«እሱን እኔ አላውቅም። ከበላይ አካል የተሰጠኝ ትዕዛዝ <ስሙ ዴቪድ ዋሽንግተን መሆን አለበት። በእስር ቤቱ ውስጥም መጠራት ያለበት በዴቪድ ዋሽንግተን ስም ነው> የሚል ነው» አለኝ።

ስአቱ ከሰሊቱ ሰድስት ስአት ስለነበር «እኔ ቅፁን አልሞላም፣ ከፈለግክ አንተው ሙላው እና ከዛ እኔ እፈርምበታለሁ» አልኩት።

ወደ ቤቱ ለመሄድ ተቻኩሎ ስለነበር ቅጹን ሞላው። እኔም በስሜ ፈረምኩበት። ፊርማዬን ሲመለከት፣ «ይህ ዴቪድ ዋሽንግተን አይልም» አለ።

«እንዴት ሊል ይችላል?! እኔ ዴቪድ ዋሽንግተን አይደለሁማ።»

«የሚገርሙ ሰው ነዎት። አታለሉኝ።»

«የምታታልለው ራስህን ነው። ስሜ ማን እንደሆነ እሳምሬህ ታውቀዋለህ። ነገ ጠዋት <ዲሞክራሲ እናራምዳለን፣ ነጻ አገሮች ነን> እያሉ ስለ ነጻነት ዘወትር የሚደሰኩሩት አገራት በትክክለኛ ስማቸው መፈረም እንደማይፈቅዱላቸው መላው ዓለም ይረዳል። ስመሆኑ የበላይ ባለ ስልጣናት ለምን ይህን እንድታደርግ እንዳዘዙህ ታውቃለህ?» ብዬ ጠየቅኩት።

«አይ፣ አላውቅም» አለ።

«አለማወቅህ በጣም ይገርማል፣ እኔ ግን አውቃለሁ። ምክንያታቸው በጣም ቀላልና ግልፅ ነው። ይህን ለማድረግ የፈለጉበት ዋና ምክንያት እስር ቤት ውስጥ ብትገድለኝ እንኳን የት እንደገባሁ የሚያውቅ ሰው እንዳይኖር ነው። ምክንያቱም በቅጹ እና በመመዝገቢያ



t.me/OLDBOOKSPDF

ጠረቀትህ ላይ ወደ እስር ቤትህ ከነጭራሹ አልገባሁማ:: ስለዚህ በእናንተ እስር ቤት ውስጥ ደብዛዬ የመጥፋቱ ወይም የመገደሌ ጥያቄ አይነሳም::»

ይህን ስለው ክው ብሎ ደነገጠ:: «ገባህ አይደል?» ስል ጠየቅኩት:: «በቃ፣ ምክንያቱ ይኸው ነው፤ አለበለዚያማ ስሜን መሰወጥ ባላስፈለገ:: እናንተም ይህን የማድረግ ስልጣን የላችሁም::»

እዚህ እስም ላይ በሁሉም ነገር ላይ ነጻነት የለም::

ወደ ኮሌጅ ለመግባት በምዘጋጅበት ወቅት ወላጆቼ ወደ ሳይንስ ኮሌጅ ወይም ወደ ህክምና ኮሌጅ እንድገባ ይፈልጉ ነበር:: ፍላጐታቸው አስገርሞኝ «ኮሌጅ የሚገባው ማነው? እናንተ ናችሁ ወይስ እኔ?» ብዬ ጠየቅኳቸው::

«ኮሌጅ የምትገባውማ አንተ ነህ:: እኛ ምን ልንሰራ እዚያ እንሄዳለን?» አሉኝ::

«እንደሱ ከሆነ ውሳኔውን ለእኔ ተዉልኝ::»

«ውሳኔውን ለአንተ መተው እንችላለን:: ግን የጠየቅንህን ካላደረግክ የገንዘብ ድጋፍ እንደማናደርግልህ እወቅ::»

«ገብቶኛል» አልኩኝ:: እናም ከቤቴ ስወጣ ሰባራ ሳንቲም አልነበረኝም:: ወደ ዩኒቨርስቲው የሚሄደው ባቡር ጣብቂ ቲኬት ሳልቆርጥ ተሳፈርኩ:: ወደ ቲኬት ተቆጣጣሪው ሄጄ ያለሁበትን ሁኔታ ነገርኩት እና «ትኬት ሳልቆርጥ እንድሄድ ትፈቅድልኛለህ?» አልኩት::

እሱም «አንድ ሰው ይህን መሰል ጥያቄ ሲጠይቀኝ ይህ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነው! ሰዎች የለመዱት መደበቅ ወይም ማታለል ነው:: ወደ ዩኒቨርስቲው እወስድሀና መውረጃህ ሲደርስ ሰዎች እንዳያስቸግሩህ በር ላይ ቆሜ አስወርድሀለሁ» አለኝ::

ዩኒቨርስቲው ከደረስኩ በኋላ በቀጥታ ወደ ምክትል ፕሬዝዳንቱ ቢሮ ሄጄ ታሪኬን በዝርዝር ነገርኩት:: እከዬም «ማጥናት የምፈልገው ፍልስፍና ነው:: ነገር ግን መማር የምፈልገውን ትምህርት የመምረጥ ነፃነት የለኝም:: ስለዚህ የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርግልኝ ስለሌለ ነፃ የትምህርት እድል ልትሰጡኝ ይገባል:: አለበለዚያ እስከሞት ድረስ በባዶ ሆዴም ቢሆን ፍልስፍና መማሬን እቀጥላለሁ» አልኩት::


t.me/OLDBOOKSPDF

«አንደሱ እንዲታደርግ፣ ምክንያቱም ጥፋተኛ የምደረገው እኔ ነኝ። ነገ የትምህርት እድል እሰጥሀለሁ» አለኝ።

ገና ከሀጻናቶቻችን ጀምሮ ነጻነታችንን እንከጠቃለን። እኛም በተራችን ልጆቻችን በእኛ ፍላጎት ለመቅረፅ እንሞክራለን።

አንድ ጊዜ ከአንድ የክርስትና ሀይማኖት ሰባኪ (ሚሽነሪ) ጋር ስንወያይ «እግዚአብሔር ሰውን በአምሳሉ ፈጠረ» አለኝ።

«ይህ የባርነት ዋነኛ መሰረት ነው። ለምንድን ነው እግዚአብሔር ሰውን በአምሳሉ የፈጠረው? እሱ ማነው? ለሰው የራሱን ምስል ሰጠ ማለት ሰውን ገና ከመጀመሪያው ጀምሮ አጥፍቶታል ማለት ነው አሉ» አልኩት።

እያንዳንዱ ወላጅም የሚያደርገው ይህንኑ ነው።

የሰው ልጅ መሰረታዊ መብት ሰራስ ነፃነት መስጠት መሆን አለበት።

በእውነተኛ የሰው ልጆች ማህበረሰብ ውስጥም ሁሉም ሰው ራሱን እንዲሆን ሊፈቀድለት ይገባል። ፍላጎቱ መዝናናት ይሁን መንገድ ዳር የሚለምን ድሀ መሆን፣ ብቻ ፍላጎቱ መከበር አለበት።

> **የሰው ልጅ መሰረታዊ መብት ሰራሱ ነፃነት መስጠት መሆን አለበት። ሁሉም ሰው ራሱን እንዲሆን ሊፈቀድለት ይገባል። ፍላጎቱ መዝናናት ይሁን መንገድ ዳር የሚለምን ድሀ ብቻ ፍላጎቱ መከበር አለበት።**

አሁንም ነፃነት በጣም ውድ ነው እላለሁ። የአንድ አገር መሪ ልትሆኑ! መንገድ ዳር ያለ ቀሽንት እያነፋ የሚለምን ነዳይ ልትሆኑ ትችላላችሁ። ዋናው ቁምነገሩ ራሳችሁን መሆናችሁ ነው። ይህን ጥልቅ ደስታ እና እርካታ ካላወቃችሁት ግን ትልቅ ነገር አምልጧችኋል ማለት ነው።



## 7. አንድ ምድር፣ አንድ ህዝብ..

እኔ የበርካታ መንግስታት መኖር ጥቅሙ አይታየኝም። በዓለም ካርታ ላይ ያን ያህል በርካታ መስመሮች መኖራቸው ለምን አስፈለገ? አስታውሱ! መስመሮቹ ያሉት ካርታው ላይ እንጂ መሬት ላይ አይደለም። ሰማይ ላይም የሉም። ካርታ ደግሞ የተሰራው በሰው ነው። ምድር ተከፋፍላ አልተሰራችም።

እዚህ ጋር ከመምህራኖቼ አንዱ ታወሰኝ። በጣም ተወዳጅ መምህር ነበር። የራሱ የሆነ ልዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች ነበሩት። እንደ አመፀኛ አይነት ሰው ነበር።

አንድ ቀን ጥቂት የካርቶን ቁርጥራጮች ይዞ መጣ እና ጠረጴዛ ላይ በታትኖ አስቀመጣቸው። ከዛም «ተመልከቱ፣ ይህ የዓለም ካርታ ሲሆን እኔም ቆራርጬ በታትኜዋለሁ። አሁን አንዳችሁም ሰው በእርግጠኝነት በትክክል በቦታቸው ላይ መልሶ በመገጣጠም የዓለምን ካርታ ሊሰራ አይችልም» አለ።

አንድ ሁለት ተማሪዎች ካርታውን መልሰው ሊገጣጥሙ ቢሞክሩም አልተሳካላቸውም። እኔም ተማሪዎቹ የሚያደርጉትን መከራ እየተመለከትኩ ለምን እንደማይሳካላቸው ማሰብ ጀመርኩ።

የአምስቱ ተማሪዎች መከራ ያስከተለት ሲያበቃ በዝርዝርነት የእኔ ተራ ደረሰ። ወዲያውኑ ሁሉንም የካርቶን ቁርጥራጮች ገለበጥኳቸው። ይህን ሳደርግ መምህሩ «ምን እያደረክ ነው?» ብሎ ጠየቀኝ።

«አንዴ ጠብቀኝ፣ እያስተካከልኩት ነው። አምስቱ ሰዎች ባይሳካላቸውም እኔ ግን ምስጥሩን ደርሼበታለሁ» አልኩት።

የካርታው ጀርባ የአንድ ሰው ምስል ይዞ ነበር። እናም ከካርታው ይልቅ የሰውየው ምስል መገጣጠም ቀላል ነበርና እኔም ይህንኑ አደረግኩ።

በካርታው አንደኛው ገፅ የሰው ምስል የተሰራ ሲሆን፣ በጀርባው ደግሞ የዓለም ካርታ ተሰሎ ነበር። እፈልገው የነበረው ፍንጭ ይኸው



t.me/OLDBOOKSPDF

ነበር። ሌሎች ተማሪዎች ካርታውን በመገጣጠም ሲሞክሩ ከጀርባው አንድ ነገር መኖሩን ተጠራጥሬ ነበር።

መምህሩ! «አንተ ተንኮለኛ ነህ! በመጀመሪያ ካርታውን ለመገጣጠም ትሞክራለህ ብዬ ነበር። ብዙም ሳልቆይ ግን ፍንጭ ለማግኘት አድፍጠህ እየጠበቅክ እንደነበር ገባኝ። ትክክለኛውንም ፍንጭ ደርሰህበታል» አሉኝ።

ዓለም የተከፋፈለችው የሰው ልጅ በመከፋፈሉ ነው። የሰው ልጅ የተከፋፈለውም ዓለም ስለተከፋፈለች ነው።

ከየትኛውም ቦታ ጀምሩ! ብቻ ሁሉም የሰው ልጅ ሳይከፋፈል አንድ እንዲሆን አድርጉ። ይህን ካደረጋችሁ መንግስታት ይጠፋሉ። የድንበሮች መስመሮችም አይኖሩም። ይህ የእኛ ዓለም ነው - አንድ ህዝብ አንድ ምድር። እኛም ምድርን ገነት ልናደርጋት እንችላለን። በአሁኑ ወቅት ሲኦልን በቃላት መግለፅ አስፈላጊ አይደለም። ሲኦል ያለው እዚሁ ነውና። ዙሪያችሁን ብትመለከቱ ታዩታላችሁ።

**ዓለም የተከፋፈለችው የሰው ልጅ በመከፋፈሉ ነው።**
**የሰው ልጅ የተከፋፈለውም ዓለም ስለተከፋፈለች ነው።**

አንድ የሰማሁትን ታሪክ ላጫውታችሁ። ሰውየው ሞተ። በህይወት እያለ ሌባ! ነፍሰ ገዳይ! አስገድዶ ደፋሪ. . . ብዙ ምን አለፋችሁ እሱ ያልሰራው ወንጀል አልነበረም። መላእክቱን ይዘውት ሲሄዱ «መቼም የምትወስዱኝ ወደ ሲኦል ነው» አላቸው።

«አይደለም» አሉት።

«ምን?» አለ ደንግጦ።

«የኖርከው ሲኦል ውስጥ ነው። አሁን የምንወስድህ ወደ ገነት ነው። አንተ አዲስ የተሻለ ሲኦል ስለፈጠርክ አሮጌው ሲኦል ባዶ ነው። ሁሉም ሀጢአተኞች የሚላኩት ወደ እዚህ ነው» አሉት።

ታሪኩ በውስጡ ትልቅ ትርጉም የያዘ ይመስላል። ምድርን ዙሪያውን ብትመለከቱ የሰው ልጅ በከፍተኛ በቃይ እና እንግልት ውስጥ ስለሚኖር ሌላ ሲኦል የሚያስፈልገው አይመስልም።

ነገር ግን ሁኔታውን በሙሉ መለወጥ እንችላለን። ይህቺ ምድር ገነት መሆን ትችላለች። ይህ ከሆነ ደግሞ የሰማዩ ገነት መኖር አያስፈልግም። ገነት ባዶ ይሆናል።

## 8፡- የእያንዳንዱ ግለሰብ ልዩ መሆን መቀበል፡-

አንድ በጣም የሚያምር ቃል ሰማስብ እስከሚያስቸግር ድረስ አላግባብ ጥቅም ላይ ውሏል። ይህ ቃል እኩልነት የሚለው ነው።

ጥቂት አሳቢዎች የሰው ልጆች እኩል ናቸው ይላሉ። እነሱን ስመቃወም የመንግስታቱ ድርጅት፣ እኩልነት የሰው ልጆች ተፈጥሮአዊ መብት እንደሆነ ይነግሩ። ነገር ግን የሰው ልጆች እኩል እንዳልሆኑ እና ሊሆኑም እንደማይችሉ ለማረጋገጥ የሚከፈ አንድም የለም። ይህ ፍጹም ስነ ልቦናዊ ያልሆነ ነው።

ሁሉም ሰው ልዩ ነው። ገና እኩል በሆናችሁበት ቅፅበት ህዝብ ትሆናላችሁ። ግላዊነታችሁ ይጠፋባችኋል። ራሳችሁን መሆናችሁ ያስቀምሉት እና ማሽን ውስጥ ያለ አንድ ዓይነት ጥርስ ትሆናላችሁ።

እኔ እኩል አለመሆንን አስተምራለሁ! ልዩ መሆንን እስተምራለሁ። እያንዳንዱ ግለሰብ ልዩ ሲሆን በልዩነቱም መከበር አለበት። እያንዳንዱ ግለሰብ ልዩ ስለሆነ ተፈጥሯዊ መብቱ ‹ለሰው ልጆች የልዩ መሆን እድገት እኩል መብት መሰጠት አለበት› የሚል መሆን አለበት።

ይህ በጣም ቀላል እና ግልፅ እውነታ ነው። ሁለት ቪ አመታት ቢያልፉም ሌላ ኢየሱስ አልተፈጠረም። ሁለት ቪ አምስት መቶ ዓመታት ቢያልፉም ሌላ ጉተማ ቡድሀ አልተፈጠረም። ታዲያ እንዴም ሁሉም ሰው እኩል ነው ትላላችሁ?

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰው እኩል አይደለም፤ ሰው ሁሉ ልዩ ነው:: እያንዳንዱ ሰውም በራሱ ዓለም እንደሆነ ተደርጐ መከበር አለበት:: የሌላ የማንም ሰው የበላይ ወይም የበታች አይደለም:: ልዩ ነው፤ ብቸኛ ነው::

በዚህ ብቸኝነቱ ውስጥም ውበት አለ:: ምክንያቱም ህዝብ ወይ ቡድን ሳይሆን ራሳችሁን ትሆናላችሁና::

## 9:- የዓለም አንድ መንግስት:-

እኔ ፊፅሞ መንግስታትን እቃወማለሁ:: ለመላው ዓለም የሚያስፈልገው አንድ መንግስት ብቻ ነው:: ይህ ከሆነ ጦርነት ሊኖር አይችልም፤ በሚሊየን የሚቆጠሩ ሰዎችንም ጦር ሰራዊቶች ውስጥ ማቆየት አያስፈልግም:: ሰዎቹን ምርታማ ማድረግ ይቻላል፤ ፋይዳ ያላቸው፣ ጥቅም የሚሰጡ ማድረግ ይቻላል:: ከሌሎች ሰዎች ጋር ቢቀላቀሉም ድህነት ድራሹ ይጠፋል::

በአሁኑ ጊዜ ሰባ በመቶ የሚሆነው የአንድ አገር ብሔራዊ ገቢ የሚመደበው ለጦር ሰራዊቷ ነው:: ለቀሪው የአገሪቱ ግልጋሎት የሚውለው ሰላሳ በመቶው ብቻ ነው:: ሀገራት ጦር ሰራዊት ባይኖራቸው የእያንዳንዱ አገር ሰባ በመቶ የሚሆን ገቢ ሰሌላ ጥቅም ይውላል::

የዚያኔ ድህነት አይኖርም፤ ነዳያንም የሚኖሩበት ምክንያት አይኖርም::

እነኚህ ነዳያንን፣ (እነኚህ ኢትዮጵያውያን) የፈጠርናቸው እኛ ነን::

በአንድ ወገን ጠንካራ ጦር ሰራዊት እንገነባለን፤ በሌላኛው በኩል ሰዎችን በረሀብ እንጨርሳቸዋለን:: እነኚህ የጦር ሰራዊቶች ምንም የሚፈይዱት ነገር የለም:: እነሱ የሰለጠኑ ነፍሰ ገዳዮች፣ የሰለጠኑ ወንጀለኞች ናቸው:: እንዴት መግደል እንደሚችሉ እያሰለጠናቸው ነው::

ስለሰብአዊነት እንናገራለን፤ ስለ ስልጣኔ እንናገራለን:: ይህም ሆኖ ሰባ በመቶ የሚሆነው ገቢአችን የሚውለው ለግድያ ነው::



t.me/OLDBOOKSPDF

2000 ዓመታት ቢያልፉም፣ ቤላ ሊየሱስ አልተፈጠረም። 2500 ዓመታት ቢያልፉም፣ ቤላ ጉተማ ቡድሃ አልተፈጠረም። ነገር ግን አሁንም ሁሉም ሰው እኩል ነው ትላላችሁ። በፍጹም ሰው እኩል አይደለም፤ ሰው ሁሉ ልዩ ነው። እያንዳንዱ ሰውም በራሱ ዓለም እንደሆነ ተደርጐ መከበር አለበት። የቤላ የማንም ሰው የበላይ ወይም የበታች አይደለም። ገለኛ ነው።

ለመላው ዓለም አንድ መንግስት ብቻ ይኑር ማለት እጅግ በጣም ትልቅ የለውጥ እንቅስቃሴ ነው፤ አብዮት ነው። መላው ዓለምም ተጠቃሚ ይሆንበታል።

ሁለተኛ በዓለም ላይ አንድ መንግስት ብቻ ቢኖር ለሰው ልጆች የሚበጅ ጠቃሚ ሥራ የሚሰራ ይሆናል። በአሁኑ ጊዜ ያሉት መንግስታት ግን ምንም ጥቅም የላቸውም፤ ለማንም ጠቃሚ አይደሉም። መንግስት ትልቅ ሀይል አለው። በአንድ ጠቃሚ መንግስት ውስጥ ያለ ፕሬዝዳንት ወይም ጠቅላይ ሚኒስትርም የተለየ ይሆናል።

የፖስታ ቤት ሹምን ብትመለከቱ በጣም አስፈላጊ ሆኖ ሳለ ሀይል ግን የለውም። ሥራ አለው፤ ሙያ አለው. . . ሀይል ግን የለውም፤ እንዲኖረውም አያስፈልግም። የባቡር ጣቢያዎችን የሚያስተዳድር ግለሰብስ ምን አይነት ሀይል አለው? የአየር መንገድ ፕሬዝዳንት ምን አይነት ሀይል አለው? ነገር ግን እነዚህ ጠቃሚ ተቋማት ናቸው።

አንድ መንግስት ብቻ ቢኖር ወዲያውኑ ጠቃሚ (አገልጋይ) ይሆናል። ይህ ግን በዚህ ጊዜያችን እውን ሊሆን አይችልም። የሌሎች መንግስታት ስጋት ይህን እንድትፈሩ ያደርጋችኋል። «መሪዎቻችሁን ጠንካራ አድርጉ፣ ለመሪዎቻችሁም ድጋፍ ስጡ» ትባላላችሁ። ነገር ግን


t.me/OLDBOOKSPDF

ጦርነት ከሌለ ሀይል የሚያስፈልገው ሰው አይኖርም። የሀይል መኖር ምክንያቱ ጦርነት ነው። ጦርነት ከምድር ላይ ካልጠፋ በቀር ሀይል ሊጠፋ አይችልም። ሁለቱ አብረው የሚሄዱ ናቸው።

ጠቃሚ የሆነ የዓለም አንድ መንግስት ቢኖር እንደ ፖሊ-ሴቶች፣ ሠራዊት ጣቢያዎች እና አየር መንገዶች ያሉ ጠቃሚ ተቋማት ሁሉ ውጤታማ ይሆናሉ። ኃይሉ (ጡንቻው) ግን አይኖረውም። የተቀበች ዓለምም ይኖረናል። እንዲኃያቶቹ ስለሆኑ ፕሬዝዳንቱ እና ጠቅላይ ሚኒስትሩን የሚወደስበት ምርጥ ዓለም ይኖራችኋል።

በአሁኑ ሰዓት ግን መሪዎቻችሁ አለቆቻችሁ ሆነዋል። በስልጣናቸው ላይ ለመቆየት በወትር በፍርሃት እንድትርዱ ማድረግ አለባቸው። ፓኪስታን ከህንድ ጋር ለመዋጋት እየተዘጋጀች ስለሆነ ስህንድ መሪዎች ሁሉንም ሀይል መስጠት ይኖርባችኋል። ቻይናም ለጦርነት እየተዘጋጀች ነው።

አዶልፍ ሂትለር የህይወት ታሪኩን በጻፈበት መፅሐፍ «በስልጣን ላይ ለመቆየት ከፈለግክ ሰዎች ሁልጊዜ እንዲፈሩ፤ በስጋት ውስጥ እንዲኖሩ አድርግ» ብሏል። ትክክል ነው። አንዳንድ ጊዜ እኮ እብዶች ትክክል የሚሆኑበት ጊዜ አለ።

**10፡- ሜሪቶክራሲ፡-**

እንግዲህ እስካሁን ዲሞክራሲ ሊሳካ አልቻለም።

በመሳፍንት፣ በንጉሳዊ፣ በየከተማ ዲሞክራሲ . . . በመሳሰሉ በበርካታ መንግስታት ዓይነት ስር ኖረናል። በአሁኑ ጊዜ ደግሞ መላው ዓለም ዲሞክራሲ በሚለው ሀሳብ ዋላው ሆኗል። ዲሞክራሲ ግን የትኛውንም አይነት ችግሮች አልፈታም። እንደውም ችግሮቹን አባብሷል።

በእነዚህ ችግሮች ምክንያት ነው ካርል ማርክስን የመሳሰሉ ሰዎች የላብ አደሩ አምባገነንነት የሚደግፉት። እኔ የላብ አደሩ አምባገነንነት ደጋፊ አይደለሁም። ነገር ግን ከዲሞክራሲ የሚሻል ሌላ ሀሳብ አለኝ።

ዲሞክራሲ ማለት ከሰዎች ለሰዎች፣ ለሰዎች የሆነ መንግስት ማለት ነው። ነገር ግን ይህ ቃላት ብቻ ነው፣ ወሬ ብቻ ነው። በዚህ ጊዜ ህንድ ውስጥ ከዘጠኝ መቶ ሚሊዮን የሚበልጡ ሰዎች አሉ። ዘጠኝ መቶ ሚሊዮን ሰዎች እንዴት ስልጣን ሲኖራቸው ይችላል? ስልጣኑን ለሌላ ሰው መውከል (መስጠት) አለባቸው።

ስለዚህ መሪዎች ህዝቡ ራሱ ሳይሆኑ በህዝብ የተመረጡ ሰዎች ናቸው። የምርጫ መስፈርቶቻችሁ ምንድን ነው? መምረጥ የምትችሉትስ እንዴት ነው? ትክክለኛውን ሰው የመምረጥ ችሎታስ አላችሁን? ዲሞክራሲያዊ ህይወት እንዲኖራችሁ ትምህርት እና ስልጠናስ ወስዳችኋል? አልወሰዳችሁም። ምንም የተደረገ ነገር የለም።

በርካታ ያልተማሩ ሰዎች በትንሽ ነገር ሊታለሉ ይችላሉ። ለምሳሌ ኒክሰን ከኬኔዲ ጋር ባደረጉት የፕሬዝዳንታዊ ምርጫ ውድድር የተሸነፉበት ምክንያት ኬኔዲ በቴሌቭዥን ሲታዩ ከኒክሰን የተሻለ ሆነው በመታየታቸው ነው። ይህ እንግዲህ የአዕምሮ ጨዋታ ነው።

ኒክሰን የደረሰባቸውን ነገር ሲረዱ ለቀጣዩ ፕሬዝዳንታዊ ምርጫ ራሳቸውን ማዘጋጀት ጀመሩ። እንዴት መቆም፣ እንዴት መራመድ፣ እንዴት መናገር እና እንዴት መልበስ እንዳለባቸው ተለማመዱ። በቴሌቭዥን ስትቀርቡ የለበሳችሁት ልብስ ቀለም ሳይቀር በተመልካች ላይ ተፅዕኖ ያሳርፋል። ሙሉ ነጭ ልብስ ለብሳችሁ በቴሌቭዥን መስኮት ብትቀርቡ ጣዕረ - ሞት ትመስላላችሁ።

ካሜራውን በደንብ መግለፅ የሚችል አንደበተ - ርቱዕ ሰው አለ። በደንብ ንግግር ማድረግ የሚችል ሰው የግድ ጥሩ የሀገር መሪ ይወጣዋል ማለት አይደለም። እናንተ ግን አንድ ሰው ቆንጆ ጫማ በመጫማቱ ይህ ጥሩ ፕሬዝዳንት ያደርገዋል ብላችሁ ትመርጣላችሁ።

ይህ ሁኔታ አብረሃም ሊንከን ለፕሬዝዳንትነት ሲመረጡ አጋጥሞ ነበር። አብረሃም ሊንከን ለህግ መወሰኛ ምክር ቤት አባላት መክፈቻ ንግግር በሚያደርጉበት ቀን ህዝቡ በሙሉ ተሰብስቦ እና ተቀምጦ ነበር። የዚህ ምክንያትም የሊንከን አባት ጫማ ሰፊ በመሆናቸው እና የጫማ ሰፊ ልጅ ታላቅ መሳፍንታትን በማሸነፉ ነበር። በዚህ በጣም ቅር ተሰኝተው ነበር።



t.me/OLDBOOKSPDF

እንደኛው መሀይም ባላባት ግን ንዴቱን መቆጣጠር አልቻለም። ሊንከን ንግግር ማድረግ ከመጀመራቸው በፊት «አንድ ጊዜ ቆየኝ። እኔን ታውቀኛለህ? አባትህ የቤተሰባችን ጫማ ሰፊ ስለነበር ከእሱ ጋር ሆነህ የቤተሰባችንን ጫማ ለመስፋት ወደ ቤታችን አብረኸው ትመጣ ነበር። አንተም ታግዘው ነበር» ሲል የህግ መወሰኛ ምክር ቤት አባላት በሙሉ በሳቅ አውካኩ። ይህ ሊንከንን ለማዋረድ የተደረገ ጥረት ነበር።

ነገር ግን እንደ አብረሀም ሊንከን ያሉ ሰዎችን ማሳፈር አይቻልም። ሊንከን «ብዙኝ ሰአት በህይወት የሌለ አባቴን ስላስታወስከኝ ከልቤ አመሰግንሀለሁ። አባቴ በመሳው አገሪቱ ከነበሩ ጫማ ሰፊዎች በችሎታ ተወዳዳሪ አልነበረውም። እኔም አባቴ ምርጥ ጫማ ሰፊ የነበረውን ያህል ምርጥ የሀገር መሪ መሆን እንደማልችል አውቃለሁ። አሁንም ይበልጠኛል» የሚል ምላሽ ሰጡ።

ለምርጫ የምትጠቀሙት ምን አይነት መመዘኛ ነው? እንዴትስ በትክክል መምረጥ ትችላላችሁ?

የዲሞክራሲ ቀናት አልፈዋል የምለው ለዚህ ነው።

በችሎታ ላይ የተመሰረተ አዲስ ስርአት ያስፈልጋል።

በመላው ዓለም በሺ የሚቆጠሩ ዩኒቨርስቲዎች አሉን። ለምንድን ነው ተራ፣ ያልተማሩ፣ መሀይም ሰዎች ለአምስት አመታት ትልቅ ስልጣን የሚይዙ ሰዎችን የሚመርጡት? በአሁኑ ጊዜ የተመረጡቹ ስልጣን በጣም ትልቁ ስልጣን ስለሆነ መላውን ዓለም ለማጥፋት ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

ሜሪቶክራሲ ማለት በአንድ የትምህርት መስክ የሰለጡኑ (የተማሩ) ሰዎች ብቻ በዚያ ጉዳይ ላይ ድምፅ መስጠት አለባቸው የሚል ነው። ለምሳሌ የአንድ አገርን የትምህርት ሚኒስትር መምረጥ ያለባቸው የትምህርት ባለሙያዎች ብቻ መሆን አለባቸው። ይህ ሲሆን ሲኖር የሚችለው ከሁሉ የተሻለ የትምህርት ሚኒስትር ይመረጣል። ለገንዘብ ሚኒስትርነት ቦታ መመረጥ ያለበት ሰው ስለ ገንዘብ (ፋይናንስ) እና ምጣኔ ሀብት የሚያውቅ መሆን አለበት። ነገር ግን ይህን በትክክል ማካሄድ የሚችሉት በምጣኔ ሀብት የትምህርት መስክ የተሰማሩ ሰዎች መሆን አለባቸው። ይህ ሙያ ያላቸውም በሺ የሚቆጠሩ ሰዎች አሉ። ለእያንዳንዱ የስልጣን ቦታ የሚመረጠው ሰው መመረጥ ያለበት በዛ የሙያ መስክ በሰለጠኑ ሰዎች መሆን አለበት።

የጤና ሚኒስትሩ መመረጥ ያለበት በዶክተሮች፣ በህክምና ባለሙያዎች እና በህክምናው ዘርፍ ምርምር በሚያደርጉ ሳይንቲስቶች መሆን አለበት። ይህ ከሆነ በምሁራኖቻችን ተጠቃሚ እንሆናለን። የሰው ልጅን ህይወትንም የተሻለ፣ ሰላማዊ፣ አስደሳች እና የተሟላ ለማድረግም በሚያመጡት ውጤት መመካት እንችላለን።

ሜሪቶክራሲ የምለው ሀሳብ ይህ ነው። አንድ ጊዜ ሁሉንም ባለስልጣናት ከተመረጡ በኋላ እነዚህ ሰዎች ፕሬዝዳንቱን እና ጠቅላይ ሚኒስትሩን መምረጥ ይችላሉ። ሰዎቹ የእኛ ከሁሉ ብርሀኖች ይሆናሉ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ እና ፕሬዝዳንቱ ከሀገሪቱ ወይም ከፓርላማ አባላት መምረጥ ይቻላል።

ለፓርላማውም ደረጃ ማውጣት አለብን። ለምሳሌ ድምፅ መስጠት ያለባቸው ቢያንስ ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው ሰዎች መሆን አለባቸው። የአንድ ሰው እድሜ ሀያ አንድ አመት መድረሱ፣ ትክክለኛ ሰው ለመምረጥ በቂ ችሎታ አለው ማለት አይደለም። በሀያ አንድ ዓመታችሁ ስለህይወት እና ችግሮቹ የምታውቁት ነገር የለም።

ስለዚህ የፓርላማ አባላትን ወይም የህግ መወሰኛ ምክር ቤት አባላትን መምረጥ ያለባቸው ቢያንስ ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው ሰዎች መሆን አለባቸው። ይህን መንገድ ከተከተልን በምሁራን የተሞላ፣ የጠራ (ግልፅ) ራዕይ ያለው መንግስት እናቋቁማለን።

አንድ ወጥ የዓለም መንግስት ከመቋቋሙ በፊት ሁሉም መንግስታት በሜሪቶክራሲ ውስጥ ማለፍ አለባቸው። የሜሪቶክራሲን ፍሬ ካጣጣሙን በኋላ እነኚህ ሰዎች ሁሉንም መንግስታት አንድ አድርገን ብናዋህድ ህይወት አስደሳች እና ለመኖር የምታጓጓ እንጂ የምትሰለች አለመሆኗን መገንዘብ ይጀምራሉ።

እስካሁን ድረስ የተደረገው ነገር በሙሉ ድንገተኛ ነ የተደረገው በነሲብ ነው። እስካሁን ድረስ ያለው ታሪካችን የአጋጣ

t.me/OLDBOOKSPDF

kived 4 @ yahoo.com

ታሪክ ነው። ይህን አካሄድ ማስቆም አለብን። አሁን መጪው ጊዜ ድንገተኛ እንዳይሆን መወሰን አለብን።

ይህ የሚፈጠረውም በእኛ ነው። የራሳችንን ዓለም መፍጠር ደግሞ ሊፈጠር የሚችል በጣም ምርጥ (ታላቅ) ነገር ነው።

1146 3793

Hana

t.me/OLDBOOKSPDF

- ... ጋብቻ ... ይቻል ይሆን?
- ... ወደ ወንድ ያደላው ለምንድነው?
- ... ወይስ እንደምንሄድ የምናስተውለው ... ነው?
- ... የባለቤትነት ... የሚያሳውቁ ... ሁለት ... ይኖራሉ ...

[illegible]

ዋጋ ብር 12.00

t.me/OLDBOOKSPDF

- [illegible] ... ማግኘት [illegible]
- [illegible] ወንድ [illegible] ለምንድ[illegible] ነው?
- [illegible] ወደት [illegible] የሚ[illegible] [illegible] ነው?
- [illegible] የለየችን [illegible] የለመጠ ሁለት ዓይነት [illegible]

[illegible] ተበሳጭላቸው [illegible]

[illegible]

ዋጋ ብር 12.00

t.me/OLDBOOKSPDF